# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

## መግቢያ

የሰው ልጅ በዚህ ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር በአምላክ ፈቃድ የመጣው የተሰጠውን ዕድሜ መልካም ሠርቶ እንዲያልፍ ነው፡፡ለዚህም ከጊዜ ወደ ጊዜ ይጥራል፣ያለፈው ትውልድ እንዴት እንደኖረና የዘመኑም ዕውቀት ምን እንደሚመስል ለማወቅ የፈረሱ ወይም የተቀበሩ አብያተ ክርስቲያናት፣ከተሞችና የጥንቱ የአህዛብ ጣኦታት በከርሠ ምድር ጥናት እየመረመረ በዘመናት ብዛት የጠፉትን የታሪክ ቅርሶች ለማግኘት ያለፈው ትውልድ የኖረበትን ሕይወትና ዘመን ለማወቅ ይደክማል፣ይታገላል፣ይጥራል፤በጥረት የተገኙትንና ያሉትን ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፊ እየደከመመ ይገኛል፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ የሥልጣኔ ምንጭና የሰው ዘር መገኛ በመሆኗ በርካታ ዓለም አቀፍ ተመራማሪዎች ስለቅድስቲቷ ሀገር ጥንታዊነት ትኩረት ሰጥተዋል፡፡ኢትዮጵያ የሚታየውንና የማይታየውን ፍጥረት የፈጠረ ፈጣሪ እግዚአብሔር መኖሩን በሕገ ልቡና አውቃ፣አምና፣ተረድታ በቅዳሴ በውዳሴ አምልኮቷን ስትፈጽም የኖረች ጥንታዊትና ታሪካዊት ሀገር ናት፡፡ቅደመ ልደተ ክርስቶስ 800 ዓመት አካባቢ የነበረ ግሪካዊ ሆሜር እና ቅደመ ልደተ ክርስቶስ 400-300 ዓመት አካባቢ የነበረ ሄሮዶቱስ ጥንታነቷን የመሰከሩላት ኢትዮጵያ፤ዝናቸው፣ታሪካቸው፣ክብራቸውና ቅድስናቸው ለትውልድ የሚነገርላቸው ሰዎች አፍርታለች፡፡እነዚህም ቅዱሳንና የታሪክ ሰዎች በሚያልፍ ሰውነት የማያልፍ መልካም ሥራ ሠርቶ በማለፋቸው ለዓለም አርአያ እንደሆኑ ሁሉ አዲሱ ትውልድም ለምርምርና ለጥናት ምቹ በሆነች በዚህች ሀገር የእንግድነት ሕይወቱን ሀገርንና ቤተ ክርስቲያንን አገልግለው መልካም ታሪክ ሠርቶ ለማለፍ የአባቶች መልካም ሥራ ትውፊታቸውንና የቤተ ክርስቲያንን ጉዞዋን ታሪክ ማወቅ ውዴታ ሳይሆን ግዴታ መሆን ይጠበቅበታል፡፡

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በቅድሳት መጻሕፍት፣በጥንታውያን የታሪክ ሰነዶችና ጥናት በሥነ ፍጥረት በዓባይ ሸለቆ ዙሪያና በቀይ ባህር አካባቢ ከታወቁት ታሪካውያን አህጉርና ሕዝብ ጎን ተገቢ ገጽታ ያላቸው ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ ከልደተ ክርስቶስ በፊት ከአዳም እስከ ሙሴ በደብረ ሲና በሕገ ልቡና፣ከሙሴ እስከ ልደተ ክርስቶስ በሕገ ኦሪት ፀንታ የቆየችና በኋላም ሕገ ወንጌልን በ34 ዓ/ም በጃንደረባው አማካይነት የተቀበለች፣በ330 ዓ/ም የኤጲስ ቆጶስነት ማዕረገ ክህነትን በአባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን አማካኝነት ያገኘችና በእነዚህ በሦስቱም ዐበይት ሕግጋት በቅደም ተከተል ስመ እግዚአብሔርን በመጥራት፣በመቀደስ፣ቃሉን በመስማት፣ በማስተማር አምልኮቱንም በሕገ አግዚአብሔር ብቻ ስትመራ በማይናወጽ መሠረት ላይ የኖረች የሃይማኖት ሀገር ስትሆን የዕድገቷም ዓላማና አቋም በዚሁ ዓይነትና መጠን የተገነባ ሆኖ ከአንዱ ትውልድ ወደ ቀጣይ ትውልድ ሲወረድ ሲወራረድ መጥቶ አሁን ካለንበት ደረጃ ላይ ደርሶ ይታያል፡፡

በጥንት ዘመን በቅዱስ ዳዊትና በጠቢቡ ሰሎሞን በሌሎችም አበው ነቢያትና ነገሥታት የታወቀች ሀገራችን ኢትዮጵያ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ከብሉይ ኪዳን በወረሰቻቸው ባህሎችና ሥርዓቶች ጥንታዊነቷ ጎልቶ ይታያል፡፡ከነዚህም ጋር በድሮውም ሆነ በአሁኑ ጊዜ የሕዝቡ መንፈሳዊ ስሜት፣ባህልና ልማድ፣ጀግንነትና ርኅራኄ፣ነፃነትና ክብር የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነትና ሀገረ እግዚአብሔርነት ያሳያል፡፡

በዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ሀገራችን ቅድመ ልደተ ክርስቶስ የብሉይ ኪዳን እምነትና ሥርዓት ተቀብላ አምልኮተ እግዚአብሔርን ስትፈጽም መቆየቷን፤በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተመሠረተችውን የክርስትና እምነት ዜና በመስማትና በመቀበል ከእስራኤል ቀጥላ እምነቱ

ከተሰበከላቸው ቀደምት ሀገሮች አንዷ መሆኗን፤እስከዛሬ ድረስም አልፎ አልፎ የተከሰቱ አያሌ ውጣ ውረድ የተዋላባቸው ስቃዮችን እንደ አመጣጣቸው በትዕግስት እያሳለፈች የቆየች የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነታችንን በትጋት በማስተማር ምዕመናንን ስትንከባከብ መኖሯን አሁንም በመንከባከብ ላይ መሆኗን እንመለከታለን።ለዚህም ታሪክን እንዴት ማወቅ ይቻላል ቢሉ **በአካለ ሥጋ ወዳሉ አባቶች በመሄድና በመጠየቅ ዘዳ 32፤7፣ቅዱሳን አባቶች ጽፈው ያወረሱንን መንፈሳዊ የታሪክ መጻሕፍትን በማንበብና ትውፊታቸውን በመቀበል፣ታሪካዊ ቦታዎችንና ገዳማትን በመጎብኘት፣በመንፈሳዊ ጉባኤዎች በመገኘትና ተከታትለው በመማር እና በመሳሰሉት መንገዶች ታሪክን ማወቅ ይቻላል**።

አፍሪካውያን በኢኮኖሚ ጥገኝነት ምክንያት ከአፍሪካዊነታቸው ጋር የማይስማማ ከቀኝ ገዢዎች የወረሱት የእምነትና የባህል ውጥንቅጥ ሲገጥማቸው ኢትዮጵያ ግን ከአፍሪካ ሀገሮች አንዷ ብትሆንም የሌሎች ዕጣ ፈንታ ሳይደርስባት ማለትም የእምነትና የባህል ወረራ ሳይገጥማት የራሷን ጠንቅቃ የምታውቅ በእምነት ከህገ ልቡና እስከ ህገ ወንጌል ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት በማድረግ የምትታወቅ ብቸኛ ሀገር ናት።ለዚህም ነው እንግሊዛዊው የታሪክ ጸሐፊ ባጅ **‹‹ኢትዮጵያ እግዚአብሔርን ሳታውቅ የኖረችበት አንድም የታሪክ ዘመን የለም** ያለው።

ኢትዮጵያ የውጭ ወራሪን በሃይማኖቷና በታሪኳ እየተከላከለች የቆየች በራሷ እምነትና በሕዝቧ ታሪክ የምትታወቅና የምትጠራ ሀገር በመሆኗ ዜጎች በማንኛውም ሀገር ቢሄዱ የበላይነት እንጂ የበታችነት አይሰማቸውም።በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ታሪኳን ትጠብቃለች ስንል ከእምነት ጋር የተያያዘ የታሪክ አጠባበቅን በተመለከተ በሌሎች ዓለማት የሌሉና የማይገኙ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ መጻሕፍት እነ መጽሐፈ ኩፋሌ፣መጽሐፈ ሄኖክና አክሲማሮስ ማስረጃ በመሆናቸው ነው።

ኢትዮጵያ የ3000 ዓመት ታሪኳ በጽሑፍ ሰፍሮ የሚገኝባት በሥልጣኔና በነፃነት ይልቁንም በፊደል፣በስነ ጽሑፍ ከጥንታውያን ግብጽና ግሪክ ጋር የምትወዳደር ናት።ከግብጽውያኖቹ ጋር በጋብቻ፣በንግድና ንጉሥ በማንገሥ በመሳሰሉት የጠበቀ ግንኙነት ነበራት።ኢትዮጵያና ግብጽ የነበራቸው ግንኙነት እጅግ የጠነከረ እንደነበር ከክርስቶስ ልደት በፊት በ490 ዓ.ዓ የነበረ የምዕራባውያን የታሪክ ፀሐፊ ሔሮዶቱስ መረጃዎችን በማጣቀስ ገልጾ ጽፏል።

ኢትዮጵያ ከውጭ ዓለማት ጋር የነበራት ግንኙነት በነዚህ በሁለቱ በግብጽና በግሪክ ብቻ ተወስኖ የቀረ ሳይሆን ኃያላን ከሚባሉት ከሶርያ፣ከፋርስና ቁስጥንጥንያ ግዛቶች ጋር እንዲሁም በየመን እና ኑቢያ ከመሳሰሉት በሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ በሃይማኖትና በሃይማኖታዊ ሥርዓት ደግሞ አምስቱ የምስራቅ አብያተ ክርስቲያናት / The Five Oriental Churches / ከሚባሉት ሀገራት ራሷንና ግብጽን ጨምሮ አርመን፣ሕንድና ሶሪያ ጋር ግንኙነቷን እስካሁን እንደተጠበቀ ይዛ ቆይታለች።

## መቅድም ክፍል አንድ

### 1.1 ታሪክ ማለት ምን ማለት ነው?

- ታሪክ ማለት ተረከ፣ተናገረ፣ተወያየ፣ተመካከረ፣አስተላለፈ ከሚለው ቃል የተገኘ ነው።
- ታሪክ ማለት ንግግር፣ምክክር፣ትውፊት ሆኖ ከአበው ለልጆች በዜና መልክ፣በንግግር መልክ፣በሥዕል መልክ፣በሐውልት መልክ፣በቅርጻ ቅርጽ እና በስነ ጽሕፈት መልክ የተላለፈ፣የተመለከተ፣የተሰጠ ፀጋ ነው።ታሪክ የምድርና የሰማይ፣የሥጋና የነፍስ ሀብት ከሚባሉት ክፍሎች አንዱ ነው።
- ታሪክ-እምነትን፣ሥርዓትን፣ባህልን፣ሃይማኖታዊ፣ማህበራዊና-ሰብአዊ ሕይወትን ያቀፈና ያየዘ ሰፊ መድረክ ነው ምሳሌ 23፡10 ዕዝ 4፡15።

## 1.2 .አጠቃላይ የታሪክ መሠረታዊ ዓላማዎች

1. ታሪክ ያለፈውን ዘመን ይዘትና እንቅስቃሴ ያስተምራል ያሳያል።
2. ታሪክ ያለንበትን ዘመን ሂደትና ይዘት ያሳያል ያስተምረናል።
3. ታሪክ ያለፈውን ዘመንና ያለንበትን ዘመን ያወዳድራል አወዳድሮም ሁለቱን ዘመናት በሁለት ሚዛን በማስቀመጥ መልካሙንና ክፉን ከሁለቱ ክፉን ትተን መልካሙን እንድንመርጥ የሚያሳየን ሲሆን ታሪክ የሁለቱን ዘመናት ሁኔታ አወዳድሮ ለመጪው ትውልድ ቆጥረንና ቋጥረን እንድናስተላልፍ አደራ ይለናል። የምናስተላልፈው ታሪክ መልካሙን በመልካምነቱ ክፉውን በክፋቱ ማስተላለፍ ግድ ይለናል።

- ታሪክ ስላለፈው የምንማርበት፣እየኖረንበት ያለውንና መፃኢ ሕይወታችንን ዕጣ ፈንታ ለመወሰን የምንጠቀምበት መሳሪያ ነው።ታሪክ በአንድ ወቅት ስለነበረው የአንድ ሕዝብ ማህበራዊ ዕድገትና የአኗኗር ሁኔታን ለማወቅ የሚጠቅም መነፀር በመሆኑ ታሪክ መጥፎውን በመተው መልካሙን ለመያዝ የሚረዳ መሣሪያ ነው።
- ታሪክ ሩቁንና ቅርቡን ለይቶ የሚያሳይ ኮምፓስ ነው።የታሪክ ሊቃውንት ታሪክን ኮምፓስ፣መወጣጫ መሰላል /ሊፍት/ ነው በማለት ለታሪክ ትርጉም ይሰጣሉ።ምክንያቱም ታሪክ ዘመንን ከዘመን ጋር አቀራርቦ ያገናኛልና።
- ታሪክ እውቀት ነው እውቀት ነው ሲሉ ሊቃውንት ፈጣሪውን ከፍጡር፣በጉን ከተኩላው፣ስንዴውን-ከእንክርዳዱ፣ቤተ-ታቦትን ከቤተ-ጣኦት፣ክርስቶስን ከዲያብሎስ፣ ብርሃንን ከጨለማ ለይቶ የሚያሳይ መሣሪያ መሆኑን ይገልጻል።ታሪክ ሚዛን ነው የዘመኑን ክብደትና ቅለት ገልጾ ያሳያል።ታሪክ መገኛ /አደባባይ/ ነው ይላሉ ሊቃውንት ምክንያቱም ያለፈውን ዘመንና ያለንበትን ዘመን አጣምሮ ይዞ ያገነኛል።
- ታሪክ መምህር ነው ያስተምራል፣ይመክራል፣ይገስጻል።
- ታሪክ እውነትና መሸጋገሪያ ድልድይ ነው ወደ መንግስተ ሰማያት ይመራናል፣በሰማይና በምድር መካከል ያሉትን ያገናኛል።

### 1.3 <u>ታሪክ በምሁራን ኃይል</u>

**1.3.1. ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት**‹‹ታሪክ አይሙት እንዲያጫውት /እንዲያወያይ/››

‹‹የራሱን እምነት፣ሥርዓት፣ባህልና ታሪክ የማያውቅ ሰውና ህጻን ልጅ አንድ ናቸው ሁለቱም በሌላ ሰው ፈቃድ ይኖራሉና /ፀሐፈ ትዕዛዝ ወ/ጊዮርጊስ ወ/ዮሐንስ/

**ሊቁ ሞት ያለው በታሪክ አንጻር የተለያየ ዓይነት ሞት አለ**

1. በሕይወት እያሉ ከእምነትና ከመልካም ሥራ ተለይቶ መኖር
2. የሥጋ ከነፍስ መለየት ተለይቶ ወደ መቃብር መውረድ
3. የነፍስ ከእግዚአብሔር መለየት ተለይታ ወደ ሲኦል መውረድ
4. የቤተ ክርስቲያን /ሃይማኖት/ ሞት

5. የአገር ሞት
6. የሕዝብ ሞት

**ሀ.በታሪክ አንጻር የቤተ ክርስቲያን /የሃይማኖት/ ሞት ተብሎ የሚጠራው**

- ምዕመናን-ከጥምቀት፣ከንስሐ፣ከምፅዋት፣ከርኅራኄ፣ከጾም፣ከጸሎትና-ቁርባን ሲለዩ
- ቅርጻ ቅርጽ፣ንዋየ ቅድሳት በብል ሲበሉ፣በዝናብ ሲበላሹ፣በሌባ ሲሰረቁ
- ምዕመናን ከእምነት፣ከምግባር ፈፅሞ ሲርቁ
- የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ከሥርዓትና ከሕግ ውጭ ሆኖ ሲዳከም ሲጠፋና ሲበላሽ
- የነገረ መለኮት ትምህርት ሲፋለስ
- የቤተ ክርስቲያን-ሥርዓት መፋለስ፣መቀላቀል፣በመናፍቃን፣ቢጽሐሳውያንና በፀራዊያን መወረር
- የቤተ ክርስቲያን ትውፊት መንገዱን ሲለውጥ የቤተ ክርስቲያን ሞት ተብሎ ይጠራል።ዕዝ 4፡15 ምሳ 22፡28

**ለ.በታሪክ አንጻር የአገር ሞት ተብሎ የሚጠራው**

- ሕዝቡ ሥራ ሲጠላ
- እምነት ሲጎድል
- ባህል፣ታሪክ፣ወግ፣ሥርዓትና እምነት ሲረሳና ሲጣስ
- ድንበር በባዕድ ግዥዎች ሲደፈርና ሲወረር የአገር ሞት ተብሎ ይጠራል።

**ሐ.በታሪክ አንጻር የሕዝብ ሞት ተብሎ የሚጠራው**

- የልጆች ከወላጆች ሥርዓት፣እምነት፣ባህል፣ታሪክ፣ትዕዛዝና መመሪያ ውጭ ሲሆኑ
- የወላጆች ልጅን አለማስተማር፣አባታዊ ግዴታንና ኃላፊነትን መርሳት

አለመወጣት ልጆችን በብቃት አለመምራት የሕዝብ ሞት ተብሎ ይጠራል።

**1.3.2. ‹‹ወጣት ተመልከት እንዳትሳሳት ተጠንቀቅ ታሪክህን እወቅ ››**/መልአከ ብርሃናት አድማሱ ጀንበር/

1.3.2 **ታሪክ በውጭ ምሁራን ፀሐፊት**

**1.በሮማውያን** «ታሪኩን እምነቱን ሥርዓቱንና ባህሉን የማያውቅ ሰውና እናቱ በፊቱ ከሴቶች መካከል ተቀምጣ እያለች ለይቶ ለማወቅ የተሳነው ህጻን ልጅ አንድ ናቸው።»

2.**ቻይናዊያን** «ታሪኩን እምነቱንና ሥርዓቱን የማያውቅ ሰውና ፊቱን ወደ ግድግዳ አዙሮ የተኛ ሰው አንድ ናቸው።»

**1.4. የታሪክ ጥቅም፡-**ታሪክ የሚከተሉትን ነገሮች እንድናውቅ እንድንማርና እንድንረዳ ያደርገናል።

- ሙሉ ትምህርትን/የነፍስና ሥጋ
- ፍፀም ቋንቋ ከነፊደሉ
- ሥነ ጽህፈት ከነጠባዩ ከነሙያው
- ሥነ ጥበብን ከነመልኩ ከነፍልስፍናው
- ሥነ ጥበብን በየዓይነቱ
- ሙሉ ታሪኩንና ቅርስ
- እምነትን ከነፍልስፍናው ከነምስጢሩ
- ነጻነትን ከነክብሩ
- አንድነት ከነጀግንነቱ/ለሃይማኖት ለሀገር
- ሀገር ከነድንበሩ ከነፍቅሩ

•ስም ከነምልክቱ ከነትርጉሙ።ትውልዱ ጀግንነትን፣አገር ወዳድነትን፣ለታሪክ፣ ለባህልና ለሃይማኖት ተቆርቋሪነትን ይዞ እንዲያድግ በማስተማርና በማበረታታት መምህራንና የታሪክ ባለሙያዎች ድርሻ ሊኖራቸው ይገባል።

2. **የታሪክ ትምህርት ምንድን ነው?** ትምህርት የሚለው ቃል መሀረ አስተማረ፣አሳየ፣መከረ፣አሳወቀ፣ገለጠ፣አብራራ ማለት ነው።

- የታሪክ ትምህርት እውቀት፣ድርሳን፣ምዕዳን/ምክር/፣ተግሳጽ ስህተትን ደግመን እንዳንሠራ የሚያደርግ ነው።
- የታሪክ ትምህርት ግዴታን የመወጣት፣ኃላፊነትን የመሸከም፣የሥራ ምድብን የማወቅና የማሸነፍን የሚገልጥ የማወቅ እውቀት ነው።ኢሳ 11፡1
- የታሪክ ትምህርት መብትን ለይቶ የሚያሳውቅ ህግና የአዕምሮ መሙላት ነው።
- የታሪክ ትምህርት አዕምሮ የመልካም እውቀትና እምነት መሳሪያነት የሚጠቅም ነው።ምክንያቱም ሰው የእግዚአብሔር ክብር መገለጫና የእግዚአብሔር ንብረት ባለአደራ ነው።የታሪክ-ትምህርት፣ለፍቅር፣ለፍትሕ፣ለነጻነት፣ለእኩልነት፣ለአንድነትና ለዘለዓለም ሕይወት መንግስተ ሰማያት ዜግነት የምንማረው ትምህርት ስለሆነ የማወቅ እውቀት ነው።
- ታሪክ ህግንና ሥርዓትን ያስተምራል።ህግ ደግሞ መልካሙን እንድንሠራ መጥፎውን እንድንተው የተሰጠ የሕይወት መመሪያ ነው።ሥርዓት ደግሞ የመልካም ሂደትና እንቅስቃሴ፣ይዘትና ጥረት፣ዕድገትና ውጤት፣ስፋትና ጥልቀት የሚለካበት መስፈሪያ ነው።
- የታሪክ ትምህርት ራሱንና ሌላውን ለመልካምና ለተሻለ ሕይወት ለመመልመልና ለማደራጀት የምንማረው

ትምህርት ነው፡፡

- የታሪክ ትምህርት ለማህበራዊ፣ለሰብአዊ፣ለሃይማኖታዊ ሥራዎች ቀና አመለካከትና በጎ ፈቃድ እንድኖረን ያስተምራል፡፡ምክንያቱም ሰው ማድረግ የሚገባው ሰውን በሰውነቱ በማህበራዊ ሕይወቱ ማድረግ ይገባል፡፡
- የታሪክ ትምህርት መጥፎን ከመልካሙ፣ጥፋቱን ከልማቱ፣ኃጢአትን ከጽድቅ፣እውቀትን ከድንቁርና ለይተን እንድናውቅ ለይተን እንድናውቅ ጥቅሙን ተረድተን እንድናደርግ የሚያስተምር ትምህርት ነው፡፡
- የታሪክ ትምህርት ወላጆች ለልጆች የሚያስተላልፉትና የሚያወርሱት የማያልቅና የማይጠፋ ሀብት ነው፡፡የታሪክ ትምህርት ልጆች በባህርና በአካል መልካም የሠሩ ወላጆቻቸውን እንዲመስሉ የሚያስተምር ትምህርት ነው፡፡
- የታሪክ ትምህርት ሰው የራሱ የሆነውን መልካም ነገር ብቻ እንዲይዝ የሌላ የሆነውን መጥፎ ነገር እንዲጠላ የሚያደርግ ትምህርት ነው፡፡
- የታሪክ ትምህርት ከመምህራን፣ከመጻሕፍት፣ከቅርጻ ቅርጽና ከአካባቢ እንዲሁም ከዘመን የምናገኘው ትምህርት ነው፡፡
- የታሪክ ትምህርት,ድርሰትን፣ኪነጥበብን፣ሥነ ጥበብን፣ሥነ-ጽሕፈትን፣ምዕዳንን፣ጀግንነትን ፣ፍቅርን፣ታማኝነትን፣ትዕግስትንና ችሎታን ያስተምራል፡፡

**3. የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሁለት ዋና ዋና መልኮች አሉት**

1. **አምላካዊ መልክ፡-ልዑል እግዚአብሔር በጊዜ ውስጥ ለዓለም መገለጡን፣ወሰን የሌለው ጥበቡን፣ፍርዱንና ምህረቱን፣ክብሩንና ለሰው ልጅ የሚሰጠውን ደስታ የሚገልጠው መልክ ነው፡፡በተለይም የእግዚአብሔር ክብርና የዓለም መድኅን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ የመሠረተውን የእግዚአብሔርን ዘለዓለማዊ መንግስት ለመግለጽ ነው፡፡**
2. ሰብአዊ መልክ፡-አጠቃላይ የሰው ልጅ ዘርን መልክሙንም ሆነ ክፉ ኑሮውን፣ ቁሳዊውንም ሆነ መንፈሳዊ ሕይወቱን፣ክፉንም ሆነ በጎ ምግባሩን የሚገልጠው መልክ ሲሆን ጠቅለል ባለመልኩ የቤተክርስቲያን ታሪክ ስንል የእግዚአብሔር መንግስት በምድር ላይ እንዴት እንደተመሠረተ.እንደዳበረና እንደተስፋፈ እንዲሁም የመንግስቱ ዜጎች ማለትም የብሉይ ኪዳንና የሀዲስ ኪዳንን አማኞች እንዴት እንዴኖሩና እንደሚኖሩ የሚገልጥ ሀተታ ነው፡፡

4. **ቤተ ክርስቲያን፡-**ቤተ ክርስቲያን የምንለው የክርስትና ሃይማኖት ሲሆን ፍቺውም ሦስት ዓይነት አወጣጥ አለው፡፡

**4.1.ምዕመናን /ክርስቲያኖች/**፡-ትምህርተ ሃይማኖትን ተምረውና አምነው፣የእግዚአብሔርን ፈቃድ አውቀውና ከዓለም ፈቃድ ርቀው፣ከሰይጣን ግብር ተለይተው፣ከመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ጋር ተስማምተው፣በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቀው ዳግም የተወለዱ፣ስመ ክርስትናን ሀብተ ወልድን ያገኙ፣የእግዚአብሔር ልጅ ሆነው በክርስቶስ ክርስቲያን በወልድ ውሉድ ተብሎ የተጠሩ፣ንጽህናቸውን በመንፈስ ቅዱስ የጠበቁና በመንፈስ ቅዱስ የከበሩ ምዕመናን --

**ቤተ ክርስቲያን** ተብሎ ይጠራሉ ሐዋ 20፡28፡፡ክርስቲያን ማለት የክርስቶስ የሆነ፣የክርስቶስ አማኝ፣ለገነት መንግስተ

ሰማያት የተዘጋጀ፣የክርስቶስ ተከታይ፣ደቀ መዝሙር /ተማሪ/፣የክርስቶስ ቤተሰብ /ማህበርተኛ/፣ የክርስቶስ ወገን/አካል/፣አለባበሱ አነጋገሩ አካሄዱ መላ ሕይወቱ ክርስቶስን የመሰለ ማለት ነው 1ቆሮ 11፤1።ምዕመናን ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስቲያን ተብለው የተጠሩት **በቂሳሪያ ከተማ በአንጾኪያ** ነው ሐዋ 9፤31 ሐዋ 12፤1።ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል በሌላ ትርጉም ዘርን፣ጎሳን፣ወገንነትን፣ዜግነትን ያመለክታል። ለምሳሌ ቤተ-ያዕቆብ፣ቤተ-እስራኤል፣ቤተ-ኢትዮጵያ እንዲል።ከቤተ-ያዕቆብ የተወለዱ ሁሉ ቤተ-እስራኤል እንደሚባል ሁሉ በመንፈሳዊና በምስጢራዊ ልደት ከክርስቶስ የተወለዱ ሁሉ **ቤተ** ክርስቲያን፣የክርስቶስ ወገኖች፣ የመንግስቱ ዜጎች ይባላሉ ። ማቴ 16፤16 ማቴ 18፤15

1ቆሮ 11፤16-18 1ቆሮ 15፤9 ገላ 1፤13 1ቆሮ 6፤19 1ቆሮ 14፤19።

**ምዕመናን /ክርስቲያኖች/** ስመ ክርስትናን ከማግኘታቸው ማለት ክርስቲያን ተብሎ ከመጠራታቸው በፊት በሚከተሉት ስሞች ይጠሩ ነበር።

**ሀ.ደቀ-መዛሙርት/ተማሪዎች/**፡-ይህም ከብሉይ ኪዳን ካህናት፣ከካህናተ አይሁድ፣ከፈሪሳዊያን፣ ከሰዱቃዊያንና ከጸሐፍት የተወረሰ ቃል ነው ። የጌታን ትምህርት የተቀበሉት ሁሉ ደቀ መዛሙርት ተብለው ተጠርተዋል ። የሐዋ 9፤1 የሐዋ 15፤1።ፈሪሳዊያን ደቀ መዛሙርት ነበራቸው ማቴ 9፤14። በዚህ አንጻር ክርስቶስን የተከተሉት ክርስቲያኖች ሁሉ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት /ተማሪዎች/ ተብሎ ተጠርተዋል።

ለ.**ቅዱሳን**፡-ቅዱስ ማለት የተለየ ማለት ሲሆን ቅዱሳን ስንል ከሌሎች ፍጥረታት ተለይቶ ለእግዚአብሔር የተሰጡ ማለት ነው።ዘሌ 19፤1 1ጴጥ 1፤15 ሐዋ 9፤32።የተለየ ያሰኘውም ከዓለማዊ ኑሮ፣ከአምልኮ ጣኦትና ከኃጢአት ተለይቶ ራስን ለእግዚአብሔር ማቅረብ ነው።ክርስቲያን ሕይወትን በሚያድስና በሚቀድስ ከቅዱስ መንፈስ የተወለደ ስለሆነ የተለየ ነው ኤፌ 6፤26 ያዕ 1፤18 1ጴጥ 1፤30።

**ሐ.አማኒያን**፡-የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራና የሚያምን ሁሉ አማኒ አማኒያን ተብሎ ተጠርተዋል።ዘፍ 12፤6 ዘፀ 14፤32 ዕን 2፤4 ማር 16፤16።

**መ.መንገደኞች**፡-ለብዙ ዘመናት አማኞች መንገደኞች የመንገዱ ሰዎች ተብሎ ተጠርተዋል ።

ሐዋ 9፤2-19 ዮሐ 14፤22።የዚህ ስያሜ መሠረታዊ መነሻ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው ትምህርት ነው። ዮሐ 14፤6 የክርስትና ጉዞ ወደ አምላክ የሚያደርስ የሕይወት መንገድ ነው።ወደ ገነት መንግስተ ሰማያት ለመድረስ መንገዱ አንድ ብቻ ነው።እሱም በእምነትና በምግባር የጸና ድልድይ ነው።መጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች መንገደኞች/ የመንገዱ ሰዎች ተብሎ መጠራታቸው ወደ ቅድስት ሥላሴ ለመድረስ አማራጭ የሌለውን የቀና መንፈሳዊ መንገድ ይዞ መጓዛቸው ነው ማቴ 7፤13።

**ሠ**.**ክርስቲያኖች፡-**ምዕመናን ለመጀመሪያ ጊዜ በዚህ ቃል /ስም/ የተጠሩት በአንጾኪያ /በሶሪያ ከተማ ነው ሐዋ 13፤1 ሐዋ 9፤31 ሐዋ 12፤1።ይህ ፍቺ ዘርን፣ጎሳን፣ወገንነትን፣ዜግነትን ያመለክታል።ለምሳሌ ቤተ-ያዕቆብ፣ቤተ-እስራኤል ከቤተ-ያዕቆብ የተወለዱ ሁሉ ቤተ-እስራኤል እንደሚባሉ ሁሉ በመንፈሳዊና በምስጢራዊ ልደት ከክርስቶስ የተወለዱ ስመ ክርስትና ሀብተ ወልድና ያገኙ ምዕመናን ሁሉ **ቤተ ክርስቲያን** ይባላሉ።ክርስቲያን ስንል የመጠሪያው ስም ማንነቱ የሚገለጸው ክርስቶስ፣ክርስትና፣ክርስቲያን፣ክርስቲያናዊ-ሕይወት ቤተ ክርስቲያን፣የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እነዚህ ደረጃ በደረጃ ሲፈጸሙ ነው።ክርስትና ስንል ሀብተ ወልድና ስመ ክርስትና ይህም ማለት በፀጋ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ማለት ሲሆን ይኸውም እግዚአብሔር አምላክ የሰው ልጅ ይድንበትና ወደ ገነት መንግስተ ሰማያት ሄዶ ይኖርበት ዘንድ

ያዘጋጀው የቅድስና መንገድ ነው። ሉቃ 13፤24 ማቴ 7፤13።

4.2.**የክርስቲያኖች-አንድነት /ማህበር/**፡-፡-ክርስቲያኖች-ለጸሎት፣ለትምህርት-ለወንጌል ለመልካም ሥራ የሚሰበሰቡበት **ሥፍራ ቤተ ክርስቲያን** ተብሎ ይጠራል።ቤተ ክርስቲያን ዘኢትዮጵያ፣ቤተ ክርስቲያን ዘግብጽ፣ቤተ ክርስቲያን ዘሶርያ እንዲል።ይህም በኢትዮጵያ፣በግብጽና በሶርያ የሚገኙ **ክርስቲያኖች ህብረት/ማህበረ ምዕመናን/** ማለት ነው 1ጴጥ 5፤13 1ጴጥ 4፤16

ሐዋ 11፤26 1ቀሮ 6፤19-20።

4.3. **ህንጻ ቤተ ክርስቲያን /ቤተ መቅደስ/**፡-ይህም የክርስቲያኖች መኖሪያ ወይም መሰብሰቢያ ቦታ ወይም ቤት ማለት ነው።ህንጻ ቤተ ክርስቲያን ወይም ቤተ መቅደስ ስብሐተ እግዚአብሔር የሚደረስበት፣ሥርዓተ ጸሎት የሚከናወንበት፣ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ የሚፈተትበት፣ምስጢራት የሚከናውኑበት፣አምልኮተ እግዚአብሔር የሚፈጸምበት፣ሰውና እግዚአብሔር የሚገናኙበት፣የሰው ልጅ የእግዚአብሔር ልጅ የሚሆንበት፣መንፈሳዊ ማህበራዊና ሰብአዊ የርኅራኄ ሥራ የሚፈጸምበት ቤት ወይም መካነ ድህነት ነው

መዝ 121፤1 1ዜና 7፤4 ሐዋ 8፤3 ዘፀ 25፤8 1ዜና 29፤1-5 2ዜና 8፤11 ሐዋ 5፤11

ሉቃ 2፤9 ዮሐ 2፤13 ማቴ 21፤19።

## መቅድም ክፍል ሁለት

## የቤተ ክርስቲያን ስያሜ

**2.1.ከሀል**¬፡-ቤተ ክርስቲያን በአይሁድ ወይም በዕብራውያን ወይም በእስራኤላውያን ከሀል ተብላ ትጠራለች።ትርጓሜውም የተጠሩ፣የተመረጡ እና የተጋበዙ ማለት ነው።

- ጥሪው ለመንግስተ ሰማያት፤ምርጫው ለእግዚአብሔር ልጅነት ሲሆን ግብዣው ለቅዱስ ሥጋው ወደሙ እንደሆነ በትርጓሜያቸው ይገልጻሉ።

**2.2. ኤክሌስያ**፡- ቤተ ክርስቲያን በግሪካውያን ወይም ፀርአውያን ወይም ዮናናውያን አጠራር ኤክሌስያ ተብላ ትጠራለች።በዓላተ እግዚአብሔርን ለማክበር የሚሰበሰቡ ሕዝበ-እስራኤል ሁሉ ኤክሌስያ ይባሉ ነበር።ይህም ህሩያን /ምርጦች/ ጉባኤ ማለት ሲሆን ትርጓውሜም የሠላም /የእርቅ ጉባኤ/ ማለት ነው።ቤተ ክርስቲያን ተጣልተው መጥተው የሚታረቁባት፣ ታመሙ መጥተው የሚፈወሱባት፣ተለያይተው መጥተው አንድ የሚሆኑባት የሠላም የእርቅ ጉባኤ ናት።

**2.3.** ኬኒሳ፡-ቤተ ክርስቲያን በግብጻውያን/በምስሮች/በኮፕቶች/ ኬኒሳ ተብላ ትጠራለች

2.4. ቸርች፡-ቤተ ክርስቲያን በእንግሊዘኛ ቸርች ተብላ ትጠራለች።ቸርች የሚለው ቃል ኪርያኮስ ወይም ኮርያ ከሚለው የግሪክ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙ የአምላክ፣የጌታ ማለት ነው።ቤተ ክርስቲያን የጌታ የአምላክ ነች መሠረቷና መስራቿ ጌታ ክርስቶስ ነውና የማንም አይደለችም።

**2.5. ቤተ ክርስቲያን**፡-በኢትዮጵያውያን ቤተ ክርስቲያን ተብላ ትጠራለች።ትርጉሙ የክርስቲያኖች መኖሪያ፣መሰብሰቢያ፣ክርስቶስ በደሙ የመሠረታት፣ሰውና እግዚአብሔር የሚገናኙባት የቅድስና አደባባይ ናት።

### 2.6. የቤተ ክርስቲያን ባህርይ

**2.6.1**. አንዲት ናት፡-ራሷና መስራቿ ክርስቶስ አንድ እንደሆነ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን በወርቅ፣በአፈር፣በገጠርና በከተማ

ብትሠራ አንዲት ናት።

ቤተ ክርስቲያን ስንል እግዚአብሔር ግዕዛን ካላቸው ፍጥረታት ጋር ያለው ግንኙነት ስለሆነ በገዳም፣በደብር፣በገጠር ብትሠራ ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት።

ቤተ ክርስቲያን ሰው ከመፈጠሩ በፊት በዓለመ መላዕክት የነበረችው የመላዕክት አንድነት /ዓለመ መላዕክት፣ከአቤል ጀምሮ እስከ ሐዲስ ኪዳን መግቢያ ድረስ የነበሩ የደጋግ ሰዎች አንድነት /ህብረት እና በክርስቶስ ደም የተመሠረተች የፀጋና የጽድቅ ምንጭ የሆነች አማናዊት የክርስቲያኖች አንድነት ናትና አንድ ባህርይ ያላት ናት።ምዕመናን እንደአንድ ልብ መካሪ፣እንደአንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው ሃይማኖታቸውን የሚመሰክሩባት የአንድ የክርስቶስ አካል ናትና ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት።ኤፌ 4፤5 ቆላ 1፤18 ኤፌ 1፤23።በተራ ካህን፣በአበምኔት፣በሊቀ ጳጳስ፣በፓትርያርክ ብትገለገል፤በተራ ግምጃ፣በወርቀ-ዘቦ ብትገለገል ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት።መስዋዕቱም ጥምቀቱም የሚገኘው ፀጋም አንድ፣ቃለ እግዚአብሔርም አንድ ነው ዘዳ 6፤4።

**2.6.2. ቅድስት ናት**፦ክርስቶስ በቅዱስ ደሙ የመሠረታት፣ያነጻት፣የቀደሳት ናትና ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ናት ኤፌ 5፤26 የሐዋ 20፤28።ቅድስና የባህርይ የሆነ የሊቀ ቀዳሲያን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ናትና ቤተክርስቲያን ቅድስት ናት 1ቆሮ 6፤19።ቤተ ክርስቲያን በኃጢአት፣ በክህደት ረክሰው የነበሩ በእምነት፣በንስሐ ወደ እርሷ ገብተው ይቀደሳሉና

ቲቶ 3፤3።የመጣበትን የኃጢአት መንገድ ትቶ በጽድቅ ጎዳና እንዲመለስ የምታደርግ የመንፈስ ቅዱስ ግምጃ ቤት ናት ኤፌ 2፤8 ቆላ 1፤21።

**2.6.3. ዓለም አቀፋዊት ናት**፦ ቤተ ክርስቲያን የሁሉም ናት፣በሁሉም ያለች ናት፣በሰማይምም በምድርም ያለች ናት ማቴ 28፤19።

- ቤተ ክርስቲያን በዘር፣በጎሳ፣በቋንቋ አትከፈልም አትወሰንም፤
- ቤተ ክርስቲያን ስለመልካም አመለካከትና አሠራር ለሁሉም የምታስተምር መንፈሳዊት ድርጅት ናት።
- ቤተ ክርስቲያን የሰብአዊነትና የርኅራኄ ሥራ የምትሠራ ከፖለቲካና ከጥገኝነት ነፃ የሆነች ለሰው ልጅ ሁሉ መልካም ሥራ የምትሠራ መንፈሳዊት አደባባይ ናት።
- ቤተ ክርስቲያን አብ የመሠረታት ወልድ ያነፃት መንፈስ ቅዱስ የፈጸማት፤መሠረቱ አብ፣ህንጻዋ ወልድ፣ጉልላቷ መንፈስ ቅዱስ የሆነች በጎ ፈቃድና ነፃነት ያላት መንፈሳዊት ሀመር ነች።
- ቤተ ክርስቲያን በዚህ አለች በዚያ የለችም የማትባል ሰማያዊትና ምድራዊት የሆነች መንፈሳዊት ተቋም ናት ገላ 3፤25-29።

**2.6.4. ሐዋርያዊት ናት**፦የዓለምን ተስፋ የፈጸመው መሲህ ለሥራው ተከታዮች አድርጎ የሾማቸው 12ቱ ሐዋርያት መሪዎችና ቤተ ክርስቲያንን ከጌታ ተረክበው ያስረከቡን እነሱ ናቸው።

- የእስራኤል ዘሥጋ ታሪክ በ12ቱ የያዕቆብ ልጆች እንደተጀመረ የእስራኤል ዘነፍስ የክርስቲያኖች እምነት የክርስትና ምስክሩ የቅዱሳን ሐዋርያት ትምህርት ነውና ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊት ናት።

**ሐዋርያት ለክርስቶስ ቤተክርስቲያን ምስክር ለመሆን የበቁበት ምክንያት**

- ክርስቶስን በዓይናቸው አይተውታል በእጃቸው ዳስሰውታል፤ትምህርቱን በጆሮአቸው ሰምተዋል 1ዮሐ 1፤1-4፣ከትንሳኤውም በኋላ አይተውታል ዮሐ 21፤7፣በኢየሱስ ክርስቶስ ተልከዋል ማቴ 28፤19፣በስሙ

ሐዋርያዊ ተአምራት ሲፈጽሙ ኑረዋል።

- ❖ ሐዋርያት በዓይናቸው ያዩትን፣በጆሮቸው የሰሙትን የቤተክርስቲያንን ሕይወት ፈጽመዋል።ስለሆነም ሐዋርያት የተናገሩት ትምህርት ለክርስቶስና ለቤተክርስቲያን ምስክር ስለሆነ ቤተክርስቲያን ሐዋርያዊት ናት።
- ❖ ቅዱሳን ሐዋርያት ያደረጉት ተአምራት፣የጾሙት ጾም፣የጸለዩት ጸሎት፣ያስተማሩት ትምህርት፣የሠሩት ሥርዓት በሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን ተፈጻሚ ሆነዋል።

### 2.6.5.ሰማያዊትና ምድራዊት ናት

- **ሰማያዊት ቤተ ክርስቲያን** ስንል በሰብአዊ፣በማህበራዊ እና በመንፈሳዊ ሕይወቱ መልካም አገልግሎት በመስጠት በምድር ላይ መልካም ታሪክ አበርክቶ፣በሕይወተ ሥጋ ከመናፍቃን፣ከከሀዲያን እና ከኃጢአት ሲታገሉ የቆዩና ተጋድሎአቸውን ፈጽመው በአፀደ ነፍስ የጽድቅና የድል አክሊል ተቀዳጅተው የሚኖሩ የመዕመናን አንድነት ሰማያዊት ቤተ ክርስቲያን ተብሎ ይጠራሉ ራዕ 5፤9-13።
- **ምድራዊት-ቤተ ክርስቲያን**፡-ስንል-አባቶች-ካህናት፣አባቶች ምዕመናን፣እናቶች ምዕመናት ፣ወጣቶችና ህጻናት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ትዕዛዝ፣መመሪያ፣ህግና ሥርዓት ሲመሩ ምድራዊት ቤተ ክርስቲያን ተብሎ ይጠራሉ።ይህ በገነት መንግስተ ሰማያት የሚገኘው የክርስቲያኖች እና በምድር ያሉት የክርስቲያኖች አንድነት /ህብረት/ ግንኙነት ስላላቸው ሕያዋን ለሙታን፤ሙታንም ለሕያዋን ይፀልያሉ ይለምናሉ ሉቃ 16፤18-31።በጸሎት በምልጃ ይገናኛሉ።ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን ሰማያዊትና ምድራዊት ተብሏ ትጠራለች።ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን ማለት የክርስቲያኖች መኖሪያ ቤት እና የክርስቲያኖች አንድነት/ማህበር ማለት ስለሆነ 1ጴጥ 5፤13 1ቆሮ 11፤18 1ቆሮ 14፤19,35።

### 2.7.ቤተ ክርስቲያን ማን ናት?፡-

- በእግዚአብሔር ኃይልና ፈቃድ የተመሠረተች የመንግስተ ሰማይ አካልና የእግዚአብሔር ቤት ናት መክ 5፤1 መዝ 121፤1።
- መሠረቱ በጸናና በከበረ ድንጋይ ላይ የተመሠረተች የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነች 1ጴጥ 2፤4-6 1ቆሮ 3፤16።ክርስቶስ በቅዱስ ሥጋውና በክቡር ደሙ የዋጃት ራሱንም በመስጠት የወደዳት ናት ኤፌ 5፤25 አፌ 1፤22።የምትታይና የማትታይ/ሰማያዊትና ምድራዊት /ባህርይ/ ገጽታ/ ያላት መንፈሳዊት ተቋም ነች።
- ከእግዚአብሔር የተወለደች ወደሚደነቅ ብርሃን የተጠራች የመንግስተ ሰማይ ክፍል ናት ዮሐ 1፤11-13 ማቴ 13፤24-48 1ጴጥ 1፤9። ሙሽራውን ምትቀበል ሙሽሪት ለዓላማ/ለድል/ የተሰለፈ ሠራዊት ትመስላለች መኃ 6፤10 2ቆሮ 11፤1-2 /2ቆሮ 10፤3-6 ኤፌ 6፤10-17 ራዕ 17፤7። በጨለማ ላለው ዓለም/ሕዝብ/ የሕይወት ቃል የምታስተምር በተራራ ላይ ያለች መብራት ናት ማቴ 5፤14 ራዕ 2፤14። ከክብር ወደ ክብር የምትሸጋገር ከክርስቶስ ጋር በሰማያዊ ሀገር ለዘለዓለም ትኖራለች።2ቆሮ 3፤18 1ተሰ 4፤15-18።
- ከመናፍቃን ድርጅት፣ከፖለቲካ ድርጅት፣ከንግድ ድርጅት የተለየችና ነፃ ነች።እነዚህ ሁሉ በሰው ፍላጎት፣ብልጠት፣ምርምርና ቅንብር የተገኙ ናቸው።ቤተ ክርስቲያን ግን በእግዚአብሔር ሃሳብ የነበረች፣ከእግዚአብሔር የተገኘች ሐዋ 20፤20፣የክርስቶስ አካልና ቤተ መቅደስ የሆነች ክርስቶስ

የመሠረታት ማቴ 16፤16-18፣ነቢያት ሊመረምሯት ያልቻሏት ፈልጎ ያላዩዋት መንፈሳዊትና ዘለዓለማዊት የእግዚአብሔር ቤት 1ጴጥ1፤10-12። ሥራዋ ሲጠናቀቅ ወደ ተዘጋጀላት ሰማያዊ ሥፍራ የምትወሰድ የሰማይ ደጅ ናት ፊል 3፤20 ዮሐ 14፤1-3።

**2.8.የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን፡-**ቅዱሳን ሐዋርያትና ሌሎች ምዕመናን በማህበር ተሰብስበው ፀሎት የሚያደርሱባት የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ወንጌላዊው የማርቆስ እናት የማርያም ቤት ናት ሐዋ 12፤12።ይህችም አማናዊቷ ቤተ ክርስቲያን ፅርሐ ጽዮን የምትባለውና በበዓለ ሃምሳ የተመሠረተች ቅዱሳን ሐዋርያት በግንቦት 18 ቀን በ33 ዓ/ም መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉባት ቤት ናት።የክርስትና ትምህርት መላዋን የሮም ግዛትና ዓለምን ያዳረሰው ከዚህ በመነሳት ነው።በክርስቲያኖች መብዛት የሮማ ነገስታት በመደንገጥ ክርስቲያኖችን ለማጥፋት ከ40 እስከ 325 ዓ/ም ድረስ ለ300 ዓመታት ከፍተኛ ዘመቻ ያካሂዱ ነበር።በዚህ ጊዜ ክርስቲያኖችን በካታኮምብ ውስጥ ፀሎታቸውን ያደርሱ ነበር።ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያንን በይፋ ለመስራት የተፈቀደላቸው በታላቁ ቁስጠንጢኖስ ዘመነ መንግስት በ4ኛው መ/ክ/ዘመን በ320 ዓ/ም ነው።ቤተ ክርስቲያንን በደሙ የዋጃትና የመሠረታት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሪዋና አፅናኟ መንፈስ ቅዱስ ነው የሐዋ 20፤28።ክርስትና ከተመሠረተች ጀምሮ ክርስቲያኖች በየቤቱና በየዋሻው እየተሰባሰቡ ለፈጣሪያችን ምስጋና ሲያቀርቡ ከቆዩ በኋላ የመጀመሪያው ህንጻ ቤተ ክርስቲያን በአውሮፓ ክፍለ አህጉር በግሪክ ሀገር በፊልጵስዩስ ከተማ ተሠርታለች።

**2.9.ቤተ ክርስቲያን በዘመናችን፡-** በዘመናችን የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን አፍአዊና ውስጣዊ ሥራዋ በድርጅታዊ አቋም /በዘዴያዊ/ አሠራር የጠነከረች ስትሆን መንፈሳዊ ሕይወቷ ግን የላላ መስሎ ይታያል።ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ግን ውሳጣዊና አፍአዊ አሠራር ስትታይ በመንፈሳዊ ይዘቷ የጠነከረች በድርጅታዊ /መዋቅራዊ አቋም/ የላላች ትመስላለች።

- በዓለም ላይ ያሉት ታላላቅ የሃይማኖት ድርጅቶች በሰው የተጀመሩ ሲሆኑ ቤተ ክርስቲያን ግን በክርስቶስ የተመሠረተች ከክርስቶስ የተገኘች ክርስቶስ የሰውን ልጅ ክርስቶስ የራሱ ልጅ የሚያደርግባት መንፈሳዊ መንግስትና ከብሉይ ኪዳን የቀጠለች የአይሁድና የአህዛብ አንድነት ናት ማቴ 5፤17 ኤፌ 2፤15።

## መቅድም ክፍል ሦስት

## የቤተ ክርስቲያን ዕድሜ

የቤተ ክርስቲያን ዕድሜ በሰባት ዋና ዋና አርዕስቶች ይከፈላል

1. ዘመነ መላዕክት
2. ዘመነ አዳም /2256/
3. ዘመነ ኖህ /1207/
4. ዘመነ አብርሃም /430/
5. ዘመነ ሙሴ /607/
6. ዘመነ ዳዊት /1000/
7. ዘመነ ሐዲስ /2008/

**3.2. ዘመነ መላዕክት፡-**የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን የዕድገት ደረጃ ዘመነ መላዕክት ነው።ይህ ዘመን መላዕክት እስከተፈጠሩበት ዘመን /ሰዓት/ ድረስ እግዚአብሔር በባህርይ ሲሰለስ ሲቀደስ /ባህርይ ባህርዩን ሲያመሰግን/ የኖረበት ዘመን ነው፡መላዕክትን ግን

- ስሙን እንዲቀድሱና ክብሩን እንዲወርሱ፣በሰውና በእግዚአብሔር መካከል አገልግሎት እንዲሰጡ፣የሰውን ፀሎትና ልመና ወደ እግዚአብሔር፤የእግዚአብሔርን ምህረትና ቸርነት ለሰው ልጅ እንዲያደርሱ፣ብስራትን /መልካም ዜናን/ ለሰው ልጅ እንዲያደርሱ የሰውን ልጅ እንዲጠብቁና ዋስ ጠበቃም እንዲሆኑ ከፈጠራቸው በኋላ ግን መላዕክት ምስጋና ውዳሴና ውዳሴ በአርያም /በልዕልና/ ጀመሩ ኢሳ 6፤1።

**3.2.. <u>ዘመነ አዳም /2256</u>**/፡-ይህ ሁለተኛው የቤተ ክርስቲያን የዕድገት ደረጃ የሚቆየው ከአዳም እስከ ኖኅ /እስከ ጥፋት ውሃ/ ነው።ይህ የቤተ ክርስቲያን የዕድገት ደረጃ

- ከአዳም መፈጠር በኋላ ቀደም ሲል ብቻቸው ሲያመስግኑ የነበሩ መላዕክት ከአዳም ጋር ማመስገን የጀሩበት፣አዳምና ለአዳም መገልገያነት የተፈጠሩ ፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪያቸውን እንዲያመሰግኑ የታዘዙበት፣ለምሳሌ እንስሳት ዘሁ 22፤29፣እፅዋት የሙሴ በትር ዘፀ 4፤2፣የያዕቆብ በትር ዘፍ 30፤37 ዘሁ 17፤2፣ድንጋዮች ሉቃ 17፣1-12፣ውሃ መዝ 76፤16፣ መዝ113፤5 እነዚህ ሁሉ አመስግነዋል።ይህ ዘመን እግዚአብሔር ሰውን በመልኩና በአርአያው ፈጥሮ ሀብትና ሥልጣን የሰጠበት፣ለሰው የሚበላውንና የማይበላውን የወሰነበት፣የሚሠራበትና የሚያርፍበትን ቀን ለይቶ የሰጠበት፣ለሰው ልጅ ከሌሎች ፍጥረታት ተለይቶ የሕይወት እስትንፋስ የተሰጠበት፣ ለሰው /ለአዳም/ ሰባት ሀብታትን በመስጠት ክብሩን የገለጠበት እነዚህም ሀብታት

  1. የእግዚአብሔር መንፈስ/ሕይወት/
  2. የእውቀት መንፈስ
  3. የጥበብ መንፈስ
  4. የማስተዋል መንፈስ
  5. የምክር መንፈስ
  6. የኃይል መንፈስ
  7. መፈራት መንፈስ

- ሰው ከእግዚአብሔር ይጠብቃትና ይንከባከባት ዘንድ መኖሪያ ገነትን አገኘ፤የሕይወት መመሪያም ተሰጠው፣
- ዓለሙን እንዲሞላ መልካም ትውልድን እንዲያፈራና እንዲበዛ እግዚአብሔር ራሱ አባት፣አዘጋጅ፣ተቀባይና ሸኚ ሆኖ ሔዋንን ለአዳም ባርኮ ሰጠ ዘፍ 2፤18-25።

**3.3.1.ሰው በስህተት ጎዳና**፡-በገነት በክብር የተቀመጠው አዳም በአራዊትና በአጋንንት ተታሎ በመብል ምክንያት ክብሩን አጣ፣የችግር ዓይኑ ተከፈተ፣ራቆቱን ሆነ፣ፈሪ ሸሽተኛ ሆነ።እግዚአብሔርም እውነተኛ ሰውን አፍቃሪና ፈላጊ አባት በመሆኑ ድምፁን በማሰማት አዳምን የፈለገበትና ያጽናናበት፤እባብ፣አዳምና ሔዋን የተቀጡበት፣ምድር እሾህ አሜከላ እንዲታበቅል እግዚአብሔር ያዘዘበት ዘመን ነው።

**3.3.2. ሥርዓተ አምልኮ በዘመነ አዳም**፡- መላዕክት የጀመረትን ውዳሴና ቅዳሴ አዳምና ሔዋን የጀመሩበት፣ፍጥረታት በሙሉ እግዚአብሔርን ያመሰገኑበት ዘመን ነው።አዳም በዕጣን አቤል በበግ መስዋዕት አመስግነዋል።በዘመነ አዳም የቤተክርስቲያን የዕድገት ደረጃ ከዘመነ መላዕክት የተለየ ነው።እያንዳንዱ ሰው

በራሱ መስዋዕት ያቀርብ ነበር፡፡ነገር ግን የተወሰነ ጊዜ፣የተወሰነ ቦታ፣የተወሰነ ሰዓት፣የተወሰነ መስዋዕት፣የተወሰነ አገልጋይ ካህን፣የተወሰነ የመገልገያ/ንዋያተ ቅድሳት/ እና የአገልግሎት ኃላፊዎች አልነበሩም፡፡ይሁን ከዘመነ መላዕክት ይልቅ በዘመነ አዳም የቤተክርስቲያን የዕድገት ደረጃ አድጎ እናያለን፡፡

**3.4. ዘመነ ኖኅ /1207**/፦ዘመነ ኖኅ ማለት ከጥፋት ውሃ /ሰብአ ትካት ዘመን/ እስከ አብርሃም ድረስ ያለው ጊዜ ሲሆን የሚቆየውን 1207 ዘመን ነው፡፡በዚህ ዘመን የነበሩ ሰዎች በዝሙት ተግባር እግዚአብሔርን በማሳዘናቸው ምክንያት ዓለም በፍል ውሃ የተቀጣበት ዘመን ነው፡፡ነገር ግን እግዚአብሔር ሰውን ጨርሰው ለማጥፋት ባለመፈለጉ ደጉን ኖኅንና ቤተሰቡ እንዲተርፍ መመሪያ የሰጠበት ዘመን ነው፡

**3.4.1. አምልኮተ እግዚአብሔር በዘመነ ኖኅ**፦ ይህ ዘመን አምልኮተ እግዚአብሔር ከግለሰብ ወደ ቤተሰብ ያደገበት ዘመን ነው፡፡ኖኅ ሦስት ክፍል ያላት መርከብ ሠርቶ ኖኅ ሊቀ ካህን፣ልጆቹ ሴም፣ካምና ያፌት ካህናት ምሳሌነት፤ልጆቹና የልጅ ልጆቹ ደግሞ ምዕመናን ምሳሌ አድርጎ አገልግሎት የጀመረበት ዘመነ ነው፡፡ኖኅ በታቦት ምትክ በመርከቡ መካከለኛው ክፍል የአዳምን አፅም አድርጎ ይጸልይ ነበር፡፡መርከቧ የቤተክርስቲያን ምሳሌ ስትሆን መርከቧን የተሸከመው ውሃ ጥምቀት ምሳሌ ነው፡፡ኖኅ ከቤተሰቡ ጋር 150 ቀናት በኋላ ከመርከብ ወርደው ላዳናቸው ለእግዚአብሔር መስዋዕት አቅርበዋል፡፡እግዚአብሔርም መስዋዕታቸውን ተቀብሎ ቃል ኪዳን ገብተውላቸዋል ዘፍ 9፤8፡፡ ኖኅ ዘመነ በምድር ላይ የተፈጸሙ ቅጣቶች በውሃ መስጠምና የባቢሎን ግንብ መፍረስና ቋንቋ መደባላለቅ ናቸው፡፡

**3.5. ዘመነ አብርሃም /430/**፦ዘመነ አብርሃም የሚባለው እስከ ሙሴ ድረስ ያለው ዘመን ሲሆን የሚቆየውን ለ430 ዓመታት ነው፡፡ከአዳም እስከ ሙሴ ድረስ ያለው ዘመን ህገ ልቡና፣ዘመነ አበው /ዘመነ ፓትርያርክ/ ተብሎ ይጠራል፡፡ይህ ዘመን አብርሃም ለሃይማኖት ምስረታ ከካራን /ኢራን/ ወደ ከነዓን /ኢየሩሳሌም/ የተጠራበት ዘመን ነው፡፡

**3.5.1. በዘመነ አብርሃም አምልኮተ እግዚአብሔር**፦ዘመነ አብርሃም አምልኮተ እግዚአብሔር ከቤተሰብ ወደ ማህበረሰብ ወይም አካባቢ ያደገበት ዘመን ነው፡፡አብርሃም ከነቤተሰቡ፣ሎጥ ከነቤተሰቡ ከነሠራተኞቻቸውና ከነጎረቤቶቻቸው ጋር ተሰብስበው እግዚአብሔርን ማምለክ እንደጀመሩ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል ዘፍ 12፤7-9፡፡ይህ ዘመን

- አብርሃምመካነ መስዋዕት ሠርቶ ለእግዚአብሔር መስዋዕት ያቀረበበት፣እንግዳን የመቀበል ሥርዓትን የጀመረበት፣የመባረክ ክብር /ዕድል/ ያገኘበት፣ከመጀመሪያው ካህን መልኬ ጼደቅ ጋር ተገናኝቶ የተባረከበት፣አስራት በኩራት፣ቀዳሚያት መክፈል የጀመረበት፣የአማላጅነትና የነቢይነት ማዕረግ ያገኘበት፣አብርሃም ልጁ ይስሐቅን ለመስዋዕትነት በማቅረብ ታዛዥነትንና ታማኝነትን ያሳየበት፣ይስሐቅ ስለርብቃ መካንነት ጸሎት በማድረግ ያዕቆብንና ኤሳውን ያገኘበት፣የእግዚአብሔር ሕዝብ መለያ የሆነው ሥርዓተ ግዝረት የተሰጠበት፣የመላዕክት አገልግሎት በይፋ የተጀመረበት፡፡

- ያዕቆብ በምስጢራዊ ትርጉም የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌነት ያላት መሰላል ያየበትና ሐውልት አቁሞ ዘይት /ቅብዓ ቅዱስ/ በመቀባት የመጀመሪያውን የቤት ክርስቲያን መሠረት የጣለበት፣የቡራኬና የስግደት ሥርዓት የተሰራበት ዘመን ነው፡፡በአጠቃላይ በዘመነ አብርሃም የቤተ ክርስቲያን የዕድገት ደረጃ እጅግ ከፍ ብሎና ሰፍቶ የአምልኮ አፈጻጸም ሥርዓት የታየበት ዘመን ነው፡፡

**3.6. ዘመነ ሙሴ /607 ዓመት /**፦ከአዳም እስከ ሙሴ ድረስ ያለው ዘመን ህገ ልቡና ወይም ዘመነ አበው ተብሎ የሚጠራ ሲሆን የሚቆየውም 3,893 ዘመን ነው፡፡በታሪክ የሃይማኖት ዐረፍተ ዘመናት በሦስት ታላላቅ

ክፍሎች ይከፈላል።

1.ህገ ልቡና /ከአዳም እስከ ሙሴ/

2. ህገ ኦሪት /ከሙሴ እስከ ልደተ ክርስቶስ/

3. ህገ ወንጌል /ከልደተ ክርስቶስ እስከ ምፅዓት/

ዘመነ ሙሴ ወይም ብሉይ ኪዳን በሁለት ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል።

ሀ. ከሙሴ እስከ ዳዊት ለ. ከዳዊት እስከ ልደተ ክርስቶስ

**3.6.1.** **ከሙሴ እስከ ዳዊት**፡- ይህ ዘመን የሚቆየው 607 ዓመት ሲሆን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በጽሑፍ ህግና ሥርዓትን የሰጠበት፣አምልኮና የአምልኮ ሥርዓት ያደገበት፣ለሰው ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት የሚቻል መሆኑ የተረጋገጠበት፣የመንፈሳዊ በዓላት አከባበር ሥርዓትና የጾም ሥርዓት የተሰጠበት፣ሦስቱ ህግጋትና ሰባቱ ትዕዛዛት ለሰው ልጅ መመሪያ ሆኖ የተሰጠበት፣ታቦትና ጽላት ደብተራ ኦሪት ሥርዓት የተሰጠበት፣የቅብዓት፣የዕጣንና የመብራት ሥርዓት፣የቤተ መቅደስ ሥርዓት ንዋያተ ቅድሳት (ልብሰ ተክህኖ፣ሥርዓተ መስዋዕት፣የመስቀል ምልክት፣የመዝሙር ሥርዓት የተሰጠበት ዘመን ነው።ዘፀ 25፤8 ዘፀ 33፤7 ዘፀ 15፤15 ዘፀ 15፤1

**3.6.1.1.<u>በሙሴ ዘመን የተገኘው በረከት</u>**

- የሙሴ ነቢይነት ዘሁ 12፤6፣ክህነት ዘለዓለማዊ ሥርዓት መሆኑ የተረጋገጠበትና ሥርዓተ መዝሙር ለሰው ልጅ የተሰጠበት ዘመን ነው፡

**3.6.1.2. በዘመነ ሙሴ ህግና ትዕዛዝን ባለመፈጸማቸው የደረሰ ቅጣት**

- አቤሮን፣ዳታንና ቆሬን ከነሕይወታቸው መሬት ተከፍታ ዋጠች ዘሁ 16፤31
- የሙሴ እህት ማርያም ሙሴን በመዳፈሯ በለምፅ ተመታች ዘሁ 12፤1
- ከስቢንና ዘንቤሪን በሞት ተቀጡ
- አፊንና ፊንሐስ ቤተ መቅደስን ባለማክበራቸው ምክንያት ታቦተ ጽዮንን አስማረኩ እነሱም በጦርነት ሞቱ አባታቸውም ሞተ ሳሙ 4፤4
- ኦዛ በድፍረት ታቦተ ጽዮን የተቀመጠችበትን ሰረገላ በመንካቱ ተቀጣ 2ሳሙ 6፤6
- ሜልኮል የእግዚአብሔርን ምስጋና በመቃወሟ መካን ሆና ተቀጣች 2ሳሙ 6፤23

**3.6.2. ከዘመነ ዳዊት እስከ ልደተ ክርስቶስ፡-**

ዘመነ ዳዊት የሚቆየው ለ1000 ዓመታት ሲሆን የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ የነበሩ መርከበ ኖኅ፣ሐይመተ አብርሃም፣ደብተራ ኦሪት አልፎ ህንጻ ቤተ ክርስቲያን መሠረት የተጣለበት ዘመን ነው 2ዜና 7፤11 2ዜና 6፤6።ለ600 ዓመታት በደብተራ ኦሪት ውስጥ የቆየች ታቦት ጽዮን ንጉሡ ሰሎሞን በሠራው ቤተ መቅደስ የገባችበትና

እግዚአብሔርም ሰሎሞን የሠራውን ቤተ መቅደስ የስሙ መመስገኛ እንዲሆን መርጦ የተቀበለበት ዘመን ነው።2ዜና 6፤6 2ኛ**ዜና** 7፤11 ሰሎሞንም የቤተ መቅደሱን ምርቃት የዓለምን ነገሥታት የጋበዘበት 1ነገ 10፤1 2ዜና 9፤1-9 እና የቤተ መቅደስ ክብርም የተገለጠበት ዘመን ነው 2ዜና 8፤11።በተጨማሪም

- ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት አዜብ /ሳባ/ ወይም ማክዳ ከሰሎሞን ጋር ወደ ቤተ መቅደስ የገባችበት
- እግዚአብሔር ለሃይማኖት ምስረታ ከሀገር ሁሉ ኢየሩሳሌምን ከሰው ሁሉ ዳዊትን የመረጠበት መሆኑን የገለጠበት 2ዜና 6፤6 የአምልኮ ቦታንና አገልጋዮችን የመረጠበት ዘፀ 28፤1፣ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ሳባ በቤተ መቅደስ ተገኝታ የመስዋዕትና የፀሎት አፈፃፀም ሥርዓትን በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ግንኙነት በዓይኗ አይታ እግዚአብሔርን ያመሰገነችበት ዘመን ነው።

### 3.6.1. በዚህ ዘመን ከታቦትና ከቤተ መቅደስ የተገኘ በረከት

- በቤተ መቅደስ የእግዚአብሔር ክብር ሞላ 1ነገ 8፤10
- እግዚአብሔር በቤተ መቅደስ ዙሪያ ተገለጠ 1ነገ 9፤1-5
- የቤተ መቅደስ ቅድስና ዘለዓለማዊነት ተገለጠ 2ዜና 8፤11 2ዜና 7፤1-17።

### 3.6.2.በቤተ መቅደስና በታቦት ላይ አመጽ በሠሩት ሰዎች ላይ የደረሰ ቅጣት

- ኦዝያን የተባለ የይሁዳ ንጉሥ መንግስትንና ክህነትን ደርቦ ለመያዝ ከሊቀ ካህናቱ ጥናውን ነጥቆ ማጠን ሲጀምር በለምፅ ተቀጣ 2ዜና 26፤16
- የአሶር /ሶሪያ/ ንጉሥ ሰናክሬ ታላቁን ቤተ መቅደስ ሊደመስስ 80000 ወታደሮችን ይዘው ሕዝቅያስ ወደ ሚገዛት ወደ ኢየሩሳሌም ቢሄድም ሕዝቅያስ ወደ እግዚአብሔር ቢጨኽ የሰናክሬ ሠራዊት እንደቅጠል ረገፉ እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ ወታደሮቹን ቀጣ 2ነገ 18፤20 2ነገ 19፤3 2ዜና 32፤20።
- ናቡከደኖፆር የቤተ መቅደስ መገልገያ ንዋያተ ቅድሳት ማርኮ በትዕቢት ለግል አገልግሎት በማዋሉ እግዚአብሔር ለሰባት ዓመታት ሳር እየበላ በዱር እንዲኖር አደረገ ።ዳን 4፤28
- ልጁ ብልጣሶርም አባቱ ዘርፎ ያመጣውን የቤተ መቅደስ መገልገያ ንዋየ ቅድሳትን ለንጉሥ ነገሥቱ በዓል መዝነኛ በማድረጉ ተመዝንክ ቀለህ ተገኘህ በሚል ቃል ተገስጿል ዳን 5፤26።ሊቀ ካህናቱ ዘካሪያስ የመልአኩን ቃል አምነው ባለመቀበሉ ልሳኑ ተዘጋ ሉቃ 1፤19-23።ከዚህ በላይ የተገለጹ የዕድገት ደረጃዎች የምሳሌያዊ ቤተ ክርስቲያን የዕድገት ደረጃዎች ናቸው።

## መቅድም ክፍል አራት

## ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን

ኢትዮጵያ ወይም ኩሽ በሚለው መጠሪያ ብዙዎች ሀገሮች እንደተጠቀሙበት አንዳንድ የታሪክ ጸሐፊዎች የዘገቡ ቢሆንም ኢትዮጵያ የሚለው ስም በመጽሐፍ ቅዱስ በየጊዜው የመጥበብና የመስፋት ሁኔታ ያጋጠመው ቢሆንም በሰፊው ብዙ ሕዝብ አቅፎ የሚገኝ መሆኑንና የምድረ ኢትዮጵያ ማዕከል አክሱም ጽዮን እንደነበረች የሃይማኖት መጻሕፍት ያስረዳሉ።በሌላ መልኩም ወሰኗን ከግሪክ እነ ሆሜር እና ሔሮዶቱስ ከእስራኤል እነ ቅዱስ ዳዊትና ነቢዩ

ኢሳይያስ የመሠረቱትን ስያሜ ሳይለቅ በአሁኑ ዘመን በወሰን ተከልሎ ላለው ሀገራችንና ሕዝባችን ኢትዮጵያዊነት የግሉ መጠሪያ ሆኖ መቅረቱን እንመለከታለን።

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በቅድሳት መጻሕፍት፣በሥነ-ፍጥረት ጥናት /አርኪኦሎጂ/ እና በጥንት የታሪክ ሰነዶች በመካከለኛው ምስራቅ ሕዝቦችና ሀገሮች በአባይ ሸለቆ ዙሪያና በቀይ ባህር አካባቢ ከታወቁት ታሪካያውን አህጉሮችና ሕዝቦች ቅድሚያ ቦታን ይዘው ይገኛሉ።በዓለም ላይ የአንድ ሀገር ታሪካዊነትና ጥንታዊነት ከሚታወቅባቸው መለኪያዎች አንዱና ዋነኛው መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን ሁሉም ምሁራንና ሊቃውንት ይስማሙበታል።በዚህ መሠረት ኢትዮጵያ ሀገራችን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከ44 ጊዜ በላይ ስሟ ተጠቅሶ ይገኛል።መልክዓ ምድራዊ አቀማመጧ፣ወንዞቿ፣በዓለም ላይ በማዕድን ሀብት ተደናቂ መሆኗና በንግዷ ተደሳች ሀገር መሆኗ ተገልጿል።ዘፍ 2፤13 ሕዝ 29፤19 ኢሳ 18፤1 ኤር 3፤10 ኢዮ 28፤19 ኢሳ 43፤3። በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 2፡13 ‹‹የሁለተኛው ወንዝ ስም ግዮን ነው፤እርሱም የኢትዮጵያን ምድር ይከባል ይላል፤በዕብራይስጡ ‹‹ኩሽ . የሚለው ቃል ሦስት ትርጉሞች ይኖሩታል።

1ኛ. ከካም ልጆች መካከል አንዱ የሆነውን ኩሽን ያመለክታል ዘፍ 10፤6

2ኛ.የኩሽ ልጅ ነገድ የሆነው ሁሉ ኩሽ ወይንም ኩሻውያን ተብለው የሚጠሩ ሲሆን፤ትርጉሙ መልከ ጠይም ለሆነው ሕዝብ ሁሉ እንደመጠሪያ ስያሜ መሆኑ ይታወቃል፤ይሁንና መልከ ጠይም የሆነው ሕዝብ ሁሉ የኩሽ ዘር ነው ማለት አይቻልም።

3ኛ.መልከ ጠይም የሆነው ሕዝብ የሚኖርበት አካባቢ መጠሪያ ስም ከግብጽ ደቡብ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ያለው አካባቢ መሆኑ ታውቋል።ከላይ እንደተገለጸው **ኩሽ** የሚለው ቃል **ዘርዐ ትውልድን** የሚያመለክትና **ዘርዐ ትውልድ የሚኖርበት አካባቢ የመጠሪያ ስም** ሆኖ መገኘቱን ነው፤ይህም ኢትዮጵያ መሆኗ ተረጋግጧል።መዝ 67፡31 አሞ 9፡7 ስለሀገራችን ታሪክና ጥንታዊነት ለመረዳት ከመሠረቱ ጀምሮ ማጥናት ያስፈልጋል።

### 4.1. ነገደ ካም /ነገደ ኩሽ/

ኩሽ የኖኅ የልጅ ልጅ ነው።ለካም አራት ልጆች ነበሩት፣እነዚህም ኵሳ /ኩሽ/፣ሚስራይ፣ፋይና ከነዓን ይባሉ ነበር።ኵሳም /ኩሽ/ አምስት ልጆች ወለደ።እነዚህም ሳባ፣ኤዌልጥ፣ሰብታ /አቢስ/፣ሬጌምና ሰበቅታ ናቸው።

ሬጌም ሳባንና ዮዳዳን ይልወዳል።እነዚህም በእስያ ደቡብ ሲኖሩ በኋላ ወደ ክፍላቸው ወደ አፍሪቃ እየተሻገሩ መጥተው ከኢትዮጵያ ጀምሮ እስከ ምስር /ግብጽ/ ወሰን ያለውን አገር እያቀኑና እያለሙ፣ከተማም እየሠሩ ኖረዋል።ዋና ከተማቸውን መርዌ ይባል ነበር።በኋላ ግን በዘመን ብዛት ጥቂት በጥቂት እያሉ እስከ አክሱም ወጥተው በአክሱም አጠገብ ሳባ የሚባለውን ከተማ ሠርተው ይኖሩ ነበር።የኩሽ ልጆች ከእስያ ወደ ኢትዮጵያ ያደረጉት ጉዞ ከክርስቶስ ልደት በፊት 3000 ዓመት አካባቢ እንደሆነ ይገመታል።በዘመን ብዛት እየበዙ ሲሄዱ መንግስት አቋቋሙ።በኢትዮጵያ የነገሡትን የነገደ ካምን ነገሥታት ስምና ቁጥር ስንመለከት ከካም ከሦስተኛው ትውልድ ከሰብታህ ይጀምራል።ሰብታህ /ሳቤታ/ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ2545-2513 ለ30 ዓመት ነግሠዋል፣ከሰብታህ እስከ ጲኦሪ 1ኛ /ከ2000-1985/ ድረስ ከነገደ ካም በኢትዮጵያ የነገሡት ነገሥታት 22 ሲሆኑ ዘመኑም 560 ይሆናል።

### 4.2. ነገደ ሴም /ነገደ ዮቅጣን/

ኖኅ ሴምን ይወልዳል፣ሴም ኤቦርን፣ኤቦር ዮቅጣንን ይወልዳል።ዮቅጣንም 13 ልጆች ነበሩት።ስለዚህም ነገደ

ዮቅጣን የሴም ልጆች ናቸው፡፡1ዜና 1፡17-20/ ሳባ የዮቅጣን 10ኛ ልጅ ነው፡፡1ኛ ዜና 1፡20-21/ የነገደ ዮቅጣን መኖሪያ በእስያ ምድር ነበር፡፡ዘፍ 10 ከ13ቱ የዮቅጣን ልጆች አምስቱ ሳባ፣ኦባል፣አፌር፣አቤማኢል፣ዐዊላ ቦታ ስለጠበባቸው ከወንድሞቻቸው ተለይተው የእስያ ደቡብ ወደ ሆነው ወደ የመን መጡ፡፡ በየመን በመልካም ኑሮ ሲኖሩ የሕንድ ነገሥታት ጦር እየላኩ የየመንን ሀገር እየወጉ ስለአውኩዋቸው ሦስቱ ሳባ፣ኦባል፣አፌር ከሁለቱ ወንድሞቻቸው ተለይተ የነገደ ካም ንጉሥ ጺኦሪ 1ኛ በነገሠበት ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ገቡ፡፡ከጥቂት ዘመናት በኋላ የእነዚህ ሦስቱ ነገደ ዮቅጣን እርስ በርሳቸው ካለመስማማታቸው የተነሳ ተለያይተው ለየብቻቸው አገር ያዙ፡፡ከነዚህም ሳባ የተባለው ትግራይን ኦባል የተባለው አዳልን /አፋር/ አፌርም ኦጋዴን ያዙ፡፡

ከነገደ ካም ወገን በኢትዮጵያ ነግሦ የነበረው ጺኦሪ 1ኛ እነዚህ ሦስቱን ነገደ ዮቅጣንን 5 ዓመት አስገብሮዋቸዋል፡፡በኋላ ግን ራማ የሚባል የሕንድ ንጉሥ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ጺኦሪን ወግቶ መንግስቱን በወሰደበት ጊዜ እነዚህ ሦስቱ ነገደ ዮቅጣን ከኦጋዴን፣ከአዳል እና ትግራይ ተላልከውና ተስማምተው በትግራይ ላይ ከነበረው ከሳባ ዘር አክናሁስን ሳባ 2ኛ ብለው አንግሠው ከሕንድ ንጉሥ ከራማ ጋር ተዋግተው ድል አደረጉና ገደሉት ሀገሪቱም ብሔረ አግዓዚ ተባለች፡፡በግዕዝ ቋንቋ አግዓዛ ማለት ነፃ አወጣ ማለት ነው፡፡ቋንቋቸውም ግዕዝ ተባለ፡፡

### 4.3. በሌላ ታሪክ ደግሞ ስለኢትዮጵያ ቀጥሎ ያለው ተጽፎአል

ኢትዮጲስ 2ኛ ሳባ የተባለው የአክናሁስ የልጅ ልጁ የቡልቃ ልጅ ነው፡፡ኢትዮጲስ 1ኛ ከ3644-3700 ዓ.ዓ ከልደተ ክርስቶስ በፊት 56 ዓመት ነገሠ አገሩም በስሙ ኢትዮጵያ ተባለ ይባላል፡፡ኢትዮጲስ 1ኛ ከሞተ በኋላ በመንግስቱ ልጁ ላክንዱን ተተካ፤ኢትዮጲስ 1ኛ ልጆች 5 ናቸው፡፡እነርሱም ላክንዱን፣ሳባ፣ኖባ፣በለው፣ከለው ናቸው፡፡የመጀመሪያ ልጁ ላክንዱን መንግስትን ወረሰ፡፡4ቱ ግን የአገር ርስትን ተካፍለው ያዙ፡፡

አግዓዚያን የተባሉት የነገደ ዮቅጣን ነገሥታት ቁጥር 52 ሲሆን ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ1985 ዓመት ጀምሮ ቀዳማዊ ምኒልክ እስከ ነገሡበት እስከ 982 ዓመት ለ1003 ዓመት ቆይተዋል፡፡ሴማውያን /ነገደ ዮቅጣን/ ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ2000 ዓመት በኋላ ሲሆን ሁለቱም ዝርያዎች የገቡት በሰሜን ኢትዮጵያ ክፍል በሆነው በአክሱም በኩል ነው፡፡እነዚህ ሁለት ሳባውያን ሕዝቦች ሳቢያን የተባለና ፊደላቱ ከፊኒቃውያን ፊደል ጋር የተዛመዱ የራሳቸው የሆነ ቋንቋና አጻጻፍ ነበራቸው፡፡ከዚያም በኋላ የሳባውያን ፊደል ከራሳቸው ጋር አዋሕደውና አሻሽለው አዲስ ቅርጽ ያለው ኢትዮጵያዊ ፊደል ፈጠሩ፡፡ይህም ፊደል ግዕዝ በመባል ይታወቃል፡፡ግዕዝ በአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ከግራ ወደ ቀኝ እንዲጻፍ ስለተደረገ እንደሳባውያን ከቀኝ ወደ ግራ የሚጻፍና የሚነበብ ሳይሆን የራሱ የሆነና የተለየ ከግራ ወደ ቀኝ የሚጻፍ የአጻጻፍ ዘዴ አለው፡፡ከመላው የአፍሪቃ አህጉር ከግብጽ በቀር የተለየ የሥነ ጽህፈት ትውፊት ለብዙ ሺህ ዓመታት ያላት ኢትዮጵያ ብቻ መሆኑዋ ራሱ የሥልጣኔ ግዙፍ ምስክር ነው፡፡

**4.4. ኢትዮጵያ የሚለው ስያሜ**፡- ኢትዮጵያ የተመሠረተችው ከጥፋት ውሃ በኋላ በዘመነ ኖኅ በኖኅ የልጅ ልጆች በካምና በሴም ዘሮች እንደሆነ ከላይ ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡የካምና የሴም ዘሮች ኢትዮጵያን ሲያቀኑ እምነታቸውን፣ሥርዓታቸውን፣ባህላቸውንና ትውፊታቸውን የአያታቸው የኖኅ የወላጆቻቸው የካምና የሴም ሃይማኖታዊ፣ማህበራዊና ሰብአዊ ህግና ሥርዓት ተመርጉዞ መሆኑን አሁን በህብረተሰቡ መካከል ያለው ሃይማኖታዊና ማህበራዊ ሥርዓት ማስረጃ ነው፡፡በዚህ መሠረት ኢትዮጵያ የሚለው ስያሜ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይዘትና ከጥንት የታሪክ መረጃዎችና ከስነ ምርምር አንጻር ምስጢራዊ ትርጉም ያለው መሆኑን ታሪክ ይገልጸዋል፡፡

**ኤቶስና ኦፕሲስ፡-** ኢትዮጵያን በስነ ሰብእ ጥናትና ምርምር ከሰው ልጆች መካከል ቀለመ ጠይሞች ሆነው የሚገኙት ዘርዐ ትውልድ ሲሆኑ የሚኖሩበት አካባቢ ከስማቸው ጋር የተዛመደ መልክ ያለው በመሆኑ መልከ ጠይም/መልከ ጠይመ ከሚለው ከግሪክ ቃላት ተወስዶ ኢትዮጵ ተብሎ ለሕዝቡ የዓይነት መጠሪያ ስም ሆኖ መስጠቱን ታሪክ ይነግረናል፡፡

**ኤቶስ** ማለት ዋዕይ በረሃማ ሙቀታማ ማለት ሲሆን **ኤፕሲስ** ማለት ደግሞ ገጽ አርአያው የጠየመ /የወየበ/ ሕዝብ ማለት ነው።ሁለቱም ቃላት ሲጣመሩ ኤቲኦፒያ ወይም ኤቲኦፒስ የሚል ቃል ይወጣዋል።

**ኤቲኦፒያ** የሀገሪቱን ቆላማነት ያሳያል ቆላ በረሃ ዋዕይ የትኩሳት ሀገር ማለት ሲሆን **ኤቲኦፒስ** ቢል የሕዝቡን ምንነት በዋዕይ በፀሐይ የለዘበ የጠቆረ የበረሃ የቆላ ሻንቅላ ማለት ነው ሲሆን ሀገርቷን በመመልከት ቆላና ሞቃት ሲሉ ሰውን ደግሞ ጠይም ቀይ ዳማ በማለት ይጠራሉ።

**በሆሜር መጽሐፍ** ደግሞ ቀዩን ወይን ኢትዮጵያ ስለሚለው ኢትዮጵያዊ ማለት ቀይ የቀይ ቀለም ያለው ሕዝብ ማለት ነው።እንደሆሜር አገላለጽ ኢትዮጵያ ማለት ቀይ የቀይ ዳማ ቀለም ያለው ሕዝብ መኖሪያ ማለት ነው።**ሆሜር/አሚሮስ/ ከ**ጥንት ሊቃውንት መካከል ቅ.ል.ክ በፊት 800 ዓ/ዓ የነበረ ግሪካዊ የታሪክ ፀሐፊና ገጣሚ ጥንታዊ ምሁር ሲሆን የተነሳውም ኢትዮጵያ ታቦተ ጽዮንን ተቀብላ በአክሱም ላይ ቤተመቅደስ ሠርታ አገልግሎት እየሰጠች ባለችበት ዘመን ነው።ምክንያቱም ታቦተ ጽዮን ወደ ኢትዮጵያ የገባችው ከክርስቶስ ልደት በፊት 1000 ዓ/ዓ ቀደም ብሎ ስለሆነ ሆሜር በተነሳበት ዘመን ሀገራችን ሰፊ የሕገ ኦሪት ሥርዓት በማካሄድ ላይ ትገኛለች።ሆሜር ስለኢትዮጵያን ሕዝብ ማንነት በተናገረበት ድርሰቱ አራት ዐበይት ነገሮችን አስቀምጧል

1. የኢትዮጵያ ሕዝብ በጉልበት ኃያል ነው።
2. የኢትዮጵያ ሕዝብ በውበት የተደነቀ ነው።
3. የኢትዮጵያ ሕዝብ በጠባይ ጭምት ነው።
4. የኢትዮጵያ ሕዝብ የትህትና፣የቸርነት፣የበጎነት ባለቤት ነው ካለ በኋላ

ይህ ታላቅ ሕዝብ ክቡር በመሆኑ ከግሪክ አስራ ሁለት አማልክቶቻችን አንዱ እንደአባት የሚቆጠረው ዋናውና የመጀመሪያው ዘውስ ኢትዮጵያውንን ለማየትና ከእነርሱም ጋር ምግብ ለመብላት ወደ ውቅያኖስ ወረደ በማለት አስቀምጧል።ይህ የሚያስረዳን ኢትዮጵያውንን የሚወዳደር ባለመኖሩ ትልቁ አምላካቸው ከትልቁ ሕዝብ ጋር መዋል የሚቻል መሆኑን ነው።

**ሔሮዶቱስ** ቅደመ ክርስቶስ ልደት 490 ዓ/ዓ የነበረ የምዕራባዊያን የታሪክ አባት ተብሎ የሚጠራው የታሪክ ፀሐፊ ሲሆን በግብጽ ለብዙ ጊዜ የተቀመጠ በመሆኑ ባገኘው በቂ ማስረጃ መሠረት ሀገራችን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውንን ሲያሞግስ **‹‹ኢትዮጵያውያን በውበት፣በቁመት፣በጉልበት፣ከሰው ሁሉ ብልጫ** ያላቸው ሕዝቦች ናቸው።ዓሳ **ተመጋቢዎችና የዕድሜ ባለፀጋዎች** ናቸው።ካለ በኋላ ኢትዮጵያ እጅግ ያማሩ ሕዝቦች፣ባለደምግባት ቆንጆዎች፣ውቦች ሰዎች ያሉባት ርኅራኄያቸው እንደ እግዚአብሔር ነው።በሰፈው ሜዳ ለመንገደኞች ማለፊያ የሚሆን ድግስ እየደገሱ ያስተናግዳሉ ምንም ቢሆን መንገደኛው የሚበላውን አያጣም።በዕድሜያቸው ከ100 እስከ 130 ዓመት ይቀመጣሉ።ነውርና ክፉ ነገር በአገራቸው የተጠላ ነው።የጤና ምንጭ የሚሆኑ ውሆች አሏቸው።ይህንን በጠጡ ጊዜ ሰውነታቸው ይታደሳል።በሀብት እጅግ ባለጠጎች ናቸው።ድንበሯም ከጂቡቲ ባህር ዳር እስከ ስናር ነጭ ዓባይ ድረስ ነው።በቆላው ልዩ ልዩ አትክልትና ፍራፍሬዎች ይገኙባቸዋል።በደቡብ ቆላ ደግሞ የዕጣን፣የላስቲክ ዛፍ፣የሰንዴል እንጨት፣ክርቤ ሌላ ብዙ ቅመማ ቅመም የሚበሉ ፍሬዎች ይገኛሉ።የከበረና የጠጠር እንቁ፣ሉልም፣ዝባድም ልየ ልዩ ዓይነት ሽቱ አሉበት። በማለት ተናግሯል።/የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ አለቃ ታዬ/

**ሰባው ሊቃናት**፡- በ2ኛው በጥሊሞስ ዘመነ መንግስት የተነሱት ሊቃውንት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ ቋንቋ የተረጎሙ ሲሆን ዘመኑም ቅድመ ክርስቶስ ልደት 284 ዓ/ዓ ነው።ሰባው ሊቃናት ነቢዩ ሙሴ የኩሽ ምድር እያለ የጻፈውን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ክፍልን ኢትዮጵያ እያለ ጽፈዋል።የኩሽ ሁለተኛ

ስም በሆነው ኢትዮጵስ ኢትዮጵያ በማለት የምንኖርባት ሀገራችንን እንደጻፈ ታሪክና ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል፡፡

**4.5. የኢትዮጵያ ድንበር**፡- ጥንት የኢትዮጵያ ግዛት ከደቡብ ግብጽ እስከ ህንድ ውቅያኖስ መዳረሻ ይደርስ እንደነበረ የታሪክ ፀሐፊው ሔሮዶቶስ ጽፈፏል፡፡ከጂቡቲ ባህር ዳር እስከ ስናር ነጭ አባይ ድረስ እንደነበር የታሪክ ምሁር ሆሜር ጽፈፏል፡፡በሰሜን ከአስዋን፣በምስራቅ ከህንድ ውቅያኖስና በምዕራብ ከሊቢያ ጋር እንደምትዋሰን ሲገልጽ በደቡብ በኩል ግን ያላትን ወሰን ለማወቅ እንደልቻለ ሲያመለክት ቅርጽዋ ወደ ደቡብ በሚመለከተው አቅጣጫ ማዕከልነት በደቡብ ምስራቅ ወደ ደቡብ ምዕራብ እንደነበር ሮማዊ ሊቅ ጥሊኒ አመልክቷል፡፡ኢትዮጵያና የሕዝቧ ማንነት በታሪክ ሰዎችና በፈላስፎች ብቻ ሳይሆን በታላቁ ቅዱስ መጽሐፍም የታወቀች ሀገር ናት፡፡

**4.6. ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ**፡- ኢትዮጵያ ሀገራችን የጥንት ስልጣኔ ምንጭ፣ኦሪትና ወንጌልን ከእስራኤል ቀጥላ በምድሯ ላይ ያስተናገደች ብቸኛ ሀገር፣ለዘመናት ያልተቋረጠ በትረ መንግስት የተፈራረቀባት፣በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ሴት ንግስት ያነገሰች፣በሌላ ዓለም የሌሉ ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት ባለቤት፣ከአፍሪካ በራሷ ቋንቋና ፊደል ያላት ብቸኛ ሀገር፣የጽላተ ሙሴና የግማደ መስቀልን በረከት የያዘች፣በሽታን የሚያጠፉ ጠበል የሚፈልቅባት፣ጠፍተው የነበሩ መጽሐፈ ሄኖክና መጽሐፈ ኩፋሌ የተገኘባት፣የዓለም ጥቁር ሕዝብ የታሪክ እንብርት፣ለመጀመሪያ ጊዜ በ4ኛው መ/ክ/ዘመን በንጉሥ ኢዛና የመስቀል ምልክት ያለው ሳንቲም ያስቀረጸች፣ለነጻነት ተምሳሌት የሆነች፣ዘመናት ያልሻራቸው የኪነ ጥበባት ክምችት ያላት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ምንጭ ያደረጉ ባህሎች ባለቤት የሆነች ብቸኛ ሀገር ናት፡፡

- ✓ ሙሴ የሥነ ፍጥረት አቀማመጥ በገለጸበት መጽሐፍ ኢትዮጵያ በግዮን ወንዝ የተከበበች ሀገር መሆኗን ጽፏል ዘፍ 2፤13፡፡ግዮን የተባለውም ወንዝ ዓባይ ወንዝ ሲሆን ይህም ወንዝና ተከዜ ግብጽንና ሱዳንን ሲመግቡ እንደሚኖሩ ዐበይት ነቢያት ይናገራሉ ኢሳ 18፤1 ሕዝ 29፤9-11፡፡
- ✓ በማዕድን በዓለም ተደናቂና የከበረች ሀገር ስለመሆኗ ኢዮ 28፤18-19
- ✓ በእግዚአብሔርና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን የማያቋረጥ ፍቅርና በአንድ አምልክ የምታምን ስለመሆኗ መዝ 67-31
- ✓ ሕዝቦቿ ለአምልኮተ እግዚአብሔር ቀናኢ ስለመሆናቸው ኢሳ 45፤14 መዝ 71፤9-10 ዳን 11፤43-45
- ✓ ኢትዮጵያ ሌሎች ሀገሮች እንደምሳሌ መጠቀሷ አሞ 9፤7
- ✓ ኢትዮጵያውያውን በኃይላቸው ተመክተው በሚሠሩት ሥራ ነቢያት ይገስጿቸው ነበር 2ኛ ዜና 14፤9-13 ሶፎ 2፤12 ሕዝ 30፤5
- ✓ ኢትዮጵያውያን መልካቸውም እንደቁራ ያልጠቆረ እንደለምጽም ያልነጣ አሳ የሚመስል ጠይም መሆኑን ኤር 13፤23
- ✓ ዜጎቿ በመጽሐፍ ቅዱስ ከፍተኛ ሥፍራ እንዳላቸው ማቴ 12፤42
- ✓ ግዛቷ እጅግ ሰፊ በመሆኑ ዜራህ/ዝሪ/ በሚባለው ንጉስ እየተመሩ ዘምተው ምድረ ይሁዳን ከያዙ በኋላ በንጉስ አሳ ድል ሆነዋል 2ኛዜና 13፤1
- ✓ በንግድ ሥራ በዓለም የታወቀች ስለሆነች ሕዝቧ በንግዳቸው በልጽገውና ተደስተው ይኖር ነበር ኢሳ 43፤3
- ✓ መጽሐፍ ቅዱስ የኢትዮጵያን ሕዝብና ምድር ሁል ጊዜ ከግብጽ ጋር በማያያዝ ይጽፋል መዝ 68፤3 ኢሳ

20፤3

- ✓ ሌሎች ስለኢትዮጵያና ስለኢትዮጵያውያን የሚናገሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች መዝ 86፤4 መዝ 73፤14 ኢሳ 11፤11 ሶፎ 3፤10 ዘፍ 12፤1-9 2ኛነገ 19፤9 2ኛዜና 16፤8 2ኛዜና 21፤16 ዘኍ 12፤1 2ኛ ዜና 12፤4 አስቴር 1፤1 አስቴር 8፤9 ኤር 39፤16 ሕዝ 30፤9 ሕዝ 38፤5 ናሆ 3፤9 የሐዋ 8፤26-39።

  - ❖ **ኢትዮጵያ በሚለው ስም ይጠቀሙ የነበሩ ሀገሮች ከሊቢያ ደቡብ የሚገኘው ሀገር፣ሱዳን/ኑቢያ/፣ህንድና የዓረብ ሀገሮች በዚህ ስም ይጠቀሙ ነበር።**

4.7. **የኢትዮጵያ ጥንታዊ ቋንቋ፦**ኢትዮጵያ በህገ ልቦና፣በህገ ኦሪትና በህገ ወንጌል እግዚአብሔርን ስታመልክ የኖረችና የምትኖር ሀገር ናት።በዓለም የምትታወቅበት የድንጋይና የሸክላ ሐውልቶች፣በብራና በግዕዝ ቋንቋ ተጽፈውና ተስለው ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፉ የመጡት ቅርጾች ሀገራችን የእምነት፣የጀግንነት፣የሥልጣኔና የባህል ባለቤት መሆኗን የሚያሳይ ነው።የኢትዮጵያና የቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ለትውልድ ሊደረሱ የቻሉት በግዕዝ ቋንቋ በብራናና በወረቀት ተጽፈው በሚገኙት መጻሕፍት ነው።እስካሁን ድረስ ያልተተረጎሙና ለምርምር ብዙ የግዕዝ ቋንቋ እውቀት የሚጠይቁ ብዙ የእምነት፣የሥነ-ምግባር፣የታሪክ፣የህግና የሥርዓት መጻሕፍት እጅግ ብዙ ናቸው።እስከ 12ኛው መ/ክ/ዘመን ድረስ በሀገራችን ሥርዓተ መንግስት የሚመራበትና የሕብረተሰቡ የጽሑፍና የቃል መግባቢያ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሆኖ የቆየው ግዕዝ ነበር።ከ12ኛው መ/ክ/ ዘመን በኋላ ግን በሰዋሰው ረገድ ሙሉ በሙሉ የግዕዝ ቋንቋ ሥርዓት የተከተለው የአማርኛ ቋንቋ በቦታው ተተክቷል።የግዕዝ ቋንቋ ከድንጋይ ዘመን እስከ ብራና ዘመን፣ከብራና ዘመን እስከ ወረቀት ዘመን በሥነ ጽሑፍ ሲያገለግል የቆየ ጥንታዊ ቋንቋ ስለሆነ ኢትዮጵያን የሥነ-ጽሑፍና የሥነ-ጥበብ ባለቤት እንድትሆን አድርጓታል።በግዕዝ የተጻፉትን የቅኔና የታሪክ፣የሃይማኖትና የፍልስፍና ድርሰቶችን አንብቦ ለመረዳትና በግዕዝ ቋንቋ የተጻፉትን መጻሕፍት በሌላ ቋንቋ ከተጻፉት ጋር በማነጻጸር ጥናትና ምርምር ለማድረግ፤በግዕዝና በአማርኛ መካከል ያለውን የቃላት ተዛምዶ ለይቶ ለማወቅ፤ዘመናውያን የሆኑ የሳይንስና የፍልስፍና ጽንሰ ሐሳቦችን ለመተርጎምና ስያሜ ለመስጠት የሚያስችሉ ጥናቶችን ለማድረግ የግዕዝ ሰዋሰው ትምህርት ማወቅ እጅግ አስፈላጊ ነው።በ*አፍሪካ ክፍለ ዓለም የራሷ* ፊደልና ጽሑፍ ያላት ሀገር ኢትዮጵያ ብቻ ናት።ጥንታዊ ብሔራዊ ቋንቋም ግዕዝ ይባላል።የዓለም ቋንቋ ሁሉ የሚጠራው በየነገዱ ስም ነው።ግዕዝ ግን በራሱ በገንዘቡ እንጂ በማንም ስም አልተጠራም።ግዕዝ ማለትም የቋንቋ ስም አዳማዊ ቋንቋ የፊደል ስም የንባብ ስም የዜማ ስም ሲሆን ዘይቤውም አልፋ እንደማለት ነው።አንድ መጀመሪያ በኵር ቀዳማዊ ርዕስ ጥንት ማለት ሲሆን ምስጢሩ ግን ጥንታዊ አዳማዊ ልሳን ማለት ነው።የግዕዝ ቋንቋ በኢትዮጵያ ጥንታዊ የጽሑፍ ቋንቋ መሆኑ ቢታመንም የጽሑፍ ቋንቋ የሆነበት ዘመን በትክክል አይታወቅም።ዶ/ር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ Ancient Medieval History of Ethiopia በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 12 ላይ እንደገለጹት ከክ.ል.በኋላ በ3ኛው መ/ክ/ ዘመን በሐውልት ላይ የተቀረጸው ጽሑፍ በኢትዮጵያ ቀዳሚው የግዕዝ ጽሑፍ እንደሆነ ይታመናል ብለዋል።

**4.8**. **የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር፦**የዘመን አቆጣጠር ማለት ስለማህበራዊ ኑሮ ጠቀሜታና የሃይማኖት ተግባሮችን ለማከናወን በሚያገለግል መልኩ ተፈጥሮአዊውን የወቅቶች ክፍፍል እርስ በእርሳቸው የማመቻቸት ዘዴ በእርሱ ላይ አመቺ የሚሆን የዘመኖች ሂደት የሚመሠረትበት የደንቦች ስብስብ ነው።የዘመን አቆጣጠር ዓመትን ወስኖ ወደ ትንንሽ ክፍሎች በመከፋፈል እነዚያ ትንንሽ ክፍሎች ደግሞ ስንት ቀኖች እንደሚኖራቸው የመወሰን ደንብ በመሆን የሕዝብና የሃይማኖት በዓላት ቀኖችን ለመወሰን ይረዳል።የዘመን አቆጣጠር ሲባል እንደ ቀኖች ወሮችና ዓመቶች ባሉ የጊዜ ርዝመቶች በመከፋፈል ዘዴ ደንብንና ሥነ-ሥርዓትን ማዘጋጀት ነው።

በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ጥንት ከሚለው ቃል ይጀምራል።ጥንትነቱም ከፍጥረተ ዓለም ከፀሐይ ከጨረቃና

ከከዋከብት ነው።የፀሐይ ጥንታት ሦስት ሲሆኑ እነርሱም ጥንተ ዕለት፣ጥንተ ቀመርና ጥንተ ፆን ናቸው።ዓለም የተፈጠረበት እሁድ ጥንተ ዕለት ይባላል።እሁድና ሰኞ ዕለተ ጠቢባን ይባላሉ።ምክንያቱም ጠቢባን ሥላሴ ከዕለታት መርጠው ዓለምን ስለፈጠሩባቸው ነው።በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ከክርስቶስ ልደት በፊት ዘመን የተቆጠረበት ጊዜ 5500 ዓመት ነው።ይህም ዘመነ ፍዳ ዓመተ ኩነኔ ዘመነ ብሉይ ይባላል።ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ጀምሮ ያለው ዘመን 2009 ዓመት ሲሆን እርሱም ዓመተ ምህረት ዘመነ ሥጋዌ ዘመነ ሐዲስ ዘመነ መሲህ ይባላል።ዘመነ ብሉይና ዘመነ ሐዲስ ሲደመሩ የድምሩ ውጤታቸው ዓመተ ዓለም ተብሎ ይጠራል።በዚህ አሁን ባለንበት ዓመተ ዓለም 5500+2009 =7509 ዓመት ነው።

## ምዕራፍ አንድ

## ኢትዮጵያ በሃይማኖት

የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ዓለማትንና በውስጣቸው ያሉትን ፍጥረታት በፈጠረ በልዑል እግዚአብሔር በማመንና ለህግጋቱም በመገዛት ለሰው ልጆች የተዘጋጀውን ድህነት በእምነት አግኝተዋል።በዚህ የረጅም የሃይማኖት ታሪክ ውስጥ በአብነት የሚጠቀሱት ሕዝበ እስራኤል ናቸው።እግዚአብሔር አምላክ ለሰዎች ሕግን ሲሰጥ መላውንም የሰው ልጅ ከተፈረደበት የኃጢአት ሞት ነጻ ያወጣው በአብርሃም ዘር አማካኝነት ነው።ለሰዎች የተሰጠው ህግም በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ማለትም ሕገ ልቡና፣ሕገ ኦሪት እና ሕገ ወንጌል ተብለው ይከፈላሉ።በነዚህ ሕግጋት የተጠቀሙም ያልተጠቀሙም ሰዎች ነበሩ አሁንም አሉ ወደፊትም ይኖራሉ።ሀገራችን ኢትዮጵያም በነዚህ ህግጋት ተመርታለች በመመራት ላይም ትገኛለች።

1.1. **ሕገ ልቡና**፡-ሕገ ልቡና ለሰው ጥንተ ተፈጥሮ ከልዑል አግዚአብሔር የተሰጠው የመጀመሪያው ሕግ ነው።ይህ ሕግ ብዕር መቅረጽ፣ቀለም መበጥበጥ፣ብራና መዳመጥ በጠቅላላው የጽሕፈት መሣሪያዎችን የማይሻ ነው።ሕግነቱም በመላዕክት የተጠና ስለሆነ ከተፈጥሮአቸው ጀምሮ እስከ አሁን አልተለወጠም ሰውም እንደመላዕክት ሃይማኖቱን በሕገ ልቡና አውቆና ጠብቆ ፈጣሪውን ፈርቶ ሊኖር እንጂ በደብተርና በእርሳስ ሊመራ አልተፈጠረም ነበር።ሄኖክ 19፤23 ነገር ግን ሰው በተፈጥሮ የተሰጠውን ዕድል አውቆ በሕገ ልቡና ክብሩን ጠብቆ መኖር በተሳነውና ጠባቂ እንደሌለው በግ በሞት መንገድ ላይ ሲቅበዘበዝ ልዑል እግዚአብሔር ቢያየው በቀለምና በወረቀት የተጻፈ ሕግን ረዳት አድርጎ ሰጠው።ኢሳ 8፤16 በሕገ ልቡና ዘመን የበደሉትንም ያልበደሉትንም ሞት አንድ አድርጎ ቢገዛቸውም ሕገ ልቡናን ጠብቀው በተገኙ ሰዎች ዘንድ የእግዚአብሔር ብርሃነ ረድኤት ፈጽሞ አልጠፋም።ሮሜ 5፤14 ሕገ ልቡና ወይም ዘመነ አበው /ዘመነ ፓትርያርክ/ የሚቆየው ከአዳም እስከ ሙሴ ድረስ ያለው 3,893 ዓ/ዓ ዘመን ነው።በዚህ ሕግ መሪነት ሰው ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ሕግ ጥሶ በተፈረደበት ፍርድ መጠን ዕውቀት በማጣቱ እግዚአብሔርን ለማግኘት የተቅበዘበዘባቸው የሞት መንገዶች ብዙዎች ናቸው።እነዚህም በሰማይ ሠራዊት በፀሐይ፣በጨረቃ እና በከዋክብት፤በምድር በሰው፣በእንስሳ እና በአዕዋፋት የተቀረጹ ጣኦታት ናቸው።

**1.2. ሕገ ልቡና በኢትዮጵያ፡-**የኢትዮጵያ ሕዝብና ዘር፣ስለኢትዮጵያ ሃይማኖትና ሀገረ እግዚአብሔርነት፣ታላቅነትና ጥንታዊነት ታላቁ መጽሐፍ ይመሰክራል። በሕገ ልቡና ዘመን ከአዳም ልጆች አንዱ ኡሪ ወይም አራም የተባለው ዓለም በተፈጠረ በ1030 ዓመተ ዓለም ጀምሮ ከልጅ ልጆቹ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው 27 ነገሥታት ነግሠዋል።ከጥፋት ውሃ በፊት 2256 ዓመት ኢትዮጵያ በራሷ አስተዳደር እየተመራች ለ1285 ዓመታት ቆይታለች።በመጨረሻም ንጉሣቸው በሶሊማን ታጊ ጊዜ በኖኅ ዘመን በጥፋት ውሃ ዓለም በሙሉ ተደመሰሰ።/ክብረ ነገስት 317-333/።ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ምድር ከጥፋት ውሃ እስከ ባቢሎን ግንብ መፍረስ ድረስ በቋንቋ ተለያይተው እስከ ሰዎች መበታተን ድረስ ለ535 ዓመታት ከ10 ወር ኢትዮጵያ ሰው አልባ ነበረች።ከዚህ በኋላ ነገደ ካም በእስያ ደቡብ ሲኖሩ በኋላ ወደ ክፍላቸው ወደ አፍርቃ ተሻግረው መጥተው ከአትዮጵያ እስከ ግብጽ ድረስ ያለውን አገር እያቀኑና እያለሙ ከተማም

እየሠሩ ኖረዋል።ይህም የሆነው ዓለም በተፈጠረ 2787 ዓመተ ዓለም ነው።ካም ኢትዮጵያን 78 ዓመት ከገዛ በኋላ ወደ እስያ ሄዶ ሶርያን እይዛለሁ ብሎ ከሴም ልጆች ጋር ተዋግቶ ሞተ።ከዚያም ልጁ ኩሽ ነግሦ ሀገሪቱ የኩሽ ምድር ተብላ ተጠርታለች።በዚህ ዘመን ኢትዮጵያ እግዚአብሔርን በሕገ ልቡና የምትከተል እንደነበረች ታሪክ ይመሰክራል።አልፎ አልፎም የባዕድ እምነት እንደነበረም ተጽፏል።ይህ ማለት ግን ኢትዮጵያ ጣኦት የሚመለክባት ሀገር አያሰኛትም የእግዚአብሔር ሕዝቦች እስራኤላውያንን ብንመለከት እንኳ ለእግዚአብሔር የተመረጡ ተአምራቱን ያዩ ሕግና ሥርዓቱን በሙሴ አማካይነት የተቀበሉ ሲሆኑ በተለያዩ ዘመናት ጣኦት የሚያመልኩ ነገሥታት ይነሱ ነበር እነኚህ ነገሥታት ጣኦት ማምለካቸውና ለጣኦት መሰዋታቸው እስራኤልን የጣኦት ሀገር ነች /ነበረች/ አያሰኛትም።በኢትዮጵያም በተመሳሳይ መልኩ የባዕድ አምልኮ እንደነበረና እንደቀረ ታሪክ ይናገራል።

## 1.3. የኦሪት ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ እንዴት መጣ ?

**1.3.1. ንግሥት ሳባ፡-** ከአክሱም ነገሥታት ሁሉ እጅግ የላቀች እንደነበረች በብዙ የታሪክ ፀሐፊዎች የሚነገርላት ንግሥት ሳባ የኖረችበት ዘመን ከ1026-982 ዓ/ዓ ከክርስቶስ ልደት በፊት ኢትዮጵያንና የመንን በአንድነት ትገዛ እንደነበረች ከተለያዩ የታሪክ ጸሐፊዎች የተገኘው መረጃ ያስረዳል።ገናናዋ ኢትዮጵያዊት ንግሥት ሳባ በመጽሐፍ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ንግሥት ሳባ፣በክብረ ነገሥት ንግሥት ማክዳ በሐዲስ ኪዳን ደግሞ ንግሥት አዜብ ተብላ ትጠራለች።ሳባ በአክሱም አጠገብ ያለው ቦታ ስም ሲሆን ዐዜብ በደቡብና በምዕራብ መካከል ያለ አቅጣጫ ነው።ይህም ስም የተሰጣት ከኢየሩሳሌም በዐዜብ በኩል የሚገኝ ኢትዮጵያንና የመንን ትገዛ ስለነበር ነው።1ነገ 10፤1 2ኛዜና 9፤1 ማቴ 12፤42።ንግሥት ሳባ በዘመኑ ከነበሩት ነገሥታት በሃይማኖትም ሆነ በሥልጣኔ ዋነኛዋ ስለነበረች በመልካም አስተዳደርና እግዚአብሔርን በመፍራት ኢትዮጵያንና የመንን በአንድነት ለ31 ዓመታት ገዝታለች።በክብረ ነገሥት እንደተገለጸው በመልኳ፣በደም ግባቷ እጅግ ያማረች፣በጥበብና በማስተዋል የተሞላች ነበረች።እግዚአብሔር በሰጣት ክብር፣ብልጽግና፣ወርቅና ብር በከበሩ ልብሶች፣በግመሎችና ባሪያዎች፣በነጋዴዎችም እጅግ የበለጸገች ነበረች።ግዛቷም እጅግ ሰፊ ነበር፤በደቡባዊ ምስራቅ እስከ ማዳጋስካር፣በሰሜንና በስተምዕራብ እስከ ግብጽና እስከ ኑብያ ዳርቻ በስተደቡብ ዛሬ ቢክቶሪያ ኒያንዛ እስከ ተባለው ባህር ነበር።

ከክርስቶስ ልደት በፊት 1000 ዓመት ያህል ቀደም ብሎ ከነበሩ ገናና ነገሥታት በምትወለደው በንግሥት ሳባ ዘመን ከኢየሩሳሌምና ከዐረብ፣ከግብጽና ከሕንድም ሀገሮች ብዙ ነጋዴዎች ወደ ኢትዮጵያ ይመላለሱ ነበር።እነዚህ ነጋዴዎች ልዩ ልዩ ዕንቁና አልማዝ፣ወርቅና ሽቱም እየገዙ በየሀገራቸው ይወስዱ ስለነበር በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያና የንግሥት ሳባ ዝና በዓለም ሁሉ ተሰማ።ንግሥት ሳባ ጠንካራ ንግሥት በመሆኗ የንግድ መስመሩ እስከ ምስር፣ኢየሩሳሌምና ሕንድ የሚዘልቀው የንግድ ድርጅቷ እንዲስፋፋና እንዲጠናከር አድርጋለች።ለንግድ እንቅስቃሴውንም የተመቻቸ ለማድረግ የሚረዷት 72 መርከቦችና 520 የግመል መንጋ ነበራት።

ንግሥት ሳባ በኢትዮጵያ የጥንት ሥርወ መንግስት 52ኛ ተራ ላይ የምትገኝ ስትሆን በነገሠችበት ዘመን በእስራኤል ጥበበኛው ሰሎሞን የነገሠበት ዘመን ስለነበረ ለሕገ ኦሪት እምነትና ሥርዓት ወደ ሀገራችን መምጣት ምክንያት ነበረች።ንግሥት ሳባ ወደ እስራኤል ይመላለስ ከነበረው ከታማኝ ሹም ታምሪን የንጉሥ ሰሎሞንን ሥጋዊና መንፈሳዊ ጥበብና ዝና ትሰማ ነበር።በንግሥት ሳባ ዘመን የእስራኤል ንጉሥ ሰሎሞን ለታቦተ ጽዮን ማረፊያ የሚሆን መቅደስ ማሠራት ጀምሮ ነበር።እሱም በተለያዩ ሀገሮች ለሚኖሩ ነጋዴዎች ለመቅደሱ ሥራ ሊጠቅሙ የሚችሉ ብርቅና ድንቅ ነገሮችን ወደ ኢየሩሳሌም እንዲያመጡ፣ዋጋቸውንም በወርቅና በብር እንደሚከፍል አሳወቀ።በዚህን ጊዜ ከኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም እየተመላለሰ ይነግድ የነበረው ታምሪን የተባለው ነጋዴ ቀይ ወርቅ፣ዘጲ እና ሌሎችንም የከበሩ ዕንቁዎችን ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ ለሰሎሞን ካስረከበ በኋላ ሲመለስ የሰሎሞንን ቤተ መንግስት ሥነ ሥርዓት ጥበቡንና ክብሩን ሁሉ ለንግሥት ሳባ ነገራት።**1.3.2.** **1.3.2.. የንግሥት ሳባ ጉዞ ወደ ኢየሩሳሌም**፡- ንግሥት ሳባም በጆሮዬ የሰማሁትን ዝና በዓይኔ ማየትና መረዳት የበለጠ ነው ብላ ከታምሪን የሰማችውን የሰሎሞንን ጥበብ

ለማየትና ከንጉሥ ሰሎሞን ጋር ለመተዋወቅ በታምሪን አማካይነት በአሽከሮችና በደንገጡሮቿ የከበሩ ገፀ በረከቶችን፣በርካታ ሽቶ ዓይነቶችን፣የከበረ ዕንቁዎችን ከ120 መክሊት ወርቅ ጋር አስይዛ ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ አድርጋለች፡፡1ነገ 10፤1-13 ንግሥት ሳባ ወደ ሰሎሞን የተጓዘችው ጥበብን ከማየትና ለመንግስቱም ክብር ከመስጠት በተጨማሪም በእውነት ሰሎሞን እግዚአብሔርን የሚያውቅ ከሆነ እግዚአብሔር ለባሮቹ ምስጢርን ይገልጻልና የተሰወረውን ያውቅ ይሆናል በማለት

1. በእንቆቅልሽ ጥያቄ ልትጠይቀውና ሃይማኖቱን ልትረዳ
2. እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም ምን እንደሠራና ምን ያህል ሕዝብ እንዳሉት ለማወቅና የሚፈጸመውን የአምልኮ ሥርዓት ለመመልከት
3. በዚያን ዘመን በዓለም የአምላክ ሀገር ተብላ የምትታወቅ አትዮጵያ ነበረችና እግዚአብሔር የሚመለክባት ሌላ ሀገር እንዳለ ብትሰማ በጆሮዋ የሰማችውን በዓይኗ አይታ ምስክርነት ለመስጠትና የሃይማኖት ወገን ለማብዛት ነው፡፡

ንግሥት ሳባ ኢየሩሳሌም ደርሳ በሰሎሞን ቤተ መንግስት አካባቢ ካረፈች በኋላ ወደ ውስጥ መግባት ትችል ዘንድ የሰሎሞን አገልጋይ ከሆኑት አንዱን ላከች አገልጋዩም የንግሥት ሳባን አጃቢዎች ብዛትና የጓዛቸውን መጠን እንዲሁም የንግስቲቱ ውበትና ተክለ ቁመና አድንቆ በእግሯ ላይ ቀንድ የሚመስል ነገር እንዳለባት ለንጉሥ ሰሎሞን ይነግረዋል፡፡ንጉሥ ሰሎሞንም ያልከኝ ሁሉ እውነት ካልሆነ ከቤተ መንግስቱ እንደሚያስወጣው ካስጠነቀቀው በኋላ ንግሥቲቱ እንድትገባ አዘዘ፡፡ንግሥት ሳባ ስጦታዎችን ይዛ ደንገጡሮቿን አስከትላ ወደ ውስጥ ሳትገባ በቤተ መንግስቱ ደጅ የተጋደመ የበለስ ግንድ በእግሯ ላይ የነበረው ቀንድ የሚመስል ነገር ወልቆ ወደቀ፡፡እሷም በእንጨቱ ተደንቃ የወለቀላትን ቀንድ ለደንገጡሯ አስይዛ ወደ ውስጥ ገባች፡፡ንጉሥ ሰሎሞንም በንግሥቲቱ የተባለው ሁሉ እንዳለ ሆኖ ሲያገኘው በእግሯ ላይ ግን ምንም ነገር አላየም ነበር አገልጋዩን ጠርቶ ያልከኝ ነገር ትክክል ስላልሆነ ከቤተ መንግስቱ ውጣ አለው፡፡ንግሥቲቱ ግን የተደረገላትን ተአምራት ነገረችው ከእግሯ የወለቀውንም አሳየችው ንጉሡም አገልጋዩ የነገረው እውነት እንደሆነና የተደረገው ተዓምርን አይቶ አመነ፡፡ ከዚህ በኋላ በጊዜው ይደረግ በነበረው የስጦታ ልውውጥ መሠረት እሷና ንጉሡ የመተያያ ስጦታ ተለዋወጡ ለንጉሡም በርካታ ስጦታዎችን የከበረ ሽቱንም ሰጠችው፡፡1ነገ 10፤10 እርሱም ብዙ የሆኑ ስጦታዎችን አበረከተላት ለእርሷም የክብር አቀባበል ካደረገላት በኋላ በሀገሯ ሳለች የሰማችውን ጥበቡን ሁሉ በዐይኗ አየች ጥያቄዎቹንም ጠየቀችው ጥበበኛ መልሱንም መለሰላት፡፡በልቧ ያለውንና ያሰበችውንም ሁሉ አጫወተችው ጥበቡንና ሠርቶት የነበረውን ቤት፣የማዕዱንም ሥርዓት፣የብላቴናዎችና የሎሌዎቹን አሠራር፣አለባበሳቸውንም ሥነ ሥርዓት፣ የወይን ጠጅ አሳላፊዎቹንም፤በእግዚአብሔር ቤት የሚያሳርገውን መስዋዕት ባየች ጊዜ ተደነቀች፡፡ እንዲህም አለች **‹‹ስለነገርህና ስለጥበብህ በሀገሬ ሳለሁ የሰማሁት ዝና እውነት ነው፡፡እኔም መጥቼ በዓይኔ እስካይ ድረስ የነገሩኝን አላመንሁም ነበር እነሆም እኩሌታውን አልነገሩኝም ነበር፡፡ጥበብህ ከሰማሁት ዝና ይበልጣል በፊትህ ሁልጊዜ የሚቆሙ ጥበብህንም የሚሰሙ ሰዎችህና እነዚህ ባርያዎችህ ምስጉኖች ናቸው አንተን የወደደ በእስራኤል ዙፋን ያስቀመጠህ አምላክህ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን እግዚአብሔር እስራኤልን ለዘላለም ወዷታልና ስለዚህ ጽድቅና ፍርድ ታደርግ ዘንድ ንጉሥ አድርጎ አስነሳህ** ብላ አመሰገነች፡፡እዚህ ላይ የተጠቀሰው የንግሥት ሳባ አነጋገር ወደ ሰሎሞን ከመምጣቷ በፊት ገና ከልጀነቷ ጀምራ ኢትዮጵያውያን ቀደምቶቹ በሕገ ልቡና ያመልኩት በነበረው በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር ታምን እንደነበር በግልጽ የሚያስረዳ ነው፡፡ንግሥት ሳባም በክብር እየተጠራች የቤተ መንግስቱን ሥርዓት፣ሥጋዊና መንፈሳዊ ጥበብ፣የሥርዓተ መስዋዕት አቀራረብ፣ ስለአምልኮተ እግዚአብሔርና ስለመንግስቱ አስተዳደር እየተረዳች ለ6 ወራት ቆይታለች፡፡

**1.3.3. ንግሥት ሳባ ከኢየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ**፡-ንግሥት ሳባ ለ6 ወራት ያህል በኢየሩሳሌም ከቆየች በኋላ ወደ

ሀገሯ ለመመለስ ስትነሳ በንጉሥ ሰሎሞን ታላቅ ግብዣ በክብር ተጠርታ በሰገነት ላይ ሆና ሥርዓተ መንግስት ሲፈፀም አየች፡፡ለመኳንንትና መሳፍንቱ የተዘጋጀውን የግብዣ አቀራረብ ሥርዓትንም ካየች በኋላ ወደ ሀገሯ ስትመለስ የታቦተ ጽዮን የውስጥ መሸፈኛ ማህፈድ፣ዘላቂ ንብረትና ማረፊያ ይሆናት ዘንድ በመሀል ኢየሩሳሌም ከሚገኘው ክፍል ሰፊ መሬት ዴር ሱልጣን (የመንግሥት መሬት)፣የእስራኤል አምላክ ካንቺ ልጅ ከሰጠኝ ይህ ምልክት ይዞ ወደ እኔ ይምጣ ብሎ ለሚወለደው ልጅ ምልክት ይሆነው ዘንድ የንግሥና ማህተም ቀለበቱን ሰጣት፡፡ስትመለስም ቀዳማዊ ምኒልክን ፀነሰች፡፡በርካታ ጌጣጌጥ እና አልባሰዓት ጋር ታላላቅ መኳንንት በሰረገላ እንዲሸኙዋት አደረገች፡፡ወደ ኢትዮጵያ አስቸጋሪ ጉዞ ጨርሳ ወደ እናት ሀገሯ ከመግባቷ በፊት ወደ የመን ገባች፡፡ከዚያም ባህረ ኤርትራ ተሻግራ ሐማሴን አውራጃ ማይበላ ተብሎ በሚጠራው ቦታ ስትደርስ ወንድ ልጅ ወለደች የወለደችውም ወንድ ልጅ ስሙን እብነ ሐኪም /የጥበበኛ ልጅ/ ብላ ሰየመችው፡፡ይህም ከጊዜ ብዛት በኋላ ምኒልክ በሚለው መጠሪያ ሲተካ እብነ መለክ /የንጉሥ ልጅ/ የሚል ተጨማሪ መጠሪያ እንደነበረው ይነገራል፡፡ንግሥት ሳባም የአንድ አምላክ እምነትን አጠናክራ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሰች በኋላ በኢትዮጵያ ሥርዓተ ብሉይ ኪዳንና ሃይማኖታዊ ትውፊት እንዲስፋፋ አድርጋለች፡፡

**1.3.4. ቀዳማዊ ምኒልክ ወደ ኢየሩሳሌም ስለመሄድ፡- ቀዳማዊ ምኒልክ 22 ዓመት ሲሞላው ከአባቱ ሰሎሞን ጋር ለመተዋወቅና ስለኢየሩሳሌም መንግስትና ቤተ እግዚአብሔር ከእናቱ የተማረውን ለማየት፤ለሀገርና ለወገን የሚበጅውን የእምነት ሥርዓት፣ካህናተ ኦሪት፣የብሉይ ኪዳን መጽሐፍትና መተርጎማን፣ትውፊትና ባህል ለማምጣትና ዴር ሱልጣንን ለማስጠበቅ ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ አደረገ፡፡ሲጓዝም ሀገሩን ስለማያውቅ ታምሪንና ብዙ አጃቢዎችን አስከትሎ ነው፡**ንግሥት ሳባም ለታቦተ ጽዮንና ለንጉሥ ሰሎሞን እጅ መንሻ አስይዘው ከብዙ መኳንንትና መሳፍንት ጋር ሠራዊትና ስንቅ አዘጋጅታ በታምሪን መሪነት ወደ ኢየሩሳሌም ላከችው፡፡ ስትልከውም ‹ይህ ልጄ በመንግስቴ እንዲነግሥ ፈቃዴ ነውና ሕገ ኦሪትን፣ሕገ መንግስትን፣ሥርዓተ ክህነትን አስተምረው፡፡ለበረከትም የሚሆን ከፊታችን አድርገን እግዚአብሔርን ለማሰብ እጅ የምንነሳበትን ሰማያዊ ከምትሆን ታቦተ ጽዮን በረከት ለማግኘት መጎናፀፊያ እንድላክልን አድርግ እግዚአብሔር መንግስትህን ይባርክ › የሚል ደብዳቤ በታምሪን ላከችለት፡፡ ሰሎሞን የሰጣትንም ቀለበት ምልክት ይሆነው ዘንድ ሰጠችው፡፡ ቀዳማዊ ምኒልክ ወደ ኢየሩሳሌም እንደ ደረሰ ብዙ ሺህ መኳንንት፣መሳፍንትና የጦር አዛዥ እና ከከተማው ህዝብ ጋር በመሆን ታላቅ አቀባበል አደረጉ፡፡ንጉሥ ሰሎሞን እግዚአብሔር ሳላስበው የሰጠኝ ልጅ ነው ብሎ ከመኳንንትና ከህዝቡ ጋር አስተዋወቀው ህዝቡም ይህንን የወለደች እናት የተባርከች ናት እያሉ አመሰገኑ፡፡ቀዳማዊ ምኒልክ ከአባቱ ጋር ከተዋወቀ በኋላ እናቱ የሰጠችሁን ደብዳቤ ሰጠው በተጨማሪም ሥርዓተ አምልኮን፣የቤተ መቅደስ አስተዳደርን፣የቤተ መንግስት አስተዳደርን፣ወደ ኢትዮጵያ ይዞ የሚመለሰውን ነገሮች ሁሉ በዝርዝር አቀረበ፡፡ከዚህ በኋላ ምኒልክ በኢየሩሳሌም ከአባቱ ጋር ሥርዓተ መንግስትን፣መጽሕፍተ ሙሴን፣ሥርዓተ ክህነትን፣የዕብራይስጥ ቋንቋን ከሊቀ ካህናቱ **ሳዶቅ** እየተማረ **ሦስት ዓመት** ቆየ፡፡

**1.3.5. የቀዳማዊ ምኒልክ ወደ ኢትዮጵያ መመለስ**፡- ቀዳማዊ ምኒልክ ወደ ሀገሩ ለመምጣት ሲዘጋጅ ቀደም ሲል ለሰሎሞን እናቱ በጠየቀችው ጥያቄ መሠረት ከ12 ነገዶች የተወጣጡ 12 ሺህ ወንድ የበኩር ልጆች፣ካህናተ ኦሪት በሊቀ ካህናቱ በሳዶቅ በኩር ልጅ አዛርያስ መሪነት፣ታቦተ ጽዮንና ሌዋውያን ካህናት፣ሙሉ ቤተ መቅደስ ዕቃዎችንና ባለሙያችንና ለቤተ-መቅደስና ለኅብረተሰቡ የሚሆኑ የባህልና የሥርዓት ማስፈፀሚያዎችን፤ለምሳሌ፣ የአባባል ፣የአለባበስ ፣የአነጋገር፣የአመጋገብ ፣የጋብቻ እና የሀዘን ሥርዓቶችን በሙሉ ይዞ ከክርስቶስ ልደት በፊት 950 ዓመት (4550 ዓ/ዓ) ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል፡፡ንግሥት ሳባ ከምኒልክ ጋር የመጣውን የእስራኤል ሕዝብ በክብር ተቀበለቻቸው፡፡የታቦተ ጽዮንን መምጣት ስትሰማ ለእግዚአብሔር መስዋዕት አቀረበች፡፡ቀዳማዊ ምኒልክም በካህኑ በአዛርያስ እጅ ተቀብቶ መንግስቱን ከእናቱ ተረከበ፡፡ንግሥት ሳባም በሰላም አርፋ በዛሬዋ በአክሱም ጽዮን ቤተ መቅደስ አጠገብ ተቀበረች፡፡ቀዳማዊ ምኒልክም ለ25 ዓመታት ኢትዮጵያን ካስተዳደረ በኋላ ከነገሠ በ58 ዓመቱ አረፎ በአክሱም ከተማ በእናቱ መቃብር አጠገብ ተቀበረ፡፡

**1.3.6. የታቦተ ጽዮን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት:-** ሕገ ኦሪት እና ታቦተ ጽዮን ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ከክ.ል.በፊት 950 ዓመት (4550 ዓ/ዓ) እንደሆነ ታሪክ ይነግረናል።የታቦተ ጽዮን ወደ ሀገራችን የመጣችበት ሁኔታ ታሪክ እንዲህ ያስተውሰናል።**ካህኑ አዛርያስ አባቱ ሳዶቅን** አብራቸው ወደ ኢትዮጵያ የምትጓዝ ታቦተ ጽዮን እንዲሰጠው ቢጠይቀውም አስቀድሞ ንጉሥ ሰሎሞን በፈቀደው መሠረት ለተለዋጭ (ለተፈቀደላቸው ሌላ ጽላት) ማስቀመጫ የሚሆን ሳጥን መጠኑ ከጽላተ ሙሴ መጠን ጋር የተስተካከለ ነበር።ሥራውንም እንደተጠናቀቀ ጽላቱ ወደሚገኝበት ቤተ መቅደስ ሳጥኑን በምስጢር ይዞ ሄደ።ከመቅደሱ በር ሲደርስ በተአምር በሩ ስለተከፈተለት ከጽላቶቹ ውስጥ በእግዚአብሔር ፈቃድና ትዕዛዝ የእስራኤል ሕዝብ መሪና ታላቅ ነቢይ ሙሴ የተቀበላትን አስርቱ ትዕዛዛት የተፃፉበትን ጽላት በወርቅ ሳጥን አድርጎ በሠረገላ ጭኖ ጉዞ ጀመሩ።በጉዞ ሳሉም **በሰባተኛው ቀን አዛርያስ ጽዮን** ከእነርሱ ጋር መሆኗን ለምኒልክ ነገረው።ቀዳማዊ ምኒልክም ይህ በሰው ፈቃድ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ የተደረገ ነው በማለት እግዚአብሔርን አመሰገነ።የታቦተ ጽዮን መወሰድም በንጉሥ ሰሎሞን ዘንድ ተሰማ።ታቦቷንም ለማስመለስ ንጉሥ ሰሎሞን ከብዙ ሠራዊት ጋር እስከ ግብጽ ድረስ ገስግሶ ሊደርስባቸው አልተቻለውም።ለንጉሥ ሰሎሞንም የጽላቷ መወሰድ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ በመንፈስ ተነገረው።ወደ ሀገራቸውም ከተመለሱ በኋላ ይህን ታሪክ ላልሰሙ እስራኤላውያን እንዳይነግሩ በምስጢር እንዲያዝና ይህን ምስጢር ያወጣ በሞት እንደሚቀጣ አብረውት ለነበሩ ሠራዊት ማስጠንቀቂያ ተሰጠ።

**1.4.ሕገ ኦሪት /የሕግ ዘመን/:-** ሰው በሕገ ልቡና 3893 ዓመት ከኖረ በኋላ በዚህ ዘመን ውስጥ በተፈጥሮ እውቀቱ ሊጠቀምበት ስላልቻለ ልዑል እግዚአብሔር በደብረ ሲና በአምሳለ ንጉሥ ተገልጦ ለዕውቀቱ አጋዥ ረዳት ይሆነው ዘንድ ሕጉን በገበታ ላይ ጽፎ በሙሴ እጅ ሰጠው።ዘጸ 19፤15-16 ይህ ዘመን የሚጀምረውም ከሙሴ ዘመን ጀምሮ ነው።ከዚህ በኋላ ዓለም በሕግ እየተመራ እግዚአብሔርን መከተል ጀመረ።ሙሴ በእግዚአብሔር ተልኮ እስራኤልን ከግብጽ ሀገርና ከፈሪኦን አገዛዝ ነፃ እንዲያወጣቸው ተላከ።እግዚአብሔር በሰጠው ሥልጣንና ኃይል ሕዝበ እስራኤልን ከፈሪኦን አገዛዝ ነፃ አውጥቶ የኤርትራን ባህር በተአምራት አሻግረዋል።በሲና ተራራ ላይ የሕግ ጽላት ሙሴ ከእግዚአብሔር ተቀበለ።**እስራኤል ከኖኅ ዕድሜ በኋላ እስከ አብርሃም በሕገ ጣኦት ከአብርሃም እስከ ሙሴ በሕገ ልቡና በአምልኮተ እግዚአብሔር የቆየች ስትሆን ከሙሴ እስከ ክርስቶስ መገለጥ ድረስ ከልዑል እግዚአብሔር የሕግ መጻሕፍት ርዳታ አግኝታ በሕገ ኦሪት ተመርታለች**።

**1.4.1. ሕገ ኦሪት በኢትዮጵያ፡-**ከክርስትና በፊት ስለኢትዮጵያ ሃይማኖት ስንናገር የአቅኚዎቿን የሕይወት ታሪክ መመርመር አስፈላጊ ነው።ከላይ እንደገለጥነው ኢትዮጵያን ያቀኑት የመምለኬ እግዚአብሔር የኖህ የልጅ ልጆች ስለሆኑ የአያታቸውን አንድ አምላክ እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር።ነገር ግን እምነታቸው በትምህርት የተደገፈ ስላልሆነና ኑሮአቸውም ከፍልስጥኤም ውጭ ስለሆነ አንዳንድ የአምልኮ ባዕድ ልምዶች ሰርገው ሳይገቡ አልቀሩም።ለምሳሌ **ከጌታ ልደት በፊት 1000 ዓመት አከባቢ ይኖሩ የነበሩ ኢትየጵያውያን በዘንዶና በሐይቅ ያመልኩና ይገብሩ እንደነበር በኢትዮጵያ ታሪከ ነገሥት ተጽፏል**።ይኸውም ታሪከ ነገሥት ታሪኩን እንደሚለው በኢትዮጵያ ሲመለክ የነበረውን ዘንዶ የገደለው የንግሥት ሳባ አባት አጋቦስ የተባለው ነው።በመቀጠልም ታሪክ ነገሥት ንግሥት ሳባ የሰሎሞንን ጥበብ ለመረዳት ከአትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም መሄዷንና ከሰሎሞን ምኒልክ የሚባል ልጅ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሳ መውለዷን ልጇም አድጎ የአባቱን አገር ኢየሩሳሌምን ጎብኝቶ ሲመለስ የሙሴን ጽላትና ካህናተ ኦሪትን እንዲሁም አያሌ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ከሊቆቻቸው ጋር ይዞ እንደመጣ ታሪክ በሰፊው ይተርካል።

የውጭ ሀገር ፀሐፊዎች ግን ያን ጊዜ በኢትዮጵያ አካባቢ በየመንና በግብጽ የነበረውን የአይሁድ ኃይልና የብሉይ ኪዳን እምነት መስፋፋት በታሪክ ስለሚያውቁ ምናልባት ኢትዮጵያ ከነዚህ ከጎረቤቶቿ ጋር በነበራት የንግድና የሥልጣኔ ግንኙነት የብሉይ ኪዳንንም እምነት ከዚያው ሸምታው ይሆናል ብለው የግምት ሐሳባቸውን በጽሑፍ ገልጸዋል።ሌሎች ደግሞ በ586 ዓ/ዓ ኢየሩሳሌም በባቢሎናውያን በተቃጠለች ጊዜ እስራኤላውያን ብዙዎቹ ተማረኩ። አንዳንዶቹም ነፍሴ አውጭኝ በማለት በየቦታው ተሰደዱ።ከእነሱም **ዮሐናን** በሚባለው ሰው መሪነት ወደ ግብጽ የተሰደዱ ነበሩ።ወደ

ግብጽ ከተሰደዱት ውስጥ ደግሞ ተከፍለው ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ነበር ይባላል።በዚህን ጊዜ ሃይማኖታቸውንና ሥርዓታቸውን ለማስፋፋት ለማጠናከር አመች ነበር ማለት ነው።በኤርምያስ 44 ላይ እንደተጻፈው ከክ.ል.በፊት 586 /4914 ዓ/ዓ/ ከባቢሎን ምርኮ በፊት በግብጽ በዝርወት የሚኖሩ ብዙ አይሁድ ስለነበሩ ምናልባት በየምክንያቱ ወደዚህች ሀገር እየገቡ ሃይማኖታቸውንና ባህላቸውን ሳያስፋፉ አልቀሩም።ምንጩና የፀሐፊዎቹ ግምት የተለያየ ቢሆንም ኢትዮጵያ ከክርስትና በፊት የብሉይ ኪዳንን እምነትና ባህል ለመቀበሏ በሐዋ.ሥራ ምዕ 8 የተመዘገበው ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት ከክርስቶስ ልደት በፊት 1000 ዓመት **‹ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር›**ብሎ የተናገረው መዝ 67፤31 ታሪክ በቂ ምስክር ሊሆን ይችላል።ጃንደረባው ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው ሊሰግድና ሊጸልይ መሆኑ ተብራርቶ ስለተተረከ ሲያነበው የነበረው ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የታላቁን ነቢይ የኢሳይያስ መጽሐፍ ስለነበር ነው።

ወደ ኢትዮጵያ ሕገ ኦሪት የመጣው ከንግሥት ሳባ ዘመን ጀምሮ ነው።ኢትዮጵያ ከኖኅ ዕድሜ በኋላ በኩሽና በልጆቹ አማካይነት በሕገ ልቡና በአምልኮተ እግዚአብሔር ስትመራ ቆይታ ከእስራኤል ቀጥላ በሊቀ ካህናቱ አዛርያስ እጅ በቀዳማዊ ምኒልክ ምክንያት በልዑል እግዚአብሔር እጅ የተጻፈውን ጽላተ ኪዳንና የሕግ መጻሕፍት አግኝታለች።ቤተ-እስራኤል ከኢትዮጵያ የምትቀድመው መጻሕፍትን በመቀበል እንጂ በእምነት አይደለም።ቤተ-እስራኤል ኢትዮጵያን በሃይማኖት የምትቀድም ቢሆን ሙሴ ኢትዮጵያዊት ሚስት በማግባቱ እንዳንጎራጎሩ ሁሉ ጽላተ ሙሴ ስትለያቸው ባንጎራጎሩም ነበር።ዘሁ 12፤1 **ነገር ግን ኢትዮጵያ ያላገኘችው ለሃይማኖቱ አጋዥ የሚሆናት ትምህርት እንጂ አዲስ ሃይማኖት ፈላጊ ባለመሆኗ ኪዳነ አብርሃምን በማሰብ ከግብጽ ባርነት ነጻ አውጥቶ ለሱ ገንዘብ እንድትሆን ቤተ-እስራኤልን የመረጠ እግዚአብሔር ኪዳነ መልከ ጼዴቅን በማሰብ ከጥንት ጀምሮ በአምልኮት ትከተለው ለነበረች ሀገሩ ኢትዮጵያ በሊቀ ካህናት አዛርያስ እጅ ኪዳኑ የጸናባት ጽዮንን ሕጉ ትዕዛዙ የተጻፈበትን መጽሐፈ ኦሪትን ሰጣት**።ኢትዮጵያ ከተቀበለችው ትዕዛዝ ማንኛውንም ሳትለውጥ ሕጉን ትዕዛዙን ጠብቃ አምልኮቱን ከቀዳማዊ ምኒልክ እስካለንበት ዘመን ድረስ አጽንታ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ሆና ኖራለች።

ከክርስትና በፊት ኢትዮጵያ ብሉይ ኪዳንን ለመቀበሏ የታሪክና የጽሑፍ ማስረጃ ብቻ ሳይሆን በሕዝቡ ዘንድ ሲሠራባቸው የሚኖሩ አያሌ ልማዶችና ባህሎች ህያው ምስክር ናቸው።እነዚህም የብሉይ ኪዳን ልማዶችና ባህሎች ባሁኑ ጊዜ በክርስትና ሃይማኖት ውስጥ እንደ ዶግማ ወይም እንደ ቀኖና ሳይሆኑ እንደልማድ ሁነው የሚጠበቁ ናቸው።እነዚህም፣

1. በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንዳይበሉ የሚከለክሏቸው እንስሳትና አዕዋፋት ዛሬም የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች አይመገቧቸውም።ዘሌ 11፤1 ዘዳ 14፤1

2. በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ የማመን ምልክት የነበረው ግዝረት በሀገራችን መፈፀሙ ዘፍ 14 በአዲስ ኪዳን ግን በክርስቶስ ላመኑ ሁሉ መለያ ምልክታቸው ወይም ማህተማቸው ጥምቀት ነው።በሀገራችን ግን ከብሉይ ኪዳን በተወረሰው ልማድ ልጅ ሲወለድ ይገረዛል፣ግዝረቱ ግን የሕግ ሳይሆን የፈቃድ ነው።ይህም ማለት ክርስቲያኖች ልጆቻቸውን ቢያስገርዙም ባያስገረዙም የራሳቸው ፈቃድ ነው።

3. የሕዝቡ ማህበራዊ ኑሮ ብንመለከት ከሕዝበ እስራኤል ከኦሪቱ አኗኗር ጋር ተመሳሳይ ነው።ለምሳሌ፣የሕዝቡ የሃይማኖት ስሜት፣በሀዘንና በደስታ ጊዜ ያለው ሁኔታ፤የበዓላት አከባበር፣ የቤተ ክርስቲያን የማህሌት ሥርዓት፣የታቦቱ ሕጉ ክብር፣የካህናቱ-አለባበስ፣ልብሰ ተክህኖ፣ካባው፣ ድርቡ፣ጽናጽሉ፣ከበሮ፣መጠምጠሚያው እንዲሁም የሕፃናቱና የሴቶቹ ጌጣጌጥ ሁሉ የብሉይ ኪዳን ሥርዓትና የሴማውያን ሥልጣኔ የሚያሳይ ነው።በሌሎች ከአረማዊነት በተመለሱ ሀገሮች ይህ ሁሉ አይታወቅም።ጠቅለል ባለመልኩ በህገ ልቡና /በዘመነ አበው/ መጻሕፍት ከመጻሐፋቸው፣ መምህራን ከማስተማራቸው በፊት አምልኮና ሥርዓተ አምልኮ ባልተደነገገበት ዘመን ወላጆቻችን ሥነ-ፍጥረታትን

በመመልከት እግዚአብሔርን ያመሰገኑበት፣ያመለኩበት፣ያመኑበት፣ስሙን የጠሩበትና ያከበሩበት ዘመን እንደነበር ሥርዓታችንና ሃይማኖታችን ይገልጻል።

ኢትዮጵያውያን በህገ ልቡና ዘመን በልቡናው ተመርሆ /በልብ መመሪያ/ ሥነ-ፍጥረትን በማየት እግዚአብሔር አምላካቸውን ሲያመልኩ የቆዩ ስለሆኑ **ኢትዮጵያ ስትመሠረት የነበረው የቤተ ክርስቲያን የዕድገት ደረጃ ሁለተኛና የአምልኮ ሥርዓትም በቤተሰብ** ነበር።ይህም ሀገርቷን የቆረቆሩት የካምና የሴም ዘሮች ስለሆኑ የወላጆቻቸውን ትውፊትና ሥርዓት ተከትለው እንደሆነ መጻሕፍት ያስረዳሉ።ዘፍ 2፤13 ዘፍ 10፤1-6 ከሙሴ መነሳት በኋላ እስከ ዳዊትና ሰሎሞን ቤተ መንግስት ወላጆቻችን ታቦትና ጽላት፣መገነኛ ድንኳንና ቤተ መቅደስ፣ንዋያተ ቅድሳት፣ካህናትና መዘምራን፣ስዕል፣በዓላትና-አጿዋማት፣አስራት፣በኩራትና ቀዳሚያት፣መስዋዕት፣ብፅዓትና ስዕለት እነዚህ ሁሉ ከአማንያን ለእግዚአብሔር የሚቀርቡና አማኒያንን ከእግዚአብሔር የሚያገናኙ የድህነት መንገዶች መሆናቸውን በመገንዘብና ተስፋ በማድረግ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ከእስራኤላውያን ባለመለየትና በመቀጠል ይህን መንገድ ይዘው ሲጓዙ ቆይቷል።ዘሁ 12፤1 1ነገ 10፤1-13 2ዜና 21፤4 ኢዮ 6፤19 መዝ 67፤31

**1.5. ሕገ ወንጌል /አዲስ ኪዳን/፦**ይህ ዘመን ከክርስቶስ መወለድ ጀምሮ እስካለንበት ዘመን ድረስ የሚያጠቃልል ሲሆን ዘመነ ሥጋዌ /ዘመነ ሐዲስ/ ወይም የምህረት ዘመነ በመባልም ይጠራል።ዘመነ ሥጋዌ በክርስቶስ የባህርይ አምላክነት በማመን የሥላሴን ምስጢር የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት በማመን በአጠቃላይ እስካሁን ድረስ ያለውን የክርስትና ጉዞን የሚያካትት ነው።ይህ ዘመን የደጋግ ነገሥታቶችን የቤተ ክርስቲያን አባቶችን መልካም ሥራና የቤተ ክርስቲያን ጉዞዋን የምናይበት ክፍል ነው።

**1.5.1. ሕገ ወንጌል /የክርስትና ሃይማኖት/ በኢትዮጵያ፦**ኢትዮጵያ በህገ ልቡና ከዚያም በህገ ኦሪት ስትመራ የቆየች የራሷ የሆነ አኩሪ ታሪክና ባህል ያላት ለማንኛውም ሀገር ሳትበገር እስካሁን ድረስ ሃይማኖቷን፣ሥርዓቷን፣ባህሏን ጠብቃ የምትኖር ብቸኛ አፍሪካዊት የክርስቲያን ሀገር ናት። የታሪኳ መሠረትም የቆመው በአምልኮተ እግዚአብሔር ነው።ኢትዮጵያ ከተመሠረተች ጀምሮ ሀገረ እግዚአብሔር ሕዝቧም እንግዳ ተቀባይ ቅዱስ ሕዝብ በመሆኑ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም በክንዷ ታቅፋ ወደ ግብጽ ስትሰደድ ከስደቷ መልስ ወደ ኢትዮጵያ መጥታ እየተዘዋወረች ከመጎብኘቷ ባሻገር ልጇ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጀርባዋ ላይ ሆኖ የኢትዮጵያን ወንዞች፣ተራሮች፣ሸንተረሮች ሁሉ እንደባረካቸው ታሪክ ይመሰክራል። ጌታም ለእናቱ ሳያዩኝ የሚያምኑ ካንቺ መወለዴን በመስማት ብቻ የሚያምኑ ብዙ ቅዱሳንና ደጋግ ሰዎች የሚወለዱባት ሀገር ስለሆነች በዚህች ሀገር የሚኖሩ ሰዎች እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ አስራት ይሁኑሽ ብሎ ሰጥቷታል።ጌታችን ለእናቱ መልሶ ስለፈሰሰው ደም ፈንታ አንገታቸውን ለሰይፍ የሚሰጡ፣ደማቸውን የሚያፈሱ ቅዱሳን ይወለዱባታል።እኔም በሰማያት የዘለዓለም ሕይወት እሰጣቸዋለሁ ብሩህ የገነትንም ርስት አወርሳቸዋለሁ ብሎ ለእናቱ ቃል ኪዳን ገብቶላታል። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም በኢትዮጵያ አድባራትና ገዳማት ለምሳሌ አክሱም ጽዮን፣ደብረ ሃሌሉያ /ደብረ ዳሞ/፣ደብረ አባይ እና ጣና ደሴት 3 ወር ከ10 ቀን መቆየቷን ታሪክ ይመሰክራል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከህገ ልቦና ወደ ህገ ኦሪት እንደተሸጋገረች ሁሉ ከህገ ኦሪት ህገ ወንጌልን ወይም የክርስትና እምነትን ከሁሉ አስቀድማ የተቀበለች ሀገር ናት።በሃይማኖት ስትታይ አቀባበሏ ከእስራኤል ወይም ከዕብራውያን ቀጥላ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን የተቀበለች ብቸኛ ሀገር ስትሆን

ኦሬንታል አብያተ ክርስቲያናት **እስክንደሪያ፣አርመን፣ህንድና ሶርያ**

ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት **የግሪክ፣የራሺያ፣የባልካን-ሀገሮች**፤

ካቶሊክ-አብያተ-ክርስቲያናት **ሮማውያን፣ጣሊያውያን** ወዘተ ወደ ክርስትና የተሸጋገሩት ከአህዛብነት ወይም

እምነታቸውን በሐዲስ ኪዳን ከ 60 ዓ/ም ጀምሮ በውጭ ሀገር መምህራን የተቀበሉ ናቸው።ኢትዮጵያ ሀገራችን ብሉይ ኪዳንን ከክ.ል.በፊት 1000 ዓ/ዓ ሐዲስ ኪዳንን በ 34 ዓ/ም የተቀበለች ስትሆን **ከእስራኤልና ኢትዮጵያ** በቀር ኦሬንታል አብያተ ክርስቲያናት እምነታቸውን የጀመሩት ከሐዲስ ኪዳን ጀምሮ ነው።ኢትዮጵያ በህገ ልቡና ስትመራ ቆይታ ህገ ኦሪትን በንግሥት ሳባና በቀዳማዊ ምኒልክ፣ህገ ወንጌልን በንግሥት ህንደኬ ዘመነ መንግስት በራሷ ልጅ በጃንደረባው በፓኮስ እንደተማረች የታሪክ ፀሐፊት አስፍተው መጻፋቸውን ታሪክ ይነግረናል።የሐዋ 8፤26-39 የክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ የገባው ወይም የክርስትና ሃይማኖትና ኢትዮጵያ የተዋወቁት መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው ከአስራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ሐዋርያው ፊልጶስ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ በጋዛ ባጠመቀው ጊዜ ነው።ይህም የሆነው ጌታ በተወለደ በ34ኛው ዓመት ባረገ በ9ኛው ወር ነው።ጃንደረባው ተጠምቆ ወደ ሀገሩ ከተመለሰ በኋላ አዲሱን ሃይማኖት ለሀገሩ አስተምሯል።ጃንደረባው ሕገ ወንጌልና ጥምቀት ሲቀበል **በመልአኩ ተላላኪነት፣በመንፈስ ቅዱስ አዛዥነት፣ከአስራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ በሆነው በፊልጶስ አጥማቂነት** እንደነበር ከ72ቱ አርድዕት አንዱ የሆነው ሐዋርያው ሉቃስ መስክሯል።ጃንደረባው ተጠምቆ ከተመለሰ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀደም ብሎ ይዞት በነበረው እምነት አዲስ ኪዳን በመጨመር ሥርዓተ ንስሐን፣ጥምቀትን፣ ፀሎትን፣ጾምን፣መስዋዕትን በማስተማርና በማስፋፋት ሰፊ አገልግሎት በመፈጸም እስከ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን እስከ 330 ዓ/ም ድረስ እንደቆየ ታሪክ ይናገራል።ከንግሥት ሳባ ጀምሮ በየዘመኑ የነገሡ ኢትዮጵያውያን ነገሥታት ከእስራኤል ጋር የጠበቀ ግንኙነት ስለነበራቸው በየጊዜው ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ አምልኮተ እግዚአብሔርን ፈጽመው ይመለሱ ነበር።ከክርስቶስ ልደት በፊት 8 ዓ/ዓ እስከ ከክርስቶስ ልደት በኋላ 9 ዓ/ም ኢትዮጵያን የመራው **ንጉስ ባዚን** ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ ኢየሩሳሌም በመጓዝ የስግደት ሥርዓት ፈጽሞ የክርስቶስን መወለድ አይቶ ወርቅ ዕጣን ከርቤ ከገበሩት ሦስቱ ነገሥታት አንዱ የኢትዮጵያ ንጉሥ እንደነበር ይተረካል።ኢሳ 60፤6 መዝ 71፤10 እንደታሪክ ምስክርነት ክርስትናን ከተቀበሉ ሀገሮች በቀደምትነት ከሚጠቀሱት ሀገሮች ኢትዮጵያ ቀዳማዊት ናት።ከክርስቶስ ዕርገት በኋላ ለሐዋርያት መንፈስ ቅዱስ በወረደላቸው ጊዜ በማርቆስ እናት ቤት ከተሰበሰቡት አባቶች መካከል ኢትዮጵያውያን እንደሚገኙበት ቅዱስ ዮንሐስ አፈወርቅ በድርሳኑ ገልጿል፡ይሁን እንጂ እምነትን ከእኛ በኋላ የተቀበሉ ሀገሮች ከእኛ ቀድሞ ሲኖዶስ፣ጳጳሳትና ፓትርያርክ ወዲያወኑ ሲያገኙ እኛ ግን ወደኋላ በመቅረታችን የእስክንደሪያ /የግብጽ/ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ጳጳሳት **ለ1,600 ዓመታት** በመላክ ቤተ ክርስቲያናችን ወደኋላ እንድትቀር አድርጓታል።ምንም እንኳ የመጀመሪያው ጳጳስ ፍሬምናጦስ **/አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን/ በ328 ዓ/ም ቢሾምም** አልፎ አልፎ ከሚሾም በቀር ባለመቀጠሉ ለመጀመሪያ ጊዜ **አራት ጳጳሳት በ1921 ዓ/ም ሲሾሞ ፓትርያርክ ደግሞ በ1951 ዓ/ም ተሹሟል**።እንዲህም ሆኖ እያለ ግን ቤተ ክርስቲያናችን የታሪክ፣የቅርስ፣የፀጋ፣የበረከትና የተአምራት ባለቤት ሆና ከሁሉም በፊት ቀድማ ፊት ለፊት የምትገኝ ናት።**ኢትዮጵያ ማለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን፤የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ማለት ደግሞ ኢትዮጵያ ማለት ነው።**

**1.5.2. ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፡-** ከጥንት ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያውያን እንደ እስራኤላውያን ልማድ በየዓመቱ ለፋሲካ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም ይወጡ ነበር።የንግሥት ሕንደኬ ጃንደረባ ባኮስ በ32 ዓ/ም የፋሲካን በዓል ሊያከብር ሊሰግድና ጸሎት ሊያደረግ ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዘ።በዚያን ዘመን ጉዞ ወደ ኢየሩሳሌም ለመድረስ 4000 ማይልስ መጓዝን ይጠይቅ ነበር።በዓለ ሃምሳን አክብሮ ወደ ሀገሩ ሲመለስ የነቢዩ የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር።ኢትዮጵያውያን መቼም ቢሆን ከእግዚአብሔር መለየት አይወዱምና የበረሃው ሙቀት ሳያሰቅቀው በሠረገላው ውስጥ ሆኖ የነቢዩን መጽሐፍ ያነባል ነገር ግን የሚያነበውን የትንቢት ቃል ሊገባው አልቻለም ነበር።የተሰውረውን መግለጥ ልማዱ የሆነው እግዚአብሔር ወንጌላዊው ፊልጶስን ወደ ጃንደረባው ላከለት።ሐዋ 8፤26 ሕፅዋ ለሕንደኬ /ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ/ ከምኩራብ ከሚሰጠው ትምህርተ ኦሪት በለመደው መሠረት ምንም ትርጉሙ የማይገባውን መጽሐፈ ኢሳይያስን ምዕ 53፤7 የተጻፈውን ኃይለ ቃል እያነበበ ተገኘ።ፊልጶስም ጠጋ ብሎ በእውኑ የምታነበውን ታስተውላለህን ሲል ጠየቀው ጃንደረባው ባኮስም በተለመደ ኢትዮጵያዊ ትህትናው የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል ሲል መለሰለት ከዚህ በኋላ የፊልጶስን በሥጋ ደካማ መሆን ሳይንቅ ወደ ሰረገላው እንዲወጣና አብሮት እንዲቀመጥ ጋበዘው።ጃንደረባው

ምንም የማይገባውን ነቢዩን መጽሐፍ እያነበበ መገኘቱ የሚያሳየው ዕብራውያን ትርጉሙ ባይገባቸውም ከነቢያት መጽሐፍ አንዱን ባነበቡ ጊዜ በነቢዩ ላይ ያደረው መንፈሰ ትንቢት በነሱ ላይ አድሮ ምስጢሩን እንደሚገልጽላቸው ያምኑ ስለነበር ነው።

ሐዋርያው ፊልጶስ ሲያነብ የነበረውን ዘርዝሮ ሰበከለት ጃንደረባውውም አመነ ወደ ወንዝ በደረሰ ጊዜም **‹‹ነዋ ማይ መኑ ይከልአኒ ተጠምቆ ››** **እነሆ ውሃ አለ እንዳልጠመቅ የሚከለክልኝ ማነው** በማለት ፊልጶስን ጠየቀው።ፊልጶስም በፍፁም ልብህ ብታምን ተፈቅዶልሃል አለው።ለብዙዎች ለማመን የምታስችግራቸውን ንጽህት እምነት ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ ሲል መሰከረ።ከኢየሩሳሌም 20 ማይልስ ርቀት በምትገኘው በቤተ ሳሮንና በኬብሮን መካከል ባለው ኮረብታ ሥር በሚመነጨው ወንዝ ተጠመቀ ቦታዋን ጋዛ በመባል ትጠራለች።ጃንደረባው ተጠምቆ በ34 ዓ/ም ወደ **ሀገሩ ከተመለሰ በኋላ በአክሱም አስቀድሞ ንግሥት ሕንደኬ በኋላም የቤተ መንግስቱ ሰዎች መኳንንቱና መሳፍንቱን ወንጌል አስተምሯቸው አጥምቋቸዋል በኋላም በሀገሩ እና በኑብያ፣በየመን ፐርሺያና ህንድ እየተዘዋወረ ክርስትና /ወንጌል/ ሰብኳል በመጨረሻም ሀገረ ስብከቱን ታኘሮባና /ታኘሮዝና/ ዛሬ ሲሎን የምትባው ደሰት ናት በዚያ ወንጌል ሲያስተምር አረማውያን በጠላትነት ተነስተውበት በሰማዕትነት አርፏል**።/ቤተ ክርስቲያንን እወቅ ገጽ 145-146/ የቤተ ክርስቲያን አባት የሚባለው አውሳብዮስም ጃንደረባው ለሀገሩ ወንጌል እንዳስተማረ በጽሑፉ አስፍሯል።በሌላ በኩል ጃንደረባው እንዳስተማረ ማስረጃ ከ34-42 ዓ/ም ኢትዮጵያውያን የገዛች ንግሥት ሕንደኬ /ጌርሻሞት/ የተባለች ንግሥት በስሟ ባስቀረጸችው የወርቅና የብር ገንዘብ **‹‹ዘሞአት በክርስቶስ/ በክርስቶስ ያሸነፈች** የሚል ጽሑፍ ያለበት ሲሆን በንግሥናዋ ዘውድና በገንዘቧም ላይ የመስቀል ምልክት ነበረበት።

### 1.6. ስለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የጸፉ የውጭ ሊቃውንት

1. ሩፊኖስና ሶቅራጥስ በኢትዮጵያ ሐዲስ ኪዳንን ወንጌላዊው ማቴዎስ አስተምሯል ብሏል።
2. አባ ጀሮም ከ317 እስከ 419 ዓ/ም የነበረው የላቲን ቤተ ክርስቲያን አባት የኢትዮጵያ ሐዋርያ ቅዱስ እንድሪያስ ነው ብሏል።
3. ዮሐንስ አፈወርቅ ደግሞ የኢትዮጵያ ሐዋርያ ቅዱስ ቶማስ ነው ብሏል።
4. አርጌንስ የተባለው የእስክንደሪያ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ወደ ኢትዮጵያ ምንም ሐዋርያ መጥተው አላስተማረም።ነገር ግን ጥቂት የአፍሪካ ሀገሮች ብቻ የወንጌል መልዕክት መድረሱን ይናገራል።
5. አውሳብዮስ በትውልድ ፍልስጤማዊ የምዕራባውያን የታሪክ አባት ሲጽፍ ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ ምንም ሐዋርያ አልተላከም።ነገር ግን ጃንደረባው ለወገኖቹ ሐዋርያ ሆነ በማለት የኢትዮጵያ ሐዋርያ እሱ ነው በማለት ወሳኝና ግልጽ የሆነውን ታሪክ አስቀምጧል።

ከላይ የዘረዘርናቸው የብዙዎች የታሪክ አቀማመጥ የተለያየበት ሃሳብ የሐዋርያት ገብቶ ማስተማር ሳይሆን አንዳንድ ፀሐፊዎች እንዳሉት በኢትዮጵያ ሐዋርያት ሲስተምሩ በሰማዕትነት ሞቱ የሚለው ነው።ሐዋርያት ሲያስተምሩ የሞቱት በአህዛብ ሀገር ጣኦታትን በመቃወማቸው በቄሳሮች ግዛት እንጂ ኢትዮጵያውያን ሰውን እንዳይገድሉ የብሉይ ኪዳን አማኞች በመሆናቸው አትግደል የሚለውን 5ኛውን አንቀጽ አውቀውና ለይተው ሲያስተምሩ የቆዩ ናቸው።ስለዚህ **ቅዱስ አውሳብዮስና አርጌንስ** ባስቀመጡት ሃሳብ መሠረት ትክክለኛው ታሪክ ፈር የያዘ ይመስላል።የዚህም ዋና ምክንያት በዚያን ዘመን ኢትዮጵያ ገናና ሀገር ስለነበረች አብዛኞች ሀገሮች ኢትዮጵያ የሚለውን ስያሜ እየወሰዱ ይጠቀሙ ነበር።በርካታ ሐዋርያት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ቢያስተምሩም ተልዕኳቸው ዓለምን ዞረው ለማስተማር ስለሆነ ኢትዮጵያም የዓለም አንዷ አካል ስለሆነችና ለክርስትና መንደር ለኢየሩሳሌም ቅርብ ስለሆነች ኢትዮጵያ መጥተው

ያስተማሩ ሐዋርያት ቁጥር በዛ ሊባል አይችልም፡፡ነገር ግን እዚህ ላይ ልንገነዘብ የሚገባን **የመጀመሪያው የኢትዮጵያ የወንጌል ሰባኪ ጃንደረባው ባኮስ** መሆኑን ነው፡፡ኢትዮጵያ በጃንደረባው አማካይነት ክርስትናን በ 34 ዓ/ም የተቀበለች ብትሆንም በሲኖዶስ ሕግ የጳጳሳት መንበር የተሰጣት በ 330 ዓ/ም ፍሬምናጦስ የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን በተሰጠው ጊዜ ነው፡፡

---

## ምዕራፍ ሁለት

## ሲኖዶስ በኢትዮጵያ

ሲኖዶስ ማለት ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ለመወሰን የሚደረግ በፓትርያርክ ሰብሳቢነት የሚመራ የሊቃነ ኤጲስ ቆጶሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ ነው፡፡ሲኖዶስ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ለመወሰን በሐዋርያት ጊዜ ተጀምሯል፡፡ከሐዋርያት በኋላ የተነሱ ሊቃነ ኤጲስ ቆጶሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ቤተ ክርስቲያንንና ዓለሙን ለማስተዳደር ሲኖዶስ በማድረግ ውሳኔን አስተላልፈዋል፤አሁንም በማድረግ ላይ ይገኛሉ፤እስከ ዘለዓለም ፍጻሜ በዚሁ ሁኔታ ይቀጥላሉ፡፡ሐዋ 15፤19-25 ከፍተኛው የቤተ ክርስቲያን የሥልጣነ ክህነት ባለሥልጣን ቅዱስ ሲኖዶስ ነው፤ሥልጣኑም በካህናት፣በዲያቆናት፣ በምዕመናንና በምዕመናት ሁሉ ላይ ይሠራል፡፡በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የሚሰበስበውና በፓትርያርኩ ሊቀ መንበርነት የሚሰበሰበው የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ በቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳደር ይግባኝ የሌለበት የመጨረሻ ውሳኔ ነው፡፡ቅዱስ ሲኖዶስ ለመሠረተ እምነትና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የበላይ ኃላፊ እንደመሆኑ ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲወራረድ ፀንቶ የመጣውን የእምነት ሥርዓት ያለምንም ለውጥ ለሚቀጥለው እንዲተላለፍ የማድረግ ግዴታና ኃላፊነት ያለበት አካል ነው፡፡በሀገራችን ይህ ጉባኤ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ እንደአሁኑ የተደራጀ ባይሆንም ከአባ ሰላማ ጀምሮ የተጠናከረ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር እንደነበር ታሪክ ይነግረናል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ኢትዮጵያ ክርስትና የተቀበለችው በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ይሁን እንጂ በሲኖዶስ ሕግ የኤጲስ ቆጶስነት መንበር የተሰጣት ግን በ4ኛው ምዕተ ዓመት በ330 ዓ/ም ነው፡፡ይህንንም ዕድል ያገኘችበትን **ሩፊኖስ የተባለ የታሪክ ፀሐፊ** እንደሚከተለው ይተርከዋል፡፡በ300 ዓ/ም አካባቢ ሜሮጵስዮስ የተባለ ግሪካዊ ነጋዴ /ፈላስፋ/ የጠቢባን አለቃና አስጎበኚም ነው ይሉታል በእስክንድሪያና በህንድ ሀገር እየተመላለሰ ይነግድ ነበር፡፡ይህ የጢሮስ /የሶርያ/ ነጋዴ በኃላፊነት ሰብስቦ ያስተምራቸው የነበሩ ፍሬምናጦስና ኤዴስዮስ /ሲድራኮስ/ ከተባሉ ሁለት ክርስቲያን ወጣት ልጆች ጋር በመሆን ከጢሮስ ወደ ህንድ ለመጓዝ በጀልባ ተሳፍረው ከአፍሪካ የባህር ወደብ በቀይ ባህር አካባቢ ይደርሳሉ፡፡ቀይ ባህርን አቋርጠው በኢትዮጵያ ጠረፍ በምትገኘው በቀድሞው የወደብ ከተማ በነበረችው አዱለስ ውሃ ለመጠጣትና ሀገር ለማየት ጀልባቸውን ከወደብ አስጠግተው ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ይገባሉ፡፡በአካባቢው የነበሩ ጠረፍ ጠባቂዎችም በተሳፋሪዎች ላይ አደጋ ጥለው ዕቃቸውን ዘርፏዋቸው፡፡ሜሮጵዮስና የጀልባ ቀዛፊዎች ወዲያው ሲገደሉ ከአደጋው ያመለጡ ሁለት ወጣቶች ፍሬምናጦስና ኤዴስዮስ /ሲድራኮስ/ በዛፍ ሥር ሲፀልዩ መጽሐፍ ሲያነቡ የአዱለስ ሰዎች አገኙዋቸው፡፡ሰዎችም በሕይወታቸው ላይ አደጋ ሳያደርሱ ልጆቹን ለሀማሴን ገዥ ለነበረው ለባህረ ነጋሽ አስረከቡት፡፡ባህረ ነጋሽም የአክሱም ንጉሥ ለነበረው **ለቀዳማዊ አልአሜዳ ወይም ኢዛና** ወስደው አስረከቡአቸው፡፡ንጉሡም ስለወጣቶቹ ከተረዳ በኋላ ከእርሱ ልጆች ከኢዛናና ሳይዛና ጋር በቤተ መንግስት አስቀምጦ የግዕዝ ቋንቋና የሀገሪቱን ባህል እንዲያወቁ አደረገ፡፡ይህም ህጻናቶቹን በክርስትና እምነት እየተኮተኮቱ እንዲያድጉ ምቹ ሁኔታ ፈጥሮለታል ባህልና ቋንቋም በደንብ አጠኑ፡፡በቤተ መንግስት ከሰባት ዓመት ቆይታ በኋላ ወጣቶቹ ተወዳጅነት እያገኙ በመሄዳቸው ፍሬምናጦስን በዕድሜና በትምህርት የበሰለ ስለነበረ የንጉሡ ልጆች አስተማሪና ሞግዚት እንዲሁም በጅሮንድ /የንጉሥ ግምጃ ቤት፣የገንዘብ ቤትና የንብረት ክፍል ኃላፊ ኤዴስዮስን ጋሻ ጃግሬ /የንጉሥ ተከታይ/ ወይም ፀሐፊ ትዕዛዝ አድርገው ሾማቸው፡፡እነሱም በአክሱም ቤተ መንግስት ታማኝነት፣ተወዳጅነትና ተሰሚነት አገኙ፡፡

የአክሱም ንጉሥ ኢዛና ሲሞት የእርሱ ልጆች ሥልጣኑን ለመረከብ ዕድሜያቸው ገና አካለ መጠን ያልደረሱና 12 ዓመት ልጆች በመሆናቸው እናታቸው እቴጌይቱ ንግሥት አሕይዋ /ሶፊያ/ ሥልጣኑን በሞግዚትነት እንድትይዝ ሁለቱ ልጆች ግን ወደ ፈለጉበት እንዲሄዱ አደረጋቸው፡ነገር ግን በእቴጌይቱ ልመና ሁለቱም ወጣቶች ልጆቿ እስኪያድጉ ድረስ በአስተዳደር በኩል እየረዷት ፍሬምናጦስ ሁለቱን የንጉሥ ልጆች ወንጌል በማስተማር ለ3 ዓመታት ያህል ከንግሥቲቱ ጋር በፍቅር ኑረዋል።የንግሥቲቱን ቃል በማክበርም በቤተ መንግስት ውስጥ በአማካሪነት ሲያገለግሏት ቆይተዋል፣ልጆቿም በክርስትና ትምህርት ተኮትኩተው አደጉ።ፍሬምናጦስ ከመንግስት ሥራው በተጨማሪ በቤተ መንግስቱ አካባቢ ያለውን የክርስትና እምነት እንቅስቃሴ ይከታተል ነበር።በዚህም ጊዜ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች እምነት ብቻ እንጂ ክህነትና የቁርባን ሥርዓት እንደሌላቸው ተረዳ ምክንያቱም እነዚህን ለማሟላት ጳጳስ ያስፈልጋል።የንጉሡ ልጆችም ለአካለ መጠን ደርሰው የአባታቸውን መንግስት ከእናታቸው ሞግዚትነት ሙሉ በሙሉ ተረክበው የንጉሠ ነገሥትነታቸውን ያዙ።እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ ቃል ተናጋሪ በመሆን በመንፈሳዊ ጥበብ እየተመሩና እየተራቀቁ የእግዚአብሔርን ሕልውና ለሕዝብ እያስተዋወቁ ለ15 ዓመታት ኢትዮጵያን አስተዳደሩ።ኢዛናና ሳይዛና ሥልጣነ መንግስቱን ከተረከቡ በኋላ ኤዴስዮስ ወደ ሀገሩ ወደ ጢሮስ /ሶርያ/ ሄዶ ካህን ሆነ።ይህንንም በኢትዮጵያ ያሳለፈውን ጊዜ በጢሮስ ከሩፊኖስ ጋር ተገናኝተው እንደተናገረው ሩፊኖስ በመጽሐፉ መግቢያ ላይ ጽፎት ይገኛል።ኢዛናና ሳይዛና ሥልጣነ መንግስቱን ከተረከቡ በኋላ ቀደም ብሎ በጃንደረባው የተሰበከው ክርስትና የሚጠናከርበትን መንገድ ያስተካክሉ ጀመረ።በዚህ መሠረትም የሚያስተምርና የሚያጠምቅ ጳጳስ እንዲያመጣ ፍሬምናጦስ ለነገሥታቱና ለንግሥት ሶፊያ ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ፍሬምናጦስን ወደ እስክንድሪያ ላኩት፡

**2.1. የፍሬምናጦስ ጉዞ ወደ እስክንድሪያ**፡-ንግሥት ሶፊያ /የአብርሃና የአጽብሃ እናት/ በንግሥት ሳባና በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግስት የኦሪት ሃይማኖት /ብሉይ ኪዳን/ መግባቱን፤በንግስት ሕንዴኬና በጃንደረባው ዘመነ ደግሞ ህገ ወንጌል /ሐዲስ ኪዳን/ ጥምቀተ ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ መግባቱን ከታሪክ በመረዳት ሲኖዶስ፣ክህነትና የክህነት ሥርዓት ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ በማጥናት ሊቃውንትንና የሀገር ሽማግሌዎችን በማሰባሰብ መልዕክተኞችን ወደ እስክንድሪያ ሄዶ ጳጳስን እንዲያመጡ እንዲላኩ አስወሰነች።በዚያን ጊዜ በአፍሪካ የክርስትና ማዕከል ወደ ነበረችው እስክንድሪያ ፍሬምናጦስ ስለጵጵስና ጉዳይ ከእስክንደሪያ ቤተ ክርስቲያን ጋር እንዲወያይ ከአክሱም ቤተ መንግስት ተልኮ ሄደ።ይህም የሆነው በ325 ዓ/ም ገደማ ነው።ፍሬምናጦስ ወደ እስክንድሪያ የሄደው ሃይማኖት /ጥምቀት/ ሊያመጣ ሳይሆን ክህነትና የክህነት አስፈጻሚ አባት ለማምጣት በመሆኑ የኢትዮጵያና የእስክንድሪያ ግንኙነት በሃይማኖት ሳይሆን በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን /በምስጢረ ክህነት/ ላይ የተመሠረተ ጥያቄ ነው።

ፍሬምናጦስና ልዑካኑ ወደ እስክንድሪያ በሄዱበት ዘመን  አርዮስ ወልድ ፍጡር ነው  ብሎ የክህደት ትምህርት ይዞ የተነሳበት ወቅት ስለነበረ የእስክንድሪያ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ባለሥልጣናት አርዮስንና አርዮሳውያንን ለማውገዝ በኒቂያ ጉባኤና በሱባኤ ላይ ስለነበሩ በ19ኛው የእስክንድሪያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በቅዱስ እለእስክንድሮስ የገባው ደብዳቤ ከ3 ዓመት ቆይታ በኋላ በ20ኛው ፓትርያርክ በቅዱስ አትናቴዎስ ተፈፀመ።ይኸውም የኒቅያውን ጉባኤ በሊቀ መንበርነት የመራው 19ኛው የእስክንድሪያ ፓትርያርክ እለእስክንድሮስ 318 ሊቃውንት አርዮስን አውግዘው ሃይማኖት አቅንተው ጸሎተ ሃይማኖትን አርቅቀው እስክመለሱ ፍሬምናጦስ ከአንድ ዓመት በላይ እስክንድሪያ ቆየ።በጊዜው 19ኛው የእስክንድሪያ ፓትርያርክና ጉባኤ ኒቅያን በሊቀ መንበርነት የመራው እለእስክንድሮስ ስላረፈ በመንበሩ ቅዱስ አትናቴዎስ ተተካ።ይህም የሆነው በ328 ዓ/ም ነው።ፍሬምናጦስ ከብዙ ጊዜ መጉላላት በኋላ የመጣበትን ጉዳይ በመንበሩ አዲስ ለሆነው ለ20ኛው የእስክንድሪያ ፓትርያርክ ለቅዱስ አትናቴዎስ በዝርዝር አቀረበ።

ቅዱስ አትናቴዎስ ተደስቶ ለኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ቋንቋቸውንና ባህላቸውን የሚያውቅ ሌላ የተሻለ ሰው

እንደማይገኝ ስለተረዳና ፍሬምናጦስ ቢሾም ከፍተኛ ጠቄሜታ ስለሚኖረው አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፍሬምናጦስን ኤጴስ ቆጶስ ዘአክሱም ወዘኩላ ኢትዮጵያ ብሎ በሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ በቅብዓትና በአንብሮተ ዕድ ሹሞ ላከው።ቅዱስ ፍሬምናጦስ ከቅዱስ አትናቴዎስ የተቀበለውን ከፍተኛ ማዕረግ ተጎናጽፎ ወደ ኢትዮጵያ በሚገባበት ወቅት ሁለቱ ወንድማማች ነገሥታትና መኳንንት ሕዝቡ በታላቅ ደስታና ክብር በአክሱም ከተማ ተቀበሏቸው።ፍሬምናጦስ ምንም እንኳ ተወላጅነቱ ሶርያዊ /ጢሮሳዊ/ ግሪካዊ ቢሆንም በህጻንነቱ ወጥቶ ያደገውና ዜግነቱም ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገ ቅዱስ አባት ነው።ፍሬምናጦስ ተሹመው ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ የኢትዮጵያ ሕዝብ የወንጌልን ብርሃን ለኢትዮጵያ ያበሩ የወንጌል ብርሃን የገለጡ ሲሉ አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን የሚል ስም ሰጥቷቸዋል።አባ ሰላማ ወደዚህ ከመጡ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ነገሥታቱን በማጥመቅ **ኢዛናን አብርሃ ሳይዛናን አፅብሐ** የሚል ስያሜ ሰጥቷቸዋል። ነገሥታቱም ከእነሱ በኋላ በኢትዮጵያ የነገሡ ነገሥታት ዓለማዊ ስማቸውን እየቀየሩ በክርስትና ስማቸው እንዲጠሩ ዓይነተኛ ምክንያት ሆነዋል።

አባ ሰላማ ከቅዱስ አትናቴዎስ የተቀበሉት ጵጵስና ብቻ አይደለም ይዘው ወደ ኢትዮጵያ የገቡት በኒቂያ ላይ የፀደቀውን **የወልድ በመለኮት ከአብ ጋር እኩል መሆኑን** የሚያምን መግለጫ ጭምር ነው።በመንግስት ደረጃ የኒቂያ ጉባኤ ውሳኔ የተቀበለ የአክሱም መንግስት ብቻ ነው።እንደኦሪቱ ሥርዓት ሊቀ ካህን የነበረው እንበረም አቡነ ሰላማ ወንጌልን አስተምረው ስላሳመኑት በክርስትና መስፋፋት ረገድ ሊተባበራቸው ችሏል።የኤጲስ ቆጶስነት ማዕረግ ተሰጥቶት ከእሳቸው በታች አድርገው ስለሾሙት ሥራቸው ይበልጥ እየተቃናላቸው ሄደ።ነገሥታቱም አብርሃና አፅብሐ ከአቡነ ሰላማ ጎን በመሆን ሥሩ የጠለቀውን የክርስትና እምነት በኢትዮጵያ እንዲስፋፋ እገዛ አድርገዋል።ከ34 ዓ/ም ጀምሮ ክርስትና በኢትዮጵያ የገባበት ዘመን ቢሆንም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተቋቋመችው ወይም ክርስትና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት ሆኖ የታወጀው በ350 ዓ/ም ነው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቀች ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያን ለመሆን መብቃቷን ታሪክ ያስረዳል።

**2.2. አቡነ ሰላማ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያበረከታቸው አስተዋጽኦ፡-** አባ ሰላማ ጳጳስ ሁነው ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ በኋላ ወዲያኑ ለአብርሃና አፅብሐ ማዕረገ ዲቁና ሰጥተው ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ ቅብዓ መንግስቱን ቀብተው እንዲነግሡ አደረጉ።እነዚህ ሁለት ቅዱሳን ነገሥታት ህገ ኦሪትን ወደ ህገ ሐዲስ ሙሉ በሙሉ በመለወጥ በመላው ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ብሔራዊ ሃይማኖት እንዲሆን በሀገረ አቀፍ ደረጃ በአዋጅ አጸደቁ።አባ ሰላማ የተሸከሙትን መንፈሳዊ ኃላፊነት በትክክል መወጣታቸውን በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም አብያተ ክርስቲያናት መስክረውላቸዋል በቅዱስነት ደረጃም አስቀምጠዋቸዋል።አባ ሰላማ በኢትዮጵያ ከሠሩቸው ብዙ መንፈሳዊ ሥራዎች መካከል

1. የክርስትና እምነትና ሥርዓት እንዲስፋፋ አድርገዋል
2. ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ በምልዓት እንዲጀመር አድርገዋል
3. በኢትዮጵያ ምድር ሙሉ የወንጌል ትምህርት ለማዳረስ የሚረዱትን ቀሳውስትና ዲያቆናት ሾመዋል።
4. አባ ሰላማ ለቤተ ክርስቲያን ካበረከታቸው ታላላቅ ሥራዎች ዋነኛው የቅድሳት መጻሕፍት መተርጎም ነው።ቅድሳት መጻሕፍትን ከሱርስት፣ከግሪክ /ጽርዕ/ ከ70 ሊቃናት ትርጉም እና ከዕብራይስጥ ወደ ግዕዝ ቋንቋ ተርጉመው ጽፈዋል።
5. የጥንቱ የሳባውያን /የግዕዝ/ ፊደል ዛሬ እንደሚነበበው ከካዕብ እስከ ሳብዕ ያለው ድምፅ አልነበረም።ግዕዙን

ብቻ አናጋሪ አድርጎ ይነበብ ነበር።ለምሳሌ ሐወለተ አከሰመ ሐውልተ አክሱም ማለት ነው።በዚህ ሁኔታ መጻሕፍትን መተርጎም አስቸጋሪ ስለሆነ አባ ሰላማ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ሊቃውንት ጋር ተማክረው በጥንታዊ ፊደል ቅርጽ መሠረት ከካብዕ እስከ ሳብዕ ያሉትን 6 ድምፅ ሰጭ ፊደላትን ተርጉመዋል።ከዚህም በተጨማሪ የኢትዮጵያ ጽሕፈት እንዳ አሁኑ አረበኛ ከግራ ወደ ቀኝ ይጻፍና ይነበብ የነበረውን በፈጠራ በማስተካከል ከቀኝ ወደ ግራ እንዲጻፍና እንዲነበብ አድርገዋል።

6. በአባ ሰላማ አማካይኝነት አብረሃ ወአፅብሃ ለታላቁ ቆስጠንጢኖስ በጻፉት ደብዳቤ መሠረት በ70 ዓ/ም ኢየሩሳሌም በጥጦስ ጠፍታ ስለነበር ጠፍቶ የነበረው ታሪካዊው ርስት ዴር ሱልጣን ለኢትዮጵያውያን ሆኖ እንዲጠበቅ አደረገዋል።

7. የመጀመሪያው መንፈሳዊ ትምህርት ቤት አቋቋመዋል።

8. በየቀበሌው አንድ አንድ ቄስ መካሪ አበ ነፍስ አደርገዋል።ይህም የነፍስ አባት ከጊዜ በኋላ ስለኃጢአት ኑዛዜ በመቀበል ንስሐ የሚሰጥ የንስሐ አባት ተብሏል።ይህም ሥርዓት እስከ ዛሬ ተጠብቆ ይገኛል።

9. የሚጠመቀውን ህጻን በእግዚአብሔር መንገድ እየመራ የሚያስተምረው እንደዋስ፣ተያዥ ሆኖ በቤተክርስቲያን ፊት መቀበሉን የሚያረጋግጥ ምዕመን አበ ልጅ /የክርስትና አባትና እናት/ ሥርዓትን ሠርቷል።ይህ ሥርዓት ከመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጋር አብሮ የተመሠረተ ቢሆንም አሁን ግን መንፈሳዊ ሥርዓቱን ለቆ የወገን ማደራጃ ሆኗል።

10. የመጀመሪያዋ ጽዋ ማህበር ማህበረ ጽዮንን በ347 ዓ/ም አቋቋመዋል።ዓላማውም ሕዝቡ እመቤታችንን ይወዳት ስለነበር በጽዮን ስም ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋትና ቃለ እግዚአብሔርን ለማዳረስ ያመች ዘንድ ማህበረ ጽዮን ብሏታል።ከዚህም የተነሳ የጽዋ ማህበር ዓላማ ስብከተ ወንጌል ለማስፋፋት፤አብያተ ክርስቲያናትን በየቦታው ለማሠራት፤የቅዱሳንን በረከት ለመሳተፍ እና ድሆችን ለመርዳት የተቋቋመ ሃይማኖታዊ ትውፊት ነው።እነዚህንና ሌሎችንም መንፈሳዊ ትሩፋቶችን ለቤተክርስቲያን በማበረከት ሐዋርያዊ ተጋድሎውን ፈጽሞ አርፈዋል።

**2.3. አብርሃ ወአጽብሃ፡-**ኢይዛናና ሳይዛና በፍሬምናጦስ በ330 ዓ/ም ከተጠመቁ በኋላ አብርሃ ወአጽብሃ ተብለው መጠራት ጀመሩ።እነዚህ ሁለት ነገሥታት ሥልጣነ መንግስቱን ከእናታቸው ከተረከቡ በኋላ ከአባ ሰላማ ጋር በመተባበር ብዙ መንፈሳዊ ሥራዎችን ፈጽመዋል።ከሥራዎቻቸውም መካከል

1. **የአብያተ ክርስቲያናት መታነጽ፡-** አብርሃ ወአጽብሃ በ330 ዓ/ም ተጠምቆ ክርስትናን ከተቀበሉ በኋላ ክርስትናን ከማስፋፋት ጋር የሚጸናበትንም መንገድ በማበጀት አስተዋጽኦ አድርዋል።በአቡነ ሰላማ አሳሳቢነት ለመጀመሪያ ጊዜ የአክሱም ባለ12 መቅደስ ባለ 5 ክፍልና ባለ72 አዕማድ ቤተ ክርስቲያን በጽዮን ማርያም ስመ አሠርተዋል።ለመጀመሪያ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን በዓለም የታነጸው በአክሱም ጽዮን ሲሆን ዘመኑም በ349 ዓ/ም ነው።በተጨማሪም በወሎ፣በአማራ ሳይንት፣ተድባበ ማርያም፣በጎጃም መርጦ ለማርያምና ጣና ቂርቆስ፣በምዕራብ ሸዋ ጎሐ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን አሠርተዋል።

**2.** ለወንጌል መስፋፋት የሚጠቅሙ አባቶች እንዲሾሙ አድርገዋል።

**3.** ሕዝቡን ከአምልኮተ ጣኦት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር፤ከህገ ኦሪት ወደ ህገ ወንጌል /ክርስትና/ መልሰዋል።ሁለቱ ነገሥታት ግዛታቸውን አስፋፍተው እስከ ኬንያና የመን፣ሶማሌና ሱዳንን አንድ አድርገው ከመግዛታቸው በተጨማሪ በእነዚህ ሀገሮች ሁሉ ወንጌል እንዲስፋፋ አድርገዋል።በኢየሩሳሌም ያለው

የኢትዮጵያ ገዳም ዴር ሱልጣን እንዲመለስ ጥያቄ ማቅረብና ተፈጻሚነት እንዲኖረው ማድረግ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እንዲሆን በ350 ዓ/ም በመወሰን ኢትዮጵያ የክርስቲያን ሀገር ሆና በዓለም እንድትታወቅ አድርገዋል።

በአፍሪካ ውስጥ ታላላቅ መምህራን የነበሩባቸው ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ሲጠፉ በኢትዮጵያ ለተቋቋመችው ቤተ ክርስቲያን ግን ማንኛውንም ችግር አልፋ እስከ ዛሬ ወንጌልን አጽንታ ለመቆየት የአባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ትምህርት ሳታጨልም በመቆየቷ ለመጀመሪያ ሐዋርያ አቡነ ሰላማ የትጋታቸው፣የፍቅር አገልግሎታቸው ፍሬ መሆኑ ሲያስደንቅ ይኖራል።አባ ሰላማ ከጃንደረባው ጀምሮ ይሰበክ የነበረው ጥምቀት በቁርባን፣በሜሮን፣በክህነት፣አፀናው።ዲቁናንና ቅስናንን በመስጠት ስብከተ ወንጌል እንዲስፋፋ አብያተ ክርስቲያናት እንዲመሠረቱ ከነገሥታቱ አብርሃ ወአፅብሃ ጋር ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ከምስራቅ እስከ ምዕራብ መንፈሳዊ እንቅስቃሴያቸውን በትጋት ጀመሩ።አብርሃ ወአጽብሃ ዘመነ መንግስት በሶማሌና በሞቃዲሾ ከተማ መቅደሰ ማርያም በመሥራት ወዲያውም በአማራ ሳይንት፣በወሎ፣እንደነተድባበ ማርያም በጎጃም መርጡለማርያም፣ጣና ቂርቆስ፣ስላሴ ቡሃጽዮን፣ሰሜን ኦሞ ብርብር ማርያም የመሳሰሉት አብያተ ክርስቲያናት ከአክሱም በመቀጠል እድል ያገኙ መካናት ናቸው።

አቡነ ሰላማ የተሸከሙትን መንፈሳዊ ኃላፊነት በትክክል ለመወጣታቸው በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥነ ጽሑፍ ብቻ ሳይሆን የተመሰከረላቸው ምዕራባውያንም ጭምር ነው።በቅዱስነት ደረጃም ይከበራሉ።ሮማ ካቶሊክ ኦክቶበር 27፣የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ኖቬምበር 30 መታሰቢያውን ያከብራሉ።አቡነ ሰላማ በእጃቸው ይይዙት የነበረው መስቀልና በግሪከኛ የቀደሱበት መጽሐፍ በጥንታዊቷ ተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ይገኛል።አቡነ ሰላማ በእግዚአብሔር ፈቃድ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያ ከመሆናቸውም በላይ ብዙ በረከቶችን ስላስገኙላት በዓመት የቅዱስነት ማዕረግ ሰጥታ ሁለት ጊዜ ሐምሌ 26 እና ታህሳስ 18 ቀን ቅዱስ አባት ብላ ታከብራለች፣በስማቸውም ቤተ ክርስቲያን አንጻለች።

<u>**አቡነ ሰላማ**</u>**፡-**

- መሠረቱ እስካሁን ያልተነዋወጸ ቤተ ክርስቲያን በስብከታቸው የመሠረቱ፣
- ቅድስናቸው በጥንት አብያተ ክርስቲያናት የተመሰከረላቸው፣
- የወንጌልን ብርሃን በመላው ኢትዮጵያ ዞሮ ያበሩ፣
- በመስቀለ ክርስቶስ የተገኘውን ሰላም ለኢትዮጵያ ያስተዋወቁ፣
- ሐዋርያዊ ግዴታቸውን በሚገባ የተወጡ፣
- በኢየሩሳሌም ላለው ርስታችን በነበሩበት ዘመን መፍትሔ ያሰጡ
- ሐዋርያዊ ሕይወት ያላቸው ታላቅና ቅዱስ የቤተ ክርስቲያናችን አባት ናቸው።

**2.4 ተሰዓቱ ቅዱሳን /480/፡-**አብርሃና አጽብሃ ከሞቱ በኋላ እስከ አፄ ካሌብ ድረስ ያለው የዘመን ልዩነት 100 ዓመት ነው።የቁስጥንጥንያ ግዛት ከታላቁ ቆስጠንጥኖስ ወዲህ የክርስትና ሃይማኖት በጣም እየተስፋፋ ሄዶ ነበር።ዳሩ ግን በታላቁ ቴዎዶስዮስና በተከታዮቹ ዘመነ መንግስት ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊቃነ ጳጳሳት፣ቀሳውስትና ዲያቆናት በበረከቱ መጠን እርስ በእርስ መለያየት ተከሰተ።ችግሩና በስደቱ ዘመን በኔሮን ቄሳር፣በዲዮቂልጥያኖስና

በመክስምያኖስ ጊዜ የነበራቸው ኅብረትና አንድነት በዚህ ዘመን ማለትም በ451 ዓ/ም አካባቢ የምቾት ጊዜ ጠፋና የቁስጥንጥንያው ከእስክንድሪያው፤የእስክንድሪያው ከሮማው ቤተ ክርስቲያን በአዲስ ሀሳብ ተለያዩ፡፡ይልቁንም ለክርስቶስ አንድ አካልና ሁለት ባህርይ አሉት የሚል አዲስ የአመለካከት ክህደት ተከሰተ፡፡ይህም ብቻ አይደለም የሥልጣንና የዘር ችግር ታከለበት፡፡በዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች ሁኬትና ፍጅት ተፈጠረ፡፡ጳጳሳቱና ቄሳውስቱ የጊዜውን መንግስት ተለጥፈው በሙግቱ ቀንቷቸው በተደላደሉበት ሰዓት ይህን የሁለት ባህርይ ትምህርት ለተራው ሕዝብ ጭምር እንዲደርስ አብልጠው ጣሩ፡፡ይሁን እንጅ በዚህ መካከል እነ ያዕቆብ ዘእንበለ ረድእ እና እነ ዲዮስቆሮስ የመሰሉ የተዋህዶ አባቶች መነሳታቸው ይታወቃል፡፡እነዚህ አንድ ባህርይ በተዋህዶ የሚሉ አባቶች ያላቸው ምርጫ መሰደድ ነበር፡፡በዚህ ምክንያት በ4ኛው መ/ክ/ዘመን መገባደጃ ላይ 9 መነኮሳት ተሰደው ወደ ኢትዮጵያ መጡ፡፡ባጭሩ እነዚህ ቅዱሳን የእስክንድሪያው ፓትርያርክ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ በኬልቄዶን ጉባኤ የአንድ ባህርይን እምነት በመደገፋቸው ምክንያት በንጉሡ መርቅያንና በንግሥቲቱ በብርክልያ ትዕዛዝ በደሴተ ጋንግራ ውስጥ ታስሮ ከመሰቃየት ከአረፈ በኋላ እነዚህ ቅዱሳን የአንድ ብህርይን እምነት በመከተላቸውና በማስተማራቸው ምክንያት ሁለት ባህርይን የሚከተሉትን መለካውያንን የሚደግፈው የሮማ ንጉሥ መርቅያን ከፍ ያለ ስቃይ ስለአደረሰባቸው በእምነት መሰሎቻቸው የሆኑ ክርስቲያኖች ወደ ሚኖሩባት ሀገር ወደ ኢትዮጵያ ተሰደው መጥተዋል፡፡ሀገራችን ኢትዮጵያ በዓለም ደረጃ ከምትታወቅባቸው ነገሮች አንዱና ዋናው እንግዳ ተቀባይነት ነው፡፡እንግዳ ስትቀበልም በሰብአዊነት፣በማህበራዊ ሕይወቱና ሃይማኖታዊ ይዘቱን በመመልከት እንደየሁኔታው ስታስተናግድ ቆይታለች፡፡ሀገራችን የተቀበለቻቸው እንግዶች ብዙ ቢሆንም ለማስረጃ ያህል

1. በተለያየ ጊዜ ከኢየሩሳሌም የተሰደዱ አይሁዶች፣
2. በሐዲስ ኪዳንም ከሶርያ /ከጢሮስ/ እና ከታናሽ እስያ ከሜሮጲዮስ ጋር አብሮ የመጡት ሁለት ወጣቶች ኤዴስዮስና ፍሬምናጦስ እነዚህ በኢዛና ቤተመንግስት በንግሥት ሶፊያ እጅ ከአብርሃና ከአጽብሃ ጋር አብሮ ያደጉ ወጣቶች፣
3. በ431 ዓ/ም በነበረው በኤፌሶን ጉባኤ የተወገዘውን ኋላም በጉባኤ ኬልቄዶን መለካውያን /ንጉሣውያን/ የሁለት ባህርይ ትምህርት /እምነት/ አንቀበልም በማለታቸው የተሰደዱ ዘጠኝ ቅዱሳን ምስክር ናቸው፡፡

ዘጠኙ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ ተሰደው ሲመጡ ኢትዮጵያን ያስተዳድር የነበረው የአፄ ካሌብ አባት ዳግማዊ ንጉሥ አልአሜዳ ነበሩ፡በዳግማዊ ንጉሥ አልአሜዳ ዘመነ መንግስት በ480 ዓ/ም በቤዛንታይን /የቆስጥንጥንያ የአንድ መንደር ስም ነው/ በጉባኤ ኤፌሶን የተወገዛውን ኋላም በጉባኤ ኬልቄዶን መለካውያን መልኩን በንባብ ሸፍነው የተቀበሉትን የሁለት ባህርይ እምነት አንቀበልም በማለታቸው በቤዛንታይን ነገሥታት ስቃይ የፀናባቸው 9 መነኮሳት ከሶርያና ከታናሿ እስያ ተሰደው ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል፡፡አባቶችንም ሀገራችን በእንግድነት ተቀብላለች፡፡እነዚህ ቅዱሳን የስደታቸው ምክንያት በጉባኤ ኬልቄዶን የተከሰተውን አዲስ ትምህርት /እምነት/ በመቃወማቸው ወደ ኢትዮጵያ የመጡትን ንጉሡ አቀባበል አደርገው በሰላም እንዲኖሩ ፈቀደላቸው፡፡

የዘጠኙ ቅዱሳን ስማቸው ገዳማቸውና የዕረፍታቸው ቀናት

| ተ.ቁ | ስም | የመጡበት ሀገር | የመሠረቱት ገዳም | ክብረ በዓላቸው ዕለት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አባ አረጋዊ | ሮም ቁስጥንጥንያ | ደብረ ዳሞ | ጥቅምት 14 ዕርገታቸው |
| 2 | አባ ጰንጠሌዎን | ሮም/ቁስጥንጥንያ/ | ከአክሱም ሰሜን ምስራቅ | ጥቅምት 6 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3 | አባ ይምዓታ | ኢጣሊያ/ቆስያ | ገርዓልታ | ጥምቅት 23 |
| 4 | አባ ገሪማ | ሮም/ቁስጥንጥንያ/ | መደራ አደዋ ሰሜን ምስራቅ | ሰኔ 17 |
| 5 | አባ ጽህማ | አንጾኪያ/ሶርያ/ | ጴደንያ | ጥር 16 |
| 6 | አባ አፍጼ | ታናሿ እስያ | የሐ/ዮሐ | ግንቦት 12 |
| 7 | አባ ሊቃኖስ | ቁስጥንጥንያ | ደብረ ቆናጽል ከአክሱም በስተሰሜን የሚገኝ ኮረብታ | ህዳር 21 |
| 8 | አባ አሌፍ | ቂሳርያ | ደብረ ሃሌሉያ | መጋቢት 11 |
| 9 | አባ ጉባ | ኪልቂያ /ግሪክ/ | ከአክሱም ሰሜን ምስራቅ | ግንቦት 29 |

ዘጠኙ ቅዱሳን በንግሥት ሳባና በቀዳማዊ ምኒልክ፣በንግሥት ህንዴኬና በጃንደረባው የተጠናከረውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት እጅጉን እንዲጠናከር አድርገዋል፡፡ ቅዱሳኑ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ለሥራቸው በር ከፋች የሆነውን ቋንቋና የሕዝቡን ባህል ጠንቅቀው ካወቁ በኋላ በአንድ አካባቢ ከመኖር ይልቅ መንፈስ ቅዱስ በመራቸው ቦታ ማስተማርን መርጠው መንፈሳዊ ዓላማቸውን ለማሳካት የአክሱም ነገሥታት እርዳታና ድጋፍ አልተለያቸውም፡፡

**የተሰዓቱ ቅዱሳን ሐዋርያዊ ተልዕኮቻቸው እና ያበረከቱት አስተዋጽኦ፡-** ተሰዓቱ ቅዱሳን ከሀገራቸው ተሰደው እንደመጡ በዘመኑ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ በነበረችው በአክሱም ለስብከተ ወንጌል የሚበቃቸውንና ለሥራቸው በር ከፋች የሆነውን ቋንቋ ጠንቅቀው ካወቁ በኋላ ሕዝበ ክርስቲያኑን ሕይወት ለውጠዋል፡፡አባ ዘጋስጫ ይህንን ሲገልጹ ምድር በሂደተ እግራቸው ተቀደሰች ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀሳቸው የተለያዩ ቦታዎች ታደሱ የትምህርታቸው መዓዛም በአካባቢዋ ሁሉ ፈሰሰ፡፡ በማለት ተናግሯል፡፡በዚህ መሠረትም የተሰዓቱ ቅዱሳን መልካም ሥራቸውንና ሐዋርያዊ ተግባራቸው ብዙ ቢሆንም ዋና ዋናዎቹን ብቻ እንመለከታለን፡፡

1. **ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ማፅናት**፡-ባዕድ አምልኮ የሚፈፀምበት ቦታ ሕንጻ ቤተክርስቲያን እንዲታነጽበት አድርጎ ቅዳሴ በዜማና በንባብ እንዲፈፀም አድርገዋል፡፡

2. **መጻህፍትን መተርጎም**፡-በአቡነ ሰላማ የተጀመረውን የመጻሕፍ ቅዱስና የፀሎት መጻሕፍትን የመተርጎም ሥራ ተከፋፍለው እስከ ፍጻሜ አድርሰውታል፡፡ለአድባራቱና ለገዳማቱ እንዲደርስም አድርገዋል፡፡በዚህ መሠረት የተሰዓቱ ቅዱሳን ዘመንና የቅዱስ ያሬድ ዘመን የመጀመሪያው የሥነ ጽሑፍ ዘመን በመባል ይታወቃል፡፡

3. ወንጌልን ማስፋፋት፡-በአንድ ሀገር ወንጌል ተሰበከ ሲባል በአንድ ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ክርስቲያን ሆነ ማለት አይደለም፡፡ክርስትና በአባ ሰላማ ተሰብኳል ሲባልም መላው ኢትዮጵያ ወንጌል ደርሷል ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡ስለዚህ ከአባ ሰላማ በፊትም ሆነ በኋላ የቤተክርስቲያን ዜጋ የመሆን ዕድል ያልገጠማቸው ኢትዮጵያውያን ነበሩ፡፡በዚህ መሠረት በሀገራችን ክርስትና ያልተዳረሰላቸው ቦታዎች ስላሉ እግዚአብሔር በሚያውቀው ዘጠኙ ቅዱሳን ለሀገራችን መምህር ሆነው መጥተዋል ማለት ነው፡ዘጠኙ ቅዱሳን ሀገራችን ወንጌልን በሚገባ በማስተማር ሐዋርያዊ ግዴታቸውን ተወጥተዋል፡፡

4. **ገዳማትን መትከል፡-** ቅዱሳን አባቶች በዓትን መስርተው የመናንያን ማህበር እንዲስፋፋ የአምልኮ ቦታ እንዲኖራቸው አድርገዋል። ተሰዓቱ ቅዱሳን ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማትን ከመትከላቸው ባሻገር በስማቸው እስካሁን ድረስ የሚጠሩ ገዳማት መስርተዋል።

5. ***ሥርዓተ ምንኩስናን ማደራጀት፡-*** ምንኩስና በግብጽ በረሃ በሲና የተጀመረ አንድ ጠንከር ያለ የክርስትና ሕይወት አኗኗር ነው።የመጀመሪያዎቹ መነኮሳት ተራ ምዕመናን ነበሩ።ምንኩስናን ወደ ኢትዮጵያ ያስገቡት ተሰዓቱ ቅዱሳን ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል አቡነ አረጋዊ ትልቅ ሚና የተጫወቱ ሲሆን የምንኩስና ሥርዓት ጀማሪ ከሆኑት ከአቡነ እንጦስ 4ኛ ትውልድ ሆነው የንኩስናን ሕይወት አስፋፍተዋል።።።

6. ከተለያዩ እህት አብያተ ክርስቲያናት በመምጣታቸው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በትምህርት ሁሉም የደረሰበትን በአንድ ጊዜ እንድትደርስበት አድርገዋል።

7. ለሥነ ጽሑፍ ዕድገት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ለኢትዮጵያ አበርክተዋል።

8. መጽሐፍተ ብሉያትንና ሐዲሳትን፣መጻሕፍተ ሊቃውንትንና መጻሕፍት መነኮሳትን ከጽርዕ /ከግሪክ/ ቋንቋ ወደ ግዕዝ የተተረገመው በተሰዓቱ ቅዱሳን ስለሆነ ሀገራችን በገዛ ቋንቋዋ መጽሐፍ ቅዱስን ካገኙ ሀገሮች እንድትመደብ አድርገዋታል።

9. ለትምህርት፣ለማህበራዊ ኑሮ፣ለሥነ ጽሑፍ መስፋፋት፣ለኪነ ጥበብ መዳበር አመቺ የሆኑ ገዳማት በቅድሚያ የመሠረቱት ተሰዓቱ ቅዱሳን ሲሆኑ ለሀገራችን የመጀመሪያዎቹ የገዳማት ህልውና ከመንፈሳዊ እውቀት ጋር ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አቅርበዋል።

10. እውነተኛውን መንገድ ይዘው፣ንጽህናቸውን ጠብቀው፣ምድራውያን መላዕክት የሆኑ የመነኮሳት ሀገር ለመሆን የበቁ አባቶች ለዚህ ሕይወታቸው አስተዋጽኦና በር የከፈቱ ተሰዓቱ ቅዱሳን ስለሆኑ የመነኮሳት /የምንኩስና/ አብነት ሆነዋል።

11. ቅዱሳት መጻሕፍትን መጻፍ፣ስብከተ ወንጌል ማስፋፋት፣አምልኮ ጣኦት አፍርሶ በምትኩ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ የሚፈተትባት ቤተክርስቲያን መስራት፣ክህነትን ከምንኩስና ጋር አስተባብሮ ለቤተክርስቲያን አበርክተዋል። ከተሰዓቱ ቅዱሳን በፊት በኢትዮጵያዊ ጃንደረባ የተሰበከችልን፣በኋላም በፍሬምናጦስ አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃንና በዘጠኙ ቅዱሳን የፀናችልን ሃይማኖታችን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ትባላለች።

**2.5. ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ስያሜና ምስጠሩ፡-**የምስራቅ አብያተ ክርስቲያናት የሃይማኖታቸው መጠሪያ ስም ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ተብሎ ይጠራሉ።እኛም ምስራቃዊት አብያተ ክርስቲያናት /ኦሬንታል አብያተ ክርስቲያናት/ ጋር አንድ እንደመሆናችን መጠን እምነታችን መጠሪያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ተብሎ ይጠራል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት በዕድገት አንጻር ስትታይ

ሀ.በህገ ልቡና /በልባዊ እውቀት/ ሥነ ፍጥረታትን በመመልከት በአበው መጠራት

ለ. በህገ ኦሪት በንግሥት ሳባና በቀዳማዊ ምኒልክ አስተናጋጅነት

ሐ. በህገ ወንጌል በንግሥት ህንዴኬና በጃንደረባው አስተማሪነት

መ. ሲኖዶስ /ጵጵስና/ እና ሥርዓተ ቤተመቅደስ አገልግሎት በአቡነ ሰላማ፣በንግሥት ሶፊያና በአብርሃ ወአጽብሃ

ፈጻሚነትና አስፈጻሚነት

ሠ. የገዳማት ምስረታና ጥንካሬ በተሰዓቱ ቅዱሳን ይህንን ደረጃ በደረጃ አልፋ ፀንታ ከዚህ የደረሰች ሃይማኖታችን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ተብላ ትጠራለች።ኦርቶዶክስ ቃሉ የግሪክ ወይም የጽርዕ ሲሆን የሁለት ቃላት ጥምር ሲሆን

1. ኦርቶስ ማለት ርትዕት፣ቀጥ ያለ፣ቀጥተኛ ማለት ነው

2. ዶክስ ማለት ማመን፣ማሰብ፣መገመት፣መተርጎም ማለት ነው።ተጠቃሎ ሲፈታ ኦርቶዶክስ ማለት ቀጥተኛ ሀሳብ፣ቀጥተኛ አስተያየት፣ቀጥተኛ ሃይማኖት፣ትክክለኛ እምነት ማለት ነው።ቀጥተኛ እምነት የተባለበት ምክንያት በቀጥታ

1 .ከጌታ ለሐዋርያት

2. ከሐዋርያት ለሰባ ሁለቱ አርድእት

3. ከ72ቱ አርድእት ለሊቃውንት

4. ከሊቃውንት ለወላጆቻችን ከወላጆቻችን ለእኛ ሳይጨመርበት፣ሳይቀነስበት፣ ሳይሻሻል በቀጥታ ጌታ እንዳስተማረ የተላለፈ በመሆኑ የሃይማኖታችን መጠሪያ በ325 ዓ/ም በኒቅያ በተደረገው ዓለም አቀፍ ጉባኤ 318 ሊቃውንት መናፍቁ አርዮስን ረትተው ሃይማኖታቸውን አፅንተው ጸሎተ ሃይማኖትን በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን እስከሚለው ድረስ አርቅቀው ተስማምተው ሲለያዩ ሃይማኖታቸው ኦርቶዶክስ ተብሎ እንዲጠራ ጉባኤው ወስነዋል።ኦርቶዶክስ በሚለው ቃል ላይ በ431 ዓ/ም በኤፌሶን በ200 ሊቃውንት በተደረገው አለም አቀፍ ጉባኤ የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ የነበረው መናፍቅ ንስጥሮስን ረትተው ክህደቱ አምላክ በሰው አደረ የሚል ስለነበረ ቃል ሥጋ ሆነ በሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መሠረት ኦርቶዶክስ በሚለው ቃል ላይ ተዋህዶ የሚለውን ቃል በመጨመር ሃይማኖታቸው ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ተብሎ እንዲጠራ ጉባኤው ወስነዋል።

**2.6. የምንኩስና ሕይወት፡-**መነኮሰ ማለት ከዓለም ወጥቶ፣ከዘመድ ከሕዝብ የተለየ የራቀ ብቸኛ መናኝ፣ በቆቡ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን የገባ፣ብቻውን የሚኖር፣ጸዋሚ፣ከፍተወተ ሥጋ የራቀ፣ድንግል የሆነ መንፈሳዊ ሰው ማለት ነው።ገዳማዊ ሕይወት ማለት በሙሉ ጊዜና ሕይወት እግዚአብሔርን ለማገልገል ቤተሰብንና ዘመድን ሀብትንና ንብረትን እንዲሁም በዚህ ዓለም ያለውን ማንኛውንም ነገር ትቶ በገዳም ተወስኖ መኖር ማለት ነው።በገዳም በተመሳሳይ ሕይወት በአንድነት የሚኖሩ ማህበረ መነኮሳት ይባላሉ።በብሉይ ኪዳን ዘመን በብሕትውና /በንጽህና በድንግልና/ መኖርን የጀመሩት ከአዳም ልጆች ከሆኑት የሴት ልጆች ናቸው።ሄኖ 9፤16-23 እንዲሁም በብሔረ ሕያዋን ከሚኖሩት ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛው ትውልድ የሆነው ሄኖክ በዚህ ዓለም ከተወለደ የዓለም አኗኗር ለመንፈሳዊ ፍላጎቱ አጥጋቢ ሆኖ ስላላገኘው በብሕትውና ኑሮ ጀምሯል ከዚያም እግዚአብሔር ሰውሮታል።ዘፍ 5፤24 እንዲሁም ቴስብያዊ ነቢዩ ኤልያስ 2ነገ 2፤11 ፤የክርስቶስ ምሳሌ የሆነው ካህኑ መልከ ጼዴቅ በድንግልና በንጽህና በቅድስና ተወስነው የኖሩ አባቶች ናቸው።በተጨማሪም በብሉይ ኪዳን መጨረሻና በሐዲስ ኪዳን መግቢያ ላይም መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ማቴ 3፤4፤ከሴት ወገንም ነብይት ሃና በምንኩስና ሕይወት ያለፉ ናቸው።

በሐዲስ ኪዳንም የብሉይና የሐዲስ ባለቤት የሆነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የብሕትይውናን ሥርዓት እንደፈጸመ ልናስተውል ይገባል።ለገዳማዊ ሕይወት ለምንኩስናና ለብሕትውና ጀማሪውና መሪውም እርሱ ነው።ማቴ 4፤1-2 ሥርዓተ ምንኩስና በመንፈሰ እግዚአብሔር የሚመራ ሲሆን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቱ ስለማዕረገ

ምንኩስና ትክክለኛ ትርጉም ሰጥቶ ተናግሯል፡፡ሉቃ 9፤62 በክርስትና ታሪክ በዘመን ሐዲስ ምንኩስና የጀመረው በቅዱስ ጳውል ከ250-314 ዓ/ም ቢሆንም ገዳማዊ ሕይወት ሥርዓት ባለው መልኩ የተጀመረው በቅዱስ እንጦንስ አማካይነት ነው፡፡እንጦንስ የኖረው ከ251-356 ዓ/ም ነው፡፡

**2.7. ሥርዓተ ምንኩስና በኢትዮጵያ፡-**ሥርዓተ ምንኩስና በኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት /ተሰዓቱ ቅዱሳን ከመምጣታቸው በፊት/ ኢትዮጵያውያን አበው በምናኔ በበረሃ ይኖሩ ነበር፡፡አባ አምንዮስ በመቀጠል በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አባ የሐኒ የተባሉ አባት በትግራይ ተንቤን አውራጃ በሐገረ ሰላም ቀበሌ የተወለደው የአባ አምንዮስ ተለይተው ወደ በረሃ በመሄድ በተጋድሎ ሲኖሩ ከቆዩ በኋላ በተወለዱ በ30 ዓመታቸው ወደ ብሔረ ሕያዋን እንደተወሰዱ ገድላቸው ይናገራል፡፡በኢትዮጵያ ሥርዓተ ምንኩስና የተስፋፋው በሁለት መንገድ ነው፡፤

1.ከውጭ ወደ ሀገር በገቡ ቅዱሳን 2. በኢትዮጵያውያን ቅዱሳን

| **ከውጭ የመጡ መነኮሳት** | **ከሐገር ውስጥ የተነሱ መነኮሳት** |
|---|---|
| አባ ሠላማ ከሳተ ብርሃን | አባ ኢየሱስ ሞአ |
| ተሰዓቱ ቅዱሳን | ጻድቁ አቡነ ተ/ሃይማኖት |
| አባ ሊባኖስ በ486 ዓ/ም | አባ በጸሎተ ሚካኤል |
| አባ ሐራ በ9ኛው መ/ክ/ዘ | ታላቁ ሊቅና ጻድቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ |
| አባ ዮሐንስ ዘጉንድ ተ/ሃይማኖት በ100 ዓ/ም | አቡነ ሀብተማርያም |
| አባ ኖባ ሶርያዊ | አቡነ አሮን ዘመቄት |
| አብነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ግብፃዊ | ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ |
| | ፃድቋ ፍቅርተ ክርስቶስና ሌሎችም |

በአጠቃላይ ኢትዮጵያውያን በሀገራቸው እንዲሁም ከሀገራቸው ውጭም በምንኩስና ሕይወት ጉዞ ከፍተኛ ተጋድሎ አድርገዋል፡፡በግብጽ ምደረ በዳ ከነበሩት መነኮሳት ውስጥም ሙሴ ኢትዮጵያዊው /ሙሴ ጸሊም/ ተጠቃሽ ነው፡፡በእነዚህና በሌሎችም ቅዱሳን አማካይነት ገዳማዊ ሕይወት ከ4ኛው መ/ክ/ዘ/ ጀምሮ የነበረ ሲሆን ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለገዳማዊ ሕይወት ወርቃማ ዘመን ነበር፡፡የነገሥታቱና የመኳንንቱ ልጆች ሳይቀሩ እየመነኑ የሚገኙት በገዳም ነበር፡፡ኢትዮጵያ ባፈራችው ቅዱሳንና በመሠረተቻችው ገዳማት ሀገርቷንና ሃይማኖቷን ከወረራና ከባዕድ ባህል ጠብቆ ያቆየው ይኸው የቅዱሳን ጸሎት ነው፡፡ኢትዮጵያ በቅዱሳኖቹ ተጋድሎና መልካም ሥራቸው ለዓለም የቀረች ቤተ መዘክር ሆናለች፡፡ነገር ግን አሁን አሁን ብዙ መነኮሳት ወደ ከተማ እየገቡ ከሕዝቡ ጋር እየተቀላቀሉ ኑሮ ስለጀመሩ ይህ ሁኔታ ከቀጠለ ምናልባት የቀደሙ አበው መነኮሳትና ባሕታውያን ተጋድሎና ዝና እንዲሁም ሕዝቡ ለገዳማዊ ሕይወትና ለምንኩስና ያለው አክብሮትና ናፍቆት እንዳይጠፋና ለመመለስ የሚያስቸግር አደገኛ ደረጃ ላይ እንዳይደርስ ያሳስባል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## ከአፄ ካሌብ እስከ ዮዲት

ከተሰዓቱ ቅዱሳን መምጣት በኋላ የአክሱም ቤተ መንግስትና መላው የኢትዮጵያ ግዛት የክርስትና ሃይማኖት ትምህርትና ስብከት በደቡብ የአረብ ግዛት በየመን ሁሉ ተዳርሶ ስለነበር በኢትዮጵያና በአረብ /የመን/ አገሮች መካከል የጠበቀ ግንኙነት ነበር።ይሁንና በዝርው /ተበትነው/ ይኖሩ የነበሩ አይሁዶች በክርስቲያን አረቦች ላይ ጥላቻ ስለነበራቸው ባላቸው ሁሉ ኃይል በመጠቀም የመንን ይዘው በቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ በቁ።እነዚህ አይሁዶች ከፍልስተ ባቢሎን ጀምሮ እስከ 70 ዓ/ም ሮማዊው ጥጦስ ድረስ በየጊዜው በተፈጸመባቸው ጦርና ወረራ እና ስደቶች ከፍልስጥኤም /ከመላው ዓለም/ እየፈለሱ ተበታትነው ይኖሩ እንደነበር ሁሉ በደቡብ አረብም በብዛት ተከማችተው ይገኙ ነበር።ይልቁንም በ70 ዓ/ም ጥጦስ በኢየሩሳሌም የነበረውን መቅደስ ባቃጠለውና ኢየሩሳሌምንም ባጠፋ ጊዜ ብዙ አይሁድ እየሸሹ ወደ የመን ፈልሰው ገብተዋል።በደቡብ አረብ ጣኦት አምላኪዎች የነበሩም ወደነዚህ አይሁዶች እምነት የተቀላቀሉ እጅግ በርካቶች ነበሩ።ሶርያ ውስጥ ከምትገኘው ንጽቢን በመባል በምትታወቀው ክፍል የሚኖሩ የአይሁዶች እምነት ተከታዮች ትውልድ ሀረጋቸው ሴይር ከሚባለውና በባርነት ተገዥነቱ ከሚታወቀው ነገድ ዘግይተው በቡድን እየሆኑ ወደ ደቡብ አረብ ገቡ።እነዚህ ከገቡ ጀምሮ ሰላም ጠፋ ውስጥ ውስጡን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ማካሄድ ጀመሩ።የፖለቲካ እንቅስቃሴያቸውም ክርስትናን የሚያጥላላ የአይሁድ እምነትን የሚያሞግስ ነበር።እነዚህ ከንጽቢን የመጡት የሴይር ወገኖች ከማንም በበለጠ ክርስቲያኖችን ይጠሉ ነበርና ለራሳቸው በየመን ላይ ፊንሐስ የሚባል ንጉሥ አንግሠው ባህላቸውንና ሃይማኖታቸውን አጠንክረው መኖር ጀመሩ።ብዙም ሳይቆዩ ንጉሡን አፍኖ በመግደል በየመን ክርስቲያኖች ላይ ጥላቻቸውን በማብዛት ስቃይና መከራ ይፈፀሙባቸው ጀመር።መካራ የፀናባቸው ክርስቲያኖችም በቁስጥንጥንያ፣በእስክንድሪያና በአክሱም ኢትዮጵያ ለሚገኙ የሃይማኖት ወገኖች አሳወቁ በዚህን ጊዜ የኢትዮጵያ ንጉሥ አፄ ካሌብ ነበሩ።በዚያን ከኖሩ ዘንድ ሃይማኖታቸውንና ባህላቸውን በማጠናከር ንጉሥም አንግሠው ይኖሩ እንደነበር ይነገራል።እነዚህ አይሁድ በአካባቢያቸው በሚኖሩ የናግራን /የመን/ ክርስቲያኖች ላይ ጥላቻ ስሜት ነበራቸው።ከ485 እስከ 515 ዓ/ም በየመን የአይሁድ ንጉሥ በእኛ ጽሑፍ ፊንሐስ የላቲን የዐረብ፣የፋርስ እና የሶርያ ጽሑፍ ማስሩክ፣ዘኑባስ/ድኑባስ፣ዱና፣አን-ዳምኖ ዱናስ ይለዋል።በደቡብ ዐረብና በናግራን የሚገኙትን ክርስቲያኖች ብዙ ስቃይና መከራ አፀናባቸው።መከራ የፀናባቸው ክርስቲያኖችም በቁስጥንጥንያ፣በእስክንደሪያና በአክሱም ኢትዮጵያ ለሚገኙ የሃይማኖት ወገኖች አሳወቁ በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ ንጉሥ የነበሩ አፄ ካሌብ ነበሩ።

### 5.1. አፄ ካሌብ

በ519 እንደነገሡ የታሪክ መዛግብት የተመሰከረላቸው አፄ ካሌብ የአይሁዳውያን ግፍና የየመን ክርስቲያኖች እልቂት አሳዝነዋቸው ሃይማኖታዊ ግዴታውን በኢትዮጵያዊ ስሜት የተወጡ ጻድቅ ንጉሥ ነበሩ።የአይሁዳዊነት መለያው ፊንሐስ በሶሪያ የታሪክ ምንጮች ማስሩክ፣በአይሁድ የታሪክ መጻሕፍት ዘኑባስ /ዱኑባስ/ እና በኢትዮጵያ ብራና መጻሕፍት ፊንሐስ በመባል ይታወቃል።በዚህ አይሁዳዊ ንጉሥ የሚመሩ አይሁዳውኖች በየመን የሚኖሩ ክርስቲያኖች ላይ የግፍ ተግባራቸውን ሲጀምሩ ክርስቲያኖቹ ሁኔታው ለሕይወታቸው እጅግ አስጊ መሆኑን ተረድተው ለማቋቋም ቢሞክሩም ቅንጣት ያህል ጥቅም አላስገኘላቸውም።የሀገሪቱ መሪ የነበረውም ማዲካርፓን ፊንሐስ በረቀቀ ዘዴ አሳፍኖ አስገደለው።ከዚህ በኋላ ሥልጣኑን በየመናውያን ላይ ዘርግቶ የንግድ በራቸውን በመዝጋት ከሀገር ወደ ውጭ ከውጭም ወደ ሀገር ማንም እንዳይገባና እንዳይወጣ የመከልከል ዘዴ ተጠቅሞ አረመኔያዊ ዓላማውን በክርስቲያኖች ላይ ለመፈጸም አመቺ ሁኔታ ስለተፈጠረለት ክርስቲያኖቹን በሰይፍ መሰየፍ፣ቤት ንብረታቸውን መዝረፍ፣ማውደምና ማቃጠል፣የሚሸሹትን አሳደው በመያዝ በየእስር ቤቱ ማስገባትና መግደል፣ጉድጓድ አስቆፍሮ እሳት እያስነደደ ክርስትናን አንክድም ያሉትን ክርስቲያኖች ሁሉ ወደዚያ እየጨመረ አቃጠላቸው አስፈጃቸው።

ፊንሐስ በየመን ካሉት ግዛቶች በመጀመሪያ ዛፋርን በማስቀጠልም ሒምያር ሐድራሙት ማራኮና ሒገሬ በተባሉ ከተሞች የሚገኙ ክርስቲያኖችንና ቤተመቅደሶችን ከነንብረታቸው አወደመ።በመጨረሻም ከተለያዩ ግዛቶች

ሕይወታቸውን ለማትረፍ በሐገረ ናግራን ተሰብስበው ወደ ነበሩት ክርስቲያኖች በማቅናት በየዋሻውና በየግድጓዱ የተደበቁትን ክርስቲያኖች በማፈላለግ በሀገረ ናግራን የተሰበሰቡትን ሕዝበ ክርስቲያን በሙሉ ወደ አደባባይ እያወጣ የሰይፍ ራት አደረጋቸው፡፡ፊንሐስ ከፈጸማቸው የግፍ ተግባሮች ለየት ያለው የናግራን ጭፍጨፋ ነው፡፡በሌሎች ከተሞች የነበሩትን ለመፍጀት ከ10 ወር በላይ ሲፈጅበት ናግራንን ግን በአንድ ቀን ሊያወድማት በደም ጎርፍ ሊያጥለቀልቃት ችሏል፡፡በአንድ ቀን ውስጥ 20 ሺህ ክርስቲያኖች ተፈጁ፡፡በዚህም ናግራን በደረሰባት እልቂት በዓለም እንድትታወቅ አድርጓታል፡፡

**5.1. የአፄ ካሌብ ዘመቻ ወደ የመን፡-** አፄ ካሌብ ከጅምሩ አንስተው ፊንሐስ በየመን ክርስቲያኖች ላይ የጥፋት ዘመቻውን ሲያራምድ የመከራው ቀማሽ ከሆኑት ክርስቲያኖች በቀረበላቸው የይድረሱልኝ ጥሪ መሠረት ሠራዊታቸውን አስከትለው ወደ የመን ዘምተዋል፡፡ፊንሐስ ግን የአፄ ካሌብን መምጣት ሲሰማ ያራምድ የነበረውን የግፍ ተግባር በመተው ሰላማዊ መስሎ መኖር ጀመረ፡፡ንጉሡም የፊንሐስ ሰላማዊ መሆን ዘለቀታ ያለው ስለመሰላቸው ለወቅታዊው ሠላም መረጋጋት ሲሉ ይዘዋቸው ከሄዱት ሠራዊት 500 በየመን አሰማርተው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ፡፡

አረመኔያዊነት ተልዕኮን ይዞ የተነሳው ፊንሐስ የአፄ ካሌብን መመለስ ተጠባብቆ እንደገና የጥፋት ዘመቻውን በመቀጠል ከላይ የተጠቀሱ ከተሞችን ናግራንም ጭምር አጥፍቶ አፄ ካሌብ ያሰማሯቸውን 500 ወታደሮችን ጨፍጭፏቸዋል፡፡በናግራን ያሉ ክርስቲያኖችም ከዚህ አሰቃቂ ግፍ ተግባር ለማምለጥ በዘመኑ ክርስቲያኖች በበዙበት በቁስጥንጥንያ፣በእስክንደሪያ እና በአክሱም ለሚገኙ የሃይማኖት ወንድሞቻቸውና መሪዎች የይድረሱልን ጥሪ አሰሙ፡፡ይህ የእልቂት ዜና የኢትዮጵያ ክርስቲያኖችንና የአክሱምን ቤተመንግስት አሳዘነ፡፡አፄ ካሌብም እነዚህ ግፍ የፀናባቸው የናግራን ክርስቲያኖች ለመታደግ ፈጣሪ እንዲገልጥላቸው ወደ አባ ጴንጤሊዎን ዘንድ ሄዶ ጉዳዩን በመግለጽ ወደ ፈጣሪያቸው ምህላና ጸሎት ያዙ፡፡የቁስጥንጥንያው ንጉሥ ዮስጢኖስም እልቂቱ ያሳዘነው መሆኑን ገልጦ ለእስክንድሪያው ሊቀ ጳጳስ ለአባ ጢሞቴዎስ ላከባቸው፡፡አባ ጢሞቴዎስም ለአክሱም ቤተመንግስት የሃይማኖት አባት እንደመሆናቸው መጠን አክሱም ለየመን ቅርብ ስለሆነች ወደ የመን ተሻግረው ክርስቲያኖችን ከእልቂት እንዲያድኗቸው የሚል መልዕክት ወደ አክሱም ቤተ መንግስት ለአፄ ካሌብ ላኩ፡፡አፄ ካሌብም በየመን የሚደረገውን የክርስቲያኖችን እልቂት ቀደም ብለው ሰምቶ ወደ አምላካቸው ጥበቡን እንዲገልጥላቸው ምህላ ይዘው ስለነበረ የአቡነ ጢሞቴዎስ የእስክንደሪያው ሊቀ ጳጳሳት መልዕክት በደረሳቸው ጊዜ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ተረድተው በዘመናቸው በነበረው የጦር ዝግጅት ቁጥሩ ወደ 70 ሺህ የሚደረስ ሠራዊታቸውን ክተት ብለው መርከቦቻቸውን ጭነው በአዱለስ የባህር በር በ524 ዓ/ም ወደ የመን ተሻገሩ፡፡ወደየመን እንደደረሱ 3 ሺህ ጦር በማሰለፍ ከመርከብ ሲወርድ ውጊያ የገጠመው የአፄ ካሌብ ጦር የአይሁድ ጦርን ከግፈኛው ፊንሐስ ጭምር ከነሠራዊቱ ደምስሰው በከተማው ለክርስቲያኖች እልቂትና ደም መፍሰስ ተባባሪ የነበሩትን በሙሉ አጠፉ፡፡ክርስቲያኖቹም ከተበተኑበት ከየሥፍራው ተመለሱ፡፡አፄ ካሌብ በየመን የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናትን ጠግነው ሌሎችንም አዲሶችን ሠርተው ከፊንሐስ ሰይፍ የተረፉትን ምዕመናንን አጽናንተውና አረጋግተው ከ10 ሺህ ሠራዊት ጋር የሚጠብቃቸውን አብርሃ የሚባል አለቃ መርጠው ሹመውላቸው ወደ አክሱም ተመለሱ፡፡ከየመን ከተመለሱ በኋላ ብዙ ጊዜ በመንግስትነት ስልጣን ሳይቆዩ በትረ መንግስታቸውን ለልጃቸው አስረክበው መንነው ልብሰ ምንኩስና ለብሰው ከአክሱም ወደ ሰሜን ምስራቅ በሚገኘው በአባ ጴንጤልዎን ገዳም ባለው ዋሻ ገብተው ተቀመጡ፡፡ፀሎቱን የሰማውንና የድል አድራጊነት ኃይል የሰጠውን አምላኩን ለማስደሰት የነገሡበትን ዘውዱን በጌታችን መቃብር በጎልጎታ እንዲሰቀልላቸው ለኢየሩሳሌም ሊቀ ጳጳስ ላኩት፡፡በምናኔ ለ12 ዓመታት ከተጋደሉ በኋላ 70 ዓመት ዕድሜያቸው በ586 ዓ/ም ግንቦት 20 አረፉ፡፡አፄ ካሌብ በሀገረ ናግራን በክርስቲያኖች ላይ የተነሳውን እልቂት ለማስወገድ ዘምተው ክርስቲያኖችን ነፃ ያወጡና በምንኩስናም ሕይወት የአበውን አሠረ ፍኖት ፈጽመው ያረፉ ደገኛ ጻድቅ ንጉሥ ስለነበሩ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የናግራን ክርስቲያኖች

ስለማዳናቸው፣ዓለምን ስለመናቃቸውና ዘውዳቸውንም ወደ ኢየሩሳሌም ስለመላካቸው ሕይወታቸውን ልዩ ስለሚያደርገው ቁጥራቸውን ከጻድቃን ጋር አድርጋ ታከብራለች። በምዕራባዊያንም ማለትም የሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንም በጥቅምት 27 ቀን በየዓመቱ ታስባለች።

### 5.2.አፄ ገብረ መስቀል

አፄ ገብረ መስቀል በዘመናቸው ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከውጭ ዓለም ጋር በተለይም ከቁስጥንጥንያና ከእስክንደሪያ ጋር የጠበቀ ግንኙነት አደርገዋል።እነዚህ ሀገሮች በጠላት እንዳይሸነፉ እርስ በእርሳቸው የመረዳዳት ባህርይ እንደነበራቸው ታሪክ ያስረዳል።አፄ ገብረ መስቀል የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ለኢትዮጵያን ሕዝብ አገልጋይ እንደመሆኗ መጠን አገልጋዮቿ በደንብ እንዲጠበቁ በአብያተ ክርስቲያናት ዙሪያ የሚገኘው መሬት ለቤተክርስቲያን አገልጋዮች መተዳደሪያ ርስት ጉልት እንዲሆን የሰጡ ታላቅ መሪ ናቸው።ከክርስቶስ ልደት በፊት 1000 ዓመታት ከሰሎሞን ለንግሥት ሳባ በኢየሩሳሌም ከተማ የተሰጣትን መሬት ገዳማት እንዲመሠረቱና ገዳማቱን እንዲጠብቅ ልጃቸውን አባ ሙሴ ገብረ መስቀልን በወጣትነት አመንኩሰው ገዳማቱ እንዲጠበቁ ያደረጉና ኢትዮጵያ ከኢየሩሳሌም ካሏት ቅድሳት መካናት ጥቂቶቹን እንዲታገኝ በማድረግ ሀገራዊና ሃይማኖታዊ ግዴታቸውን በመወጣት አደራ ፈጻሚ የነበሩ መሪ ናቸው።የደብረ ዳሞ ቤተ ክርስቲያን የታነፀውና ታላቁ የዜማ አባት ቅዱስ ያሬድም የተነሳው በዚህ ዘመን ስለሆነ አፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግስት ቤተ ክርስቲያን ፍፁም ለውጥ ያደረገችበት ዘመን ነው።

አፄ ገብረ መስቀል ዘመን በ505 ዓ/ም በሚያዝያ 5 ከአባቱ አዳምና ከእናቱ ታውክሊያ በአክሱም ከተማ የተወለደውና ያደገው ቅዱስ ያሬድ የተነሳበት ዘመን በመሆኑ ለቤተክርስቲያን አዲስ ምዕራፍ የተከፈተበት ዘመን ነው።ቅዱስ ያሬድ ሦስት ዓይነት ስልት ወይም ድምፅ ያለውን ዜማ ከመላዕክት ተምሮ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በአፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግስት አበርክቷል።የቅዱስ ያሬድ ዜማ በማህሌት፣በሰዓታትና በቅዳሴ ወዘተ የሚያገለግል ዜማ ነው።ቅዱስ ያሬድ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ /መሪነት/ ብሉያትና ሐዲሳት መጻሕፍትን፣ የሊቃውንት መጻሕፍትን፣ድርሳትና ገድላትን መሠረት ያደረገ አምስት ድርሰቶችን ዝማሬ፣መዋስዕት፣ምዕራፍ፣ድጓና ጾመ ድጓ አዘጋጅቶ ለቤተ ክርስቲያን አበርክቷል።እነዚህ ድርሰቶች ተወዳዳሪ የሌለው ሰማያዊና ምድራዊ ዜማ ግዕዝንና አራራይና ዕዝል በማዜም ምስጋናውንም ለ4ቱ ክፍላተ ዘመን ለክረምት፣ለበጋ፣ለመፀው /ለጥቢ/ እና ለፀዳይ /ለበልግ/ እንደሚበቃ አድርጎ አዘጋጅቶ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብቸኛ ሀብት አድርጎ አበርክቷል።ሰውና መላዕክት ስሙን እንዲቀዱሱ ክብሩን እንዲወርሱ የተፈጠሩ መሆናቸውን አስፍቶና አምልቶ ተናግሯል።ነቢያት ክርስቶስ ይወርዳል ይወለዳል እያሉ ትንቢት መናገራቸውን፤ጌታም የተነገረው ትንቢትና የተቆጠረው ሱባኤ ሲፈጸም ወደዚህ ዓለም መምጣቱንና ሰው መሆኑን፣ሥጋ መልበሱን ተናግሯል።ሐዋርያትም ወረደ ተወለደ በማለት

የሰበኩትን ስብከት ከነምስጢሩ እየገለጠ ጽንሰቱን፣ልደቱን፣ጥምቀቱን፣ህማሙን፣ሞቱን፣ትንሳኤውንና ዕርገቱን በየማነ አብ በዘባነ ኪሩብ መቀመጡን፤ዳግመኛ ለጻድቃን ሊፈርድላቸው ለኃጢአን ሊፈርድባቸው መምጣቱን በየዘመናቱ፣በየወራቱና በየቀናቱ እየለየ በተከናወነ ዜማ ለሰው በሚረዳ ትርጓሜ እየተረጎመ ከማዜሙም በላይ የተዋህዶን ምስጢር በብዙ ዓይነት መልኩ አገልቶ አሳይቷል፡፡ቅዱስ ያሬድ ከፈጣሪ ምስጋና በኋላ ነቢያትና ሐዋርያትን፣ጻድቃንና ሰማዕታትን፣መላዕክትና ሥራቸውን እየተናገረ አወድሷቸዋል፡፡ይልቀንም በንጽሐ ሥጋ በንጽሐ ነፍስ በንጽሐ ልቡና ፍጽምት ሆና አምላክን የወለደች ድንግል ማርያምን አመስግኗታል፡፡ንጉሡ አፄ ገብረ መስቀል የቅዱስ ያሬድ ድርሰቱ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲውል ተቀብሎ ሊቃውንቱ ቢያሳውቅ ፈቃደኛ ስላልነበሩ ምህላ ይዘው ፈቃደ እግዚአብሔርን እንዲጠይቁ አዘዘ፡፡ወር በገባ ከ1 እስከ 7 / ከልደታ እስከ ሥላሴ ምህላ ይዘው ፈቃደ እግዚአብሔርን አግኝተው ድርሰቱን እንዲቀበሉ ምልክት አገኙ፡፡ስለዚህም ነው ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ከ1 እስከ 7 ምህላ የሚታደርገው፡፡ቅዱስ ያሬድ ከደረሳቸው የዜማ ድርሰቶች ሌላ አንቀጸ ብርሃንና ይወድስዋ መላዕክት የተባሉትን የእመቤታችን የምስጋና ድርሰቶችም አሉ፡፡

ቅዱስ ያሬድ በጣና ቂርቆስ ለ29 ዓመታት አስተምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ የዜማ መጻሕፍቱን በዚህ ገዳም ውስጥ ጽፏል፡፡መደባይ ታብር በሚባል ቦታ የ14ቱን የቅዳሴ ዜማ ብሉይና ሐዲስን በማስማማት አዘጋጅቶ አበርክቷል፡፡ቅዱስ ያሬድ ከመላዕክት የሰማውን ዜማ በመድረስ ኢትዮጵያን ከዓለም በማስተዋወቁ የቤተ ክርስቲያንና የኢትዮጵያ መቅረዝ ነው፡፡የቅዱስ ያሬድ የዜማ መጻሕፍት አምስቱ ጸዋተው ዜማ ይባላሉ፡፡ምንጫቸውም ብሉይ ኪዳን፣ሐዲስ ኪዳን፣መጻሕፍተ ሊቃውንት፣መጽሐፈ መነኮሳት፣መጻሕፍተ አዋልድ ማለት ድርሳናት፣ገድላት እና ተአምራት ናቸው፡፡ቅዱስ ያሬድ ለቤተ ክርስቲያን ካቆየልን ትውፊቶች የሆሳዕና በዓል አከባበር እና የተቀጸል ጽጌ በዓል ተጠቃሽ ናቸው፡፡ከ530-544 ዓ/ም ድረስ የተነሳው ቅዱስ ያሬድ ጠቅለል ባለመልኩ ኢትዮጵያዊ ርዕሰ ሊቃውንት፣ብሉይና አዲስን አስማምቶ የተረጎመ፣የቅኔን መንገድ በኋላ ለተነሱ ሊቃውንት በር የከፈተ፣ከነሞዛሪት በፊት የዜማ ምልክት /ኖታ/ በዓለም ላይ የሠራ፣ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የመንፈሳዊ ሀብት የሆነ፣ከመላዕክት የሰማውን ዜማ ለወገኖቹ ያበረከተ፤የዜማ መጻሕፍት በመድረስ ለኢትዮጵያ ያስረከበ ሊጠፋ የማይችል የኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መቅረዝ ነው፡፡

የአፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግስት የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ከፍተኛ ደረጃ የደረሰበት በመሆኑ ወርቃማው ዘመን ተብሎ ይጠራል፡፡ከ4ኛው አስከ 7ኛው መ/ክ/ዘመን የነበረው ጊዜ ፍፁምና የተሟላ አገልግሎት የተጀመረበት ጊዜ ነው፡፡ከቅዱስ ያሬድ በኋላ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አንዳንድ ጊዜ መዳከሙን ታሪክ ያስረዳል፡፡ለዚህም ምክንያት የሆኑ ነገሮች የቤተ ክርስቲያን ለሁለት መከፈል፣የእስልምና እምነት ፍልስፍና መነሳት፣የአይሁድ እንቅስቃሴ፣የካቶሊክ ሰርጎ ገብነት፣የቅባትና የፀጋ እምነት መነሳት፣የፕሮቴስታንት እምነት ፍልስፍና መነሳት፣የቱርኮችና የግብፆች፣የሱዳኖችና የጣሊያን እንግሊዞች በሀገሪቱ ያደረጉት የነበረው ተደጋጋሚ ጥፋቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

እነዚህ ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መዳከም ምክንያት ቢሆኑም ቁልፉን ይዘው በመክፈትና በመዝጋት ቤተ ክርስቲያኗን ያዳከሟት ግን የእስክንደሪያው ቅዱስ ሲኖዶስ የሚልካቸው ጳጳሳት ናቸው፡፡የእስክንደሪያው ሲኖዶስ ለ1600 ዓመታት አንድ መቶ አስራ አንድ /111/ ጳጳሳት ወደ ኢትዮጵያ ልከዋል፡፡በነዚህ ዘመናት የሚመጡ ጳጳሳት የሀገሪቱን ቋንቋና ባህል የማያውቁ የአረብ ዜጎች ስለነበሩ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መዳከም ከፍተኛ እገዛ አደርጓል፡፡በዚህ ሁኔታ ከ4ኛው እስከ 7ኛው መ/ክ/ዘመን የነበረው አፍሪካን ስብከተ ወንጌልን የማዳረስ ዕቅድ እግሩን ሊሰበስብ ችሏል፡፡ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ሳይቋረጥ ቀጥሎ ቢሆን ኖሮ አሁን የሚታየው የአፍሪካውያን ወንድሞቻችን እምነትና ባህል ውጥንቅጥ ሊሆን አይችልም ነበር፡፡ያ የሃይማኖትና የባህል ውጥንቅጥ ወደ እኛም ባልደረሰ ነበር፡፡

**5.3. የእስልምና መነሳት**፡-ከ451 ዓ/ም ከኬልቄዶን ጉባኤ በኋላ ቤተ ክርስቲያን ለሁለት በመከፈሏ አዳዲስ መናፍቃን ለመነሳት በር በመክፈቱ እ.ኤ.አ.በ570 ዓ/ም በኢትዮጵያ አቆጣጠር 562 ዓ/ም የተወለደውና እስከ 25 ዓመቱ ግመል ጠባቂ እና እስከ 40 ዓመቱ ደግሞ ዋሻ ገብቶ በብሕትውና ቆይቶ 40 ዓመት ሲሞላው ነቢይ ነኝ መልአኩ ገብርኤል የቁርዓን መጽሐፍ አስተማረኝ እያለ የተነሳው መሐመድ መንቀሳቀስ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮ በ622 ዓ/ም መሐመድ ከመካ ወደ መዲና ተንቀሳቅሶ ሂጂራ /ስግደት/ በመጀመር እስላማዊ እንቅስቃሴ ጀመረ፡፡በዚህ ዘመን በመሐመድ እስላማዊ ፍልስፍና እምነት እንስቅስቃሴ በተነሳው ተቃወሞ ምክንያት የመሐመድ ተከታዮች ወደየሀገሩ በስደት ባደረጉት ጉዞ የተወሰኑቱ በ7ኛው መ/ክ/ዘመን ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ ታሪክ ይናገራል፡፡በዘመኑ በኢትዮጵያ የነበረው መሪ **ንጉሥ አርማህ** ስደተኞቹ እስላሞች ተይዘው ቀርበው ሲጠየቁ ሃይማኖተኞች መሆናቸውን እንደሚፆሙ እንደሚጸልዩ እንደሚሰግዱ ምፅዋትም እንደሚሰጡ ስለገለጡ የነገረ መለኮት ባለሙያ ያልሆኑ መሪ አማኞች ከሆኑ ይቀመጡ ብሎ ፈቃድ ሰጡ፡፡መሐመድም ይህን ሰምቶ ለንጉሥ አርማህ ምስጋና ከማቅረቡ ሌላ ኢትዮጵያን እንዳይነኩ በቁርዓን ላይ እንዳሰፈረው ቁርዓን ይመሰክራል፡፡የመሐመድ ተከታዮች ግን የመሪያቸውን ቃል ባለማክበር በ16ኛው መ/ክ/ዘመን በአፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግስት ኢትዮጵያዊው ግራኝ መሐመድን ተገን በማድረግ እስላሞች ኢትዮጵያን እንደወረሩ ከፍተኛ ጥፋትን እንዳደረሱ ታሪክ ይናገራል፡፡

**5.4. አይሁዶች /ፈላሾች/ በኢትዮጵያ**፡-የመን ከአፄ ካሌብ በኋላ ለ100 ዓመታት ያህል በኢትዮጵያ መንግስት ሥር ነበረች፡፡አፄ ካሌብ ፊንሐስ የተባለውን የአይሁድ መሪ ድል አድርጎ ሀገርቷንና ሕዝቧን ለኢትዮጵያውያን እንደሰጠ ታሪክ የመዘገበ ቢሆንም ከ100 ዓመታት በኋላ ግን የመን በፋርሶች /በኢራን/ እጅ ወደቀች፡፡በኢትዮጵያውያን ጠበብት የተገነባች የየመን ከተማ ከነቅርሶቿ ወደመች፡፡በመቀጠልም መሐመድ ፋርሶችን በማስለቀቅ የመንን ያዛት፡፡መሐመድ በቀይ ባህርና በሜዲትራንያን ባህር ዙሪያ ያሉት ሀገሮችን በሙሉ የክርስቲያኖች መግቢያና መውጫ በሮች የሆኑትንም ጭምር በቁጥጥር ሥር አዋለ፡፡ከዚህ በኋላ የየሀገሩ የክርስቲያን መሪዎችን ሁሉ ወደ እስልምና ለመለወጥ ጥረት አደረገ፡፡ለቁስጥንጥንያ መሪ ለሕርቃል፤ለኢትዮጵያ መሪ ለአርማህ የእስልምና ሃይማኖት ተቀበሉ የሚል መልዕክት ጽፎ እንደነበረና እንዳልተሳከለት ታሪክ ይገልጻል፡፡ቀደም ብለን እንደገለጽነው

ከ622 ዓ/ም /ከ7ኛው መ/ክ/ዘመን ጀምሮ የመሐመድ እስላማዊ እንቅስቃሴ ቢደረግም ከፍተኛ ስደት በገጠመው ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ተከታዮች ሰላም ስለገጠማቸው በቁርዓንን ሀበሻን /ኢትዮጵያን/ አትንኩት መልካም ሕዝብ ነውና በማለት በጽሑፍ እንዳረጋገጠው ታሪክ ይገልጻል።ግብጽና የሰሜን አፍሪካ ሀገሮች በሙሉ ከ7ኛው መ/ክ/ዘመን በኋላ በእስልምና ሃይማኖት ተዋጡ በጣት የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች በስተቀር የመንግስት ባለስልጣናትም ጭምር በእነሱ እጅ ተያዙ።ቤተ ክርስቲያኒቷም በእስላም መሪዎች እጅ ወደቀች።ቅድሳት መካናት እንደተራ ቦታ፣ንዋየ ቅድሳት እንደተራ ዕቃ፣ክህነትም እንደተራ ሙያ ተደርጎ ተቆጠረ።ሙሉ በሙሉ የእስልምና መንግስት ሥልጣኑን በቁጥጥሩ ሥር አዋለ።ቅዱስ ሲኖዶስም ያለ እስልምና ፈቃድ እንዳይንቀሳቀስ ማዕቀብ ተጣለበት።የሚሰየመው ጳጳስም ከእስልምና ጉባኤ ጋር አግባቢነት ያለው እንዲሆን ተወሰነ።ከዚህ ዘመን ጀምሮ የኢትዮጵያና የእስክንድሪያ አብያተ ክርስቲያናት በሞትና በሕይወት መካከል ወደቁ።በተላይም ኢትዮጵያ ከፍሬምናጦስ ጀምሮ ራሷን ልጅ ባለመተካቷ ከፍተኛ ችግር ገጥሟታል።ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው የግብር ጫና የተጀመረው፤የግብር አሰጣጡም ጳጳሳትን ለማምጣት ከኢትዮጵያ ወደ ግብጽ በሚላኩት ሉዑካን ከፍተኛ እንግልት ይደርስባቸው ነበር።እንግልቱም በተላኩት ኢትዮጵያውያን፣በሿሚው ፓትርያርክ፣በሚመጣው ግብጻዊ ጳጳስ ስለሆነ ግብሩም ለሱልጣን /ለእስላሙ መንግስት/፣ለሿሚው ፓትርያርክ፣ለቅዱስ ሲኖዶስ፤ለተሿሚው ጳጳስ፣አንዳንድም ጊዜ ጳጳሱ ለነበሩበት ገዳምም እንደነበር ታሪክ ያስረዳል።ግብጻውያን አባቶች ከእስላሙ መንግስት ተጽዕኖ የተነሳ ወላዋዮችና አታላዮች እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

እንግዲህ በ4ኛው መ/ክ/ዘመን የተጀመረው የጵጵስና ማዕረግ ከአቡነ ሰላማ በኋላ ባለመቀጠሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በእስክንደሪያ ቤተ ክርስቲያን ሥር ወደቀች፣ለምዝበራም ተጋለጠች፣ግብር እየከፈለች የምታመጣቸው ጳጳሳት ሕዝቡ በማይሰማቸው የአረበኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ስለነበሩ ለብዙ ዘመናት ቤተ ክርስቲያኒቱን አደቀቋት ዕድገትዋንም አቀጨጩዋት።ይሁን እንጂ ከመጡት ከ111 አባቶች በጣት የሚቆጠሩ አባቶች መልካም ሥራን የሠሩ ሲሆን አብዛኞቹ ግን መጥተው ያራመዱት የነበረው የግብጽን የእስላሙን መንግስት የሚያስደስት ተልዕኮና ፖለቲካ እንደነበር በታሪክ ተገልጿል።በሌላ በኩል የኢትዮጵያና የግብጽ መንግስታት ሲጋጩ ቤተ ክርስቲያን ግብር መክፈል ስታቆም ለብዙ ዓመታት ጳጳሳት እንዳይመጡ የተደረገበት ዘመናት እንደነበር ታሪክ ያስታውሰናል።

## 5.5.አንበሳውድም ዘመነ መንግስት

በአክሱም ዙፋን ከ822-841 ዓ/ም 19 ዓመት ከሁለት ወር የነገሠው የኢትዮጵያ ንጉሥ በድግናዣን የሚባል ነበር።ነገር ግን ይህ ንጉሥ ሲሞት አንበሳ ውድም የሚባለው ሕፃን ልጁ ነገሠ።የነገሠውም ሕፃን ገና ኃይል ያላበጀ ሥርዓተ መንግስት ያላጠና ነበርና ሀገርና ሕዝቡን ማስተዳደር አለመቻሉን ዮዲት የተባለች ፈላሻ በሰሜንና በላስታ አውራጃ የሚኖሩትን ፈላሾች ወገኖቿን ይዛ ወደ አክሱም ገሰገሰች።የአክሱም መኳንንትም ሕፃኑ ንጉሣቸው 841-842 ዓ/ም ከ10 ወር ያህል እንደነገሠ ዮዲትን ሸሽተው ንጉሥን ይዘው ወደ ሸዋ ገሰገሱ።ከዚህ በኋላ ዮዲት 842

ዓ/ም ነገሠችና የግፍ ተግባሯን ተያያዘች።

**5.6. የዮዲት /ጉዲት/ መነሳት፦**ከአፄ ገብረ መስቀል እስከ ዮዲት ድረስ 300 ዓመታት ነው።አይሁድ /እስራኤል/ ብዙ ጊዜ ስደት ደርሶባቸዋል።ስደቱም በረሀብ ምክንያት ወደ ግብጽ ተሰደው 430 ዘመን ተቀምጠዋል።ወደ ሀገራቸውም ከተመለሱ በኋላ ከሰሎሞን መንግስት ቀጥሎ አስሩ የያዕቆብ ልጆች እስራኤል ተብሎው በሰሜኑ ክፍል ዋና ከተማቸውን ሶርያ /አሶር/ ሲያደርጉ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች ደግሞ ይሁዳና ብንያም በደቡብ ክፍል ይሁዳ /አይሁድ/ ተብለው ዋና ከተማቸውን ኢየሩሳሌም አደረገው መንግስታቸው ለሁለት ተከፍሏል።ሰሜኑ ክፍል በአሶራውያን ሲሰደዱ የደቡብም ክፍል በናቡከደነፆር ለ70 ዓመታት ከኢየሩሳሌም ተሰደው በባቢሎን /ኢራቅ/ በባርነት ተገዝተው ቆዩ።የባቢሎን መንግስት ሲዳከም በባቢሎናውያን የተማረኩ አይሁድ በአንድነት በፋርስ /ኢራን/ መንግስት ቅኝ አገዛዝ ሥር ተያዙ።ምርኮኞቹ ወደ ሀገራቸው የመመለስ ነፃነት እንዳላቸው የፋርስ መንግስት በአዋጅ አፀደቀላቸው።ዘመኑም እነ ኤርምያስ፣ሕዝቅኤል፣ዳንኤልና ሠለስቱ ደቂቅ፣ካህኑ ዕዝራ፣ዘሩባቤልና ነህምያ፣አስቴርና መርዶክዮስ የነበሩበትና ኢየሩሳሌምን መልሶ ለመገንባት የተነሱበት ዘመን ነው። መጽሐፍ ቅዱስንና ታሪክን ስናጠና ከአዳም እስከ ሙሴ /3842 ዓመት/ ድረስ የነበሩ ሰዎች ሁሉም እንደ የፍላጎታቸው ነበር ሲተዳደሩ የነበሩት፤ከሙሴ እስከ ሳኦል /589 ዓመት/ ግን በካህናትና በመሳፍንት ሲመሩ ቆይተዋል።ከሳኦል እስከ ሰሎሞን 543 ዓመት/ ደግሞ በነገሥታት እየተመራ ቆይተው በሰሎሞን ልጅ ኢዮርብዓም ጀምሮ ግን በሁለት መንግስት ተከፍለዋል።ከዚህ ከእስራኤል መንግስት ክፍፍል ተነስተን አይሁድ ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደገቡ እናያለን።

ከላይ በታሪካችን መግቢያ ላይ እንደተገለጸው አይሁድ ወደ ኢትዮጵያ መግባት የጀመሩት ከቀዳማዊ ምኒልክ /ከሰሎሞን/ ዘመንና ከዚያም በፊት ነገደ ዮቅጣኖች ጀምሮ ወደ ሀገራችን እየፈለሱ ከገቡት እስራኤላውያን ገሚሶቹ ክርስትናን ሲቀበሉ ገሚሶቹ አንቀበልም ብለው በሀገሪቱ ደጋማ ቦታዎች በተራራማው ክፍል ይኖሩ እንደነበር ታሪክ ይገልጻል።ወደ ሀገራችን ሲገቡም ከፊሉ በስደት፣አንዳንዱ በራሱ ፈቃድ ነበር።ከአብርሃ ወአጽብሃ ዘመነ መንግስት እስከ ፍሬምናጦስ /አባ ሰላማ/ ስብከት ድረስ ክርስትና በመላው የኢትዮጵያ ግዛት ሲደርስ እነዚህ የአይሁድ ወገኖች በኦሪት እምነታቸው ጸንተው ኢትዮጵያዊው ጭምር ለ1034 ዓመታት የብሉይ ኪዳንን እምነት ይዘው ከቆዩ በኋላ በ34 ዓ/ም ወደ ሐዲስ ኪዳን ሲሸጋገሩ ማለትም ብሉይና ሀዲስን አንድ አድርገው ተቀብለው ሲመሩ እነሱን ግን አዲሱን ሃይማኖት ክርስትናን አንቀበል በማለት ጥቂቶቹ ከብዙሃኑ ተለይተው ያፈነገጡና የሸሹ ለብቻቸው በቀድመው እምነታቸው ጸንተዋል።በዚህም የተነሳ ከክርስቲያኑ ጋር አለመግባባት በመፍጠራቸው ከአክሱምና ከዙሪያዋ እየተሰደዱ በሰሜንና በወገራ በወልቃይት በላስታ ተቀመጡ።እነዚህም ወገኖች ወደ ህብረተሰቡ ባለመጠጋታቸው ፈላሾች /ፈላስያን/ ወይም ከቦታ ወደ ቦታ የሚፈልስ ሂያጅ የሚል ስም ተሰጣቸው።እነዚህ አይሁዶች /ፈላሾች/ የሰሜኑ ሀገራችን ክፍል ተራራማ ስለሆነ በዚህ ሥፍራ ሆነው የተፈጥሮን ምሽግ እየተጠቀሙ ሊወጋቸው የሚመጣውን ሁሉ እየተከላከሉ ይመልሱ ነበር።ቁጥራቸው እየበዛ ኃይላቸው እየበረታ ሲሄድ ከመካከላቸው ጌድዎን የተባለውን ሰው መሪ /ንጉሥ/ አድርገው መርጠው ሹመውት ይተዳደሩ ጀመር።ይህም ጌዴዎን የተባለው ሰው ዮዲት /አስቴር/ የተባለች መልከ መልካም ልጅ ነበረችው ከአባቷ ቀጥላ በፈላሾች ነግሣ

ነበር።በዘመኗም በ842 ዓ/ም በአክሱም የድንግናዣን ልጅ አንበሳ ውድም የተባለ ሕጻን ነግሦ ሀገሪቱን በአንድነት ማስተዳደርና መምራት ባለመቻሉ ይህን አጋጣሚ ተጠቅማ ዮዲት /ጉዲት/ ወይም እሳቶ መናገሻው ከተማ ወደ አክሱም በመዝመት ንጉሡን በማባረር ከተማውን በቁጥጥር ሥር እንዳዋለች ታሪክ ይናገራል።

**5.7. ዮዲት /ጉዲት/ በኢትዮጵያ፡-**ህፃኑ ንጉሥ ሀገሩን ለማስተዳደር አለመቻሉን የሰማች ዮዲት ዘመዶቿን በክተት ሠራዊት አሰልፋ ወደ አክሱም ገሰገሰች፣ህፃኑ ንጉሥ ከነመኳንንቱ ጋር ወደ ሸዋ ስለሸሹ ዮዲት አክሱም ከተማ ገብታ ከተማውን ወረረች በክርስቲያኖች ላይ ከአባቷ የወረደ ጥላቻ ስለነበራት በአብርሃ አጽብሃ የተሠራችውን በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የነበረችውን የድንግል ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ጭምር የክርስቲያኖች ቅርስ የነበረውን በሙሉ አቃጠለች።ከክርስትና በፊትም ሆነ በክርስትና ዘመን የተሠሩ ብዙ ሐውልቶችን አፈራረሰች።መጻሕፍትና ሌሎች የቤተ ክርስቲያን ንዋየተ ቅድሳት ሁሉ ተደመሰሱ።አያሌ ክርስቲያኖችና ካህናትም ከድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ጋር አብረው ተቃጠሉ።ከዚህ ከጭካኔዋም የተነሳ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዮዲት የተባለው ስሟ ተቀይሮ ጉዲት አስቴር የተባለውም ስሟ ተቀይሮ እሳቶ እየተባለ ተጠራ።

**5.8.. የአንበሳ ውድም ወደ መንበሩ መመለስ፡-** ዮዲት 842-882 ዓ/ም ድረስ ለ40 ዓመታት የመከራና የስቃይ አገዛዝ ከገዛች በኋላ ሞተች።ሕፃን የነበረው አንበሳ ውድምም ወደ አክሱም ተመልሰው በመግባት የመንግስታቸውንም ሥልጣን ያዙ።በዚህ በ40 ዓመታት ውስጥ በኢትዮጵያ ከውጭ የግብጽ እስላሞች ተጽዕኖ በውስጥ ደግሞ የጉዲት ቃጠሎ ቤተ ክርስቲያን ያለ አገልጋይ እንድትቀር አድርጓታል ተጠናክሮ የነበረው ክርስትናም ወደኋላ መመለስ ጀመረ።በዚህን ጊዜ በሀገሪቱ የሃይማኖት መሪ ጳጳስ ስላልነበረ የሕዝቡ ተወካዮች ወርቅና ብራቸውን ጭነው ጳጳስ ለማምጣት እንደተለመደው ወደ ግብጽ ሄዱ።በዘመኑ በእስላሞች ትዕዛዝ የሊቀ ጳጳሱ መቀመጫ ከእስክንድሪያ ወደ ካይሮ ተዛውሮ ነበርና መልዕክተኞቹ ካይሮ ደርሰው ጭኖ የወሰዱትን ገጸ በረከት **ለሊቀ ጳጳሱ ለአባ ቆዝሞስና ለካሊፋው** ካከፋፈሉ በኋላ ምርጫ ተደርጎ **አቡነ ጴጥሮስ** የተባሉት የኢትዮጵያ ጳጳስ እንዲሆኑ ተመርጠው ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡም በእስላሞቹ ምክንያት በአክሱም መንግስት ላይ በወረደው አደጋ ከ911-995 ዓ/ም ድረስ ለ84 ዓመታት የጳጳስ መምጣት ተቋርጦ ስለነበር የአክሱም ሕዝብና ንጉሡ በሃይማኖታዊ ናፍቆት በታላቅ ክብርና ደስታ ተቀብሏቸዋል።ጳጳሱ በኢትዮጵያ ብዙ ሥራ በማከናወን ላይ እያሉ ንጉሡ ታሞ ሊጠይቁት ወደ ቤተ መንግስት ይሄዳሉ፣ንጉሡም እንደሚሞቱ ተረድቶ ከሳቸው በኋላ አልጋውን የሚወርሰውን ለማወቅ አባቴ እኔ መሞቴ ነው ከሁለቱ ልጆቼ መንግሰቴን ተረክቦ ሕዝቡን ሊያስተዳድር የሚችለው የትኛው ይመስሎታል አላቸው ጳጳሱም በቅንነት መንፈስ አልጋህን ለትንሹ ልጅህ አውርስ አሉት።ወዲያውም ንጉሡ ሞቱና ትንሹ ልጅ የአባቱን አልጋ ወረሰ።በዚህን ጊዜ ግን የበኩር ልጁ በጳጳሱና በነገሠው ወንድሙ ላይ የበቀል እርምጃ ለመውሰድ ያስብ ጀመረ፡፡በዚህ ሃሳብ ላይ እንዳለ ከግብጽ ከአባ እንጦንስ ገዳም የመጡ **አባ ሚናስና አባ ፊቅጦር** የሚባሉ ሁለት መነኮሳት ስለነበሩ ሀዘኑን ለነሱ ገለጠላቸው።እነሱም በተንኮል ተነሳስተው ከእስክንደሪያው ሊቀ ጳጳስ ከአባ ቆዝሞስ የተላከ አስመስሎ **‹‹አባ ጴጥሮስ ከእስክንድሪያው መንበር በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ያልተሾመ**

**አታላይና ሕገወጥ ጳጳስ ነው።አባቱን ዙፋን ሊወርስ የሚገባው የበኩር ልጅ ነው** የሚል ደብዳቤ አርቅቀው ይሰጡታል።ልጁም ይህን ጽሑፍ ባገኘ ጊዜ ብዙ ደጋፊዎችን ሰብስቦ ወንድሙን ለመገልበጥ ውጊያ ገጠመው።በጦርነቱም ድል ስለቀናው ወንድሙን ገልብጦ ከዙፋኑ አውርዶ እሱ ነገሠ።ወዲያውኑ አቡነ ጴጥሮስ ወደ ወህኒ ቤት ተላኩ።ይህን ተንኮል ከተበተቡ አንዱ አባ ሚናስ ጳጳስ ሆኑ።ከጥቂት ጊዜ በኋላ አባ ሚናስና ግብረ አበሩ በነአባ ፊቅጦር መካከል ጠብ ተጀመረ፣አባ ፊቅጦር የአባ ሚናስን ወርቅ ሰርቆ ወደ ግብጽ ተመለሰ።በዚያም ሃይማኖቱን ወደ እስላምና ለውጦ ቆብን ጥሎ ተቀመጠ።ይህ ሁሉ የአታላይነት ተግባር መፈጸሙ በእስክድሪያው ቤተ ክርስቲያን የተሰማው ዘግይቶ ነበር።እንደተሰማ ግን **ሊቀ ጳጳሱ አባ ቆዝሞስ በአባ ሚናስ ላይ ውግዘት አስተላለፈበት የአቡነ ጴጥሮስንም ሕጋዊ ጵጵስና አረጋገጡ**።ንጉሡም የአባ ሚናስን አታላይነት በሰማ ጊዜ ወዲያው ገደለው።አቡነ ጴጥሮስ ግን በእስር ቤት እያሉ ሙተው ስለነበር መንበሩ ያለ ሊቀ ጳጳስ ቀረ።ከ911-995 ዓ/ም ድረስ ከአበባ ቆዝሞስ በኋላ የተነሱ **አራት ሊቃነ ጳጳሳት አባ መቃርስ፣አባ ቴዎፋንስ፣አባ ሚናስና አባ አብርሃም ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ጳጳስ** አልመጣም።በነዚህ 84 ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ባለማግኘቷ በሃይማኖት በኩል ብዙ ችግር ደርሶባታል።ሕዝቡ ተስፋ ቆርጠውና ተደናግጠው እግዚአብሔር ቢጣላን ነው እንጂ መች ይህ ሁሉ መከራ ይደርስብን ነበር እያሉ ዘኑን ጧት ማታ ወደ እግዚአብሔር ያቀርብ የነበረበት የመከራ ዘመን ነበር።እግዚአብሔር ግን ይህን ሕዝብ ጨርሶ አልረሰውም።

### 5.9.አፄ ድልነዓድ ዘመነ መንግስት /902-912/

ንጉሥ ድልነዓድ ከአንበሳውድም ቀጥሎ ከ902-912 ዓ/ም ድረስ ለ10 ዓመታት ያህል እንደነገሠ በነገሥታት ዝርዝር ተገልጿል።የቤተ ክርስቲያን የታሪክ ጸሐፊና ሊቅ የሆኑት ብላተን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ዋዜማ በተሰኘ መጽሐፋቸው ገጽ 21 ላይ እንደገለጹት ድልነዓድ ከአባቱ ከአንበሳውድም ቀጥሎ የነገሠ ነው ብለውታል።እዚህ ላይ የምንረዳው ነጥብ ቢኖር ድልነዓድ ወንድሙን ገድሎ የነገሠ መሆኑን ነው።ድልነዓድ በ10 ዓመት የንግሥና ዘመኑ ሕዝቡን በተረጋጋ ሁኔታ ለማስተዳደር አልተቻለውም።ይህም የሆነበት ምክንያት

1. በደቡብ ግብጽ የነበሩ አረቦች /እስላሞች/ ግብጽን በኃይል ይዘው በሚያስተዳድሩበት ጊዜ ለአክሱም መንግስት ተገዥ የነበሩትን በምስራቅና በኤርትራ ባህር ዳር የሚገኙት የምጽዋ ዳህላቅ ደሴቶች በአረቦች እጅ መግባትና በነዚህም ወደቦች ለአክሱም መንግስት በግብር በግብዣና በቀረጥ የሚገባው የንግድ ጥቅም መዝጋት፣

2. የአክሱም መንግስት ወደቡን በማስነጠቁ በሀብትም በግዛትም በመደህየቱ፣

3. የአክሱም መንግስትን በኃይልና በሀብት ግዛትም መደህየት የተመለከቱና በሰላም ጊዜ እየገበሩ ሲሸፍቱም በወታደር እየዘረፉ እየተፈቱ ይቀመጡ የነበሩ የሰሜንና የአገው ፈላሾችና የላስታ ነገዶችም ተገዥነታቸውን አንቀበልም በማለት በኃይል በመነሳታቸው።በነዚህ ምክንያቶች ድልነዓድ በአክሱም ተቀምጦ ኢትዮጵያን ለመግዛትና በሰላም ለመኖር አልተቻለውም።ለአክሱም መንግስት መውደቅም ምክንያት የሆነው ይህ እንደሆነ

ተመዝግቧል።

አፄ ድልነዓድ ሕዝቡን ወደ ሰላም ለመመለስ ጥረት ቢያደርጉም የጦር አዛዡ የነበረው መራ ተክለ ሃይማኖት መሶበ ወርቅ የተባለች ሴት አግብቶ አፄ ድልነዓድን ለመዋጋት ዘመተበት።በጦርነቱም ድል አድርጎ አፄ ድልነዓድንም እንደአባቱ ወደ ሸዋ አሸሽቶ የአፄ ድልነዓድን መንግስት በኃይል ወስዶ በኢትዮጵያ ነገሠ ስመ መንግስቱንም **ዛጉዌ** ብሎ ሰየመው።

እስከዚህ ድረስ ያለው ታሪክ ከዘመነ አበው /ከሰሎሞናዊ መንግስት/ እስከ ዛጉዌ ሥርዌ መንግስት ያለው ዘመን ሂደት፣ዕድገትና እንቅስቃሴ የሚያሳይ ሲሆን የኢትዮጵያ ዋና መናገሻ ከተማም አክሱም ማዕከል በማድረግ የተፈጸመ ታሪክ ነው።ከዚህ በመቀጠል ደግሞ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ከአክሱም ወደ ላሊበላ በመዛወር የተፈጸመውን ታሪክ እንመለከታለን።

# ምዕራፍ አራት

# ከዮዲት እስከ አፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግስት

# /922-1268/

በዚህ ምዕራፍ የኢትዮጵያ ቤተ መንግስት እስከ 922 ዓ/ም ድረስ መናገሻ ከተማውን በሀገራችን በሰሜኑ ክፍል በታሪካዊቱ ከአክሱም ወደ ላስታ /ሮሐ/ የተዛወረበት የታሪክ ክፍል መሆኑን እንረዳለን።ይህም ከአክሱም ወደ ላስታ /ወሎ/ በመዛወር የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ላሊበላ የሆነበትና የአክሱም መንግስት ወድቆ የዛጉዌ መንግስት የተመሠረተበት ነው። በዚህን ጊዜ በዮዲት ወረራ ተደናግጦ የነበረው ክርስቲያኑ ሕዝብ የሃይማኖቱ ስሜት ከእንደገና ተቀስቅሶ የተቃጠሉትን አብያተ ክርስቲያናትን ማደስ፤የፈረሱትን መልሶ መጠገን፣የተቃጠሉ መጻሕፍት ከእንደገና ማጻፍ ብዙ ጥረት ተደርገዋል።የክርስቲያኖቹም ፍቅርና መተባበር ሥራውን ሁሉ እንድ ቃና ረድቷል።የነገሥታቱና የመኳንንቱ ልጆች በወጣትነት ዘመናቸው እየመነኑ ገዳም በመግባታቸው ምንኩስናዊ ሕይወት በጣም ተስፋፍቶ ነበር።የኢትዮጵያ ሥርወ መንግስት እስከ 925 ዓ/ም ድረስ ሰሎሞናዊ ሥርወ መንግስት /የሰሎሞን ዘሮች የንግሥት ሰባና የቀዳማዊ ምኒልክ ልጆች/ ሲመራ ቆይቷል።ወደ ላስታ የተለወጠው ሥርወ መንግስቱ ከእነሱ ዘር ውጪ የዛጉዌ ሥርወ መንግስት ተብሎ ይጠራል።ስለዛጉዌ መንግስት መመሠረት ሲነሳ መራ ተክለ ሃይማኖት ተጠቃሽ ሲሆን የዛጉዌ ሥርወ መንግስት መሠረትም መርሃ ተክለ ሃይማኖት ተብሎ ይጠራል።የአክሱም ሥርወ መንግስት ወደ ላስታ ሲዛወር በዛጉዌ /በላስታ/ ከነገሡት ነገሥታት በቤተክርስቲያን ተካፋይነት ያላቸው ነገሥታት ብዛታቸው **ሰባት** ሲሆኑ አጠቃላይ **የነገሡት ግን 11** ናቸው።

### 6.1.**መራ ተክለ ሃይማኖት (912-925)**

የአክሱም መንግስት የነበረው አፄ ድልነዓድ ሀገሪቱን በአግባቡ ማስተዳደር ባለመቻሉ የባህር ወደቦችና የንግድ ማዕከሉ በአረቦች በማስያዙ የላስታ ወይም የአገው ነገዶች መንግስትነቱን አንቀበልም በማለት ግብር ከመክፈል ተቆጥበው መንግስቱ በይዞታ፣በንግድና በሀብት እንዲዳከም አደረጉት።ይህን ሁኔታ የተመለከተ የላስታ ወገኖች መሪ የሆነው መራ ተክለ ሃይማኖት ወገኖቹንና ሠራዊቱን ሰብስቦ በአፄ ድልነዓድ ላይ ዘምቶ አፄ ድልነዓድን እንደ አባታቸው እንደ አንበሳ ውድም ወደሸዋ እንዲሸሹ አድርገው መንግስቱን በቁጥጥሩ ሥር አደረገ።

የኢትዮጵያ መንግስት ከአክሱም ወደ ላስታ /ዛጉዌ/ ከተዛወረ በኋላ ከላሊበላ በፊት ያሉት የዛጉየ ነገሥታት የሠሩት ሥራ ቢኖርም በዘመኑ ተጽፎ ወደ ዘመናችን ያልተተላለፈ በመሆናቸው ታሪኩን ብዙ መተንተን አይቻልም።ነገር ግን ከታሪከ ነገሥት መጽሐፍ ውስጥ በመጠኑ እንደምናገኘው መራ ተክለ ሃይማኖት ከ912-925 ዓ/ም ለ13 ዓመታት የዛጉየን መንግስት ከመሠረቱና ከመሩ በኋላ በተከታታይ ከእሳቸው ልጆችና የልጅ ልጆቹ አስር ነገሥታት የገዙ ሲሆን የግዛት ዘመናቸው 925-1268 ዓ/ም ሲሆን አጠቃላይ 343 ዓመት ይሆናል።እነሱም፣

1. **ጠጠውድም** **6. ይምርሐነ ክርስቶስ**

**2. ጃን ስዩም** **7. ቅዱስ ሀርቤ /ገብረ ማርያም/**

**3. ግርማ ስዩም** **8. ቅዱስ ላሊበላ**

**4. መይራሪ** **9. ነአኩቶ ለአብ**

**5. ሀይብይ .** **10. ይትባረክ ናቸው።**

### 1.**ጠጠውድም /925-965/**

ጠጠውድም የመራ ተክለ ሃይማኖት ልጅ ሲሆኑ ከ925-965 ዓ/ም ጀምሮ ኢትዮጵያን አስተዳድሯል።የዛጉዌ ሥርወ መንግስት መናገሻ ከተማ በላሊበላ /በላስታ/ አካባቢ የተረጋገጠና የተደላደለ በሆነ ጊዜ ንጉሠ ነገሥት ጠጠውድም ከመንገሣቸው ከ83 ዓመት በፊት በዮዲት ጉዲት ወረራ ተደናግጠው የነበረውን ሕዝበ ክርስቲያን በዘመነ መንግስታቸው በመሰብሰብ በመምከርና በጋራ በመሥራት ተነሳሽነት እንዲኖራቸው የሕዝቡን ስሜት በሞራል እየቀሰቀሱ የተቃጠሉ መጻሕፍት ከእንደገና እንዲጻፉ፣የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናት ተመልሰው እንዲሠሩና እንዲጠገኑ፣የፈራረሱ ሐውልቶች እንዲሠሩ፣የመኳንንቱና የመሳፍንቱ ልጆችም በወጣትነታቸው እየመነኑ ገዳም በመግባት የምንኩስና ሕይወት እንዲጠናከር አድርገዋል።በዚህ ዘመን የግብጽ ክርስቲያኖች ከእስላሞች ፊት እሸሹ ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸው ተጽፎ ይገኛል።ይህም በኢትዮጵያ የተረጋጋ ሕይወት ስለነበረ ከአረብ እስላሞች ተጽዕኖ የተነሳ ነው።

### **2.ጃን ስዩም /965-1005/**

ጃን ስዩም ከ965-1005 ዓ/ም ድረስ የነበሩ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሲሆኑ ከጃን ስዩም በፊትና በዘመናቸውም በኢትዮጵያ ጳጳስ ባለመኖሩ በዚያን ዘመን ሱዳን የክርስቲያኖች መናኸሪያ ሀገር ስለነበረች በሱዳን /ኑቢያ/ ንጉሠ ነገሥት በጊዮርጊስ በኩል ለእስክንድሪያው ሊቀ ጳጳስ ለነበሩት ለአባ ፊላታዎስ ንጉሡ አንድ መላዕክት ላኩ።መልዕክቱም **‹‹አባቶቻችን በአቡነ ጴጥሮስ ላይ በሠሩት በደል እግዚአብሔር ተቆጥቶናል ሀገራችን በአባር፣በቸነፈር፣በጦርነት ብዙ ስቃይ ተቀበለች፣ምዕመናኑና ካህናቱ አለቁ፣አብያተ ክርስቲያናቱም በጦር ወረራ ፈረሱ፤ከመፍረስም የተረፉት በካህናት መታጣት ተዘጉ።ይህን ሁሉ ችግራችንንና መከራችንን ተገንዝበው ሀገራችንን የሚባርክልን ከእግዚአብሔር የሚያስታርቀን ጳጳስ ይላኩልን** ›የሚል ነበር።ይህ መልዕክት አባ ፊላታዎስ እንደደረሳቸው የእስክንድሪያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጳጳስ ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ ፈቀደ ወዲያውም ምርጫው ተከናውኖ ከገዳመ አስቀጥስ ከአባ መቃርስ ገዳም የተመረጡ **አባ ዳንኤል** የተባሉ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ተብለው ተሾሙ።ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡም ለብዙ ዘመን አዝነውና ተክዘው የነበረው ክርስቲያን የናፍቆትና የደስታ ስሜት የተቀላቀለበት እንባ እያለቀሰ ተቀበላቸው።እሳቸውም የፈረሰውን በማሠራት፣ያዘነ የተከዘውንም በማጽናናትና

በማረጋጋት ሐዋርያዊ ተልዕኳቸውን ሲፈጽሙ ቆዩ።በዚህ ዘመን የእስክንድሪያ ቤተ ክርስቲያን የእስላሙ መንግስት ወደ ኢትዮጵያ በሚላከው ጳጳስ ምክንያት ሊቃነ ጳጳሳቱን ግብር ክፈሉ፣እኛን ሳታስፈቅዱ ወደ ኢትዮጵያ ጳጳስ አትላኩ በማለት ብዙ ሲያስሯቸው ሲፈቷቸው ኑረዋል።ለዚህ ነበር ለቁጥጥር እንዲመቻቸው ጥንታዊውን የእስክንድሪያውን መንበረ ፓትርያርክ መቀመጫ ነቅሎ ወደ ካይሮ ያዛወሩት።ሲወርድ ሲዋረድ በቆየው የክርስቲያኖች ልማድ መሠረት የእስክንድሪያ ሊቃነ ጳጳሳት ለኑቭያና ለኢትዮጵያ ንጉሥ ያስተላልፉት የነበረው ሐዋርያዊ መልዕክት በአባ ዘካሪያስ ሊቀ ጵጵስና ዘመን 996-1023 ዓ/ም የእስላሞቹ መሪ ከሊፋ እል ሐኪም እንዳይላክ ከመከልከሉም በላይ በስውር ወደ ኢትዮጵያ ጳጳስ ልካሃል ተብሎ አባ ዘካሪያስ ለብዙ ጊዜ እንደታሰሩ ታሪክ ይነግረናል።የግብጽ ክርስቲያኖችም መከራ ስለፀናባቸው ወደ ሮምና ቁስጥንጥንያ እንዲሄዱ በትምህርተ ሃይማኖት ስለማይመስሏቸው ኑቭያ በእላሞች ስለተወረረች በቀጥታ ወደ ሃይማኖት ወንድሞቻቸው ወደ ኢትዮጵያ መጡ።የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግስትም እንደተለመደው የወንድምነት አቀባበል አደረገላቸው።በዚህን ጊዜ በኢትዮጵያ የነበሩት አባ ዳንኤል አርፈው ስለነበር ሌላ ጳጳስ ለማስመጣት ወደ ግብጽ መልዕክተኛ ተላከ።ያን ጊዜ የእስክንድሪያ ሊቀ ጳጳሳት የነበሩት አባ ክርስቶዱሎስ (ገብረ ማርያም ) ቀደም ሲል በኑቭያና በኢትዮጵያ የሚገኙትን መስጊዶች ሁሉ አፈራርስ ብለህ አባ ፊቅጦርን ወደ ኑቭያ አባ ቄርሎስን ወደ ኢትዮጵያ ልከሃል ተብሎ ተወንጅለው ወህኒ ቤት ገብተው ስለነበር ኢትዮጵያውኑ መልዕክተኞች ጳጳስ አላገኙም።በዚህ መካከል አብዱም የሚባል ግብጻዊ እስላም የሐሰት ደብዳቤ ይዞ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ አባ ቄርሎስ ነኝ ብሎ የጵጵስና አቀባበል ተደረገለት።የዚህ ሰው ሐሰት በግብጽ እንደተሰማ የግብጽ ቤተ ክርስቲያንና የመንግስቱም ባለሥልጣናት ወዲያው እንዲያዝ ወደ ኢትዮጵያ መልዕክት ላኩ ቀጣፊውም ተይዞ በዳህላቅ በኩል ወደ ግብጽ ተወስዶ አንገቱን በሰይፍ ተቀርጦ እንደሞተ ታሪክ ያስረዳል።ሊቀ ጳጳሳት የነበሩት አባ ክርስቶዱሎስ (ገብረ ማርያም) አርፈው በምትካቸው አባ ቄርሎስ /ዘካሪያስ ሊቀ ጳጳስ እንደሆኑ ወደ ኢትዮጵያ ጳጳስ ለመላክ የግብጽ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ዝግጅት አደረገ።ነገር ግን ያን ጊዜ ግብጽን ይገዛ በነበረው በድር እል ጀማል ተጽዕኖ ወደ ኢትዮጵያ የተላኩት ቅዱስ ሲኖዶስ የመረጣቸው ሳይሆኑ የእስላሞቹ ወዳጅ አቡነ ሳውሮስ ነበር።

### 3. ግርማ ስዩም (1005-1045 ዓ/ም)

በግርማ ስዩም ዘመነ መንግስት የኢትዮጵያን ሃይማኖት የሚመራ ሕዝቡን የሚያስተምር መንግስቱን የሚባርክለት ጳጳስ ስላልነበር ንጉሡ መልዕክተኞችን ወደ ካይሮ ልኳል።ነገር ግን ከላይ እንደተገለጠው ያን ጊዜ የተላኩት አባት ቅዱስ ሲኖዶስ የመረጣቸው ሳይሆኑ በግብጽ መሪ በከድር አልጀማል ተጽዕኖ የእስላሞች ወዳጅ የሆኑትና ለጥቅም ያደሩት አቡነ ሳዊሮስ ነበሩ።አቡነ ሳዊሮስ ወደ ኢትዮጵያ እንደገባ የኢትዮጵያ ንጉሥ ግርማ ስዩምና ሕዝቡ ካህናቱም ጭምር የደስታ አቀባበል አደረጉ።ነገር ግን አቡኑ ከድር አልጀማል ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ምንም ሥራ ከመጀመሩ በፊት በኢትዮጵያ ለሚኖሩ ዐረብ እስላሞች መስጊዶች እንዲሠሩ አደረጉ እስላሞቹም በኢትዮጵያ ሃይማኖታቸውን እንዲያስፋፉ የሐሳብ ድጋፊ ይሰጧቸው ጀመር።አቡኑ በኢትዮጵያ **ሰባት መስጊዶች** እንዲሠሩ አዘዘ።መስጊዶቹ ከተሠሩ በኋላ ከዳር እስከ ዳር የኢትዮጵያ ሕዝብ ተነሱባቸው ንጉሠ ነገሥቱም በጣም ተቆጣ ሳይውል ሳያድር ሕዝቡ ወጥተው **ሰባቱን መስጊዶች አመድ** ካደረገ በኋላ ይህንንም የእስላም መንግስት መልዕተኛ ጳጳስ አንልፈገውም በማለት መስቀሉንና ቆቡን ተረክበው ወህኒ ቤት ጨመሩ።ይህንን ካደረጉ በኋላ ከጳጳሱ ጋር አብሮ የመጠውን ወንድሙን ወደ ግብጽ እንዲመለስ አደረጉ እሱም ከተመለሰ በኋላ በሕዝቡና በመንግስት የሆነውን ሁሉ ለግብጹ መንግስት ሪፖርት አደረገ።የግብጽ መንግስት መሪ ከድር አልጀማልም በቁጣና በድንፋታ ለግርማ ስዩም እንዲህ የሚል መልዕክት ላከ «**በሀገርህ የፈረሱ መስጊዶች ከእንደገና ካልተሠሩ፣እስላሙ ህብረተሰብ ባይጽናና፣የተወሰዱ ንብረቶች ባይመለሱ በግብጽ /በኮፕት/ ምድር የታነጹትን አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አመድ አደርጋለሁ፤ክርስቲያኑንም የቤተ ክርስቲያን ኃላፊዎችንም ወደ ወህኒ አወርዳቸዋለሁ**››በማለት የዛቻ ደብዳቤ ለግርማ ስዩም ላከ።የኢትዮጵያ ንጉሥ ግርማ ስዩምም በኢትዮጵያዊነት ወኔ ተቀስቅሰው ዛቻውን ከምንም ሳይቆጥር አጸፋውን እንዲህ ሲል መለሰለት «**ከግብጽ አብያተ ክርስቲያናት አንዲት**

**ድንጋይ ቢትነሳ፣ሕዝቡ ቢታሰርና ንብረቱ ቢዘረፍ የእስላም መመኪያ ወደሆነችው ወደ መካ መዲና ተሻግሬ የእስላሞች መስገጃ አመድ አድርጌ ወደ አንተው ወደ ግብጽ መጥቼ አንተንና ሕዝብህን አመድ ካደረኩ በኋላ ትቢያውን ካይሮ እልካለሁ፤በመቃብርህ ላይም አብያተ ክርስቲያናትን እሠራለሁ** ›በማለት አስፈሪና የከረረ ደብዳቤ ከመጻፉም በላይ ወዲያኑ ለመዝመት ዝግጅት በማድረጉ ከድር አልጀማል ሃሳቡን በመቀየር አስታራቂዎችን ይፈልግ ጀመር፡፡ምክንያቱም በዚህ ዘመን የአውሮፓ የክርስቲያን ነገሥታት የመስቀል ጦርነት የሚል ስያሜ ኢየሩሳሌምን ከአረብ እስላሞች ነፃ ለማውጣት በመካከለኛው ምስራቅ የመስቀል ጦርነት በአረቦች ላይ የተጀመረበት ወቅት ስለነበረ የግብጽ እስላም ዐይኑን ወደ ጦርነት ሲያዘነብል የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግስት ዐይኑን ደግሞ በግብጾች ላይ በማነጣጠሩ እንኳንስ አብያተ ክርስቲያናት ሊያፈርስ ቀርቶ ከነካተው ቤተሰብ ለመሆን ጀመር፡፡ከዚህ በኋላ ከግርማ ስዩም ቀጥሎ ከመራ ተክለ ሃይማኖት ከመጀመሪያ ሚስቱ ከመራተ ክርስቶስ የተወለዱ መይራራና ሀይብይ/ሀርየያ/ በመሀል ነግሠዋል፡፡እነዚህ ነገሥታት መይራራ ከ1045-1060 ዓ/ም ለ15 ዓመታት ሀርብያ ደግሞ ከ1060-1077 ዓ/ም ለ17 ዓመታት ያህል ከመንገሣቸው ውጭ ስለንግሥና ዘመናቸው ሁኔታ የተፃፈ መረጃ የለም፡፡

4. **ይምርሐነ ክርስቶስ (1077-1117 ዓ/ም)**

ይምርሀነ ክርስቶስ ቅድስናን ከንግሥና ጋር አጣምሮ የኖሩ በመሆኑ የቅድስና ማዕረግ ተሰጥቶታል፡፡በዛጉዌ የነገሥታት ዝርዝር ውስጥ ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ፣ቅዱስ ገብረ ማርያም /ሀርቤ/፣ቅዱስ ላሊበላና ቅዱስ ነአኵቶ ለአብ አራቱ ነገሥታት በቅድስና የኖሩ ናቸው፡፡በቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ዘመነ መንግስት በኢትዮጵያና በግብጽ እስላም መንግስት መካከል የሻከረ ግንኙነት እንደነበር ታሪክ ይገልጻል፡፡ይህም አቡነ ሳዊሮስ የተባሉ አጭበርባሪ የእስላሞች ወዳጅ በግርማ ስዩም ዘመን መንግስት ከታሰሩበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ኢትዮጵያ ጳጳስ ማምጣት አልተቻለም፡፡ይሁን እንጂ ንጉሡ ከብዙ የመላላክ መልዕክት በኋላ አባ ጊዮርጊስ የተባሉትን ጳጳሳ አስመጥቶ ነበር፡፡አባ ጊዮርጊስም እንደ አቡነ ሳዊሮስ ለቤተ ክርስቲያን ምንም ሳይሠሩ ስስታምና ገንዘብ ሰብሳቢ ስለነበሩ ተራ ነጋዴ ሆኖ በመገኘታቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዐይናችን አጥፋልን በማለት ለንጉሡ አቤቱታን በማቅረብ ወዲያውኑ እንዲባረሩ ተደርጓል፡፡፡፡

ይምርሐነ ክርስቶስ ብዙ በእስክንድሪያ ቤተ ክርስቲያንና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ እስላሞች የሚፈጽሙትን ከፍተኛ በደልና ጫና በመገንዘብ የሚያደርሱትን ግፍ ለመበቀል በእነሱ ላይ ወሳኝ እርምጃ ለመውሰድ ተዘጋጁ፡፡ይኸውም የዐባይን ወንዝ ለመገደብ መሞከር ነው፡፡ይምርሐነ ክርስቶስ የግድቡን ሥራ ለማቀላጠፍ ጠበብትንና አማካሪዎችን በማዘጋጀት የግድቡን ሥራ በመጀመር ላይ እንዳሉ የዐባይ ውሃ በግብጽ እየቀነሰ በመሄዱና የግብጽ ሕዝቦች በውሃ እጦት በመሰቃየታቸው የግብጽ እስላሙ መንግስት ተደናግጠው አማላጅ ሁነው የዐባይን ውሃ እንዲያስለቅቁ በዘመኑ የእስክንድሪያ ፓትርያርክ የነበሩ አቡነ ሚካኤል ተልዕኮ ወደ ኢትዮጵያ መጡ፡፡ፓትርያርክ ሚካኤል ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ይምርሐነ ክርስቶስ ቤተ መንግስት በመግባት ውሃው ቢቋረጥ መስጊድ ብቻ ሳይሆን ቤተ ክርስቲያንም ይቋረጣል፣እስላሙ ብቻ ሳይሆን ክርስቲያኑም ያልቃል አሁንም ከግብጽ ተልኬ የመጣሁት ይህንኑ ለእናንተ ለልጆቼ ለመግለጥ ነው ብለው ለንጉሡና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ልመናቸውን አቀረቡ፡፡ጥፋቱም እንዳይደገም ተማፀኑ፡፡በዚህን ጊዜ ውሃው ተለቀቀ ሊቀ ጳጳሱም ደስ ብሏቸው ሸኚ ደብዳቤ ይዘው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ፡፡

1. **ቅዱስ ሐርቤ /ገብረ ማርያም/ (1117-1157)**

ይምርሐነ ክርስቶስ ልጅ ስላልነበራቸው የጃን ስዩም የወንድሙ ልጅ ሀርቤ ነገሡ፡፡በሀገራችን ሀርቤ ወይም ገብረ ማርያም በአረቦች ቀኑዳ በፈረንጆች ሲኖዳ (ሽኑዳ) ተብለው የሚጠሩ ቅዱስ ሀርቤ ከሌሎች ነገሥታት ልዩ የሚያደርጋቸው ለመጀመሪያ ጊዜ የነፃነትና የመብት ጥያቄ ለእስክንድሪያው ሲኖዶስ ማቅረባቸው ነው፡፡ብዙ

ሃይማኖታዊና ብሔራዊ ሥራዎችን የሠሩ ደገኛ ንግሥ ናቸው፡፡ቅዱስ ሀርቤ ለእስክንድሪያ 70ኛው ሊቀ ጳጳስ ለአባ ገብርኤል 2ኛ ያቀረቡት ጥያቄ ኢትዮጵያውያን ከራሳቸው ልጆች ጳጳሳት መምረጥ እና መሾም እንዲችሉ የሚል ከፍተኛ ትግል የተደረገበት እንደሆነ ታሪክ ይገልጻል፡፡በዚህ መልኩ ሃይማኖታዊ፣ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ሥራዎችን ለመስራት በር ከፋች መሪ እንደሆኑ እናያለን፡፡የቅዱስ ሀርቤ ኢትዮጵያዊ ጳጳስ ይሾምልን የሚለው ጥያቄ በ1131-1145 ዓ/ም ባለው ዘመን መካከል በኢትዮጵያ ለነበሩ ጳጳስ ለአቡነ ሚካኤልና ለፓትርያርክ ገብርኤል 2ኛ ነበር ያቀረቡት፡፡ለጥያቄው መንደርደሪያ የተደረገውም **የሀገርቷን ስፋትና ርቀት፣የሕዝቡን ብዛት፣በቋንቋ አለመግባባት፣የእስልምና ሃይማኖት እየተስፋፋ መምጣት፣የሚመጡ ጳጳሳት ቁጥር ማነስ፣የሚመጡ ጳጳሳት በዋናው ከተማ ብቻ መቀመጥ፣ስብከተ ወንጌልን ማስፋፋት ትቶ ለዲቁናና ለቅስና ብቻ መኖር እና ተዘዋውሮ በኅብረተሰቡ መካከል አለመገኘት** የሚሉና እነዚህን የመሳሰሉትን መሠረታዊ ሃሳቦች ላይ ሰባት የኢትዮጵያ ጳጳሳት እንዲሾሙላቸው ልዑካኑን ወርቅ፣አልማዝና ብሩን አስጭኖ ወደ እስክንድሪያ ላኩ፡፡በቅዱስ ሀርቤ ጥያቄ ካሊፋዎችና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በከፍተኛ ሁኔታ ተደናገጡ፡፡አንድ አጭር መልስም መለሱ እሱም **አንድ ጳጳስ በቂ** ነው የሚል ነበር፡፡ቅዱስ ሀርቤ ሌላ ጥያቄ ጠየቁ ከእናንተ የተላኩት አቡነ ሚካኤል ያረጁ ስለሆኑ ምትክል አንድ ኢትዮጵያዊ ይሾምልን *አሉ፡፡* ***ጳጳስ ላይ ጳጳስ አናደርግም*** *አሉ፡፡በዚህ ምክንያት በቅዱስ ሀርቤ፣በአቡነ ሚካኤልና በፓትርያርኩ መካከል ከፍተኛ ጸፀብ ተጀመረ፡፡ፓትርያርኩ አቡነ ገብርኤል አርፎ በተተኪው በአቡነ ዮሐንስ ጊዜ* ይህንን ጥያቄ ድጋሚ ቢያቀርቡም ከነካተው ጳጳስ እንዳይላክ አደረጉ፡፡ያም ሆነ ይህ በቅዱስ ሀርቤ አነሳሽነት የተጀመረው ጥያቄ ዛሬ ተሟልቶ ኢትዮጵያ የራሷን ልጆች በራሷ መሬት ላይ እስከ ፓትርያርክነት ድረስ ለመሾም ስለበቃች የቅዱስ ሀርቤ ሐሳብ ተፈጸመ ለማለት ይቻላል፡፡ቅዱስ ሀርቤ በዚያ በጨለማው ዘመን የመብትና የነፃነት ጥያቄ በማቅረብ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈሉ የተባረኩና የተመሰገኑ ንጉሠ ነገሥት በመሆናቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስታስታውሳቸው ትኖራለች፡፡

### 7. ቅዱስ ላሊበላ /ገብረ መስቀል/ (1160-1197)

ቅዱስ ላሊበላ አባታቸው ጃን ስዩም እናታቸው ኪዮርና /ኬረወርና/ ይባላሉ፡፡ኬረወርና ማለት በአገውኛ ቤተ ክርስቲያን ማለት ነው፡፡ቅዱስ ላሊበላ የተወለደው በ1101 ዓ/ም ታህሳሥ 29 ቀን በዕለተ ማክሰኞ ላስታ ቡግና ወረዳ ሩሐ ከተባለች እንደ ቤተ መንግስት ወይም እንደእልፍኝ ሲጠቀሙባት ከነበረች ፍልፍል ውስጥ ነው፡፡ቅዱስ ላሊበላ ሲወለዱ መላዕክት በነጫጭ ንብ ተመስለው ሐፃኑን ከበው መላ ሰውነቱን ምንም እንዳይነካው ይከላከሉ ነበር፡፡ከሕፃኑ ከንፈርም እያረፉ ማር ይቀስሙት ነበር፡፡በዚያን ጊዜ እናቱ ያን ድንቅ ተአምር ስታዩ ተደነቀው ማር ሲያቀምሱት በማየታቸውም ስሙን ላል አሉ፡፡ላል ማለት በአገውኛ ንብ ማለት ወይም ማር ማለት ነው፡፡ይህ ስያሜ ከጊዜ ብዛትም ላል ይበላል የሚለው ስያሜው ላልበላ በማለት አሳጥረውታል፡፡

ቅዱስ ላልበላ ደምግባታቸው ቁመታቸው መልካቸው ያማረ የተዋበ የትንቢት ልጅ ነበሩና እህታቸው ርብቃ እየናቀች እኔ ንግሥት ሳልባል እርሱ ንጉሥ ሊባል እኔ ቆንጆ ሳልባል እርሱ ውብ ሊባል አይገባውም ማለት በቅናት ተነሳስታ በመርዝ ገድላዋለች፡፡በጊዜ ሞቱም ቅዱስ ገብርኤል ወርዶ ነፍሳቸውን ወደ ሰማይ አሳርጎ የሰማያትን ምስጢራት እልፍ አዕላፋት መልዕክት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ በመንበሩ ዙሪያ እንደሚያመሰግኑ አሳያቸው፡፡ከፈጣሪው አቅርበው አምላኩም ላሊበላን እንዲህ አለው  ወዳጄ ላሊበላ የጠራሁህ እኔ ነኝ በኢትዮጵያ ላይ 40 ዓመት ትነግሣለህ ከአንዲት ቋጥኝ ድንጋይ 10 ቤተ መቅደሶችን ታንፃለህ ረዳት የሚሆኑህም መላዕክት እንጂ ሰው አይደለም  አለው፡፡ቅዱስ ላሊበላም እኔ ደካማ ነኝ ይህ እንዴት ይሆንልኛል አቅምስ ከየት አገኛለሁ አሉ፡፡አምላክም

ስሙ በአንተ ይሁን እንጂ መሠረታቸውም ፍፃሚያቸውም እኔ ነኝ አለው፡፡ቅዱስ ላልበላም ቃሉን ተቀብለው ቅዱስ ገብርኤልም የሰማያት ህቡዕ ምስጢራትን አሳይቶ በ3ኛው ቀን ነፍሳቸውን ከሥጋቸው አዋሐዳት፡፡ቅዱስ ላልበላም በፍጥነት ተነሱ አጠገባቸው ያሉትም ሰዎች ደነገጡ፡፡

ቅዱስ ላሊበላ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ከሰው ጋር ከመኖር ከአራዊት ጋር መኖር ይሻላል በማለት በዱር በጫካ ኖረዋል፡፡በዚያም እያሉ በፈቃደ እግዚአብሔር መስቀል ክብራን ያገቡ ዘንድ በታላቁ መልአክ በቅዱስ ገብርኤል ተነገራቸው በሥርዓተ ህግም መስቀል ክብራን አግብተው ስሙ ይትባረክ የሚባል አንድ ልጅ ወልደዋል፡፡ቅዱስ ላልበላ ቤተሰቦቻቸው ሳይሰሙ ባለቤታቸው መስቀል ክብራን አክሱም ከአባ ጴንጤሌዎን ገዳም አስቀምጠው እሳቸውም በአክሱም ቤተ መቅደስ ለሰባት ቀን ያህል በጸሎት ቆይተው ጉዞቸውን ወደ ኢየሩሳሌም አደረጉ፡፡በኢየሩሳሌምም ክርስቶስ የተወለደበትን፣ያደገበትን፣የተጠመቀበትን፣ግርማ መለኮቱን የገለጠበትን፣የተሰቀለበትን፣ የተቀበረበት ፣ያረገበትን ቦታዎች ለ13 ዓመት በመቆየት ተዘዋውረው ከተመለከቱ በኋላ ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል፡፡የአክሱም ቤተ መንግስት ወደ ላስታ ሲዘዋወር በዛጉዌ (ላስታ) ከነገሡት ነገሥታት ቅዱስ ላሊበላ 9ኛው ንጉሠ ነገሥት ሆነው የንግሥና ዙፋናቸውን ከወንድማው ልጅ ከቅዱስ ሀርቤ ተረከቡ፡፡ ቅዱስ ላሊበላ የአክሱም ቤተ መንግስት ወደ ላስታ ሲዘዋወር በዛጉዌ (ላስታ) ከነገሡት ከሁሉም ነገሥታት መካከል ስመ ጥሪ የሆኑና በመላው ዓለም የታወቁ ንጉሥ ናቸው፡፡

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መንግስታቸውን ተረክበው ቤተ መንግስቱን መካነ ልዕልት ብሎ ሰይሞ ቦታው ላይ ቤተ መንግስት ሠርተው ሕዝቡን በሰላም በሃይማኖት ይመሩ ጀመር፡፡በዘመነ መንግስታቸውም እንደሌሎች ነገሥታት ርስት ጉልትን ለራሳቸው ያልሰበሰቡ፣ንጉሥ ነኝ ብሎም ስልጣናቸውን ጨብጠው አስተዳደሩን ጨቁነው ቁጭ ብዬ ልቅጣ ልፍረድ ሳይሉ ስልጣናቸውን ለሕዝብ ትተው ለ10 ዓመታት ያህል አብያተ ክርስቲያናቱን የሚያንጹበት ዕቃዎችን ያዘጋጁ ነበር፡፡ከዚያም አቅራቢያ ታላላቅ ቋጥኝ ድንጋዮች መኖራቸውን ስላረጋገጡ በግዛታቸው የሚገኙትን ዜጎች አዙዋቸው ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ማነፅ ጀመሩ፡፡የሥራው መሪ ምንም ራሳቸው ቢሆኑም በዘመኑ የነበሩት ዜጎች ሁሉ ጥበብ ተገልጾላቸው በፈቃደ እግዚአብሔር እየተረዱ ሥራውን እያፋጠኑ ይሠሩ ነበር፡፡የሥራውን ዘመን በ23 ዓመት እንዳተጠናቀቀ የሚነገር ሲሆን በአጠቃላይ ከዐለት ተፈልፍለው ያሠራዋቸው አብያተ ክርስቲያናት በመላው ኢትዮጵያ ወደ 23 ይደርሳሉ፡፡ቅዱስ ላሊበላ በዘመነ መንግስታቸው ከሠራቸው ታላላቅ ሥራዎች መካከል የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሚያስታውሰው ዐቢይ ታሪክ በአንድ ከተማ ከአንድ ቋጥኝ ተፈልፍለው ያነጿቸው አስራ አንዱን ቤተ መቅደሶች ናቸው፡፡እነርሱም፡-ቤተ ደናግል፣ቤተ ገብርኤል፣ቤተ ማርያም፣ቤተ አባ ሊባኖስ፣ቤተ መድኃኒዓለም፣ቤተ መርቆሬዎስ፣ቤተ መስቀል፣ ቤተ አማኑኤል፣ቤተ ጎልጎታ፣ቤተ ጊዮርጊስ እና ቤተ ቅዱስ ሚካኤል ናቸው፡፡የቦታውንም ስም የተወለዱበት ሥፍራ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ሮሐ አሉ፡፡

ቅዱስ ላሊበላ በነገሡበት ዘመን የእስክንድሪያ ሊቀ ጳጳስ አባ ማርቆስ 4ኛ ነበሩ፡፡በዚህ ዘመን የነበረው የግብጽ

ሱልጣን /መሪ/  አልአዲን አቡበከር ኢካን ኢዮብ ይባል ነበር፡፡ቅዱስ ላሊበላ እንደነገሡ ገፀ በረከቱን አስጭኖ ጳጳስ ለማስመጣት መልዕክተኞችን ወደ ግብጽ ላኩ፡፡ከላይ የተገለጸው የግብጽ ሱልጣን በክርስቲያኖች ላይ ከባድ ተጽዕኖ አድርጎ መነኮሳቱንም ፈጅቱቸው ስለነበር ለጵጵስና የሚመጥን መነኩሴ በመጥፋቱ መልዕክተኞቹ ለ3 ወራት ያህል ከተጉላሉ በኋላ በመጨረሻም ለሱልጣኑ አቤት አሉ፡፡እሱም የሚፈልገው ይህን ስለነበር ወዲያው ምርጫ እንዲደረግና ጳጳስ ተሹሞ እንዲላክ ፈቀደ፡፡ምርጫው ተከናውኖ **አቡነ ሚካኤል** የሚባሉ ጳጳስ ተሾሙ፡፡እሳቸውም ወደ ደብረ ሮሐ ሊገቡ ጥቂት ሲቀራቸው ከዚያ በፊት እንደሚደረገው በንጉሡና በእቴገዪቱ እንዲሁም በመላው ሕዝብና ካህናቱም ታላቅና የደመቀ አቀባበል ተደርጎላቸው ወደ ደብረ ሮሐ ገቡ፡፡ጳጳሱም በኢትዮጵያ ከአምስት ዓመት በላይ አልቆዩም፡፡በዚህ ዘመን ውስጥ የእቴጌዪቱ የመስቀል ክብራ ወንድም /ዘመድ/ ገብሮን የሚባለውን ኤጲስ ቆጶስነት ሹመውት ስለነበር ሕዝቡ ይወደው ነበርና በዕለት ግጭት ወርቅ ሰርቆብኛል ብለው አስገደሉት፡፡በዚህም ሚች ወገኖች ወንድማችንን በግፍ ያስገደለውን ነፍሰ ገዳይ ጳጳስ አንፈልግም የሚል ስሜት ስለአደረባቸው ወደሀገራቸው ተመለሱ፡፡ነገር ግን እዚያ ሲደርሱ እቴጌዪቱ ወንድማቸውን ኤጲስ ቆጶስነት እንድሾምላቸው ጠይቀውኝ ሾምሁት እሱም ሹመቱን እንዳገኘ ሀገሩ ነውና ሕዝቡን፣ቀሳውስቱንና ዲያቆናቱን እያስተባበረ የጵጵስናውን ሥራ ጨርሶ ቀማኝ፤ከዚያም አልፎ ተርፎ ለሕይወቴ የሚያስገኝ ሆነ፡፡በዚህም ምክንያት ሸሽቼ ወደ ሀገሬ ተመለስኩ ብለው ነገራቸው፡፡

ሊቀ ጳጳሱም ጉዳዩን ለማጣራት አባ ሙሴ የሚባሉ መነኩሴ ወደ ኢትዮጵያ ላኩ፡፡አባ ሙሴ ጉዳዩን ሲያጣሩ አንድ ዓመት ቆይተው ወደ ግብጽ ሲመለሱ አፄ ላሊበላ ከሱ በፊት ከነበሩ ነገሥታት ለየት ያለ ገፀ በረከት ለሊቀ ጳጳሱ ልዩ የሆነ የወርቅ ዘውድ /አስኬማ/፣ለሱልጣኑ አንድ ዝሆን፣አንድ የሜዳ አህያ፣አንድ አንበሳ እና አንድ ቀጭኔ ከነ ነፍሳቸው አስይዘው ጳጳስ ለማስመጣት ወደ ግብጽ መልዕክተኞችን ከአባ ሙሴ ጋር ልከዋል፡፡እነዚህ ሁሉ በካይሮ ከተማ እንደኤግዚቢሽን ለሕዝብ ሁሉ ሲታዩ ብዙ ቀን ቆዩ፡፡አባ ሙሴም አቡነ ሚካኤል ወደ ሀገራቸው ለመመለስ የበቁት በፈፀሙት የነፍስ መግደል ወንጀል እንደሆነ ለሊቀ ጳጳሱ በጽሑፍ አቀረቡ፡፡ሊቀ ጳጳሱም በመዐልቃ ገዳም አያሌ የግብጽ ክርስቲያኖችን ሰብስበው አባ ሙሴ ያመጡትን መረጃ ካቀረቡ በኋላ ጳጳሱን አቡነ ሚካኤልን የጳጳስነቱን ሥልጣን ገፈፉ፤በቦታቸውም ምርጫ ተደርጎ ከአባ እንጦንስ ገዳም ሁለት መነኮሳት **አባ ይስሐቅ የኢትዮጵያ ጳጳስ፣አባ ዮሴፍ ኤጲስ ቆጶስ** ተብለው በመጋቢት ወር 1210 ዓ/ም ተሹመው ወደ ኢትዮጵያ መጡ፡፡

ቅዱስ ላሊበላ በነገሡበት ዘመን በመካከለኛው ምስራቅ ኢየሩሳሌምን ከእስላሞች እጅ ለማላቀቅ 3ኛው የመስቀል ጦርነት ይካሄድ የነበረበት ዘመን ስለነበር የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ወደ ኢየሩሳሌም ያደረጉት የነበረው ጉዞ ተቋርጠው ነበር፡፡የጦርነቱ ዓላማ ይህ ቢሆንም በሮማ ካቶሊክ የሚመራ እንጂ መላው የምስራቅ አብያተ ክርስቲያናት አልተቀላቀሉም፡፡ይህ የተፋፋመ ጦርነት የተካሄደው በናዝሬትና በጥብርያዶስ መካከል ሲሆን ተዋጊዎቹም **ከካቶሊኮች ወገን የጀርመን ንጉሥ ፍሬዴሪክ ባርባሩስ፤የእንግሊዝ ንጉሥ ሪቻርድ ልበ አንበሳ፤የፈረንሳይ ንጉሥ ፊልጶስ አገስት** ናቸው፡፡በእስላሞቹ በኩል ደግሞ **ሳላህ አዲን** የተባለው እነዚህን ሁሉ

አሸንፎ ኢየሩሳሌምን መልሶ በቁጥጥሩ ሥር አደረገ፡፡**<u>ኔዎፊቶስ</u>** የተባለው ቆጵሮሳዊ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ፀሐፊ በ1189 ዓ/ም ሳላህ አዲን በ3ኛው የመስቀል ጦርነት ኢየሩሳሌምን በያዘ ጊዜ የክርስቲያን ቅርሶች ዋናዎቹን

- በቅዱስ መቃብር አጠገብ ያለውን ዕሌኒ ንግስት ቅዱስ መስቀሉን ያስወጣችበትን ዋሻ እና
- በቤተልሔም ጌታ የተወለደበትን ጎል ለቅዱስ ላሊበላ በስጦታ ያበረከተው መሆኑን ጽፏል፡፡

በአጠቃላይ ቅዱስ ላሊበላ መላው ኢትዮጵያ ሲገዙ ለልጅ ልጆቼ ቤት አዳራሽ ልሥራ ሳይሉ በድንኳን እየኖሩ ለክርስቲያን ልጆቹ መውጫ መውረጃ የጽድቅ መሰላል አንጾ ያረፉ ጻድቅ አባትና ንጉሥ ናቸው፡፡ቅዱስ ላሊበላ መዋዕለ ዘመናቸውን በሰላምና በጽኑ እምነት ካሳለፉ በኋላ በተወለዱ በ97 ዓመት ከ5 ወር በነገሡ በ40 ዓመት ሰኔ 12 ቀን 1197 ዓ/ም አርፈዋል፡፡በጊዜ ዕረፍቱም አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ተገኝተው ሥርዓተ ግንዘቱን ገንዘው ቀብር እርሳቸው ባሉበት አሁን ከሚገኘው ከቅዱስ ሚካኤል መንበር ውስጥ ተቀብሯል፡፡

7. **ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ /1197-1237/**

ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ የቅዱስ ላሊበላ ወንድም የቅዱስ ሀርቤ /ገብረማርያም/ ልጅ ሲሆኑ የተወለዱት በብስራተ መልአክ ነው፡፡ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ ከንግሥናቸው በፊት የእመቤታችንን ቤተ መቅደስ ለመሥራት አቅደው በኪምስ፣እንድሪያስና ሳኦል የሚባሉ ሦስት ግብጻውያን ጠቢባን እንዲፈቀዱላቸው ጠይቆ በጥያቄቸውም መሠረት ሦስቱም ተፈቅደውላቸው ከእነርሱ ጋር በመሆን ቅዱስ ላሊበላ ጀምሮ ያልፈጸማትን የእመቤታችንን ቤተ ክርስቲያን ሥራውን በ7 ወር ውስጥ ጨርሶ ኅዳር 21 ታቦቷ ገብቷል፡፡

ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ ሙሉ ለሙሉ ንግሥናቸውን ከመረከባቸው በፊት የአንድ አውራጃ ገዥም ነበሩ፡፡ቅዱስ ላሊበላ አስቀድሞ ስለነአኩቶ ለአብ መወለድ መልአኩ ባበሰራቸው ጊዜ ንግሥናቸውንም የሚረከበው ነአኩቶ ለአብ መሆኑን ነግሮአቸው ነበርና ቅዱስ ላሊበላ ነአኩቶ ለአብን አስጠርቶ ንግሥናቸውን አስረከቡ፡፡ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ በዘመናቸው ሁሉ ከመላእክት ጋር ወደ ሰማይ እየወጡ ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገሩ ነበር፡፡በየቀኑ ብረትና ድንጋይ ተሸክሞ ሺህ ጊዜ ይሰግዱ ነበር፡፡በ20 ዓመታቸው ንጽሕተ ማርያም የተባለች ሚስት አግብተው እስከ 25 ዓመት ድረስ ሁለቱም በድንግልና ሲኖሩ ቅዱስ ሩፋኤልና እመቤታችን በየተራ ለነአኩቶ ለአብ ተገልጸው ልጅ ትወልዳለህ ብለው አበሰሩት ከዚያም ስሙ በኃይለ መስቀል የተባለ ልጅ ወለዱ፡፡

ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ የተከተሉት የአመራር መንፈስ የአባታቸውን የሀርቤን የአመራር ዘዴ ነበር፡፡በላሊበላ ዘመነ መንግስት ከግብጽ ተሹሞ ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ጳጳስ አባ ይስሐቅ ከላሊበላ ሞት በኋላ ብዙ ቆይተው ሞቱ፡፡በመጀመሪያ አባ ሚካኤልን ቀጥሎም አባ ይስሐቅን ሹሞ ወደ ኢትዮጵያ የላኩት ፓትርያርክ ዮሐንስ በዘመኑ ከነበሩ ግብጻውያን ፓትርያርኮች ስለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተሻለ ግንዛቤ ያላቸው ይመስላል፡፡እኚህ ፓትርያርክም የአባ ይስሐቅን መሞት እንደሰሙ ያለ ምንም ማቅማማት ተተኪ ጳጳስ ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ ፍላጎት

ነበራቸው ግን በካሊፋዎቹ ተጽዕኖ ፍላጎታቸው አልተሳካም።

ነአኩቶ ለአብ አባታቸው ሀርቤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ራስ ለማስቻል ያደረጉት ውጣ ውረድ እንደአንድ እርምጃ አድርገው ተመልክተውታል።ነገር ግን የኢትዮጵያውያንን ራስ የመቻል ጥያቄ ቸል ያሉት ግብጻውያኖች በዚህም ዘመንም አቋማቸው ጽኑ ነበር።ነአኩቶ ለአብም የመጨረሻ እርምጃቸው ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ተመካክረው የራሳቸው ጳጳስ እንዲሾሙም መመሪያ ሰጥተዋቸው እንደነበር አንድንድ የታሪክ መጻሕፍት ዘግበዋል።ያም ሆነ ይህ ነአኩቶ ለአብ ለዛሬው ራስን የመቻል ውጤት እንደ አባታቸው የታገሉ ቅዱስ ንጉሥ ናቸው።ነአኩቶ ለአብ ከ1197-1237 ዓ/ም ለ40 ዓመታት ያህል ኢትዮጵያን አስተዳድሯል።ከነአኩቶ ለአብ ቀጥሎም የነገሡ ቅዱስ ላሊበላ ልጅ ይትባረክ ሲሆኑ እኚህ ንጉሥ ከ1237-1245 ዓ/ም ለ8 ዓመታት ከመንገሣቸው ውጭ የተጻፈ ታሪክ አልተመዘገበላቸውም።

## ምዕራፍ አምስት

## ከአፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዘመነ መሳፍንት (1245-1283)

የኢትዮጵያ መንግስት በኃይል ወደ ዛጉዌ ዘር ካለፈ ከ333 ዓመት ቆይታ በኋላ በ13ኛው መ/ክ/ዘመን ወደ **ሰሎሞናዊ ሥልጣን /ቀዳማዊ ምኒልክ ዘር/** ወደ አፄ ኩኖ አምላክ ከተመለሰበት ጊዜ ጀምሮ አፄ ቴዎድሮስ እስከ ነገሡበት 1845 ዓ/ም ድረስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና በሀሪቱ ላይ በርካታ መንፈሳዊ ክንውኖች የተፈጸመበት ዘመን ሲሆን በዚያው መጠንም የክርስትናው ተፃራሪ የሆኑ ተግባሮችም ታይተውበታል።በዛጉዌ ነገሥታት ዘመን እየተያዙ እንዳይታሰሩና እንዳይሞቱ እየፈሩ በዱርና በዋሻ እየተደበቁ ዘራቸው ሳይጠፋ የቆዩ የቀዳማዊ ምኒልክ ወገኖች ዘጠኝ ናቸው።ነገር ግን ለንግሥና የበቁት ድልነዓድና ይኩኖ አምላክ ብቻ ናቸው።ይኸውም ድልነዓድ በዛጉዌ ነገሥታት ሥልጣኑን ከመነጠቁ በፊት 10 ዓመት የዛጉዌ መንግስት ካለፈ በኋላ ደግሞ ይኩኖ አምላክ 15 ዓመት ከመንገሣቸው በስተቀር ሌሎቹ ሰባቱ እድሜያቸውን በስደትና በመከራ የጨረሱ ናቸው።

### 7.1. አፄ ይኩኖ አምላክ /ተስፋ ኢየሱስ/ 1270-1283

አፄ ይኩኖ አምላክ ከዛጉዌ መንግስት በኋላ የቀዳማዊ ምኒልክን የንግሥና ዘመን የጀመረ ንጉሥ ነው።የንግሥና ዘመኑም ከ1245-1260 ዓ/ም ድረስ እንደሆነም በነገሥታት የንግሥና ተርታ ተገልጿል።አፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግስት ከግብጽ የመጣ ጳጳስ አልነበረም።በመሆኑም ንጉሡ ጳጳስ ለማስመጣት ከግብጽ ሱልጣን ከሩቅ አዲስ ባይባር ጋር በየመኑ ሱልጣን በሐምዳኒድ በኩል ይጻጻፉ ነበር።ነገር ግን በወቅቱ የነበረውን የእስላሞች ንቅናቄ በመደገፍ ሱልጣኑ ጳጳስ ተሹሞ እንዲመጣ አልፈቀደም።እንዲያውም በግብጽና በኢትዮጵያ መካከል የነበረውን የፖለቲካ ግንኙነት ሳይቀር አቋረጠ።

ገድለ ተክለ ሃይማኖት እንደሚለው አቡነ ተክለ ሃይማኖት አረማውያንን አስተምረው አጥምቀው ቀድሰው ለማቁረብ ጽላትና ሜሮን አጥተው ተቸግረው ወደ እግዚአብሔር ቢጸልዩ አረማዊው ንጉሥ መተሎሜ ያረከሰውን ጽላት ባርከው እሳቸው እንዲቀድሱበት ከእግዚአብሔር መታዘዛቸውንና በዚሁም ቅጽበት የጵጵስናውን ሥልጣን በተአምራት ከእግዚአብሔር መቀበላቸውን ሲገልጽ ሊቃነ ጳጳሳት እንደሚሾሙ ሌሎች ጳጳሳት ሳይሆን አንተን ግን እኔ ሾምሁህ አላቸው ይላል።በኋላም አቡነ ዮሐንስ የሚባሉ ጳጳስ ከግብጽ መጥተው ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት በግማሽ ኢትዮጵያ ጳጳስ እንዲሆኑ መፍቀዳቸውን ገድለ ተክለ ሃይማኖት ይገልጻል።በአፄ ኩኖ አምላክ ዘመን ያለው የኢትዮጵያ ክርስትና እንቅስቃሴ በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ሐዋርያዊ ተግባር የተወሰነ ነው።በዚህም መላዋን ኢትዮጵያን ወንጌል መስበክ ድውያንን በመፈወስ፣አብያተ ክርስቲያናትን በማነጽ በጸሎታቸውና በትሩፋታቸው የወንጌል ብርሃን አብርተዋል።አረማውያንን በማስተማር ከአምልኮተ ጣኦት ወደ አምልኮተ አግዚአብሔር መልሰዋል።በመጨረሻም በዓታቸውን ደብረ ሊባኖስ ገድመው በጾምና በጸሎት ተጋድሎአቸውን ፈጽመዋል።

ከይኩኖ አምላክ ዘመን በኋላ በልጁ በያግብዓ ጽዮን ዘመነ መንግስት ከ1268-1277 ዓ/ም ኢትዮጵያ ከግብጽ ጋር የነበራት ግንኙነት ስለተሻሻለ አባ ዮሐንስ የተባሉ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ሰላማ የተባሉ ጳጳስ ሹመው ወደ ኢትዮጵያ ልከዋል።

### 7.2. ያግብዓ ጽዮን ዘመነ መንግስት (1285-1294)

ያግብዓ የአፄ ይኩኖ አምላክ ልጅ ሲሆን በዘመነ መንግስቱ በግብጽና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ግንኙነት እየተሻሻለ ስለሄደ ጳጳስ ተሹሞ ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል።

### 7.3. አፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግስት (1297-1327)

በአፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግስት 1297-1327 ዓ/ም የኢትዮጵያ ጳጳስ አቡነ ያዕቆብ ነበሩ።የአፄ ይኩኖ አምላክና የአፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግስት በኢትዮጵያ የክርስትና እምነት እየታደሰ የሄደበትና የሥነ ጽሑፍና ብሕትውና ወይም የምንኩስና ሕይወት ያደገበት ዘመን ነው።የአምደ ጽዮን ዘመነ መንግስት ሥነ ጽሑፍ የዳበረበት ዘመን ስለነበር 2ኛው የሥነ ጽሑፍ ዘመን ይባላል።ምክንያቱም አምደ ጽዮን በዮዲት ወረራ በቃጠሎ የጠፉትን ታሪክ ሁሉ ሳይረሳ በሀገሩ ያሉ ታሪክ አዋቂዎችን አሰባስቦ መንፈሳዊ የሆነውንና የነገሥታቱን ታሪክ እንዲጻፍ አድርገዋል።በዚህ ዝግጅት ውስጥም ክብረ ነገሥትና ታሪከ ነገሥት ዘአክሱም የተባሉ መጻሕፍት በዘመኑ የተጻፉ ናቸው።በዚህ ዘመን ሌሎች ብዙ መጻሕፍት ተተርጉመዋል፣ብዙ ሥነ ጽሑፎች ተጽፈዋል፣የተለያዩ የጸሎት፣የታሪክ፣የሥርዓተ ቅዳሴና የግብረ ሕማማት መጻሕፍት ከአረብኛ ወደ ግሪክ የተተረጎሙና በግዕዝ የተጻፉ አሉ።ከአረብኛ የተተረጎሙ ውዳሴ ማርያም፣መጽሐፈ ግንዘት፣ሥርዓተ ቅዳሴ እና መጽሐፈ ኪዳን ሌሎችም ገድለ ሰማዕታትና ገድለ ሐዋርያት የተተረጎሙ መጻሕፍት ናቸው።

### 7.4. አፄ ሰይፈ አርዕድ ዘመነ መንግስት (1327-1355 ዓ/ም)

ይህ ዘመን በግብጽ የእስላሙ መሪ ሱልጣን መርዋን አልጋዴን  በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ወርቅና ብር ለእኔ መገበር አለባችሁ በማለት ጳጳሳቱን ቢያስገድዳቸውም ጳጳሳቱ ግን ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ምክንያት 84ኛው የእስክንድሪያ ሊቀ ጳጳስ አባ ማርቆስን ያሠረበት ዘመን ነበር፡፡ሱልጣኑ ሊቀ ጳጳሱን ካሰረ በኋላ ለአፄ ሰይፈ አርዕድ የሚያስፈራራ መልዕክት እንደጻፈ እና  አፄ ሰይፈ አርዕድም ሊቀ ጳጳሱን ለማስፈታት ሲሉ በኢትዮጵያ በንግድ ሥራ ይተዳደሩ የነበሩ እስላም ግብጻውያንን ሰብስበው ስላሠሩ ሊቀ ጳጳሱ እንዲፈቱ የተደረገበት ዘመን ነው፡፡በተጨማሪም ታሪከ ነገሥት እንደሚለው አፄ ሰይፈ አርዕድ አቡነ ማርቆስን ለማስፈታት ላዕላይ ግብጽ ድረስ ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት ብለው ወደ ግብጽ በመዝመት በእስላም መሪ የሚመራውን ጦር ድል እንዳደረጉ በዚህም ከሱልጣኑ የይቅርታ መጠየቂያ ገጸ በረከት እንደተሰጣቸው ይነገራል፡፡አፄ ሰይፈ አርዕድም ሊቀ ጳጳሱም አስፈትተው የተሰጣቸውን ገፀ በረከት ብርና ወርቅ በኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን በመታሰቢያነት እንዲቀመጥላቸው በመላክ ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል፡፡(ስንክሳር ጥቅምት 19 ቀን)

## 7.5. አፄ ዳዊት ዘመነ መንግስት (1365-1395 ዓ/ም)

አፄ ዳዊት አፄ ሰይፈ አርዕድ የልጅ ልጅ ሲሆኑ በዘመናቸውም በግብጽ የነበረው ችግር በሰላም ተፈቶ የነበረው ክርስቲያኖችን የማንገላታት እንቅስቃሴ ከእንደገና አገርሽቷል፡፡በእስክንድሪያ የሚገኙት ክርስቲያኖች ሁሉ ወደ እስልምና እንዲጠቃለሉ ታወጀ ሊቀ ጳጳሳቱም ታሰሩ፡፡በዚህ ጊዜ አፄ ዳዊት እንደ ሰይፈ አርዕድ በብዙ ሺህ የሚቆጠር ባለፈረስ፣ባለበቅሎ፣ባለግመልና እግረኛ ጦር አስከትለው ወደ ግብጽ ዘመቱ፡፡አፄ ዳዊት ካርቱም እንደደረሱም ግብጽ ድረስ ምን ያደክመኛል በማለት ካርቱም ላይ የአባይን ውሃ ገደበው ወደሱዳን በረሃ እንዲፈስ አደረጉት፡፡ግብጻውያኑም አፄ ዳዊት በወሰዱት እርምጃ ተደናግጠው ለአፄ ዳዊት 120000 ወቄተ የሚሆን ወርቅ እጅ መንሻ ላኩ፡፡አፄ ዳዊትም የተሰጣቸውን እጅ መንሻ ገፀ በረከት ከምንም ሳይቆጥሩ ነገር ግን በመታሰቢያነት በዚያው  በእስክንድሪያ ቤተክርስቲያን እንዲቀመጥላቸው በመስጠትና በወርቁም ምትክ ጌታ የተሰቀለበት ግማደ መስቀል እንዲሰጣቸው ጠየቁ፡፡ግብጻውያኖቹም በአባይ ውሃ ሕይወታቸው ከምታልፍ **ንግስት እሌኒ ከተቀበረበት አስቆፍራ ያስወጣችውን የጌታችንን ቅዱስ መስቀል፣ወንጌላዊው ሉቃስ የሳለውን ምስለ ፍቅረ ወልዳ፣የጌታ አክሊለ ሶክ በለቀ ጳጳሳቱ አስይዘው አፄ ዳዊት ባሉበት ካይሮ ድረስ ላኩላቸው፡፡አፄ ዳዊት መስቀሉን መስከረም 10 ቀን 1395 ዓ/ም ተረከቡ**፡፡መስቀሉንም ይዞ ጉዞ ላይ ሳሉም መስከረም 21/1395 ዓ/ም በሕልማቸው  መስቀሌ በመስቀል ይቀመጣል የሚል ራዕይ ታያቸው፡፡አፄ ዳዊት ቅዱስ መስቀሉን አስይዘው ወደ ምድረ ኢትዮጵያ ጉዞአቸውን እያደረጉ ሳሉ ምንም ሳይታመሙ በድንገት ጥቅምት 2 ቀን 1395 ዓ/ም መስቀሉን በተረከቡ በ29ኛው ቀን **ስናር** ከሚባል ቦታ ሲደርሱ አረፉ፡፡አፄ ዳዊት ኢትዮጵያን ለ30 ዓመት ከ6 ወራት አስተዳድሯል፡፡አፄ ዳዊት ዘመነ መንግስት አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የተነሱበትና እስከ 26 የሚደርስ ባሁኑ ጊዜ ከግራኝ ወረራ ተርፈው ያሉት መጻሕፍት በአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የተጻፉበትና የቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ጽሎት (Order of prayer) በአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የነግህ፣የሠርክ፣የመዓልት፣የሌሊት ተብሎ የተነደፈበት ዘመን ነው፡፡

## 7.6. አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግስት (1437-1468)

አፄ ዘር ያዕቆብ /ቆስጠንጢኖስ/ የአፄ ዳዊት ልጅና የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ደቀ መዝሙር ናቸው።አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ከ1437-1468 ዓ/ም እንደነገሡ ተመዝግቧል።ዋዜማ የተሰኘው የብላተን ጌታ ኅሩይ መጽሐፍ ደግሞ የንግሥና ዘመናቸውን ከ1426-1460 ዓ/ም በማለት አስቀምጠዋል።ያም ሆነ ይህ የዘመኑ ርቀትና ቅርበት ቢለያይም አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ለ34 ዓመታት እንደነገሡ ተመዝግቦ ይገኛል።ታሪክ ስለአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ሲመሰክር ከእሳቸው በፊት ከነበሩት ነገሥታት ከአብርሃ ወአጽብሃ፣ከአፄ ካሌብ እና ከአፄ አምደ ጽዮን በኋላም እስከ 18ኛው መ/ክ/ዘመን ድረስ ከነበሩ መሪዎች መካከል እንደ ዘርዓ ያዕቆብ ያለ ስመጥር ንጉሥ ለኢትዮጵያ አልተነሳም ይላል።

አፄ ዘርዓ ያዕቆብ በንግሥና ዘመናቸው ከፈጸሙት ተቀዳሚ ተግባር በአባታቸው ዘመነ መንግስት ከእስክንድሪያ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት የነበረውን ቅዱስ መስቀል ወደ ኢትዮጵያ ማድረስ ነበርና በተገለጠላቸው ራዕይ መሠረት መስቀሉን ከሱዳን አምጥተው መስከረም 21 ቀን 1443 ዓ/ም በአንባሰል አውራጃ ደብረ ከርቤ በሚባለው ተራራማ /መስቀለኛ/ ሥፍራ አስቀምጠዋል።በተጨማሪም ለስነ ጽሑፍና ኪነ ጥበብ መስፋፋትና ባዕድ አምልኮ ከምድረ ኢትዮጵያ ጨርሶ እንዲጠፋ የታገሉ መሪ ናቸው።በቁጥር ወደ ዘጠኝ የሚሆኑ መጻሕፍትን በተጨማሪም ሥርዓተ ቤተ መንግስትንና ሥርዓተ ምልክና /የቤተ ክህነት ሥርዓት/ መጽሐፍ ተሻሽሎ እንዲጻፍ አድርገዋል።ተስፋፍቶ የነበረውን አምልኮተ ጣኦት በማጥፋት ክርስቲያኖችን በማስተማር **በየወሩ በዓላት እንዲከበሩ** የተደረገበት ዘመን ነው።በዚህ ዘመን ደቂቀ እስጢፋ የሚባሉ ካህዲዎች ለእመቤታችንና ለቅዱስ መስቀል ስግደት አይገባም የሚል የክህደት ትምህርት ይዞ ስለተነሱ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ሊቃውንቱና ምዕመናኑ ባሉበት ጉባኤ ዘርግተው በጉኤው ደቂቀ እስጢፋ እንዲገኙ አድርገው ተከራክረው ደቂቀ እስጢፋኖስ ለመርታት ችሏል።እነሱም በምዕመናን ውሳኔ ከነተከታዮቻቸው ጋር በሞት ተቀጡ።

አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ለግብጽ ክርስቲያኖች ታላቅ እገዛም አድርገዋል።ይህም በግብጽ የምትገኝ ደብረ ምጥማቅ ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን በዘመኑ በኃይል አይለው የነበሩ እስላሞች አቃጥሏት ነበር።በዚህን ጊዜ ክርስቲያኖች በእምነት ለሚመስሏቸው ሀገሮችና ወገኖች የድረሱልን ጥሪ አስተላለፉ።ንጉሡ ይህን በሰሙ ጊዜ ሠራዊት አስከትለው ወደ ግብጽ ወርደው እስላሞችን ፀጥ አድርገው ከሰይፍ የተረፉ ክርስቲያኖችን አጽናንተው የፈረሰችውን ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን አሠርተው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ።እስላሞቹ የአፄ ዘርዓ ያዕቆብ መመለሳቸውን ካረጋገጡ በኋላ ለ2ኛ ጊዜ ቤተ ክርስቲያኗን እንዳልነበረ አደረጓት።ንጉሡም ለ2ኛ ጊዜ ወደ ግብጽ ለመሄድ መንገድ ሲጀምሩ እመቤታችን ተገልጻ **‹‹ልጅ ዘርዓ ያዕቆብ ሆይ እኔ ወደ አንተ እመጣለሁና ወደዚህ ሁለተኛ አትምጣ** ›አለቻቸው እሳቸውም ወደ ቤተ መንግስታቸው ወደ ሰላድንጋይ ተመለሱ።ከዕለታት በአንድ ቀን በቤተ መንግስታቸው አካባቢ ባለው ገላጣማ ቦታ ላይ ብርሃን ያያሉ በብርሃኑም ውስጥ እመቤታችን **በሰባት ሠረገላ ተቀምጣ በጻድቃኔ ማርያም** አገኟት።

በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግስት በፍሎሬንስ (በኢጣሊያ ከተማ) በተደረገው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት

ጉባኤ ኢትዮጵያውያን መነኮሳት ተሳታፊ ሆነዋል።የጉባኤው ዓላማ የቱርክ እስላሞች እየተበራከቱ አይለው የክርስቲያን ሀገሮችን ሁሉ ስለያዙ ክርስቲያኖች በመካከላቸው ያለውን ልዩነት አስወግደው የጋራ ጠላታቸውን የሆነውን ወራሪ እስላም ለመቋቋም ነበር።ነገር ግን በጉባኤው የምስራቅና የምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት ስላልተስማሙ ጉባኤው ወደ ተጠበቀው ስምምነት ሳይደርስ ተበትኗል።

ከአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ቀጥለው የነገሡት ልጃቸው በዕደ ማርያም ከ1460-1470 ዓ/ም ሲሆኑ እኚህ ንጉሥ በንግሥናቸው ሳይዘልቁበት በወጣትነታቸው ገዳም ገብተው በተጋድሎ እንዳለፉ ይነገራል።በኢትዮጵያ የነገሥታት ታሪክ ውስጥ በመንፈሳዊነት ከአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ቀጥለው የሚታወቁት አፄ ናዖድ ናቸው።አፄ ናዖድ ከ1487-1500 ዓ/ም የነገሡ ሲሆን መልክዐ ማርያም ደርሰዋል፣ዜማ፣ቅኔ፣ብሉይንና ሐዲስ ኪዳንን ተምረዋል።

### 7.7. አፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግስት (1500-1533)

ቁስጥንጥንያ በሞንጎልያና በቱርክ እስላሞች ከተያዘችበት ከ1453 ዓ/ም እና መላው ታናሽ እስያ ክርስቲያኖች በእስላሞች ቁጥጥር ሥር ከዋሉ በኋላ የሞንጎልያና የቱርክ እስላሞች ከሃይማኖት ወንድሞቻቸው ከዐረብ እስላሞች ጋር ኃይላቸውን አስተባበሩ።ወረራው ተስፋፍቶ መላው ሰሜን አፍሪካ እና የአውሮፓ ደቡብ ግሪክ፣ስፔይን፣አልባንያ፣ቡልጋሪያ፣ሩማንያና ዩጎዝላቪያ እነዚህ ሁሉ የቱርክ ግዛት ሆኑ።ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ኢትዮጵያ ለውጭ ወራር የማትመች ተራራማ ሀገር ስለሆች አልተደፈረችም።ነገር ግን እዚሁ ኢትዮጵያ ወሰን የተወለደው ግራኝ መሐመድ በስመ እስላም ከቱርክ ባለስልጣናት ጋር እየተላላከ የኢትዮጵያን ክርስቲያን ሕዝብ ለመደምሰስና ሀገሪቱን ለቱርክ ለማስረከብ ተነሳ።

ይህ አድማ በቤተ መንግስት እንደተሰማ ባለስልጣናቱ ወደ ክርስቲያን ሀገሮች እርዳታ ቢጠይቁም እርዳታ የተጠየቁ ሀገሮች ካቶሊኮች ስለሆኑና ኢትዮጵያም የሮማን ካቶሊክ እምነትና ሥርዓት ስልላተቀበለች እርዳታው ዘገየ።በመካከልም ግራኝ መሐመድ ከቱርክ መንግስት ጋር እየተላላከ በስውር ያሰለጠነውን ወታደር አሰልፎ ባለማቋረጥ ለ15 ዓመታት ኢትዮጵያን ወረረ።የቱርክ ጥይትም በኢትዮጵያ ላይ ነደደ።በወርቅና በብር የተሠሩ አብያተ ክርስቲያናት ገዳማትና አድባራት ወደሙ።ከነዚህም የደብረ ሊባኖስ የአቡነ ተክለሃይማኖት ገዳም ተጠቃሽ ነው።ካህናትና መነኮሳት፣የሃይማኖት መጻሕፍትና የታሪክ ሰነዶች በእሳት ተቃጠሉ።ከሞት የተረፉ ምዕመናንም በሰይፍ እየተገደዱ የእስልምናን ሃይማኖት እንዲቀበሉ ተደረገ።የግራኝ ወረራ በቤተክርስቲያንና በምዕመናኑ ሕይወት ላይ ያደረሰው ጉድለት **የቤተ ክህነት የሙያ ደረጃ ዝቅ ማለት፣ያለካህን ፈቃድ ማግባት፣በሆነ ባልሆነ ምክንያት ሚስት ከባል ባልም ከሚስት መፋታት፣ከብዙ ሴቶች ብዙ ልጆች መውለድ በአጠቃላይ ምዕመናን በቤተ ክርስቲያን የሚፈጸመውን ምስጢራዊ ተሳትፎ ማለትም ንስሐን፣ቁርባንንና ተክሊልን እየረሱት መሄዳቸው** ግራኝ መሐመድ ጥሎት በሄደው እስላማዊ ልምድ ተስበው ነው።

**ብዙ የክርስቲያን ቦታዎች ስማቸው ተፋልሶ ቀርተዋል ለምሳሌ በባሌ በአቡነ አኖሬዎስ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት**

**ደቀ መዝሙር ስም ይጠራ የነበረው ቦታ ዛሬ ኑራ ሁሴን እየተባለ ይጠራል።ምንም እንኳ በክርስትና እምነት የሚከለክል ሕግ ባይኖርም በኢትዮጵያ ጥሬ ሥጋ መብላት የተጀመረው ከግራኝ ወረራ በኋላ** ነው።ይህም ሕዝቡ በዱር በገደል ሲንከራተትብዙ ጊዜ ስለኖረ እህል ስለማያገኝ አውሬ እያደኑ ይበሉ ስለነበር ነው። አፄ ልብነ ድንግል በስደት እንዳሉ አርፈዋል፡፡ከእሳቸውም በኋላ ልጃቸው አፄ ገላውዴዎስ ነግሠዋል።

## 7.8. አፄ ገላውድዎስ ዘመነ መንግስት (1533-1549)

አፄ ገላውዴዎስ ከ1533-1549 ዓ/ም ድረስ የነገሡ ሲሆን በርሳቸው ዘመነ መንግስት የካቲት 21 ቀን 1542 ዓ/ም ግራኝ ተገደለ።ግራኝ መሐመድ በወረራው ተሸንፎ ከተወገደ በኋላ የጠፉትን ምዕመናን ፈልጋ ለማግኘትና ወደ ህጽኗም ለመመለስ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ደክማለች ድካሟም በከንቱ አልቀረም ብዙዎቹ ተመልሰዋል።ፈርቶ ወደ እስልምና የገባውንም የደብረ ሊባኖሱ እጨጌ እንባቆም መጽሐፈ ቄዴር እየደገሙ ፀበል እንዲረጭና ወደ ሃይማኖቱ እንዲመለስ አድርገው ብዙዎቹ ተመልሰዋል።መጽሐፍ ቄደርንም የጻፉት እሳቸው ናቸው።

**የካቶሊካውያን አመጣጥ፡-** ካቶሊኮች የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች ብለን ከምንጠራቸው መካከል ዋነኞቹ ሲሆኑ የአመጣጣቸውም ታሪክ እንደሚከተለው ነው።ግራኝ መሐመድ በተነሳበት ዘመን በተከታታይ ንጉሥ የነበሩ አፄ ልብነ ድንግልና ልጃቸው አፄ ገላውዴዎስ የግራኝ መሐመድን ሠራዊት በጦርነት መቋቋም ሲያቅታቸው አፄ ገላውዴዎስ ከፖርቹጋል መንግስት 400 የሚሆን ሠራዊት እንዲመጣላቸው ጠየቁ።በጠየቁት መሠረትም ሠራዊቱ ተልኮላቸዋል።ከዚህ በኋላ አፄ ገላውዴዎስ በለስ ቀንቷቸው በጦርነቱ ግራኝ መሐመድን ድል አደረጉ።ከድሉ በኋላ የፖርቹጋል ሠራዊት ብዙዎቹ ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ ጥቂቶቹ እዚሁ ኢትዮጵያ ውስጥ ቀረ።ከቀሩትም መካከል በኢትዮጵያና በፖርቹጋል መካከል ይላላክ የነበረው ቤርሙዴዝ የሚባለው መናፍቅ ለአፄ ገላውዴዎስ እንዲህ የሚል ጥያቄ አቀረበላቸው « **ግራኝን ለመዋጋት አባትዎ የፖርቹጋል መንግስትን እርዳታ ሲጠይቁ ከሀገራቸው ቆርጦ ለፖርቹጋል መንግስት ለመስጠት፣ከግብጽ ጳጳሳት ማስመጣት ቀርቶ ከሮማ እንዲመጣ ለማድረግ እና በመላው ኢትዮጵያ የሮማ ካቶሊክ ሃይማኖት ብሔራዊ ሃይማኖት እንዲሆን ቃል ገብተውልን ነበርና ይህ እንዲፈፀም አለበት እኔም የመጀመሪያው አቡን ልባል ውል ነበርና ፈርሙልኝ** የሚል ጥያቄ አቀረበ።አፄ ገላውዴዎስም ለፖርቹጋል መንግስትም ሆነ ለሮማ ባለስልጣናት አባታቸው የገቡት ቃል ኪዳን ምን እንደሆነ አላወቁም።ስለዚህም ስለተደረገልን እርዳታ የገንዘብ ስጦታ እናደርጋለን እንጂ ኢትዮጵያን ቆርሰን አንሰጥም፤የሮማ ካቶሊክ ሃይማኖትም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት ይሁን ብለን አናውጅም፣ ከእናንተ መሐል ኢትዮጵያን የወደደ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ መኖር ይችላል።መኖር ያልፈለገ ዋጋውን እየተቀበለ መሄድ ይችላል ከአሁኑ በኋላ በሀገሬ የሌላ ሀገር ባንዲራ ተሰቅሎ ለማየት አልፈልግም የሚል መልስ ሰጡ። በወቅቱም የነበሩ ሊቃውንትና ከእስክንድሪያ የመጡ ጳጳስ አቡነ ዮሴፍም ንጉሡ እንዳሉት በወንድማማችነት የተደረገ እርዳታ ወርቅና ብር እንጂ ኢትዮጵያ ተቆርሳ ለፖርቹጋል መንግስት አትሰጥም፣ሃይማኖታችንንም አንለውጥም ብለው ከቤርሙዴዝ ጋር ተከራከሩ።ይሁን እንጂ ካቶሊኩ ቤርሙዴዝ ሀሳቡን ባለመቀበል ተናዶ በራሱ ጊዜ እንቅስቃሴ ሲያደረግ በመገኘቱ ወደማረፊያ ቤት

እንዲገባ ተደረገ፡፡ከእስር ቤት አማላጅ ልኮ ተፈታ በንዴትም ወደ ሀገሩ ተመልሶ የሆነውን ሁሉ ለፖርቹጋል መንግስትና ለቫቲካን ቤተ ክህነት ሪፖርት አቀረበ፡፡ የፖርቹጋል መንግስትና የሮማ ፓፓ ጳውሎስ 3ኛ ቤርሙዴዝ ባቀረበው ሪፖርት ተወያይተው ተጨማሪ ሌሎች ሚሲዮናውያንን ለመላክ ተስማሙ፡፡ነገር ግን ይህ ከመሆኑ በፊት ከሚላኩት ሚሲዮናውያን የኢትዮጵያን ባህልና ቋንቋ ለማስተማር የኢትዮጵያ ኮሌጅ የሚባል ትምህርት ቤት በቫቲካን የቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ተከፈተ፡፡በዚህ ትምህርት ቤት ለመጀመሪያ የሰለጠኑት **ዣን ኦኔዝ ባሬኖ፣አንድሬ አቢዮዶ እና ሚልኪዎሪ ካርኔሮ** ናቸው፡፡እነዚህ ለሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ክብር እንደጦር ወታደር ሆነው የሚያገለግሉ ኢየሱሳውያን የሚባሉት ክፍሎች በእምነት ጽኑአንና እንግዳ ተቀባይ የሆነው ኢትዮጵያውያንን ቆብ ደፍተው፣ ቀሚስ ለብሰው፣መጽሐፍ ቅዱስና መስቀል ይዘው ሕዝቡ እርስ በርስ ሲጣላና በጦርነት ሲተላለቅ እነሱ የሚፈልጉትን ለመፈጸም እንዲችሉ መከሩ፡፡የሮማ ካቶሊክና መንግስት ዓላማው መንግስትን ከቤተ ክህነት፣ነገሥታቱን ከመሳፍንቱና ከመኳንንቱ እና ከሕዝቡ ጋር ለማፋጀት ስለነበር ይህም ተሳክቶላቸው ካቶሊካውያን በፈጸሙት ሴራ የእርስ በርስ ጦርነት 8000 ሕዝብ እንዳለቀ ይነገራል፡፡ከእነዚህ ለሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ክብር እንደጦር ወታደር ሆነው ከሚያገለግሉ ኢየሱሳውያን መካከል አንዱ የመጀመሪያ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሌሎቹ ኤጲስ ቆጶሳት ተብለው ነበር፡፡ነገር ግን ፓትርያርክ የተባለው በ1548 ዓ/ም በመጋቢት ወር ህንድ ሀገር ሲደርስ ሞተና በምትኩ አንድሪያ አቢያዶ ፓትርያርክ ተባለ፡፡በዚህን ዘመን የካቶሊካውያን ትምህርት ሁለት ባህርይ የሚለው በሮማውያን ጥበብ የተመሠረተ የምንፍቅና /የክህደት/ ትምህርት በሀገራችን እየተስፋፋ ሥር እየሰደደ በመምጣቱ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ከጳጳሳቸው ከአቡነ ዮሴፍ ጋር ሁነው ከሚሲዮናውያኑ ጋር ክርክር ገጠሙ፡፡ሚሲዮናውያኖቹም ለጊዜው የተሸነፉ መስለው ከክርክሩ ሸንጎ ዘውር አሉ፡፡ከዚህ በኋላ አፄ ገላውዴዎስ አርፈው የወንድማቸው ልጅ አፄ ሚናስ ነግሠዋል፡፡

### 7.9. አፄ ሚናስ ዘመነ መንግስት (1549-1553)

የአፄ ገላውዴዎስ የወንድም ልጅ በነበሩ በአፄ ሚናስ ዘመነ መንግስት ሚሲዮናውያን ሸሽተውት የነበረውን ክርክራቸውን ቀጠሉ፡፡የኢትዮጵያ ሕዝብና ካህናቱም በተከታታይ ያለማቋረጥ ተቃውሞን አቀረቡ፡፡ንጉሡም የካቶሊኩን ጳጳስ አንድርያ አቢያዶን አስጠርተው ሁለተኛ የሮማ ባህልና ሃይማኖት በኢትዮጵያ ምድር እንዳይሰብክ ከለከሉት፡፡አቢያዶም በአፄ ሚናስ ተግሳጽ ተቆጥቶ የስም ማጥፋት ዘመቻ ያካሄድ ጀመረ፡፡ንጉሡን ለማስገደልና የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች እንዲያዙ ከእስላሞች ጋር በምስጢር እየተገናኘ የተንኮል ወጥመድን ማጥመድ ጀመረ፡፡ይህ ተግባር ስለተነቃበት ከግብረ አበሮቹ ጋር በግዞት እንዲቆይ ተደረገ፡፡ከዚያም አምልጦ በኢትዮጵያ ዙሪያ ከሰፈሩት ከኢትዮጵያ ጠላቶች ከቱርኮች ጋር ተቀላቀለ፡፡ንጉሡም ይህን ሲሰሙ ከቱርክ ጋር ተዋግተው ሚሲዮናውያኑን ለመማረክ ዘመቱ፡፡ነገር ግን ለማድረግ ስላልቻሉ ወደ ምጽዋ እንዲሰደድ አድርገው ተመለሱ፡፡

### 7.10. **አፄ ሰርፀ ድንግል ዘመነ መንግስት (1564-1596)**

**በ**አፄ ሰርፀ ድንግል ዘመነ መንግስት አንድርያ ለፖርቹጋል መንግስት የፖርቹጋል ጦር ኃይል የኢትዮጵያን የባህር

በር እንዲይዝ ይህም የፖርቹጋልን መንግስትና ሕዝብ ከመጥቀሙም በላይ ኢትዮጵያውያን የላቲንን ባህል እንዲቀበሉ ያስገድዳቸዋል የሚል ሃሳብ አቀረበ።ነገር ግን ፖርቹጋል መንግስት ሃሳቡ የማያዋጣው መሆኑን ስለተረዳ አልተቀበለም።

### 7.11. **አፄ ዘድንግል ዘመነ መንግስት (1597-1607)**

በአፄ ዘድንግል ዘመነ መንግስት በአማራ ሳይንት በኩል እኔ ክርስቶስ ነኝ የሚል ሐሳዌ መሲህ ተነስቶ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገውን በማስመሰል 12 የሐሰት ሐዋርያት፣72 የሐሰት አርድዕት፣36 የሐሰት አንስት (ሴቶች) መርጦ ያሰራጭ ጀመር። በኋላ ግን በንጉሡ ትዕዛዝ ተይዞ ወደ ንጉሡ ፊት ቀርቦ ቢጠየቅ አዎ እኔ ክርስቶስ ነኝ ከድንግል ማርያም ተወልጄ ሞቼ ተነስቼ ወደ ሰማይም ዐርጌ ነበር።ከቤተ እስራኤል በመወለዴ እስራኤል ያልሆኑት ሁሉ ባዕድ አድርጎኝ እንዳይለዩኝ አሁን ደግሞ ከቤተ አህዛብ ከምትሆን ከመርዓተ ወንጌል ተወለድኩ አላቸው።ንጉሡም **‹‹ሰይጣን በሰው እያደረ እንዴት ይጫወትብናል** ብለው በመገረም በሰይፍ እንዲቀጣ አደረጉት።በአፄ ዘድንግል ዘመነ መንግስት **1603 ዓ/ም በአባ ጴጥሮስ ፖኤዝ** የሚመሩ ሌሎች ላቲኖች መጡ።አፄ ዘድንግል ከነዚህ ጋር በመሆን **ከሮማው ፓፓ ቀሌምንጦስ 7ኛ እና ለእስፓኙ ንጉሥ ከፊልጶስ 3ኛ** ጋር የወዳጅነት መስመር ዘረጉ።በመጨረሻም ካቶሊኮችንና ኮፕቶችን እያከራከሩ ሀሳባቸውን ከካቶሊኮቹ ጋር አደረጉ ይባላል።በዚህም ጊዜ ንጉሡ ከጦር መሪው ከደጀ አዝማች ላዕከ ማርያም ጋር ተስማምተው ተዋህዶ ሃይማኖታቸውን ለውጠው ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት ዞረዋል እየተባለ በካህናቱና የምዕመናኑ የተቃውሞ ድምፅ እየበረከተ ሄደ።በዚህ ምክንያት በዚያን ዘመን የነበሩት ከእስክንድሪያ የመጡት ጳጳስ አቡነ ጴጥሮስ **‹‹ለንጉሡ ለዘድንግል የሚታዘዘውን ገዝቻለው** › ብለው መኳንንቱንም ሕዝቡንም አወገዙ።በዚህ ምክንያት አፄ ዘድንግል ከገዛ መኳንንቶቻቸው ጋር ተዋግተው ሞቱ።ከዘድንግል በኋላ አፄ ያዕቆብ 2ኛ ነግሠው ስለነበር ከሱስንዮስ ጋር ጦርነት ገጠሙና ሱስንዮስ አፄ ያዕቆብን በጦርነቱ ገደላቸው።

### 7.12. **አፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግስት (1626)**

አፄ ሱስንዮስ ከመንገሻቸው በፊት ጳጳስ ስለአስገደሉ የቤተ ክህነቱ ሰዎችና እውነተኞቹ ክርስቲያኖች ቂም ይዘውባቸው ስለነበር በነገሡ ጊዜ አልተደሰቱም።አፄ ሱስንዮስም በቤተ ክህነቱና በህዝቡ ዘንድ እንደተጠሉ ያውቁ ነበርና ቅያሜው እየባሰ በሄደ ጊዜ በአጠገባቸው ያሉትን ሚሲዮኖችና የውጭ አገር ሰዎችን ባለሙዋል አደረጉዋቸው፤ለካቶሊክ ሚሲዮኖቹም የራሳቸውን ቤተ ክርስቲያን የሚተክሉበትንና የሚተዳደሩበትን ሰፊ መሬት ከደንቢያ ሰጡዋቸው።ጴጥሮስ ፖኤዝ የሚባለው የካቶሊኮችን አለቃ ከፍሬሞና አስመጥተው በአጠገባቸው አስቀመጡት፤ደንበኛ ሥርዓተ ንግሣቸውን ለማክበር አክሱም ጽዮን በብዙ መኳንንትና ቀሳውስት ታጅበው በሄዱ ጊዜ ጴጥሮስ ፖኤዝንም ስለፍቅሩ ይዘውት ሄደው ነበር።ጴጥሮስ ፖኤዝ የሀገሪቱን የአምልኮት ማቅረቢያ ቋንቋ ግዕዝ በማጥናት በጥበብ ይሰብክና ይቀድስ ነበር።ወደ ንጉሡም እየቀረበ የሮማ ካቶሊክን እምነት ቢቀበሉ የፖርቹጋል መንግስት የጦር መሣሪያ ያስታጥቀውታል እያለ ይሰብካቸው ነበር።ከዚያም እንደተመለሱ **በ1600 ዓ/ም ለእስፓኝና**

**ለፖርቹጋል ንጉሡ ለዶን ፊልጶስና ለሮማው ፓፓ ለጳውሎስ 5ኛ** በጴጥሮስ ፖኤዝ እጅ የጦር መሣሪያ ጥያቄና በውስጡ የካቶሊክ ሃይማኖትን (ዶግማ) በመደገፍ በሮማ ቤተ ክርስቲያን እንተዳደራለን የሚል ጽሑፍ የነበረበት ደብዳቤ ላኩ።ንጉሡ የሮማ ካቶሊክን እንደደገፉ ስላወቁ ሚሲዮናውያን በዋና ዋና መናኸሪያቸው በትግሬ፣በደምቢያ፣በየቤቱ፣በየገበያውና በየልቅሶ ቤት እየዞሩ የካቶሊክን ሃይማኖት ለማስፋፋት ይጥሩ ነበር።ምንም እንኳን ካቶሊክ ሃይማኖትን ደገፉ ተብሎ ቢታሙም ለሰባት ዓመታት ያህል በይፋ አልተጠመቁም።በ1622 ዓ/ም በጴጥሮስ ፖኤዝ እጅ ከነቤተሰቦቻቸው በሮማ ካቶሊክ ሥርዓት ተጠመቁ።ካቶሊክነታቸውን በይፋ አስታወቁ።በዚህ ዓመት ጴጥሮስ ፖኤዝ ሞተ።

በዚህን ጊዜ አልፎንሱ ሜንዴዝ የተባለ የእስፓኝ ተወላጅ በሮማው ፓፓ ጎርጎርዮስ በ1621 ተቀብቶ በየካቲት ወር 1623 ዓ/ም የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ተብሎ ተሰየመ።ሁለት ኤጲስ ቆጳሳት ረዳት ሆነው ተሾሙ አንዱ መንገድ ላይ በህንድ ሲሞት አልፍንሱና አንዱ ኤጲስ ቆጶስ ከ18 ቀሳውስት ጋር ሰኔ 21/1625 ዓ/ም ትግሬ ደረሱ።አፄ ሲስንዮስ ለሮማው ፓፓ ለኡርባን 8ኛ ለሮማ ካቶሊክ መንበር ታማኝ መሆናቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ ላኩ።ይህም የሆነው 1626 ዓ/ም ነው።የካቲት 11/1626 ዓ/ም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በሮም ቤተ ክርስቲያን ሥር እንድትተደዳር የሚል አዋጅ ከሱስንዮስ ቤተ መንግስት ታወጀ።ፓትርያርኩም የኢትዮጵያ ባህልና ሥርዓት በማጣጣልና በማንቋሸሸ የሮማን ግን በማጋነንና በማከባበር አዲስ የፕሮፓጋንዳ ለውጥ አወጁ።ሱስንዮስና አልፎንሱ በመተባበር ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች እንደገና እንዲጠመቁ፣ካህናቱ በሮማውያን ሥርዓት እንደገና እንዲካኑ፣አብያተ ክርስቲያናቱም በሮማውያን እንደገና እንዲባረኩ፣በውስጣቸው ያለው ምስራቃውያን ሥርዓት የተሳለው የቀለም ሥዕል ቀርቶ በሮማውያን ሥርዓት ከድንጋይ የተጠረበ (የተቀረጸ) ምስል እንዲቆም፣የሮማውያን የቅዳሴ ሥርዓትና የቀን መቁጠሪያ በኢትዮጵያ እንዲሠራበት፣ዓርብና ረቡዕ መፆሙ ቀርቶ ቅዳሜ እንዲፆም እና የቅዳሜ ሰንበትነት እንዲሻር የሚል ሕግ አወጡ።ወደ ካቶሊክ እምነት ያልገባና ይህንን ህግ ያላከበረ የአካል ቅጣት ይፈጸምበታል የሚል አዋጅ እንዲታወጅ አልፎንሱ ለንጉሡ አቅርቦ ንጉሡም ተስማሙ።

**አቡነ ስምዖን** ለኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተቆርቋሪ ሆኑትን ክርስቲያኖችን ይዘው ከንጉሡ ጋር ጦርነት ገጠሙ።ንጉሡ የአባቶቻችን ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ለውጠዋልና እርሳቸውን የተከተለ **ውጉዝ ከመ አርዮስ** ብለው አወገዙ።በጦርነቱም ከጳጳሱ ጋር ሆነው አዝማች የነበሩት **ዩልዮስና አባ ዲዮስቆሮስ** ከብዙ ካህናት ጋር በጥይት ተመተው ወደቁ። **አቡነ ጴጥሮስ** በዚህን ጊዜ መስቀላቸውን ጨብጠው በጀግንነት የሃይማኖት ልጆቻቸውን በማደፋፈር ላይ እንዳሉ በጦር ተወግተው ሞቱ ድልም ለሱስንዮስ ሆነ።ከዚህ በኋላ በንዴት የቅዱሳን አጽም ካረፈበት እየወጣ ይቃጠል ጀመር ካህናት መነኮሳትና ምዕመናን ልጅ አዋቂ ሳይባል የተዋህዶ ሃይማኖት ልጅ የሆነ ሁሉ ብዙ ስቃይ ደረሰባቸው።በአጠቃላይ በሱስንዮስ አደባባይ ከ8000 በላይ ሕዝብ ከተለያየ አካባቢ መጥተው ረገፉ።በዚህም የተነሳ ለሰባት ዓመታት ያህል በኢትዮጵያ የሃይማኖት ጦርነት ተደረገ።

የንጉሡ ልጃቸው ፋሲል /አቤቶ/ በዚህ የሃይማኖት ጦርነት ጊዜ በጣም ተቸግረው ነበር።ምንም እንኳ

ከአባታቸው ጋር እየሆኑ ስለሃይማኖታቸው የሸፈቱትን ሰዎች ለመውጋት በአባታቸው ጎን ቢሰለፉም ከጦርነቱ ተመልሰው ወደቤታቸው ሲገቡ ግን የሞቱትን ሰዎች ሬሳና ቁስለኞ በማስመልከት የሕዝቡ የእርስ በርስ መተላለቁ እያሳዘናቸው ነገሩን እንዲያበርዱት አባታቸውን እንዲህ በማለት ይመክሩ ነበር **«የአባቶቻችንን ሃይማኖት በመለወጠዎ ምክንያት ለምን የገዛ ህዝብዎን እርስ በርስ በያስተላልቁታል እያሉ ከአባታቸው ጋር ይጨቃጨቁ ነበር፡፡ አሁንም ተመልሻለሁ ይበሉ፣ህዝቡም ወደ ጥንቱ ሃይማኖት እንዲመለስ አዋጅ ይንገሩት እያሉ ያባብሉዋቸው ነበር /የኢት/ታሪክ ከአፄ ልብነ ድንግል እስከ አፄ ቴዎድሮስ ም.29፣ገጽ 138/** ፡፡ሱስንዮስ በነገሡ በ27ኛው ዓመት ታመው እንደበታቸው ተዘጋ፡፡በዚህ ጊዜ ታሪከ ነገሥት እንደሚለው ልጃቸው ፋሲል /አቤቶ/ ደንግጠው እግዚአብሔር ይህን ደዌ በአባቴ ላይ ያመጣባቸው የክርስቲያኖችን ደም በከንቱ ስላፈሰሱ እና ሃይማኖታቸውን ስለለወጡ ተቀይሞ ይሆናል ሲሉ አባቴ አንደበታቸው ተዘግይቶ ክፉኛ ታመዋልና አትርሱኝ እኔም ያዘዛችሁኝን ሁሉ እፈጽማለሁ **«በጸሎታችሁና በሀዘናችሁ አባቴን እድኑልኝ**›ብለው ወደ ገዳማቱና አድባራቱ መልዕክት አስተላለፈ፡፡በወቅቱ ከሸዋ ተሰደው ሄደው በመተማ አጠገብ አዲስ ገዳም መሥርተው ይኖሩ የነበሩ ዝነኛ አባት አባ አምደ ስላሴ የገዳማቸውን መነኮሳት አስከትለው አፄ ሱስንዮስ ታመው ወደ ነበሩበት በመምጣት ቀን በልዩ ልዩ ጸሎት በሌሊት በሰዓታት ሦስት ሱባኤ በፀሎት በምህላ እግዚአብሔርን ሲለምኑ ቆይተው አጥምቀው ስለአቀረቡዋቸው ንጉሡ የተዘጋ አንደበታቸው ተከፈተ፡፡

በዚህ ጊዜ ለልጃቸው ለአቤቶ **«የእስክንድሪያ ሃይማኖት ትመለስ የሮም ሃይማኖት ትርከስ ፋሲል ይንገሥ** ብለህ አዋጅ አናግር ብሎ ለልጃቸው ለአቤቶ ተናገሩ፡፡አዋጁም ታወጀ ሕዝቡም ተደሰተ ገዳማትና አድባራት የደስታ ደወል አሰሙ በየዋሻውና በየበረሃው በሜንዴንዝ አልፎንሱ የተሰደዱ መምህራንና መነኮሳት መጽሐፎቻቸውን፣ታቦቶቻቸውን እየያዙ ወደ ቦታቸው ተመለሱ፡፡ሃይማኖታቸውን የካዱ ንስሐ እየገቡ ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው እንዲመለሱ ተፈቀደላቸው፡፡አፄ ሱስንዮስም ብዙ አልቆዩም በነገሡ በ28ኛው ዓመታቸው በ1625 ዓ/ም በታህሣሥ ወር ስለአረፉ ልጃቸው አፄ ፋሲል ነገሡ፡፡

### 7.13. አፄ ፋሲል /ፋሲለደስ/ ዘመነ መንግስት 1625

አፄ ፋሲል /ፋሲለደስ/ ሲነግሡና መንግሥታቸው ሲደላደል ሊቃውንቱ በእጨጌ በትረ ጊዮርጊስ መሪነት የብዙ ህዝብ ደም ፈስሶአልና ከሮማዊው ጳጳስ ከአልፎንሱ ጋር ተከራክረን ስለደማቸው እንፋረዳለን አዋጅ ይነገርልን ብለው ተደብቆ ከነበረው ከአልፎንሱ ሜንዴዝ ጋር ለመከራከር ሊቃውንቱ ለአፄ ፋሲል ነገሩዋቸው፡፡ንጉሡም እሺ ብለው አዋጅ አናገሩላቸው፡፡ሊቃውንቱም ከየሀገሩ ተሰበሰቡና ጎንደር የክርክር ጉባኤ ተደረገ፡፡በዚህ ጊዜ ዕጨጌ በትረ ጊዮርጊስ የተማሩ ሊቅ ነበሩና ለሊቃውንቱ አፈ ጉባኤ ሆነው ቆሙ፤ሜንዴዝ አልፎንሱም ወገኖቹን እነፖኤዝን ይዞ ቆመ፤በመጀመሪያ አልፎንሱ ዕጨጌ በትረ ጊዮርጊስን **«የአብ የባህርይ ልጁ ታሞ፣ሞቶ ዓለምን አዳነ የሚል ንባብ ከብሉይና ከሐዲስ ማስረጃ ስጡኝ ብሎ** ጠየቃቸው፡፡ዕጨጌም ጳውሎስ ወደ ሮሜ በጻፈው መልዕክቱ **«እግዚአብሔር ጠላቶቹ ስንሆን በልጁ ሞት አዳነን** ይልብሃል ቢሉት መልስ አጥቶ

ዝም አለ፡፡ቀጥሎም ማሸነፊያ ያገኘ መስሎት  የእግዚአብሔር ፊቱ ወዴት ነው   ብሎ ቢጠይቃቸው በጉባኤው መብራት አብርተው  ይህ መብራት ፊቱ ወዴት ነው  ብለው መልሰው ጠየቁት፤ለዚህም መልስ አላገኘም ዕጨጌም ‹‹የዚህ መብራት ፊት በዚህ ገጽ ነው እንደማይባል የእግዚአብሔርም ፊት በአራቱ ማዕዘን ነው ብለው ረቱት፡፡ይልቁንም **‹‹የእግዚአብሔር ፊቱ ክፉ ወደ ሚሠሩ ሰዎች ነው››**የሚለውን የዳዊትን መዝሙር ጠቅሰው ፊታቸውን ወደ አልፎንሱ አዙረው በጥፊ መቱት ይላል ታሪኩ፡፡በጉባኤውም አልፎንሱ ተረታ አፄ ፋሲልም አልፎንሱ ያደረገውን ሁሉ መግለጽ ለፖርቹጋል ካቶሊክ ፓትርያርክ ጽፈው አልፎንሱ ከሀገር እንዲወጣ አደረጉ፡፡አልፎንሱ ግን አሞኛል ብሎ በሀማሴን ተኝቶ ከጎንደር ተከትለውት ለነበሩት ሁለት ኢትዮጵያውያን የቅብዓትና የፀጋ እምነት አስተማራቸው፡፡ከዚህ ሌላ አልፎንሱ ወደ ህንድ ደርሶ ኢትዮጵያን ለመውረር ያቀረበውን ሃሳብ አፄ ፋሲል ሰምተው ማንም የውጭ ሀገር ዜጋ ያለ እሳቸው ፈቃድ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ ካደረጉ በኋላ የካቶሊክ ጉዞ ጥቂት ዓመታት ጋብ አለ፡፡

አፄ ፋሲል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት የሚያምኑ ክርስቲያንና አባታቸው ባዕድ ሃይማኖትን በመከተላቸው በሕዝቡ ላይ የደረሰበትን መከፋፈልና ስቃይ ስለሚያውቁ በሃይማኖት ሰበብ የሚመጣ ማንኛውም የውጭ ኃይል ከቤተ ክርስቲያን ጎን ሆነው ይከላከሉ ነበር፡፡በተዋህዶዎችና በሮማ ካቶሊክ መካከል በተደረገው ጦርነት የተዋህዶዎች የጦር አበጋዝ ሁነው የዋሉት ብፅዑ አቡነ ስምዖን በጦር ተዋግተው ከሞቱ በኋላ አንድ ግብጻዊ ጳጳስ ነኝ የሚል መጥቶ ሕዝቡን ሲያታልል ጓዳኛው ሌብነቱን ነግሮበት ታስሮ ይኖር ነበር፡፡ኋላም ግን አፄ ፋሲል ወደ ግብጽ ተላልከው አቡነ ማርቆስ የተባሉትን ጳጳስ አስመጡ፡፡የቅባትና የፀጋ እምነት እንደሰደድ እሳት ውስጥ ውስጡን ተያይዞ ስለነበር አዲሱ ጳጳስ እንደመጡ ቅብዓቶች ከተዋሕዶዎች ጋር እንከራከር ቀን ይቀጠርልን ብለው አመለከቱ፡፡በዚህ ጊዜ በሃይማኖት የርስ በርስ መለያየት ተጀመረ፡፡ንጉሡና ጳጳሱ በተገኙበት እንዲከራከሩ ተፈቀደ፡፡በተወሰነው ቀን ከሁለቱም የተወከሉ ሰዎች ክርክሩ ተደርጎ የተዋህዶ ተወካዮች አሸነፉ፡፡የሚሲዮኖቹ ሃሳባቸው እርስ በእርስ አለያይተው ዘወር ለማለት ኋላም እነሱ በዘሩት ልዩነት ወንድማማች ሲጋደሉ ለመሳቅ ከተመቸም አስታራቂ መስሎ ገብቶ አገርን ለመያዝ ስለሆነ ከገላውዴዎስ ዘመነ መንግስት ጀምሮ ባንድነት ሁነው ከውጭ የመጣ የሃይማኖትም ሆነ የሀገር ጠላታቸውን ድል ሲያደርጉ የኖሩ ኢትዮጵያውያን እዚህ በአልፎንሱ ተንኮል በተመረዙ ሁለት ሰዎች ስብከት ተለያይተዋል፡፡የሮማ ሃይማኖት ቅርንጫፍ አዲስ ትምህርት ሆን ተብሎ ሕዝቡን ለማለያየት የተተከለ እሾህ ስለሆነ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ካህናትን ብቻ ሳይሆን ሕዝቡንም ከመንግስት መንግስትንም ከሕዝብ ማለያየቱን ቀጠለ፡፡ኤዎስጣቴዎስ የተባለው ሀገሩ ጎጃም ስለነበር በሀገሩ ጎጃም ቅብዐትን አስፋፍቶ ስለነበር የጎጃም ባላባቶችና ከሊቃውንቱም ብዙዎቹ ቅብዓቶች ነበሩ፡፡ቁርንጭ መናፍቅ ተክለ ሃይማኖትም የፀጋን ሃይማኖት በጎንደር በሸዋ ስላስተማረ ሊቃውንቱ ሁሉ ይተማሙ ነበር፡፡

### 7.14. ቀዳማዊ ዮሐንስ /አዕላፍ ሰገድ  (1660-1674)

በቀዳማዊ ዮሐንስ ወይም አዕላፍ ሰገድ ዘመነ መንግስት ተሰሚነት የነበራቸው ቅባቶች ነበሩ፡፡በልጃቸው በአፄ

በአድያም ሰገድ ኢያሱ ዘመነ መንግስት 1674-1698 ዓ/ም ግን ወደ ቤተመንግስት መግቢያ አላገኙም የሃይማኖት ክርክርም አልተነሳም፡፡

### 7.15. አፄ ተክለ ሃይማኖት ዘመነ መንግስት

በዚህ ዘመን እንደገና ጉባኤ እንዲደረግ ተወሰነና ንጉሡ ጳጳሱ በተገኙበት ጉባኤ ተደረገ፡፡ በዚህ ጉባኤ ላይ ተዋሕዶዎቹ ረቱ፡፡ጳጳሱም አቡነ ማርቆስ ከእንግዲህ ወዲህ ክርስቶስን በቅብዓት የባህርይ ልጅ የሚለውን ሁሉ አወገዛለሁ አሉ ለጉባኤው ከጎጃም ወደ ጎንደር የመጡትን ቅብዓቶች ሁሉ አሠሩአቸው፡፡

### 7.16. አፄ ቴዎፍሎስ ዘመነ መንግስት

አፄ ቴዎፍሎስ እንደ አባታቻቸው ጉባኤ ሠርተው ክርክር ሳይሰሙ ክርስቶስ በቅብዓት የባህርይ ልጅ ነው የሚል አዋጅ አወጁ፡፡በዚህም ምክንያት የውስጥ ለውስጥ ትርምስና በንጉሡም ላይ ጥላቻ ተፈጠረ፡፡

### 7.17. አፄ ዮስጦስ ዘመነ መንግስት

በውስጥ ያለው ብጥብጥ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ በ1714 ዓ/ም አፄ ዮስጦስ የጦር መሣሪያ እንዲያቀብሏቸው ሦስት የካቶሊክ ሚሲዮኖችን በወልቃይት ዐይነ እግዚእ በሚባል ቦታ በድብቅ አስቀምጠው ይማከሩ ኑሮ እሳቸው ከሞቱ በኋላ ምስጢር ተገለጠ፡፡ሰዎቹም የመጡት አንዱ ከኦስትሪያ ሁለቱ ከሮም ነበር ስማቸውም ሚካኤል፣ሳሙኤል እና ዳዊት ይባሉ ነበር፡፡

### 7.18. አፄ ዳዊት አብራክ ሰገድ ዘመነ መንግስት (1717 ዓ/ም)

አፄ ዳዊት አብራክ ሰገድ ሲነግሱ እነ አባ መዝሙረ የተባሉ ከላይ በተጠቀሱ ሚሲዮኖችና በአፄ ዮስጢኖስ መካከል ስለነበረው የውስጥ ግንኙነት የተደበቀውን ምስጢር አውጥተው የተደበቁት ሚሲዮኖች ይቅረቡልን ብለው አቤቱታ አቀረቡ፡፡ጉዳዩን ለመስማት በተሰበሰበው ጉባኤ መካከል ቀርበው ሃይማኖታቸውን ሲጠየቁ ካቶሊክ መሆናቸውን አረጋገጡ፡፡በዚህን ጊዜ የተሰበሰቡ ሊቃውንትና የሃይማኖት ሰዎች በሱስንዮስ ዘመን ብዙ ደም ያፈሰሱት ወገኖች አይደሉምን በማለት ይሙት ፍርድ ፈረዱባቸው፤ወዲያውም የሞት ቅጣት ተፈጸባቸው፡፡እነዚህ ከተገደሉ በኋላ ቅብዓቶች ከተዋሕዶዎች ጋር ለመከራከር ጉባኤ እንዲደረግላቸው ንጉሡን ጠየቋቸው፡፡ንጉሡም ፈቀዱ የንጉሡ ቢትወደድ ዘጊዮርጊስ የሚባል ቅባት ስለነበር ንጉሡ ጉባኤው ላይ እንዲገኙ ስለአዘዙ ተዋሕዶዎች አልተቀበሉትም፡፡ንጉሡ ራሳቸውን ከሀሜት ለማዳን ሲሉ ጉዳዩ የሃይማኖት እንጂ አስተዳደርን የሚመለከት ስላልሆነ ወደ ንጉሥ መቅረብ የለበትም በጳጳሱ መታየት አለበት ብለው ወደ ጳጳሱ አቡነ ክርስቶዶሉ /ገብረ ማርያም/ መሩት፡፡ጳጳሱም እንደቀደሙት አባቶች ቆራጥ ሳይሆን አድር ባይነት ያጠቃቸው ስለነበረ የንጉሡን ዝንባሌ ተመልክተው **‹‹ሃይማኖትዎ ምንድነው ተብለው ቢጠየቁ ሃይማኖቴ ተዋህዶ ነው** በማለት ፈንታ ሃይማኖቴ ከኔ በፊት እንደነበሩት እንደ አባ ማርቆስና እንደ አባ ሲኖዳ ነው ብለው መለሱ፡፡በዚህ ጊዜ ቅባቶች በቢትወደዱ

ዘጊዮርጊስ አቅራቢነት ወደ ንጉሡ ቀርበው ጳጳሱ የተናገሩትን ነገሯቸው።ንጉሡም የአባ ማርቆስና ሲኖዳ ሃይማኖታቸው ምን ነበር አሏቸው እነሱም ቅብዓት ነው ብለው በድፍረት ተናገሩ።ንጉሡም እንግዲያውማ በተዋህዶ የባህርይ ልጅ የሚሉት ተረቱ፣በቅብዓት መንፈስ ቅዱስ የባህርይ አምላክ ሆነ የሚሉት ረቱ ብላችሁ አዋጅ ንገሩ አሉ አዋጁም ተነገረ።የተዋህዶ ወገኖች በጳጳሱ መልስና በአዋጁ አዝነው ጳጳሱን ብቻቸው ባሉበት ቢጠይቋቸው ሃይማኖቴ ተዋህዶ ነው አሏቸው።በዚህ መልስ ደስ ብሏቸው ተሰብስበው ንሴብሖ እያሉ ሲዘምሩ ንጉሡ ወሬ ደርሶቸው አዋጁን ጥሰዋል ብለው ተናደዱ።ንዴታቸውንም ለመወጣት በጎንደር አካባቢ የሚኖሩ ጀዊ የሚባሉትን እስላሞችና የአረማውያን ክፍሎች አስታጥቀው በተሰበሰቡበት ቤት አንድ ስንኳ ሳያተርፉ ፈጁዋቸው።በዘመኑ የነበሩት እጨጌ ተክለ ሃይማኖትንም እግራቸውን ከከብት ጭራ ጋር አስረው መሬት ለመሬት ራቁታቸውን እየጎተቱ አውለው ገደሏቸው።በዚህን ጊዜ በአልፎንሱና በሱስንዮስ ጊዜ ከተፈጸመው ግፍ የማያንስ ግፍ ተፈጽሟል።

## ክምዕራፍ ስድስት ፍል ስምንት

## ከዘመነ መሳፍንት እስካሁን  (1769-2009)

ዘመነ መሳፍንት ኢትዮጵያ በመሳፍንት አገዛዝ እንደቅርጫ ሥጋ የተከፋፈለችበት ዘመን በመሆኑ ቤተ ክርስቲያን እየተዳከመች የሄደችበት ጊዜ ነው።በዚህ ዘመን ነገሥታቱን ለምስል አንግሠው ሀገሪቱን በአምባገነንነት ሲመሩ የነበሩ መሳፍንትና መኳንንት እርስ በርሳቸው ስለማይስማሙ አንዱ ሌላውን ለማጥፋት ከውጭ ሀገር መሣሪያ ለማስገባት በሚሲዮኖቹ አማካይነት ወደ የመንግስታቱ ይላላኩ ስለነበር አጋጣሚውን ተጠቅመው ሚሲዮኖቹ ሃይማኖታቸውን ለማሰራጨት አመቺ ጊዜ ሆነላቸው።በሰሜኑ ክፍል በተለይም ኤርትራ ብዙ ክርስቲያኖች ለብዙ ዓመታት ካህናትና የሃይማኖት መምህራን ባለማግኘታቸው የእስላም ወረራ በመጣባቸው ጊዜ ወደ እስልምና የሄዱበትና ሌሎችም ንዋያተ ቅድሳትን ተሸክመው በረሃ ለበረሃ በመዞር ሃይማኖታቸውን እንደጠበቁ በታሪክ ይታወቃል።በዚህም ምክንያት በኋላ አባቶች አልፎ ልጆች ሲተኩ ወደ እስልምና ሃይማኖት ተሳቡ የራሳቸውን ባህል ስላጡት የቱርኮችንና የዓረቦችን ባህል ተሸከሙ።በደቡባዊና በምዕራብ የነበረው የክርስትና ታሪክ በሰሜን ከነበረው የማያንስ ነበር አሁን ግን ሁሉንም አረም ውጦት ተገኘ።

ስለደቡብ ክርስትና ታሪክ ሲወሳ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የመጀመሪያው ሐዋርያዊ ጉዞአቸውን በ13ኛው መ/ክ/ዘመን ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ አድርገው ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እና ገዳማት ማሳነፃቸውንና መመስራታቸውን ገድላቸው ይነግረናል።ተልዕኮአቸውንም ፈጽመው በደብረ ሊባኖስ ገዳማቸው በተወሰኑ ጊዜም በመላው ኢትዮጵያ 12 ደቀ መዛሙርቶቻቸውን አሰማርተዋቸዋል።በክርስትናቸው የጸኑትም እስከ አራት ትውልድ ድረስ ካህን አይተው ስለማያውቁ አጽዋማትና በዓላትን ሳይቀር ባህረ ሀሳብ ሳይኖራቸው ራሳቸው በልማድ ያወጧቸው ነበር።በካህን ማጣት ምክንያት ብዙዎች ክርስቲያኖች እምነት እንጂ ጥምቀት አልነበራቸውም።በዚህ ሳቢያ ከዓረብና ከሱዳን ነጋዴዎች ጋር ወዳጅነት በመፍጠራቸው ምክንያት የእስልምና ሃይማኖትን ያለምንም ችግር ተቀበሉ።ብሔራዊና

ክርስቲያናዊ ስማቸውንም ትተው በአረብ ስም መጠራት ጀመሩ፣በወንጌል ፈንታም ትምህርቱ ቁርዓን ሆነ።

በዚህ ጨለማ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ስትቸገር በመከራዋ ላይ መከራ ለመጨመር በመሀል ሀገር ያለውን ክርስቲያን ለመከፋፈል በ1831-1847 ዓ/ም ድረስ የሮማ ፓፓ ጎርጎርዮስ የላቲን ሚሲዮኖችን በብዛት ላከባት።በኋላም ጉግልዬልም ሞሳላ የተባለ ካቶሊክ በከፋና በአንዳንድ በደቡብ ኢትዮጵያ ግዛቶች እየተዘዋወረ ክርስቲያኑን የሚለያይ ትምህርት ያስተምር ጀመር ነገር ግን ሕዝቡ አልተቀበለውም።በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በኢየሩሳሌም ጥንት በጎልጎታ ውስጥ የነበሩንን አያሌ ቦታዎች የተነጠየቅነው በዚህ በዘመነ መሳፍንት ነው።የታሪክ ይዞታ ካላቸው ግሪክ፣አርመን፣ኢትዮጵያ፣ሶርያና ግብጽ መካከል ኢትዮጵያ ከዚህ ተለይታለች።በየዓመቱ ለትንሳኤ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም ይደረግ የነበረ ጉዞም ተቋረጠ።በኢየሩሳሌም ገዳም ውስጥ የነበሩ መነኮሳትም በችግርና በህመም አለቁ።

በ1830 ዓ/ም የነበሩት አቡነ ቁርሎስ ከሞቱ ወዲህ በኢትዮጵያ ጳጳስ ስላልነበረ በ1834 የመጡ ጳጳስ አቡነ ሰላማ የቅብዓትና የፀጋ ክፍሎችን እያወገዙ የተዋህዶ እምነትን ሲያስተምሩ ብዙ ብጥብጥ ተነሳ በጳጳሱና በተዋህዶቹ ላይ ያደሙ ጀመር።አቡነ ሰላማ የተዋህዶዎቹን ሊቃውንት አስከትለው ወደ ትግሬ ተሰደዱ።ያን ጊዜ ትግሬን የሚገዙት ደጃዝማች ውቤ በፀጋነት ይታሙ ስለነበር አቡነ ሰላማ ዕረፍት አጥተው ደጃ ዝማች ካሳ (ቴዎድሮስ) በሃይማኖት ፍፁም የተዋህዶ ልጅ መሆናቸውን ሰምተው አብረዋቸው የነበሩ ሊቃውንት በማስከተል ወደ ደጃዝማች ካሳ በመምጣት ኢትዮጵያን አንድ ማደረግ የሚቻለው አንድ ሃይማኖት ብቻ ሲኖር መሆኑን ጧት ማታ ይነግሩዋቸውና ጠቃሚ ምክር ይመክሩዋቸው ነበር።ደጃ ዝማች ካሳም ምክራቸው ደስ ስላላቸው የተዋህዶ ሃይማኖት ዶግማ በጽሑፍ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ጠየቋቸው።አቡነ ሰላማም አብራርተው አቀረቡ።ደጃ ዝማች ካሳም ይህንን የአቡኑን እምነት ያልተቀበለ ከፍ ብሎ አንገቱን ዝቅ ብሎ ባቱን ይቀጣል ብለው አዋጁን አፀደቁ።በዚህ አዋጅ መሠረት በ1846 ዓ/ም የካቶሊክ ሚሲዮንን ሲመራ የነበረ ያዕቆብ የተባለ ኢጣሊያዊ በምፁዋ በኩል ኢትዮጵያን ለቆ እንዲወጣ ተደረገ።የቅብዓት እምነት ተከታይ የነበሩ አባ ገብረ ሚካኤል የተባለ መነኩሴም በእስራት እንዲቀጡ ተደረገ።

### 8.1. ዳግማዊ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት (1845-1863)

ከ1845-1863 ዓ/ም አፄ ቴዎድሮስ 2ኛ እስከ ነገሡበት ጊዜ ድረስ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ጎንደር ነበረች።በ1847 የካቲት ደጃ ዝማች ካሳ በአቡነ ሰላማ እጅ ተቀብተው ዳግማዊ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ነገሡ።አፄ ቴዎድሮስ መንግታቸውን ለማሳደግ የነበራቸው ጥበብ በጣም የላቀ ነበር፤በውጭ አስተዳደራቸው ኢትዮጵያ በዓለም እንድትታወቅ አድርገዋል።ነገሡ በነገሡ በ5 ዓመት በ1862 ዓ/ም በጥቅምት ወር የእስክንድሪያው ፓትርያርክ አባ ቁርሎስ 4ኛ የመጀመሪያው የፓትርያርካዊ ጉብኝት ለማድረግ ወደ ኢትዮጵያ መጡ።የመጡበትም ምክንያት

1. ከኢትዮጵያን ወደ እስክንድሪያ የሄዱት ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን ያዩላቸውና ይባርኩላቸው ዘንድ ለምነዋቸው ስለነበር ኢትዮጵያን አይተውና ባርከው ለመመለስ፤

2. አፄ ቴዎድሮስ ከቱርኮች ጋር ተጣልተው ስለነበር ለማስታረቅ

3. በካይሮ ያለውን የቅዱስ ማርቆስ ካቴድራል ለማሳደስ አስበው ስለነበር እርዳታ ለመጠየቅ ነበር ይባላል። ወደ ኢትዮጵያ ሲደርሱ ታላቅ አቀባበል ተደርጎላቸዋል።በውይይቱም ወቅት አፄ ቴዎድሮስ ሌላውን ሁሉ ጥያቄ በደስታ ሲቀበሉ ከቱርክ መንግስት ጋር እርቅን ያድርጉ የሚለው የፓትርያርኩ ጥያቄ አፄ ቴዎድሮስን ስለአስቆጣቸው አልተቀበሉትም፤እንዲያውም ፓትርያርኩ የሃይማኖት አባት ሆነው እንዴት ለቱርኮች አማላጅ ሆኑ በማለት በፓትርያርኩ ላይ ጥርጣሬ አደረባቸው፤በዚህ ምክንያት ፓትርያርኩን እስር ቤት አስገበዋቸው ግን የቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ እንዳይጎድፍ ብለው መኳንንቱ መሳፍንቱ መክረው ዘክረው ለንጉሠ ነገሥቱ ሀሳብ በማቅረብ አፄ ቴዎድሮስ ፓትርያርኩን ከእስራት ፈትተው ለካቴድራሉ ማሠሪያ የሚሆን ብዙ ወርቅና የዝሆን ጥርስ ሰጥተው ወደ ሀገራቸው መልሰዋቸዋል።**አፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን ከተዋህዶ ሃይማኖት ተዋህዶ ሃይማኖትን ከኢትዮጵያ ነጥለው የማያዩ ሃይማኖታዊና ብሔራዊ መሪ ነበሩ**።በዘመናቸው በኢትዮጵያ የነበሩትን ሚሲዮናውያንን ሁሉ ሰብስበው ኢትዮጵያ የራሷ የወንጌል መምህራን አሏት ይልቁንስ እናንተ የሰለጠናችሁበትን ለእኛም የሚያስፈልጉንን ብረት ማቅለትና መቀጥቀጥ (ቴክኖሎጂ) አስተምሩን ብሏቸው ነበር ይባላል።ነገር ግን በጊዜው አፄ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያም ሆነ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያሰቡት ከግብ እንዳይደርስ በዙሪያቸው የነበሩት ኢትዮጵያውያን ሹማምንት ሁሉ ለሀገር ግንባታ ዕድገት አላማ ሁሉም ተባባሪዎች ባለመሆናቸው በተላይም የካቶሊክ እምነት ተከታይ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ከኢጣሊያና ከፈረንሳይ መንግስት ወኪሎች ጋር እየተመሳጠሩ ሀገራቸውን ለማልማት የያዙት ትግላቸው ፍፃሜ እንዳያገኝ ያውኳቸው ነበር።አፄ ቴዎድሮስ በዘመናቸው የቱርክ መንግስትን ከኢየሩሳሌም ለማስወጣት የማያወላወል ሀሳብ ነበራቸው።በተለይም 1863 ዓ/ም በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ይዞታ የነበሩትን ሁሉ የቱርክ መንግስት ለሌሎች አብያተ ክርስቲያናት በመስጠቱ ተናደው ስለነበር በቱርክ ላይ ለመዝመት ቁርጥ ሀሳብ አድርገው የጦር መሣሪያ ጥያቄ የእንግልዝ ንግሥት ለነበረችው ለቪክቶሪያ መልዕክት ልከው ነበር።ነገር ግን የእንግልዝ መንግስት ከቱርክ ጋር የጦር ቃል ኪዳን ስለነበራቸው ጥያቄያቸው መልስ አላገኘም።በዚህ ምክንያት አፄ ቴዎድሮስ ከእንግልዝ መንግስት ጋር ተጣሉ።በኢትዮጵያ ታሪክ እንደምናውቀው ከሞትም ያደረሳቸው የዚሁ ጠንቅ ነው።አፄ ቴዎድሮስ በመሳፍንት የተከፋፈለች ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግስትና የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመፍጠር ለ15 ዓመት ከጣሩ በኋላ ከእንግሊዞች ጋር በተፈጠረው አለመግባባት ሽጉጣቸውን ጠጥተው አረፉ።

ይሁንና ከ4ኛው መ/ክ/ ዘመን ጀምሮ እስከ 17ኛው መ/ክ/ዘመን ፍጻሜ ድረስ ማለት በእነ አብርሃ ወአጽብሃ፣በአፄ ካሌብ፣በእነ አፄ ገብረ መስቀል፣በእነ ቅዱስ ሀርቤ /ገብረ ማርያም/፣በእነ ቅዱስ ላልበላ፣በእነ አፄ ይኩኖ አምላክ፤በእነ ቀዳማዊ አፄ ዳዊት፣በእነ አፄ ዘርዐ ያዕቆብ፣በእነ አፄ ናኦድ፣በእነ አፄ ገላውድዎስ፣በእነ አፄ ሰርፀ

ድንግል፣በእነ አፄፋሲልና በመሳሰሉት ዘመነ መንግስት እንደነበረው ሁሉ ከአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት ጀምሮም እስከ 20ኛው መ/ክ/ዘመን አፄ ምኒልክ፣በንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱ፣በግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ቤተ መንግስቱና ቤተ ክህነቱ በሀዘኑም፣በደስታውም፣በሞት በሕይወቱም አንድ ሁነው ያስተዳደሩበት፣የሠሩበት ጥሩ ጊዜ የነበረ መሆኑንና  በነዚህ ዘመናት የሀገራችንና የቤተ ክርስቲያችን የአስተዳደር ዕድገት በበለጠ ጎልቶ የታየበት ጊዜ እንደነበር ታሪክ ይነግረናል።

### 8.2. አፄ ዮሐንስ 4ኛ ዘመነ መንግስት  1863

አፄ ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ የነገሡ አፄ ዮሐንስ 4ኛ እንደ አፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ ይመኙ ስለነበር ከውጭ በሚመጡ ሚሲዮኖች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ያደርጉ ነበር።ወንጌልን በሰፊው ለማስተማር እንዲያመችና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በራሷ ልጆች እንድትመራ፣እንድትባረክና እንድትቀደስ በ11ኛው መቶ ዓመት በንጉሥ ሀርቤ ዘመነ መንግስት ተጠይቆ ሳይሳካ የቀረውን ጥያቄ እንደገና በማንሳት ኢትዮጵያውያን ቆሞሳት፣ኤጲስ ቆጶሳት ሆነው እንዲሾሙላቸው በዘመኑ የነበሩትን እስክንድሪያው ፓትርያርክ ቄርሎስ 5ኛን ጠይቀው ነበር።ነገር ግን ጥያቄያቸው መልስ ስላላገኘ ስለጉዳዩ ቁስጥንጥያ ከሚገኘው ከአርመኑ ፓትርያርክ ጋር መጻጻፍ ጀምረው እንደነበር ታሪክ ይነግረናል።ቀጥሎም ከእንደገና ኢትዮጵያውያኑ ፈንታ ግብጻውያን ኤጲስ ቆጶሳት በብዛት እንዲላኩላቸው የእስክድሪያውን ፓትርያርክ በድጋሚ ጠይቀው አራት ግብጻውያን ኤጲስ ቆጶሳትን የላኩላቸው መሆኑ ይታወቃል። እነሱም **አቡነ ዮሐንስ፣አቡነ ጴጥሮስ፣አቡነ ሉቃስና አቡነ ማቴዎስ** የሚባሉ ናቸው።አፄ ዮሐንስ ሀገሪቱ በሚሲዮናውያን እንዳትከፋፈል ካላቸው ጥረት የተነሳ ከዕለታት በአንድ ቀን ሚሲዮናውያንን ከነመሪዎቻቸው ጠርተው ምን ልታደርጉ መጣችሁ ብለው ጠየቋቸው።እነሱም ወንጌል ልንሰብክ ነው ብለው መለሱ፣ንጉሡም ወንጌል አንድ ነው፣እግዚአብሔርም አንድ ነው፣እኔም ለሀገረ ወንጌል ለመስበክ የሚበቁ ጳጳሳትና ቀሳውስት አሉኝ ለማን ለመስበክ ትፈልጋላችሁ አሏቸው።እነሱም በዚህ ሀገር ለሚኖሩ ይሁዲዎችና እስላሞች ብለው መለሱላቸው።ንጉሡም ወደ ኢትዮጵያ ስትመጡ የአይሁድን ሀገር ኢየሩሳሌምን የእስላሙን ሀገር ግብጽን ሊቢያን ሰዑዲ አረቢያንን የመንን እንደምን አልፋችሁ መጣችሁ።አሁንም እኔ የሀገሬን ሕዝብ የእጅ ሥራ ጥበብ የሚያስተምሩ እቀበላለሁ እንጂ እናንተን አልፈልግምና ሀገሬን ልቀቁልኝ ብለው በምፅዋና በመተማ በኩል አስወጧቸው።

አፄ ዮሐንስ በዘመናቸው ኢትዮጵያ በሚሲዮናውያን እንዳትከፋፈል ካደረጉት ጥረት ባሻገር በግራኝ ወረራ የተጎዱ አብያተ ክርስቲያናት ለምሳሌ ደብረ ሊባኖስ ገዳም፣በኢየሩሳሌም ደብረ ገነት ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን አሠርቷል።የወሎ ባላባት የነበሩ **መሐመድ አሊን ሚካኤል** በሚል ስያሜ ራሳቸው ክርስትና አባት ሆነው እንዲጠመቁ በማድረግ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውለታ አድርገዋል።የቅብዓትና የፀጋ እምነት የተዳከመው በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግስት ነው።የአፄ ዮሐንስ በዘመነ መንግስታቸው የግብጽና የሊብያ፣የሱዳንና የኢትዮጵያ እስላሞች ግንባር ፈጥረው   ደርቡሽ   በሚል ስም አንድ ሆነው ሦስት ጊዜ ዘምተው ተዋግተዋቸው ሁለት ጊዜ አፄ ዮሐንስ

ድል አድርገው ከአባረሩዋቸው በኋላ በሦስተኛው እንደገና ተመልሰው በጎንደርና በትግራይ ያሉትን ሊቃውንት አርደው አብያተ ክርስቲያናትን አቃጥለው ብዙ ግፍ ማድረሳቸውን ስለሰሙ መተማ ላይ ጦርነት ገጥመው በሰማዕትነት አርፈዋል፡፡የኢትዮጵያን ድንበር አልፈው ምዕመናንን ሲያሰቃዩና አብያተ ክርስቲያናትን ሲያፈርሱ ከነበሩ የሱዳን ማህዲስቶች /ደርቡሾች/ ጋር በመተማ ሲዋጉ በጀግንነት አረፉ፡፡

### 8.3.አፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት (1882-1906)

ዳግማዊ ምኒልክ የሸዋ ንጉሥ ሆነው ከ1858-1881 ዓ/ም ለ23 ዓመታት ሲመሩ ቆይተው አፄ ዮሐንስ ሲሞቱ ከ1882-1906 ዓ/ም የመላው ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆኑ፡፡አፄ ምኒልክ አንዳንድ የኢትዮጵያ ክፍሎች ሲቀሯቸው የዛሬይቱን ኢትዮጵያ ወሰን ከልለው ያስረከቡን መሪ ናቸው፡፡በዘመናቸው ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ አስተዋጽዖ አበርክተዋል፡፡ከነዚህም መካከል ለአያሌ አብያተ ክርስቲያናት የመተዳደሪያ ርስት እንዲተከልና ለቀሳውስትና ለዳያቆናት ሰፊ መሬት እንዲሰጣቸው ማድረግ፣በመሳፍንት የተከፋፈለች ኢትዮጵያን አንድ ለማደረግ የቴዎድሮስና የአፄ ዮሐንስን ዓላማ በመከተል የደቡብ ኢትዮጵያ ግዛት ሲያስሱ ከግራኝ ወረራ ጀምሮ በካቶሊካውያንና በመሳፍንት መከፋፈል ዘመን ጠፍተው የነበሩ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት እንዲታደሱ ማድረግ፣በኢየሩሳሌም የዴር ሱልጣን ገዳማትን ከግብጽ ጋር በነበረው ድርድር የኢትዮጵያ መነኮሳት መውጫ መግቢያ አጥተው ተቸግረው ስለነበር ወደ ቱርክ መንግስት መልዕክተኛ ልከው የዴር ሱልጣን በር እንዲከፈት አድርገዋል፤ሀገሪቱን በትራንስፖርት፣በመገነኛ ብዙሃን፣በጀግንነትና በታሪክ የበለጸገች እንድትሆን ትልቅ ድልድይ ያበጁ መሪ ናቸው፡፡ለውጭ ወራሪ /ለፋሽስት ኢጣሊያ እጅ አልሰጥም ሀገሬን አላስደፍርም በማለትም አድዋው ጦርነት የድል ባለቤትነት ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ናቸው፡፡ይህ ሁሉ ሲሆን ከውጭ ወደ ሀገራችን በሚገቡ ሚሲዮኖች ላይ ግን የሚደረግ ቁጥጥር ስላልነበረ በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግስት የተባረሩት ሚሲዮኖች ሁሉ እየተመለሱ መጡ፡፡

### 8.4. ንግስት ዘውዲቱ ዘመነ መንግስት (1909-1922)

በንግሥት ዘውዲቱ ዘመነ መንግስት ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ መልኩ ተለውጦ ዘመናዊ አስተዳደር የተጀመረበ ዘመን ነው፡፡መስከረም 4/1919 ዓ/ም የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጉባኤ ተመሠረተ፡፡በንጉሥ ሀርቤና በአፄ ዮሐንስ የተጀመረው ኢትዮጵያ የራሷን ልጆች ጳጳስ መሾም አለባት የሚለው ጥያቄ ፍፃሜን ያገኘው በንግሥት ዘውዲቱ ዘመነ መንግስት ነው፡፡ግብጻው የኢትዮጵያ ጳጳስ አቡነ ማቴዎስ ከሞቱ በኋላ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከራሷ ልጆች ጳጳስ መሾም አለባት የሚል ጥያቄ ወደ እስክንድሪያ /ኮፕቶች/ ቀርቦ በኢትዮጵያና በኮፕቶች መካከል ለሦስት ዓመታት ያህል ውይይት ከተደረገ በኋላ ግንቦት 18/1921 ዓ/ም አራት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ካይሮ ላይ ተሾሙ፡፡እነሱም

1. አቡነ አብርሃም------------------መምህር ደስታ

2. አቡነ ይስሐቅ-------------------መምህር ወልደ ኪዳን

3. አቡነ ጴጥሮስ--------------------መምህር ኃይለ ማርያም

4. አቡነ ሚካኤል------------------መምህር ኃይለ ሚካኤል ሲሆኑ አቡነ ቄርሎስ የተባሉ ግብጻዊ ሊቀ ጳጳስ አብረው ተሹመው መጥቷል።በዓመቱ በ1922 ዓ/ም 19ኛው የእስክንድሪያ ፓትርያርክ አባ ዮሐንስ ኢትዮጵያን በመጎብኘት ላይ እንዳሉ የደብረ ሊባኖስ እጨጌ የነበሩትን ገብረ መንፈስ ቅዱስን ጥር 1/1922 ዓ/ም አዲስ አበባ በዓታ ለማርያም ቤተክርስቲያን አቡነ ሳዊሮስ ብለው ሾሟዋቸል።ይሁን እንጂ ሊቀ ጳጳሳት ሁነው የሚመሩት ግን የግብጹ ሊቀ ጳጳስ ነበሩ።

### 8.5. ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ (1922-1966)

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እንደሌሎች ነገሥታት ሁሉ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን በርካታ መልካም ሥራ ሠርቷል።በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት መመራት በጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ ከኢትዮጵያ አስተዳደር ውጭ የነበረችውን የኤርትራ ግዛትን በመጀመሪያ በፌዴሬሽን ቀጥሎ  በሕዝቡ ፍላጎትና ሙሉ ድምፅ ከእናት ሀገርዋ ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል አድርጓል።በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጉዞ ላይም ታላቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል በርካታ አብያተ ክረስቲያናት አንጽዋል።አድባራትና ገዳማት እንዲስፋፉ ጥረት አድርገዋል።ከዚህም በተጨማሪ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለ1600 ዓመታት የጵጵስና መብት ተነፍጋ የቆየችበትን ዘመናት በመመርመር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የራሷን አባቶች በራሷ ቤተ ክርስቲያን እንድትሾም የምትችልበትን ደረጃ አስይዘዋል።በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ አራት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ሲሾሙ በ1940 ዓ/ም አምስት ኢትዮጵያውያን አበው ቆሞሳት ተመርጠው ጵጵስና እንዲሾሙ በመጠየቁ በቤተ ክርስቲያኒቱና በእስክንድሪያው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ መካካል ብዙ መጻጻፍና ውጣ ውረድ ተደርጎ በመጨረሻም የስምምነቱ ሐሳብ እንድታወቅ ሐምሌ 13/1940 ዓ/ም በአዲስ አበባ ታላቅ ጉባኤ ተካሄደ።በጉባኤውም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንና በእስክንድሪያ ቤተ ክርስቲያን መካከል የነበረው አለመግባባት ተወግዶ ወደ ፍጻሜ በመድረሱ አምስቱ ተመራጮች አበው ሐምሌ 16/1940 ዓ/ም ወደ እስክንድሪያው ፓትርያርክ በመሄድ ጵጵስና ተሹመዋል።እነሱም

1. እጨጌ ገብረ ኢየሱስ-----------------ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ

2. መምህር ገሪማ------------------------ብፁዕ አቡነ ሚካኤል

3. ሊቀ ሥልጣናት መልዕክቱ------------ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ

4. መምህር ዘርፈ ብርሃን-----------------ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ

5. መምህር ጌታሁን------------------------ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ ናቸው።

እነዚህ አምስት ጳጳሳት በተሾሙ በ8ኛው ዓመት ኢትዮጵያ በግፈኛው ፋሽስት ተወረረች።ሞሶሎኒ ኢትዮጵያን ከፋፍሎ ለመግዛት ባደረገው ዘመቻ በ1929 ዓ/ም በሊቢያ ዋና ከተማ በትሪፖሊ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ለማፈራረስና ክርስቲያኖችንም ለመፍጀት የሚገልጥ አዋጅ ተነገረ።አዋጁም **የፋሽስት ጣሊያን በሊቢያና በኢትዮጵያ ለሚኖሩ እስላሞች የሰላም ዋስትና ለመስጠት አስቧል።ትክክለኛ ፍትሕና ብልጽግናም ለእስላሞች ያደርጋል የነቢዩ መሐመድንም ህግ ያስከብራል፣ከዚህም በላይ ለመላው ዓለም እስላሞች ያለውን ቅንና መልካም አስተሳሰብ ሊገልጥ ይወዳል** ›የሚል ነበር።ሞሶሎኒ አዋጁን በሥራ ላይ ለማዋል ከሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በተደረገለት ርዳታ የራያንና የሶማሊያን እስላሞች አስነስተው የብዙ ክርስቲያኖች ደም አፈሰሰ በሴት፣በህፃንና በሽማግሌ ሳይቀር የኢትዮጵያ ክርስቲያን ሁሉ ላይ ግፍ ተፈፀመ።ብዙ ገዳማትንና አድባራትን አፈራረሰ፣ኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከብዙ ጠላት እየተከላከለች ያቆየቻቸውን የታሪክና የሃይማኖት ቅርሶቿን ዘርፎ ወስዶ ለቫቲካን አስረከበ።በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ስታስቲክስ ክፍል እንደዘገበው 2000 አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ተቃጥለው ከጥቅም ውጭ ሆነዋል።በአርበኝነት ለሃይማኖታቸውና ለሀገራቸው ክብር ሲሉ ከኢጣሊያ ጋር ፊት ለፊት ተዋግተው የሞቱትን የተዋህዶ ልጆች ክርስቲያኖች ሳይጨምር በአድባራትና በገዳማቱ፣በደብረ ሊባኖስ፣በላሊበላ፣በአክሱም፣በጎንደርና በዝቋላ ብዙ ባህታውያንና መነኮሳት ለሃይማኖታቸውና ለሀገራቸው ክብር መስዋዕት ሆነዋል።

ከጳጳሳት ታሪካቸው ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መመኪያ የሆኑ የምስራቅ ኢትዮጵያ **ሊቀ ጳጳስ አቡነ ጴጥሮስ ቀዳማዊ እና የሸሬ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ሚካኤል በፋሽስት ጣሊያን** ተገለዋል።አቡነ ጴጥሮስ ወደሚገደሉበት ሲወሰዱና ወደ ቦታው ሲደርሱ አካባቢውን በአራቱ ማዕዘን ከባረኩ በኋላ በሕዝቡ ፊት ቆመው እንዲህ አሉ።**‹‹ፋሽስቶች የሀገራችንን ሕዝብ ሽፍታ ቢሏችሁ እውነት አይምሰላችሁ ሽፍታ ማለት ያለሀገሩ መጥቶ የሰውን ርስትና ሀብት የሚቀማ አብያተ ክርስቲያናትን የሚያቃጥል ደም የሚያፈስ ይህ ሁሉ በመካከላችሁ የቆመው አረመኔ የኢጣሊያ ፋሽስት ነው።የኢትዮጵያ ሕዝብ ለእርሱ እንዳይገዛ ውጉዝ ነው።የኢትዮጵያ መሬትም እንዳትቀበለው ውጉዝ ትሁን** ብለው ተናገሩ።ከንግግራቸው በኋላም የጠላት ጦር በመትርየስ ተኲሶ ገደላቸው።እዚህ ላይ ለቤተ ክርስቲያን ታሪክ አስከፊና አሳፋሪ ሆኖ የሚታየው የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመደምሰስ ቫቲካን ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ከሞሶሎኒ ጋር መተባበር ነው።እንዲያውም ከሞሶሎኒ ጎን ተሰልፈው ምክር ይሰጡ ነበርና ብዙ ካህናትንም ያስፈጁ የወታደር ልብስ ልብሰው የመጡ የሮማ ካቶሊክ ቄሶች ናቸው ይባላል።ሮማ ፓፓው የተቀደሰ ዘመቻ ነው ብለው መድፉንና ታንኩን ባርከዋል።በዚህ ሁሉ ድርጊታቸው በዓለም ክርስቲያኖች ዘንድ ተነቅፈውበታል (የኢት/ቤ/ክ/ታሪክ ገጽ 89)።

ከዚህ ሁሉ መከራና ውጣ ውረድ በኋላ ከላይ እንደተገለጸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን

በትዕግስትና በትህትና ሆና የጵጵስናውን መብት ካገኘች በኋላ ደረጃ በደረጃ የሊቀ ጵጵስናውን መብት ግብጻውያን ይፈቅዱ ዘንድ ጠየቀች።ጥያቄውም ለግብጻውያን ከባድ ቢሆንም አንሰጥም ብለው መከላከል ስለማይችሉ በግድም በውድም ተፈቅዶ **ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ተብለው ለመጀመሪያ ጊዜ ጥር 6/1943 ዓ/ም ተሾሙ።**

**በሰኔ 21/1951** ዓ/ም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከሊቀ ጵጵስና ወደ ፓትርያርክነት መንበር ከፍ አለች። በካይሮ በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን **ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚል የመጨረሻ ሥልጣን እርከን ሆኑ**።ኢትዮጵያ የራሷን የፓትርያርክነት መንበር ካገኘች በኋላ በየዘመኑ በተሾሙት ፓትርያርኮች በርካታ ጳጳሳትን በመሾም በሀገረ ስብከቱ በመደልደል የወንጌል አገልግሎት እንዲስፋፋ አደርጋለች በማስፋፋት ላይም ትገኛለች።

በአጠቃላይ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት በርካታ መንፈሳዊ ተግባሮች የተከናወኑ ሲሆን እንዚህን መንፈሳዊ ዕድገቶችን ለማቀጨጭ ፋሽስት ኢጣሊያ በሀገሪቱ ላይ በ1928 ዓ/ም ለተከታታይ አምስት ዓመታት ቤተ ክርስቲያንና ኢትዮጵያን ለማጥፋት የግፍ ወረራ አካሄዷል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክነት የመሩ አባቶች

1. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሰኔ 21/1951-1963 ዓ/ም

2. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ግንቦት 1/1963-1968 ዓ/ም

3. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ 23/12/1968-1980 ዓ/ም

4. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ነሐሴ 29/1980-1983 ዓ/ም

5. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሰኔ 5/1984-2004 ዓ/ም

6. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማቲያስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሰኔ 2004 ዓ/ም

### 8.6.ደርግ ዘመነ መንግስት /1966-1983/

ከ4ኛው መቶ ዓመት ጀምሮ እስከ 1967 ዓ/ም መነሻ ድረስ ብሔራዊ ሃይማኖት ሁኖ ቤተ መንግስቱንና ቤተ ክህነቱን አቀራርቦ ለ1600 ዘመናት ያህል ሲሠራ የነበረው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በተለይም በ1948 ዓ/ም የወጣው ሕገ መንግስት እንዳይሰራ በ1967 ዓ/ም የወጣው ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ማቋቋሚያ አዋጅና በ1980 ዓ/ም የጸደቀው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት በቤተ መንግስቱና በቤተ ክህነቱ መካከል የነበረውን የቀረበ ግንኙነት በአዋጅ ሻረ።ከዚያን ጊዜ ጀምሮ

በሁለቱም ዘንድ የነበረው ይፋ የሆነ የሃይማኖትና የአስተዳደር ግንኙነት ሊቋረጥ የቻለ ቢሆንም የደርግ መንግስት እስከ ወደቀበት ግንቦት ወር 1983 ዓ/ም ድረስ ጠቅላይ ቤተ ክህነቱን አስተዳደር የሚመራ ዋና ሥራ አስኪያጅ ከመሾም አልተገታም ነበር።ይሁንና በ1987 ዓ/ም የጸደቀው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 11 መንግስትና ሃይማኖት የተለያዩ መሆናቸውን ሲገነግግ ሃይማኖት በመንግስት መንግስትም በሃይማኖት ጉዳይ እንዳይገባ ሕገ መንግስቱ በግልጥ አስቀምጧል።

ይህ የሃይማኖት እኩልነት አዋጅ በሁሉም የእምነት ድርጅቶች ላይ እንዲሠራ በመደረጉ ከደርግ ውድቀት በኋላም ተያይዞ በመጣው በተለመደው አሠራር ሲንቀሳቀስ የቆየው አስተዳደር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንም እንደሌሎች የእምነት ድርጅቶች የራሷን አስተዳደር በራሷ ሥራ አስኪያጅ የመምራት ኃላፊነት እንዳለባት በመገንዘብ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ባደረጉት ጥረት ከ1987 ዓ/ም ጀምሮ በራሷ ሥራ አስኪያጅ እንድትተዳደር ተደርጓል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከ4ኛውና ከ13ኛው መቶ ዓመት ጀምሮ የነበረው የአስተዳደርና የኤኮኖሚዋ አቋም ከ1967 ዓ/ም ጀምሮ ግን ለዘመናት ታገኝ የነበረው ጥቅም ሁሉ በደርግ መንግስት አዋጅ ከየካቲትና ከሐምሌ 1967 ዓ/ም ጀምሮ ተቋርጧል።ይህ በዚህ እንዳለ በ1965 ዓ/ም በነጋሪት ጋዜጣ በወጣው ቃለ ዓዋዲ የቤተ ክርስቲያናችን መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ከሕዝበ ክርስቲያኑ በሚሰጥ አስተዋጽኦ ከስእለት፣ከሙዳየ ምጽዋትና ከመንግስት በሚገኝ የድጎማ ገንዘብ እንድትተዳደር ተደርጓል።

በደርግ ዘመነ መንግስት በኢትዮጵያና በቤተ ክርስቲያኗ ላይ ብዙ ጥፋት ደርሰዋል።የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቅዱስ ፓትርያርኩ፣ሊቃነ ጳጳሳቱና ካህናቱ ለብዙ ዓመታት በእስር ቤት ተሰቃይተዋል፤በመጨረሻም ቅዱስ ፓትርያርኩ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በታላቁ ቤተ መንግስት በዙፋኑ ሥር የሚገኝ ለወይን ጠጅ ማቀዝቀዣ የተዘጋጀው ዋሻ ውስጥ ታስሩ ቆይተው በግፍ ተገድለዋል።ብዙ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ተከታይ የሆኑ ባለሥልጣናትና ምዕመናን የተገደሉበት ቦታ እንኳ ሳይታወቅ በጥይት ተደብድበው ሰማዕት ሆነዋል።በርካታ በምዕመናን ልገስና የተሠሩ ፎቆችና ቪላ ቤቶች፣መንፈሳዊና ዘመናዊ ትምህርት ቤቶች እና መሬቶች ተወስደዋል።

### 8.8. በኢህአዲግ ዘመነ መንግስት /1983-እስካሁን ድረስ/

ቤተ ክርስቲያኒቱ ከማንም ጥገኛነት ነፃ ሁና የሥልጣን ባለቤት ከሆነችበት ከ1951 ዓ/ም አንስቶ እስከ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት እስከመሆን ደርሰው የአብያተ ክርስቲያናቱን አስተዳደር በሀገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ በመምራት የምትታወቅ መንፈሳዊት ተቋም ናት።በዚህም መሠረት በ20ኛው ምዕተ ዓመት ቤተ ክርስቲያናችን ቀደም ሲል ከነበራት የአመራር ምዕራፍ ወደ ላቀ ደረጃ ለመሸጋገር እንድትበቃ አስችለዋታል።ቤተ ክርስቲያናችን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማህበርን ከመሠረቱት አንዷና

የመጀመሪያዋ ናት፡፡የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት መሥራች አባልም ናት፡፡የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት መሆን የኢትዮጵያ ዞርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለ1600 ዘመናት ያህል የኮፕት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ ጥገኛ ሁና የኖረችበትን ዘመን ለማዘከር የሚረዳ ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የሚመራው በቅዱስ ፓትርያርኩ ሊቀ መንበርነት ሲሆን ቅዱስ ፓትርያርኩ ቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊውንና ማህበራዊውን አገልግሎት በተቀላጠፈ አሠራር ለማከናወን ትችል ዘንድ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ዘመናዊ አስተዳደርና የሥራ አመራር እንዲኖራት ጥረት አድርገዋል፡፡በብፁዕነታቸው ዘመን ከተሠሩ ሥራዎች መካከል፡- 49 ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ተሹመዋል፣በደርግ የተወረሱትን የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅንና የቤተ ክርስቲያኒቱን ሕንፃዎችንና ቪላ ቤቶችን አስመልሰዋል፣የከሳቴ ብርሃን አባ ሰላማን ኮሌጅ አቋቁመዋል፣የቅዱስ ጳውሎስን ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት ወደ ኮሌጅ ደረጃ ከፍ አድርገዋል፣የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅን ዩኒቨርሲቲ ለማድረግ የመሠረት ድንጋይ ጥለዋል፣በርካታ በሀገሪቱ መንፈሳዊና ዘመናዊ ትምህርት ቤቶች የቅድስት ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ጭምር እንዲከፈቱ አድርገዋል፣በድርሰትና በመጻሕፍት ህትመት በኩል አዳዲስ መጻሕፍት በሊቃውንት ጉባኤ ተዘጋጅተውና ታትመው ለማስተማሪያነት ውለዋል፣ብዙ መጻሕፍትም ከግዕዝ ወደ አማርኛ ተተርጉመው ታትመዋል፤ከሁሉም በላይ 81 ቁጥር ያለው መጽሐፍ ቅዱስ በሊቃውንት ከግዕዝ፣ከፅርዕ፣ከዕብራይስጥ ቋንቋዎች ተገናዝበውና ትርጉሙ ተስተካክሎ ታትመዋል፡፡በጤናም በኩል ኤች አይ ቪ ኤድስን በመከላከል ረገድ ከፍተና ጥረት አድርገዋል፤በማህበረሰብ ልማት በኩልም የጉድጓድ ውሃና የመስኖ ውሃ፣የንብ ርባታ፣የከብት ርባታ፣የሽመና ሥራ የጎጆ እንዲስትሪዎችን በማቋቋም በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያናችን የምትሰጠው በርካታ መንፈሳዊ ፣ሰብአዊና ማህበራዊ አገልግሎቶች ከምንጊዜም በላቀ መልኩ በብፁዕነታቸው ዘመን ተከናውነዋል፡፡

**አክራሪ እስላም በኢህአዲግ ዘመነ መንግስት፡-** በ1983 ዓ/ም የተፈጸመውን የመንግስት ለውጥና በለውጡ ምክንያት የተፈጠረውን ግርግር መጠቀሚያ በማድረግ በሐረርጌና በአርሲ ያለው አክራሪ እስላም ከ1984-85 ዓ/ም ድረስ ቁጥራቸው በደንብ ያልታወቀ አያሌ ካህናትንና ምዕመናን በአርባጉጉ አውራጃና በምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ በአሰቦት ገዳምና በአካባቢው ፈጅተዋል፣ብዙ አብያተ ክርስቲያናትንም አቃጥለዋል፡፡በአርሲ ሀገረ ስብከት በአርባጉጉ አውራጃ ከ670 በላይ ካህናትና ምዕመናን ክርስቲያኖች ታርደዋል፤ግማሾቹ በእሳት ተቃጥለዋል፤ግማሾቹ እየተቆራኙ ወደ ገደል ተወርውረዋል፡፡ቁጥራቸው ያልተወቁ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በከባድ መሳሪያ ተደብድበው ተቃጥለዋል፤ቅርሳቸው ተዘርፈዋል፡፡43000 ምዕመናን ተሰድደዋል፡፡በምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት በተለይም በአሰቦት ገዳም /ደብረ ወገግ/ አቡነ ሳሙኤል ገዳምና በአካባቢው ያሉ መነኮሳትና ምዕመናን በብዛት አልቀዋል፤የተወሰኑ አብያተ ክርስቲያናትም ተቃጥለዋል፡፡በ1998 ዓ/ም ህዳር 8 እና 9 ቀን በአርሲ ሀገረ ስብከት በኮፌሌ ወረዳ በቆሬ ከተማና በአንሻ ሰበካ 6 ምዕመናን ተገድለዋል፤ከ100 በላይ የሆኑ ክርስቲያኖች ቤታቸው ተቃጥለው ተሰደድዋል፤ በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ፈቃድና ትዕዛዝ በ1916 ዓ/ም በታላቁ

ካህን በመምሬ ዳኜ ርዳቸው /አባ ወልደ ጻድቅ/ የተተከለችው ቅደስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተቃጥላለች።በ1999 ዓ/ም በጅማ አጋሮ እና በኢሉባቦር ሀገረ ስብከት በሥርዓተ ንግስ እና በጸሎት ላይ ያሉ ካህናትና ምዕመናን ተቃጥለዋል በአሰቃቂ ሁኔታ ታርደዋል፤800 የምዕመናን ቤቶች ተቃጥለዋል።በተመሳሳይ በ1998 እና 1999 ዓ/ም በወለጋ፣በኢሉባቦር፣በጅማ፣በአርሲ፣በደቡብ ወሎ 12 አብያተ ክርስቲያናት በእስላሞች ተቃጥለዋል።በ2007 እና 2008 ዓ/ም በምስራቅ ሸዋ በሲራሮ ወረዳ አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለዋል፤በርካታ ምዕመናን ቤት ንብረት አጥተው ተሰድደዋል። (የኢት/ኦ/ተዋ/ቤ/ክ/ታሪክ ከልደት እስከ 2000 ዓ/ም ገጽ 291-292)

**ዋቤ መጻሕፍት**


- መ/ር ኃ/ሥላሴ ይግዛው አሁን አባ ሉቃስ የኡመራ ሀ/ስ/ ሊ/ጳጳስ ትምህርታዊ ሺት ሀዋሳ ካህናት ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት 1992
- የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/ ታሪክ / በአቡነ ጎርጎርዮስ 1979 ዓ/ም/
- አንብር መስቀልየ በዲበ መስቀል /በግሸን ከርቤ ማርያም ቤ/ክ የልማት ኮሚቴ 1990/
- ኢትዮጵያዊ በማንነቱ ፍለጋ /ንቡረ ዕድ ኤርምያስ በ1993/
- ታቦተ ጽዮን ፍለጋ /ትርጉም በማህበረ ቅዱሳን 1993/
- ዋዜማ /ብላተን ጌታ ኅሩይ/
- ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት /ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ/
- የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት
- የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናንትና ዛሬ 1990
- የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/ታሪክ ከልደት ክርስቶስ እስከ 2000 ዓ/ም
- የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ታሪክ የመ/ገ/ጽ/ቅ/ጊ/ቤ/ክ/ሰ/ት/ቤት ትምህርታዊ ሺት 1999/

ዲያቆን  ከበደ በቀለ

2009

ሀዋሳ ደብረ ሰላም ቅድስት ሥላሴ

ቤተክርስቲያን ፈለገ ሰላም ሰንበት ት/ቤት